# ክፍል 1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት መሠረታዊ ሃሳቦች

## 1.1. መግቢያ

በአጸደ ሕጻናት ከ 4-5 ዓመት እድሜ ክልል የሚገኙ ሕጻናት በስኬት እንዲያድጉና እንዲዳብሩ ከዕድሜያቸውና ከደረጃቸው ጋር በተመጣጠነ መልኩ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል። ሕጻናት ስለ አካባቢያቸው መረጃ ሊሰበስቡና ሊማሩ የሚችሉት የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም ስለሆነ የተለያዩ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን በማከናወን እንዲጫወቱና አካባቢያቸውን በመፈተሽ እንዲማሩ በቂ የእንቅስቃሴ ነጻነት ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። ከቁሳቁሶች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት የነገሮችን ምንነት እዲያስተውሉ፤ በነገሮች መካከል ስላለው አንድነትና ልዩነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው አካባያቸውን እንዲያስሱና በደረጃቸው የተለያዩ ሙከራዎችን ማከናወን እንዲችሉ አካባቢውን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

> የአፀደሕፃናት ዋና ዓላማ
>
> ህፃናትን በአካል፤ በአእምሮ፤ በማህበራዊ ኑሮና በስሜት በማነጽ ለመደበኛ ትምህርት ቤት ማዘጋጀት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል።

ይህ አጋዥ ጽሁፍ ቀደም ሲል ከተዘጋጀው የቀጠለና ከ 4-5 ዓመት ዕድሜ ክልል ላሉ ህጻናት የተዘጋጀ ሲሆን በአምስት የእድገትና መዳበር ዘርፎች ላይ ማለትም በአካልና በእንቅስቃሴ፣ በማህበራዊና ስሜታዊ ክንዋኔ መዳበር፣በቋንቋ፣ በሂሳብ እና አካባቢን በመፈተሽና በመረዳት ላይ ትኩረት በማድረግ በየዘርፉ ህጻናት ሊደርሱበት የሚገባን የሚጠበቅ ውጤቶችና ብቃቶች፣ የመርጃ መሳሪያዎችን ዝርዝርና የማስተማሪያ ዘዴዎችን ጥቆማ አካቶ ቀርቧል። በተጨማሪም ህጻናቱ በቀሰሙት ልምድ በየዘርፉ ምን ያህል ክህሎት እንዳዳበሩ ለመገምገም የሚያስችል የመከታተያ /የመመዘኛ/ ቅጽ ግልጽ በሆነ መልኩ ተዘጋጅቷል። ይህ መመዘኛ መምህራንና ወላጆች ህጻናትን በማሳደግና በማዳበር ሂደት ላይ የሚያከናውኗቸውን ተግባራትና የሚጎድሉ ነገሮችን በጊዜ በማወቅ ለእያንዳንዱ ህጻን አስፈላጊውን ትኩረት እንዲሰጡ እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል።

የመርጃ መሳሪያዎችን በተመለከተ የተጠቀሙት ሙሉ በሙሉ በቂ ናቸው ማለት ሳይሆን መምህር እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ፈጠራን በመጠቀም ህጻናት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ከማይችሉ ማቴሪሎች ተጨማሪ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት መጠቀም ይችላሉ።

በየርእሶቹ የተጠቆሙት የማስተማሪያ ዘዴዎች ለጥቆማ ያህል የተቀመጡና አቅጣጫን የሚያሳዩ ስለሆነ ተጨማሪ ተግባራትን በተጠቆመው መንገድ ማዘጋጀትና ከህጻናት ባህሪያት ጋር በተጣጣመ መልኩ ሰፋ አድርጎ ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል።

ይህ አጋዥ ጸሁፍ በራሱ እቅድ እንዳልሆነ በመገንዘብ ደረጃውን የጠበቀ እቅድ አዘጋጅቶ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል። ሽልማትን በተመለከተ የተቀመጡ ሀሳቦች በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ህጻናት ለሚያሳዩአቸው መልካም ስነ ምግባሮችና ድርጊቶች የሚሰጣቸው ሽልማት አብዛኛውን ጊዜ ከተለያዩ ነገሮች በቀላሉ ሊሰሩ የሚችሉ መጫወቻዎች፣ ጌጣጌጦች፣ ስዕሎች ወዘተ... እንደ ሽልማት የሚያገለግሉ ሲሆን ጭብጨባም ሆነ የቃል ሙገሳ እንዲሁም ጭንቅላትን መደባበስ እንደ ሽልማት ሊቆጠር እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

## **1.2.** የህጻናት አስተዳደግ መሰረታዊ መርሆዎች

1. ልጅነት ከሰው ህይወት አንዱ ክፍል እንጂ ለወደፊት ህይወት ማዘጋጃ መንገድ ብቻ አይደለም።
2. ህጻናት የተሟላ ስብእና መዳበር /አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ/ ጤንነት ሊኖራቸው ይገባል።
3. ህጻናት በተቀናጀ መልኩ መማር ያለባቸው ሲሆን የትምህርት ዓይነቶችን መበታተን ተገቢ አይደለም።
4. ህጻናት በራሳቸው እንዲማሩ የውስጥ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው።
5. ህጻናት ራሳቸውን በራሳቸው በስርዓት መምራት እንዲለማመዱ እድል መስጠት አስፈላጊ ነው።
6. ህጻናት የተለያዩ ነገሮችን የሚቀበሉበት የዝግጁነት ጊዜ /ወሳኝ ጊዜ/ አላቸው።
7. ለህጻናት የትምህርት መጀመሪያ ሊሆን የሚገባው ማድረግ የሚችሉት እንጂ ማድረግ የማይችሉት አይደለም።
8. የህጻናት ፈጠራና ምናብ ሊዳብር የሚችለው በተመቻቸ ሁኔታና አካባቢ ነው።
9. ማህበራዊ ግንኙነት /ከእኩዮቻቸውና ከአዋቂ ሰዎች ጋር የሚደረግ መስተጋብር/ ለህጻናት ስብእና መዳበር አስፈላጊ ነው።
10. ጥራት ያለው ትምህርት በህጻናቱ ትምህርት በሚሰጥበት ተጨባጭ ሁኔታና ህጻናቱ ሊያውቁ በሚገባቸው ጭብጥ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል። (Tina Bruce – Early Childhood Education)

## **1.3.** ከ **4-5** ዓመት እድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት ባህሪይና የመዳበር ለውጦች

በዚህ የእድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት፡-

- የሰውነታቸውን ሚዛን በተሻለ ሁኔታ መጠበቅ /መቆጣጠር/ ይችላሉ

- ራሳቸውን ችለው የተለያዩ ተግባራቶችን ማከናወን ይሞክራሉ
- ረቂቅ እና ጉልህ የእንቅስቃሴ ክህሎትን እያዳበሩ ይመጣሉ
- ጉልበት ያላቸው፣ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ በእንቅስቃሴያቸው ቀልጣፋ እየሆኑ ይመጣሉ
- አዳዲስ ነገርን ለመሞከርና ለመፍጠር ፍላጎት ይታይባቸዋል እንዲሁም ለሚያደርጓቸው ነገሮች ምክንያት ለመስጠት ጥረት ያደርጋሉ
- የራሳቸውንና የሌሎችን ባህሪያት በተወሰነ ደረጃ መመዘን ይጀምራሉ
- ከራሳቸው ውጪ ያሉ ሌሎች ሰዎችንና ነገሮችን በጥልቀት መመልከት ስለሚጀምሩ ራሳቸውን በይበልጥ የመገንዘብ አዝማሚያ ይታይባቸዋል
- አካባቢያቸውን መፈተሽ፣ የሌሎች ልጆችን ጨዋታ መመልከትና በአካባቢያቸው ስላሉ ነገሮች ባህሪያት ማወቅ ይጀምራሉ
- የተለያዩ ተግባራቶችን ሲያከናውኑ በአእምሮአቸው ውስጥ ዓላማ /ግብ/ ማስቀመጥ ይጀምራሉ
- በጨዋታ አማካኝነት ስለወደፊት ያቅዳሉ
- በምናባቸው የሚፈጥሯቸውን አስፈሪ ነገሮች /ለምሳሌ ጭራቅ/፣ ብቻ መሆንና ጨለማን ይፈራሉ
- ከሌሎች ጋር አብሮ በመጫወት ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነትን ማዳበር ይጀምራሉ
- ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የውድድርና የፉክክር ስሜትን ማዳበርና ጥሩ ያልሆነ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን መቆጣጠር ይጀምራሉ
- ነገሮች እንደሚፈልጓቸው ሳይሄዱላቸው ሲቀር የመጨነቅና የመከፋት ስሜት ይታይባቸዋል
- የሌሎችን ስሜት መረዳት ይጀምራሉ
- በህብረት ጨዋታ ላይ መሳተፍ ያስደስታቸዋል
- ስለ ራሳቸውና ስለሚያውቁት ነገር ለሌሎች መናገር ይችላሉ

## 1.4. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ስለ ህጻናት አስተዳደግና ትምህርት ሊገነዘቡ የሚገቧቸው ተጨማሪ አንኳር ነጥቦች

ሀ. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት አዲስ ነገርን ለመማር የሚያነሳሷቸው ምክንያቶች

- ፍላጎትና ጉጉት መኖር፦ ህጻናት ገና ሲወለዱ ጀምሮ ነገሮችን የመመልከት፣የመረዳትና የማወቅ ፍላጎት ያላቸው ሲሆን ይህ ፍላጎታቸው አካባቢያቸውን እንዲፈትሹና እንዲያውቁ ያነሳሳቸዋል፤ በመሆኑም

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንና ወላጆች ህጻናት አካባቢያቸውን ለማወቅና ለመረዳት ያላቸውን ፍላጎትና ጉጉት ለማርካት በሚያደርጉት ጥረት እድሉን መስጠትና ማበረታታት ይኖርባቸዋል።

- ድርጊቶችን የማከናወንና ግብ ላይ የማድረስ ፍላጎት፡- ድርጊቶችን የማከናወንና ግብ ላይ የማድረስ ፍላጎት መኖር ህጻናት የተለያዩ ተግባሮችን ራሳቸው ችለው ማከናወንን እንዲለማመዱ ያደርጋቸዋል። በተለይ ፈታኝ ከሆኑ ድርጊቶች /ተግባሮች/ ጋር መጋፈጣቸው በተሻለና በቶሎ ተግባሮችን እንዲያከናውኑና ግብ እንዲያደርሱ ይረዳቸዋል። በመሆኑም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንና ወላጆች ህጻናት ራሳቸውን ችለው የተለያዩ ተግባሮችን እንዲያከናውኑ እድሉን መስጠትና ከግብ እንዲደርሱ ክትትል በማድረግ ማገዝና ማበረታታት ይኖርባቸዋል።
- ወላጅንና መምህራንን ደስ የማሰኘት ፍላጎት፡- ህጻናት የሆነ ነገር በማድረግ ወላጆቻቸውንና መምህራኖቻቸውን በማስደሰት ህጻናት የሚያደርጉትን መልካም ነገር እውቅና በመስጠት ማበረታታት ያስፈልጋል።
- አዋቂዎችን የመምሰል ፍላጎት፡-ህጻናት አዋቂዎችን የመምሰል ፍላጎት /ምኞት/ ብቻ ሳይሆን ያላቸው በሚችሉት አቅም እነሱን ለመምሰል ይጥራሉ። ይህንንም ፍላጎታቸውን ለማሟላት አዋቂዎችን በመኮረጅ ይማራሉ። ስለዚህ በህጻኑ አካባቢ የሚገኝ ሰው ለህጻኑ ጥሩ ሞዴል ሆኖ መገኘት ይኖርበታል።
- ሽልማትን ለማግኘት መፈለግ፡- ልጆች ሽልማትን መውደዳቸው በከፍተኛና በተሻለ ሁኔታ እንዲማሩ ይረዳቸዋል። ወላጆች፣ መምህራንና ሌሎች ሀላፊነት ያለባቸው ሰዎችህጻናት በጣም ትንሽ መልካም ተግባር /ምግባር/ ሲያከናውኑ በመሸለም ጠንክረው እንዲማሩና ተፈላጊውን ባህሪይ እንዲለማመዱ ማነቃቃት ይኖርባቸዋል። እንደዚሁም ወቀሳንና ቅጣትን በተቻለ መጠን መቀነስና ማስወገድ ያስፈልጋል። መምህራን ህጻናት እንዳይረበሹ፣ እንዳይሰጉና እንዳይፈሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ፍርሃት፣ስጋትና ጭንቀት ህጻናት በአግባቡ እንዳይማሩ ያግዳቸዋል።

ለ.በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዕድሜ ያሉ ህጻናት ሊማሩ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች

ህጻናት በዚህ ጊዜ ይማራሉ ለማለት አስቸጋሪ ቢሆንም በእርግጥ ህጻናት ሁኔታዎች በተመቻቸ ጊዜ ሁሉ ይማራሉ። ይኸውም፡-

- ደስተኛ ሲሆኑ፡- ህጻናት የተለያዩ ተግባራቶችን በማከናወንና በመለማመድ ሊማሩና ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት ደስተኛ ሲሆኑ ነው። ስለዚህ በቤትም ሆነ በአጸደ ህጻናት ፍቅር፣እንክብካቤና ደስታ የተሞላበት አካባቢን በመፍጠር ህጻናት ደስተኛ ሆነው በጥሩ ሁኔታ እንዲማሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

- ፍላጎት ሲኖራቸው፡- ህጻናት አንድን ነገር ለመማር የሚችሉት በመጀመሪያ ደረጃ ለመማርና ለማወቅ ፍላጎት ሲኖራቸው ነው። ህጻነት ሁልጊዜ የሚያስደስታቸውን ነገር ሲያገኙ በተሻለ ሁኔታ ይማራሉ። ስለዚህ ለህጻናት የሚቀርቡ ማንኛውም ተግባራት አስደሳችና በየጊዜው ተለዋዋጭ መሆን እንደዚሁም ህጻናትን በተገቢው ሁኔታ የሚፈትኑና የመማርና የማወቅ ፍላጎታቸውን የሚያነሳሱ መሆን ይኖርባቸዋል።
- ዝግጁ ሲሆኑ፡- ህጻናት ሁሉን ነገር በአንድ ጊዜ መማር አይችሉም። ምክንያቱም የሚገኙበት የመዳበር ደረጃ የተለያዩ ተግባሮችን ለመማርና ለማከናወን ያላቸውን ዝግጁነት ይወስነዋል። አብዛኛውን ጊዜ አዋቂዎች ህጻናት አዲስ ነገርን ለመማር ዝግጁ ባልሆኑበትና ባልደረሱበት ጊዜ እንዲማሩና እንዲያውቁ ይጫኗቸዋል። ይህ ደግሞ ህጻናቱ እንዲጨነቁ፣ እንዲሰላቹና በመማር ሂደቱ ላይ ጥላቻ እንዲያድርባቸው በማድረግ በወደፊት የመማር ሂደታቸው ላይ ትልቅ እንቅፋት ይፈጥርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነገር እያንዳንዱ/ዷህጻን የመማር ፍጥነቱ/ቷ የተለያየ መሆኑን መገንዘብ ነው።

## ሐ. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት አዲስ ነገር የሚማሩባቸው መንገዶች

- በድርጊት፡- ለህጻናት በማየትና በማዳመጥ ከመማር የበለጠ ምቹና የተሻለ መንገድ ድርጊቶችን በማከናወን መማር ነው። ህጻናት ትኩረት ሰጥተው በማዳመጥ ለረጅም ጊዜ መማር ይከብዳቸዋል። ነገር ግን ድርጊቶችን በማከናወን በንቃት የተሻለ ሊማሩ ይችላሉ።
- በማሰብና በመፈተሽ፡-ህጻናት አካባቢያቸውን እንዲፈትሹ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል። ህጻናት የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም /በመያዝ፣በመጨበጥ፣በመቅመስ፣ በማዳመጥ፣ ወዘተ.../ የሚያጋጥማቸውን ነገር ለማወቅ ጥረት ያደርጋሉ። ውጤቱ አርኪ ከሆነላቸው ይደግሙታል። ካልሆነ መተውን ይመርጣሉ። ነጻ የሆነ ፍተሻና አሰሳ ህጻናት ነገሮች /ዕቃዎች/ እንዴት እንደሚሰሩና በቀጣይ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዲረዱ ይረዳቸዋል።
- ጥያቄ በመጠየቅ፡- በማዳመጥና በመናገር የህጻናት የማወቅ ፍላጎትና ጉጉት ብዙ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ የሚያደርጋቸው ሲሆን ህጻናት መልሱን እያወቁ እንኳን ለማረጋገጥ ይጠይቃሉ።ወላጅና መምህራን በተቻለ መንገድ ህጻናትን ማነጋገር፣ የሚሉትን ማዳመጥና ለጥያቄዎቻቸው በወቅቱ ተገቢውን መልስ በመስጠት የህጻናትን የመማርና የመመራመር ፍላጎት ማነቃቃትና ማበረታታት ይገባቸዋል።
- በመመልከት **(**ሞዴሊንግ**)**፡-_ ህጻናት አዋቂዎችንና ታላላቆቻቸውን በመመልከት ይማራሉ። እንደ አዋቂዎች ለማድረግና ለመናገር ሙከራ ማድረግ ይወዳሉ። ህጻናት አዋቂዎችን መመልከት ብቻ ሳይሆን የአዋቂዎችን ሚና ወስደው ለመጫወትም ይሞክራሉ። በመሆኑም የህጻናት ወላጆች መምህራንና ከህጻናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁሉ ለህጻናቱ ጥሩ ሞዴል መሆን ይኖርባቸዋል።

- በመሞከር፣ በመሳሳትና በመለማመድ፡-_ህጻናት አንድን ተግባር ለማከናወን የተሻለውን መንገድ እስኪያገኙና ማከናወን እስኪችሉ ድረስ በተደጋጋሚ በመሞከር፣ በመሳሳትና በመለማመድ ይማራሉ። በተለይ የዕድሜ ዕኩዮቻቸው ማድረግ የቻሉትን ነገር እስኪችሉ ድረስ ያለመሰልቸትና ያለማቋረጥ ይሞክራሉ። በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት ከሚያስደስታቸው ነገር አንዱ አልችለውም ብለው ያሰቡትን ነገር መቻላቸውና ከዕድሜ እኩዮቻቸው ተሽለው /በልጠው/ መገኘታቸው ነው። በመሆኑም ወላጅና መምህራን ህጻናቱ ራሳቸውን ችለው የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን እንዲችሉ ማበረታታት ያስፈልጋል።

## 1.5. የወላጆች ተሳትፎ በህጻናት አስተዳደግና ትምህርት

ወላጆች የመጀመሪያዎቹ የህጻናቱን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የመጀመሪያዎቹ አስተማሪዎችና በቀጣይ ህይወቱ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ናቸው።

> የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ህጻናትን ተንከባክበው በማሳደግና በማስተማር ለመደበኛ ትምህርት ቤትና ለቀጣይ ህይወታቸው የማዘጋጀት ሀላፊነት አለባቸው። ሀላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት የሚችሉት ግን ከሚያሳድጓቸው ህጻናት ወላጆች ጋር በጋራ በመስራት ነው።

ጥናቶች ወላጆችም ሆኑ የህጻናት አሳዳጊዎች ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር የስራ አጋርነት በመፍጠር በህጻኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ የሚሳተፉ ከሆነ ሶስቱም አካሎች /ህጻናቱ፣ ወላጆችና መምህራን/ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገልጻሉ።

ወላጆች ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር አብረው ሲሰሩ ህጻናቱ በትምህርት ብቻ ሳይሆን በወደፊቱ ህይወታቸውም ውጤታማ ይሆናሉ። በራስ መተማመንን፣ ስለራሳቸው አዎንታዊ አመለካከትንና ባህሪን ያዳብራሉ እንዲሁም ጥሩ ማህበራዊ ልምድን በመመስረትም ደስተኛ ይሆናሉ። ወላጆችም ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ጋር በመጠኑ ይተዋወቃሉ፤ ከሌሎች ወላጆች ጋር ልምድን ይለዋወጣሉ፤ በወሳኝ የመዳበር ወቅት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረጋቸው ደስተኞች ይሆናሉ እንዲሁም ለልጃቸው እድገትና መዳበር አስፈላጊውን ነገር አቅም በቻለ መጠን የማድረግና የሚከሰቱ ችግሮችንም በወቅቱ መፍትሄ የመሻት እድልን ያገኛሉ።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንም ወላጆች ህጻናትን በማሳደግና በማስተማር ስራ ላይ ከጎናቸው ሆነው እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሰሩ ከሆኑ በስራቸው ውጤታማና ደስተኛ ይሆናሉ፤ ስለህጻኑ እድገትና መዳበር መረጃ ማግኘት ይችላሉ በተጨማሪም ወላጆችን በማሳተፋቸው በሀሳብ፣ በእወቀት፣ በጉልበትና በማቴሪያል ድጋፍ ያገኛሉ።

በመሆኑም ወላጆች ይህንን ተመልሶ ሊገኝ የማይችለውን የህጻኑን ወርቃማ ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር በህጻናት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት በተለያዩ ፕሮግሞች ህጻናትን በመምራት የሚሳተፉት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ቢሆኑም ከላይ እንደተገለጸው የወላጅ ሚና ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ከተገለጸው በተጨማሪ ህጻናቱን ስለቀን ውሎዋቸዉ እንዲያወሩ እቤታቸዉ በሚገቡበት ጊዜ አብረው የሚሰሩትን /የሚያወሩበትን/ ስራ በመስጠትና እንደአስፈላጊነቱ ስለህጻናቱ ለመነጋገር ጊዜ በማመቻቸት ወላጆች አብረዉ የሚሰሩበትንና በህጻናቱ አስተዳደግ ላይ በተገቢው አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱበትን አቅጣጫ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

ወላጆች በሕፃናት አስተዳደግ ትምህርት እንዲሳተፉ ለማበረታታት ጠቃሚ መንገዶች

- ወላጆች በልጆቻቸው የእድገትና የመማር ሂደት ላይ ተሳታፊ የመሆንና ልጆቻቸውን በትምህርት ቤት ጥሩ እንዲሆኑላቸው ያላቸውን ፍላጎት መረዳት
- ወላጆችን የሚደግፍና የልጆችን የመማር ሂደት ሊረዱ የሚችሉበትን ፕሮግራም መንደፍና መተግበር
- ቋሚ የሆነ ከወላጅ ጋር ግንኙነት መፍጠር /ሕፃኑን በመቀበያና በመሸኛ ሰዓት፣ በመገናኛ ደብተር፣ በስልክ፣ ወዘተ.../
- የተለያዩ የማንቂያና ግንዛቤ የማስጨበጫ ስልቶችን መንደፍ /የቡድን ውይይት በማካሄድ፣ አጫጭር ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት፣ ወዘተ.../
- ወላጆች በሕፃኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታት /እረፍት ሰዓት ሕፃናቱን እንዲያጫውቱ፣ ተረት እንዲተርቱ፣ በሽርሽር ወቅት እንዲረዱ በማድረግ፣ ወዘተ.../
- ወላጆች ዕለት በዕለት ከልጆቻቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ስለተማሩት ነገር እንዲወያዩ ማድረግ
- የልጆቻቸውን የዕለት ተዕለት ለውጥና መሻሻል እንዲያጤኑ ማድረግ

## 1.6.የመጽሐፉ አጠቃቀም

በዚህ አጋዥ መጽሐፍ ላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃቶች፣ ዓላማ፣ ተግባር፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማና ምዘና በሚል ትኩረት እንዲያገኙ ምልክቶችና ደመቅ ብለው የተቀመጡ ሐረጎች በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ። የእነዚህ ምልክቶችና ሐረጎች ትርጉም በተጠቃሚዎቹ የቅድመመደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ሊታወቁ ይገባል። ትርጉማቸውም እንደሚከተለው ተቀምጧል።

ምልክቶች በተጠቃሚዎች ሊታወቁ የሚገቡ ሐረጎች



የሚጠበቁ ውጤቶች ፡- ሕፃናት በተጠቀሱት የብቃት ደረጃዎች ላይ ሲደርሱ በእነሱ ላይ ሊታዩ የሚገባቸው ለውጦች ናቸው።



ብቃቶች ፡- ብቃቶች ሕፃናት የተለያዩ ተግባራትን በመተግበር ወይም በማከናወን ሊደርሱባቸው የሚገቡ የብቃት ደረጃዎችን ያመለክታሉ።



ተግባር ፡- በአንድ ክፍለ ጊዜ ሊታቀዱና (lesson plan) ሊተገበሩ ለሚችሉ ተግባራት በርዕስነት የተቀመጠ ቃል ነዉ። ተግባራቱ በአንድ ክፍለ ግዜ እንዲከወኑ ታሳቢ ተደርገው የተዘጋጁ ተከታታይነት ያላቸው ክንውኖች ሲሆኑ በአንድ ብቃት ሥር ከአንድ በላይ ተግባር ሲኖር ተግባራቱ እንደየአስፈላጊነቱ ሊደጋገሙ እና ከአንድ ክፍለግዜ በላይ ሊተገበሩ ይችላሉ።



ዓላማ ፡- ተግባራቱ ከተተገበሩ ወይም ክፍለ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ሕፃናት ሊያገኙት የሚችሉትን ጥቅም ወይም ሊደርሱባቸው የሚችሉትን የብቃት ደረጃዎች የሚጠቁም ነው። የክፍለ ጊዜ ዕቅድ ዓላማ ሆኖም ሊያገለግል የሚችል ነው።



የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሕፃናት የሚፈለገው ብቃት ላይ እንዲደርሱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመደገፍ /ለማስተላለፍ/ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸውንና እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ መሣሪያዎችን ያመለክታሉ:: መሣሪያዎቹ እንደሚከናወነው ተግባር፣ እንደሕፃናት ዕድሜ እና የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ በመምህራን ሊታወቅ የሚገባው ነገር በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቆሙት የመርጃ መሣሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሣሪያዎችን መጠቀም እንደሚቻል ነው። መምህራን በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንደ መርጃ መሣሪያ አድርገው መጠቀም ይኖርባቸዋል።

ምልክቶች                በተጠቃሚዎች ሊታወቁ የሚገቡ ሐረጎች



የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-በዚህ ሐረግ ሥር የተቀመጡት ሐሳቦች /ተግባራት/ ተግባሩን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ለመምህራን እንደ ጥቆማ የተቀመጡ ሲሆን ተግባር ላይ ለማዋል መምህራን ዕቅድን በማዘጋጀት የሕፃናትን ስሜት ማሰባሰቢያ፣ የክፍለ ጊዜውን ርዕስ ማስተላለፊያ መንገዶችንና በተግባሩ መጨረሻ የማጠቃለያ ዘዴዎችን በማካተት ሊጠቀሙ ይገባል።



ምዘና ፡- ሕፃናቱ በየብቃቱ ሥር የተቀመጡትን ተግባራት በመተግበር ሂደቱና ከተገበሩ በኋላ የደረሱበትን ደረጃ ለመገምገም የሚረዳ ነው።

የምልከታ መከታተያ ቅጽ ፡- በዚህ አጋዥ ጽሁፍ በየመዳበር አቅጣጫዎቹ ወይም ጭብጦች መጨረሻ ላይ የምልከታ መከታተያ ቅጽ ተቀምጧል። ይህ ቅጽ በዓመት ውስጥ ሶስት ጊዜ /በዓመቱ መጀመሪያ፣ አጋማሽና መጨረሻ/ መሞላት ይኖርበታል። ሆኖም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ላይ የሚገኙ ህጻናት የሚመዘኑት በተከታታይ ምዘና ሆኖ ምዘናው በየዕለቱ፣ በየሳምንቱና በወሩ መጨረሻ ላይ ሊደረግ ይገባል። በቅድመ መደበኛ ት/ቤት የሚካሄደዉ ተከታታይ ምዘና በየጊዜዉ በህጻናት ላይ የሚታየዉን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ የመዳበር ለውጦችን በመከታተል መመዘን እንጂ በጽሁፍ ፈተና የሚከናወን ምዘና እንዳልሆነ መገንዘብ ለመምህራንም ሆነ ለወላጅ በጣም አስፈላጊ ነው።
በዚህ አጋዥ ጽሁፍ ላይ በየጭብጡ መጨረሻ የተቀመጠዉ የምዘና ቅጽ የማጠቃለያ መሆኑን መምህራን ተገንዝበው የህጻናቱን እድገትና ለውጥ በየጊዜው መከታተልና መገምገም የሚኖርባቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በአባሪዉ ላይ

የተቀመጡትን የምዘና ናሙና እና በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተቀመጡትን የምዘና ጥቆማዎች መጠቀም ይቻላል።

መዝሙሮች  እና ተረቶች፡- በየተግባራቱ ስር የተጠቀሱት መዝሙሮች እና ተረቶች በመጽሀፉ መጨረሻ ገጾች ላይ አባሪ ተደርገዋል።

## 1.7 የህጻናት አስተዳደግና ትምህርት እቅድ

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ለአስተዳደግና ትምህርት ስራ ሶስት ዓይነት ዕቅዶች ይታቀዳሉ። እነርሱም የዓመት፣ የወርና የዕለት ናቸው። ከዕለት ዕቅድ ጋር እንደ አባሪ ሆኖ የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅድ /Lesson plan/ ይዘጋጃል።

**የዓመት ዕቅድ**

- **የዓመት ዕቅድ፡-** ይህ የዕቅድ ዓይነት የቅድመ መደበኛ መርሀ ትምህርትን መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ ሲሆን በዓመት አንድ ጊዜ ለአስር ወራት ይዘጋጃል፡፡

**የወር ዕቅድ**

- **የወር ዕቅድ፡-** በወር ውስጥ የሚገኙትን ሳምንታት አጠቃሎ በየወሩ ለየወሩ የሚታቀድ ሲሆን የወር ዕቅድ ላይ የሚጠቀሱት በየዕለቱ የሚከናወኑት ዋና ዋና ፕሮግራሞች፣ ጭብጥና ርዕሶች ናቸው፡፡

**የዕለት ዕቅድ**

- **የዕለት ዕቅድ፡-** የዕለት ዕቅድ ለህጻናት አስተዳደግና ትምህርት በየዕለቱ የሚያከናወኑትን ተግባራት ህጻናትን ከመቀበያ ሰዓት እስከ መሸኛ ደረስ ያሉትን በሚከናወኑበት ሰዓት ቅድም ተከተል ይዞ የሚገኝ ሲሆን የዋና ዋናዎቹ ፕሮግራሞች ጭብጥና ርዕስ በቀጥታ ከወር ዕቅድ ላይ ተወስደው የሚሞሉ ናቸው፡፡ ሌሎች በየዕለቱ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚታቀዱት የቁርስ፣ የእረፍት፣ የምሳ፣ የመኝታ እና የመሸኛ ሰዓታት በየእለቱ የሚታቀዱ ናቸው፡፡

የዕለት ዕቅድ ማቀጃ ቅጽ አራት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ሰዓትን፣ ሁለተኛው የዕለቱን የስራ ይዘት፣ ሶስተኛው የክንውኑን ሂደት፣ አራተኛው ሊታረሙ የሚገባቸውን ማለትም በክንውኑ ሂደት ያጋጠሙ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ነገሮች የሚጠቀስባቸው ናቸው። የዕለት ዕቅድ በየዕለቱ ምን መሰራት እንዳለበት፣ የታቀደው እንዴት እንደተሰራ እና በህጻናቱ ላይ ምን ለውጥ እንደመጣ በጊዜው ያለተሸፈነ ችግር ካለ ወደፊት የሚታረምበት ሁኔታ እንዲመቻች የሚጠቅም ስለሆነ በየዕለቱ የህጻናትን ለውጥ ለመከታተልና ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ ስለሚጠቅም አስፈላጊ ነው።

የክፍለ ጊዜ ክንውን ዝግጅት፡- ይህ ሌሰን ፕላን በመባል የሚታወቀው ሲሆን በየዕለቱ ለሚከናወኑት ዋና ዋና ፕሮግራሞች የሚዘጋጅ ነው። ዝግጅቱ በህጻናት እድገትና መዳበር ላይ የተመሰረተና ዝርዝር አስፈላጊ ነጥቦችን የሚጠቁም ሊሆን ይገባል።

የክፍል ጊዜ ክንውን /ትምህርት/ ዝግጅት ማዘጋጃ ቅጽ

<table>
<tr><td>ቀን</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ቡድን</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ፕሮግራም</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ጭብጥ</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ብቃት</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ርዕስ</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td colspan="4">ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት /ጨዋታ/ በኋላ ህጻናት<br>1. ____________________<br>2. ____________________<br>3. ____________________</td></tr>
<tr><td colspan="2">የመርጃ መሳሪያዎች</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td colspan="2">የማስተማሪያ ዘዴዎች</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td colspan="2">የፕሮግራሙ ዝርዝር ሂደት</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td colspan="2">የመምህሩ ተግባር</td><td>ጊዜ</td><td>የህጻናቱ ተግባር</td></tr>
<tr><td colspan="2"></td><td></td><td></td></tr>
</table>

ቀን፣ ቡድን፣ ጭብጥና ርዕስ የሚወሰደው ከዕለት ዕቅድ ውስጥ ሲሆን የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅዱ /ሌሰን ፕላን/ ለየትኛው እድሜ እንደተዘጋጀ እንዲታወቅ ነው።

ብቃት፡- የሚወሰደው ከዓመት ዕቅድ ላይ ሲሆን ህጻኑ ሊደርስበት የሚገባውን የለውጥ ደረጃ የሚያመላክት ነው።

ዓላማ ፡- በክፍለ ጊዜው ህጻናቱን በማሳተፍ ከተከናወነ በኋላ ህጻናት የሚያሳዩትን ለውጥ የሚያመላክት ሲሆን ዓላማዎቹ ሲነደፉ በአንድ ክፍለ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚሆኑ ታስቦ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ከርእሱ ጋር መሄድ አለመሄዳቸው ትኩረት ሊሰጠውና ከህጻናቱ አቅም አንጻር ሊተገበሩ የሚችሉ፣ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው ሊሰሩ የሚችሉ፣ ሊመዘኑ የሚችሉ እና ተገቢና ግልጽ መሆናቸውን በማሰብ ሊዘጋጁ ይገባል። በእቅድ ላይ ሲቀመጡም በተራ ቁጥር ተለይተው ቢቀመጡና ባይበዙ ለአፈጻጸም ምቹ ይሆናሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ፡- የመርጃ መሳሪያዎች ርዕሱን ከህጻናቱ ደረጃ አንጻር በቀላሉና ህጻናቱን ሊያሳትፉ፣ ሊያዝናኑና ሊያስደስቱ በሚችሉ መልኩ ለመተግበር እንዲቻል የምንመርጣቸው ሲሆኑ እንደአካባቢያችን ሁኔታ በቀላሉ ሊገኙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች የተዘጋጁ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡

የማስተማሪያ ዘዴዎች ፡- ዓላማዎችን ለመተግበር የምንጠቀምባቸው ስልቶች ሲሆኑ የሚመረጡት ከህጻናት ዕድሜና ደረጃ፣ ከክፍለጊዜው ርዕስና ከዓላማዎቹ አንጻር ሊሆን ይገባል፡፡ የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅድ /ሌሰን ፕላን/ ዘዴዎች ሲቀመጡ ግልጽ በሆነ መልኩ እንዴት ልንጠቀምባቸው እንደሆነ በሚጠቁም ሁኔታ ቢሆኑ ትምህርቱን ለሚያቀርበው ሰው ይጠቅማሉ፡፡

የፕሮግራሙ ዝርዝር ሂደት ፡- ፕሮግራሙ እንዴት እንደሚጀመር፣ እንዴት ዓላማዎቹ እንደሚተገበሩ፣ እንዴት ፕሮግራሙ እንደሚጠቃለልና የመምህሩንና የህጻናቱን ተግባር የሚወስደው ጊዜም በዚሁ ላይ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

ህጻናት ተማሪዎች ሳይሆኑ ለተማሪነት ህይወት የሚዘጋጁ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ማንኛውም ፕሮግራም የህጻናቱን የማወቅ ተግባር የሚቀስቀስ፣ መርጃ የሚያስጨብጥና ክህሎትን የሚያለማምድ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህንን ለመተግበር የሚያስችለው ዕቅድ በመስራት ስለሆነ ስራዉን ለማሳለጥ ለዕቅድ ከፍተኛ ቦታ ልንሰጠው ይገባል፡፡

# ክፍል 2. የመዳበር አቅጣጫዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

## 2.1. ለተገቢው ዕድገትና የአካል ጥንካሬ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ

### 2.1.1 ማብራሪያ

የአካል መዳበር ከሕፃናት የመዳበር ዘርፎች አንዱ ሲሆን በተገቢው ሁኔታ እንዲያድግ፣እንዲዳበርና አስፈላጊውን ለውጥ በማምጣት ለቀጣዩ ደረጃ ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። ይህንንም ማድረግ የሚቻለው የደረሱበትን ደረጃ በማጠናከርና ለቀጣዩ ደረጃ እንዲደርሱ እገዛ በማድረግ ነው። የአካል መዳበር ከሌሎች የመዳበር ዘርፎች ጋርም የተያያዘ ስለሆነ ሌሎችን በማዳበር ሂደት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ መረሳት የለበትም።

የአካል መዳበር የአካል ክፍሎችን ጤና ከመጠበቅና ከመንከባከብ ጋር የተያያዘነው። ይህም በየእለቱ አካልን ለመጠበቅ ከሚከናወነው የንፅህና አጠባበቅ ጋር በሰፊው ቁርኝት አለው። ሕፃኑ/ኗ የራሱን አካል ሲለይና ስለራሱ ግንዛቤ ሲኖረው በተሻለ መልኩ ራሱን ወደ መጠበቅና ከሌሎች ጋር ግንኙነት ወደ መፍጠር ሊያመራ ይችላል። ስለዚህ የአካል መዳበር ስር የታቀፉት የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች ህፃኑን ራሱን ከመገንዘብ፣ ከማወቅ ጀምሮ ራሱን ወደ መጠበቅ የሚያደርሱ ክህሎቶችን እንዲለምድ ማገዝ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

### 2.1.2. አጠቃላይ ዓላማዎች

- ህፃናት በደረጃቸው ራሳቸውን መገንዘብ፣ መግለፅ፣ ከሌሎች ጋርም ግንኙነት የመፍጠር አቅማቸውን ለማዳበር
- የሰውነት ክፍሎቻቸውን መለየት፣ መጥራትና በሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የመናገር ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ
- የስሜት አካላቶቻቸውንና የአካል ክፍሎቻቸውን በተገቢው ደረጃ መጠቀምና መንከባከብ እንዲችሉ ለማድረግ

### 2.1.3. የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር
    1.1. እራሳቸውን መግለጽ ይችላሉ
    1.2. ከማንም ጋር በነፃነት ግንኙነት መፍጠር ይችላሉ

2. የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ተግባራቸውን መናገር

    2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ

    2.2. በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናውኑትን ተግባራት በትክክል መናገር ይችላሉ

3. ዓይኖችን መንከባከብ

    3.1. ዓይኖቻቸው በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ

4. ጆሮዎችን መንከባከብ

    4.1. ጆሮዎቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ

5. የማሽተት ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ

    5.1. በማሽተት የተለያዩ ነገሮች ሽታ መለየት ይችላሉ

6. የመቅመስ ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍን መንከባከብ

    6.1. የምግቦችን ጣዕም መለየት ይችላሉ

    6.2. አፋቸውን በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ

7. በመዳበስ ነገሮችንና ሁኔታዎች መግለጽ

    7.1. ስለ ነገሮችና ቁሶች ባህርይ፣ የሙቀት መጠንና ቅርጽ መለየት ይችላሉ

8. ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ሥርዓቶችን መለማመድ

    8.1. የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ

9. አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ

    9.1. አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ

10. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም

    10.1. በሰውነት ክፍሎቻቸው ተገቢውን እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ

11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ

    11.1. ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ማድነቀና በጥንቃቄ መያዝ ይችላሉ

### 2.1.4 የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | 1.1 ራሳቸውን መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ ራስን ማስተዋወቅ

ዓላማ ፦ ራሳቸውን ለሌሎች ያስተዋውቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የሕፃናት ፎቶግራፎች፣ ትልቅ ነጭ ወረቀት፣ባለ ቀለም ወረቀቶች፣ ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በትልቅ ነጭ ወረቀት ላይ በክፍል ውስጥ የሚገኙትን ሕፃናት ጉርድ ፎቶግራፎች በጣም ሣይጠጋጉ መለጠፍ
- ከፎቶግራፎቹ ሥር ስማቸውን እና የልደት ቀናቸውን በመፃፍ ማዘጋጀት እና መለጠፍ
- የራስን ስም፣ አድራሻ እና የግል ፍላጐት መንገር
- እያንዳንዳቸው በየተራ እየወጡ በተለጠፈው ወረቀት ላይ ያለውን ፎቶአቸውን በመጠቆም ስማቸውን፣ አድራሻቸውን፣ የልደት ቀናቸውን፣ የግል ፍላጐታቸውን እና ማከናወን የሚችሉትን እንዲናገሩ ዕድል መስጠት እና ማበረታታት

ምዘና ፦ ስማቸዉን፣ አድራሻቸዉን፣ የልደት ቀናቸውን፣ እና የግል ፍላጐታቸዉንበመናገር ራሳቸዉን ማስተዋወቅ መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- ራስን መግለጽ

ዓላማ ፡- የልደት በዓላቸዉን በጋራ ሲያከብሩራሳቸውን መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትልቅ ነጭ ወረቀት፤ባለ ቀለም ወረቀቶች፣ የመልካም ልደት መግለጫ ካርዶች ናሙና፤ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በአንድ ወር ለተወለዱ ሕፃናት በወር መጨረሻ አንድ ላይ ልደታቸውን ማዘጋጀት
  ለምሣሌ፡- በመስከረም ወር በተለያየ ቀናት የተወለዱ ቢኖሩ በመስከረም ወር መጨረሻ አንድ ላይ ማክበር
- የልደት በዓላቸው ለሆነው ሕፃናት የመልካም ልደት መግለጫ ኮፍያ፣ ካርድ እና የክፍል ማስጌጫዎችን ከሕፃናት ጋር በመተባበርና እንዴት እንደሚሠራ በማሣየትማዘጋጀት
- የልደት በአላቸዉን የሚኩብሩት ህጻናት ስለራሳቸዉ እንዲናገሩ ማበረታታት

ማስታወሻ ፡- የልደት በዓላቸዉን በሚያከብሩበት ቀን በተቻለ መጠን ሁሉም ሕፃናት እንዲሳተፉ ወላጆችን አስቀድሞ መንገር ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ልደታቸውን በጋራ ሆነው ሲያከብሩ ራሳቸውን መግለጽ መለማመዳቸዉን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | 1.1. 1.2. ከሌሎች ጋር በነፃነት ግንኙነት መፍጠር ይችላሉ:: |

**ዓላማ ፦** የእረፍት ቀናቸውን እንዴት እንዳሳለፉ ለጓደኞቻቸው ሲናገሩ የንግግር ስርአትን ይለማመዳሉ።

**የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦**

- መምህር የእረፍት ቀናቸውን እንዴትና ከማን ጋር እንዳሳለፉ በአጭሩ ለህፃናት መንገር
- ሰኞ ዕለት ጠዋት በቅድሚያ ቅዳሜ እና ዕሁድን እንዴት እንዳሳለፉ በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እንዲናገሩ ማድረግ
- ሲናገሩ ራስ ማሻሻት፣ እጅ ማፍተልተል እና የመሣሡሉት ባህሪዎች ተገቢ አለመሆናቸውን በቅድሚያ ማስረዳት
- ሲናገሩ ካቃታቸው ፍንጭ በመስጠት ማበረታታት

**ምዘና፦** የእረፍት ቀናቸውን እንዴት እንዳሳለፉ ለጓደኞቻቸው ሲናገሩ ተገቢውን የንግግር ሥርዓት ተከትለው መናገራቸዉን ትኩረት ሰጥተዉ በማዳመጥ እና በማየት መገምገም።

**ተግባር አንድ ፡- የንግግር ስርዓትን መልመድ**

ዓላማ፡- በ ... ማመን እና ራስን የማክበር ስሜትን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- በመስሎ መጫወት ማዕዘናት የሚገኙ የተለያዩ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የመስሎ ጨዋታ ማዕዘናትንአስቀድሞ ማደራጀት እና ሚና ማከፋፈል
  ለምሳሌ፡- ቤተሰብ፣ ሱቅ፣ ክሊኒክ ወዘተ...
- በመረጡት ቦታ እና ጨዋታ የፈለጉትን ሚና በመምረጥእንዲጫወቱ ማድረግ
- ሲጫወቱ የጨዋታውን ሂደት በማይረብሽ መልኩ ክትትል ማድረግ
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደ አንድ የጨዋታው አባል በመሆን በጨዋታው ውስጥ በመሳተፍ ማስተካከል

ምዘና ፡- በመስሎጨዋታው ሂደት ትኩረት ሰጥቶ በመከታተል በራስ የመተማመን እና ራሳቸውን የማክበር ስሜታቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- ከሌሎች ጋር በነፃነት በመጫወት በራስ የመተማመን እና ራስን የማክበር ስሜታቸዉን ያዳብራሉ።

**ተግባር ሁለት ፡- መስሎ ጨዋታ መጫወት**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህፃናቱንከክፍል ውጭ ይዞ መውጣት
- በህብረት ሆነው በየተራ “እያ ጅቦ” እና “ጭራ ነቀላ” ጨዋታን ማጫወት
- “እጅ ለእጅ ተያይዘን” የተባለውን መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ማዘመር

ምዘና፡- ከሌሎች ጋር በነፃነት በመጫወት በራስ የመተማመን እና ራስን የማክበር ስሜት ማዳበር መጀመራቸዉን በጨዋታዉ ወቅት መገምገም።

**ተግባር ሦስት፡- ከሌሎች ጋር በነፃነት መጫወት**



**ተግባር አራት፡- እንቆቅልሽ መጠያየቅ**

ዓላማ ፡- በነፃነት ከጓደኞቻቸው ጋር እንቆቅልሽ በመጠያየቅ ይጫወታሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መምህር እንቆቅልሽ መጫወት የሚፈልግ/የምትፈልግ ህጻን በመጋበዝ ከመምህር ጋር እንቆቅልሽ እንዲጫወት/እንድትጫወትማድረግ
- በመቀጠልም ፈቃደኛ የሆኑ ሁለት ህፃናትን በመጋበዝ ባዩት መሠረት እንዲጫወቱ ማድረግ
- ሁሉም ህፃናት ከፈለጉት ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ባህላዊውን እንቆቅልሽ በነፃነት እንዲጨዋወቱ እድል መስጠት

ምዘና ፡- ህጻናቱ በነፃነት ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን እንቆቅልሽ በመጠያየቅ መጫወታቸውን በማየት መገመገም

| የሚጠበቅውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2.የሰውነት ክፍሎችን መለየት እና ተግባራቸውን መናገር | 2. 2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ:: |

## ተግባር አንድ ፦ የሰውነት ክፍሎችን መለየት

ዓላማ፦ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የሰው ስዕልን በማንጠልጠል ሕፃናቱ ምን እንዳዩ መጠየቅ
- በስዕሉ ላይ ያዩትን የሰውነት ክፍሎች ከራሳቸው የሰውነት ክፍል ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ

  ለምሳሌ፦ይህ ምንድን ነው? እናንተ ይህ ዓይነት አላችሁ ወይ? እስቲ አሳዩ ወዘተ... እያሉ ጥያቄዎችን በየተራ መጠየቅ

ምዘና፦ የሰውነት ክፍሎቻቸውን መለየታቸዉን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

**ተግባር ሁለት ፡- የሰውነት ክፍሎችን መጥራት**

[illegible] ይጠራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ (ከለር)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሰው ምስል እንዲሠሩ ወረቀት፣እርሳስ እና ባለቀለም እርሳስ (ከለር)ማደል
- በአቅማቸው የሠሩትን በማየት ማድነቅ
- ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- በሰሩት ስዕል ላይ የሚታዩትን የሰውነት ክፍሎች እያሳዩ በስም እንዲጠሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎቻቸውን በሰሩት ስዕል ላይ ለይተው መጥራት መቻላቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ።




**ተግባር ሦስት ፡- የሰውነት ክፍሎች ፐዝል መገጣጠም**

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎች ፐዝል ይገጣጥማሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎች ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ፐዝል እንዴት መገጣጠም እንደሚቻል ማሳየት
- ለሁሉም ህጻናት ፐዝሎቹን መስጠት
- እንዲገጣጥሙ በማድረግ ማጫወት



ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎችፐዝል መገጣጠምመቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- የሰውነት ክፍሎች ሞዴል መስራት

ዓላማ፡- የሰውነት ክፍሎች ሞዴል በመስራት መጠሪያዉን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጭቃ፣ የተቦካ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከጭቃ ወይም ከተቦካ ወረቀት የሰው ሞዴል እንዴት እንደሚሰራ በቅደም ተከተል ማሣየት
- እንዲሠሩ መምራት እና ማገዝ
- የሰሩትን በማየት ማድነቅ
- በሰሩት ሞዴል ላይ የሚታዩትን የሰውነት ክፍሎች እንዲያሳዩ እና እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎች ሞዴል በመስራት መጠሪያውን መናገራቸዉን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡-የሰውነት ክፍሎች መዝሙር መዘመር

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎች መዝሙር በመዘመር የሰውነት ክፍሎቻቸውን ለይተዉ ይጠራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት ወይም መፅሃፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የሰውነት ክፍሎችን የሚጠቁሙ መዝመሮችን ማዘመር
- በሚዘምሩበት ጊዜ የተጠቀሰውን የሰውነት ክፍል መንካታቸውን መከታተል

ለምሣሌ፡- የስሜት አካላት መዝሙር መጨረሻ ላይ እግር አለኝ እራመዳለሁ፣ እጅ አለኝ እይዛለሁ ወዘተ... የሚል በመጨመር ማዘመር

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎች መዝሙር በመዘመር የሰውነት ክፍሎቻቸውን ለይተዉ መጥራታቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መለየት እና | 1.3. 2.2. በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው |

| | |
|---|---|
| ተግባራቸውንመናገር | የሚያከናውኑአቸውን ተግባራት በትክክል መናገር ይችላሉ:: |

ተግባር አንድ ፡- የሰውነት ክፍሎች ተግባራትን መናገር

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎቻቸውን ተግባራት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ስዕሉን በማሣየት የሰውነት ክፍሎችን እንዲጠሩ ማድረግ
- ቀጥሎም መምህር አንድ የሰውነት ክፍል ሲጠሩ ሕፃናት ተግባሩን እንዲናገሩ በማድረግ ማጫወት

  ለምሣሌ፡- መምህር በእግራችን ሲሉ ሕፃናቱ እንራመዳለን በማለት እንዲመልሱ ማድረግ።

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎቻቸውን ተግባራትመናገር መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ እንቆቅልሽ በመጫወት የሰውነት ክፍሎቻቸውን ተግባራት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የእንቆቅልሾች ስብስብ መጽሀፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የሰውነት ክፍሎችና ተግባራቸውን የሚገልፁ እንቆቅልሾችን በመፍጠር እንዲጫወቱ ማድረግ

  ለምሣሌ፦እንቆቅልሀ/ሽ

  ምን አዉቅልሀ/ሽ

  ሲነቁ እከፍታለሁ

  **ተግባር ሁለት ፦ የሰውነት ክፍሎች እንቆቅልሽ መጫወት**

  መልስ ፦ ዓይን ?

ምዘና ፦ እንቆቅልሽ በመጫወት የሰውነት ክፍሎቻቸውን ተግባራት መለየታቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- እንቅስቃሴዎች እና ድርጊቶችን በመመልከት የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት ይናገራሉ።

ተግባር ሦስት ፡- እንቅስቃሴዎችን እና ድርጊቶችን መግለጽ

የመ ... ሲያከናውኑ የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሰዎች የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች እና ድርጊቶች ሲያከናውኑ የሚያሣዩ ስዕሎችን ማሣየት
- በስዕሉ ላይ የሚያዩትን እንቅስቃሴዎች እና ድርጊቶች እንዲናገሩ መጠየቅ
- እንቅስቃሴዎቹ በምን የአካል ክፍል እንደተደረጉ መጠየቅ



ምዘና ፡- እንቅስቃሴዎች እና ድርጊቶችን በመመልከት የሰውነት ክፍሎች ተግባራትን መናገር መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- የማዛመድ ጨዋታ መጫወት

ዓላማ ፡- የማዛመድ ጨዋታ በመጫወት የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍልን የሚያሳይ ስዕል፣ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን/ድርጊቶችን /ሰዎች ሲያከናውኑ የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የአካል ክፍሎችን እና ሰዎች የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያከናውኑ የሚያሳዩ ስዕሎች መቆራረጥ
- ለህጻናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም ጎላ ብለው የተሳሉ ስእሎች የያዘውን የማዛመጃ ሰሌዳ በማሳየት /ሰዎች የተለያዩ ድርጊቶችን ወይም እንቅስቃሴዎችን ሲያከናውኑ የሚያሳይ/ ያዩትን እንዲናገሩ ማድረግ
- የማዛመጃ ሰሌዳውን /የተለያዩ የሰውነት ክፍልን የሚያሳይ/ ከተቆራረጠው ስእል ጋር እንዴት ማዛመድ እንደሚቻል በተግባር ማሳየት
- በመቀጠል የተቆራረጠውን ስዕልና ማዛመጃውን ለህጻናቱ በየጠረጴዛቸው ማደል
- ተመሳሳዮቹን ስዕሎች በማዛመድ እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- በማዛመድ ጨዋታ የሰውነት ክፍሎችን ከተግባራቱ ጋር ማዛመድ መቻላቸውን በማየት መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. 3. ዓይኖችን መንከባከብ | 3.1 ዓይኖቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ፡- የአይን ጥቅምን መናገር

ዓላማ ፦ የአይንን ጥቅም ይናገራሉ፡:

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ ድርጊቶችን የሚያሣይ ስዕል፣ የዓይን ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ስዕሎቹን በማሳየት ድርጊቶቹን እንዲናገሩ ማድረግ
- የተወሰኑ ህጻናት በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት እንዲቆሙ ማድረግ
- የተለያዩ ድርጊቶቹን እንዲከውኑ ማድረግ
- የተቀመጡት ህጻናት ድርጊቶቹን እንዲናገሩ ማድረግ
- በምን የሰዉነት ክፍላቸዉ እንዳዩ በመጠየቅ ማወያየት
- አይናቸው ለምን እንደሚጠቅምና በአይናቸው ምን ምን ነገሮችን ማየት እንደሚችሉ በመጠየቅ የአይንን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፦ የአይንን ጥቅም መናገራቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ የአይንን ስእል ማድመቅ

ዓላማ ፡- የአይንን ስዕል ያደምቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዓይን ስዕል፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር/፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በነጠብጣብ የተሳለ የዓይን ስዕል ለእያንዳንዳንቸው መስጠት
- በመጀመሪያ እንዴት ማድመቅ እንደሚችሉ ማሳየት
- በመቀጠል እንዲያደምቁ ማድረግ
- ሲጨርሱም የሰሩትን በማየት ማድነቅ እና ማበረታታት

ምዘና ፡-የአይንን ስዕል ከመስመር ሳይወጡ ማድመቃቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡ - ስለ አይን መዝሙር መዘመር

ዓላማ ፡- መዝሙር በመዘመር የአይንን ጥቅም ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዓይን ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የአይንን ስእል ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ በመለጠፍ ምን እንደሆነና እነሱም እንዳላቸው እንዲናገሩና እንዲያሳዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት
- ስለዓይን የተዘመረ መዝሙር እንዳለ በመግለጽ በጥሩ ድምጽ መዝሙሩን መዘመር
- በመቀጠልም ስንኝ በስንኝ በመዘመር ማለማመድና አብሮ መዘመር

  ዓይን አለኝ አያለሁ
  ዓይን አለኝ አያለሁ
  ዓይን አለኝ አያለሁ
  አካባቢዬን አስተውላለሁ
  ከምንምጋር አልጋጭም
  በመንገድ አስተውዬ እያየሁ ስለምሄድ

- ከመዝሙሩ የወጡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የአይንን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- መዝሙር በመዘመር የአይንን ጥቅም መናገር መቻላቸውን ከመዝሙሩ በኋላ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- አይናቸውን በመሸፈን መጫወት

ዓላማ ፡- አይናቸውን በመሸፈን ነገሮችን ፈልገው በማግኘት ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዓይን መሸፈኛ ንፁህ ጨርቅ ወይም መሐረብ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለህፃናቱ <<ያእቆብ>> የተባለውን ጨዋታ እንደሚጫወቱ በመንገር የጨዋታውን ሂደትና ህግ አጠር አድርጎ መግለፅ
- አንድ ህፃንን ከህፃናቱ ፊት በማስወጣት ላላ አድርጎ አይኑን በማሰር ሳያይ በድምፅ ብቻ የተደበቀውን እቃ ፈልጎ እንዲያገኝ ማድረግ
- ወደ እቃው ወዳለበት አካባቢ ሲጠጋ <<ያእቆብ>> በማለት ህፃናቱ እያጨበጨቡ ፍንጭ እንዲሰጡት በማድረግ ማጫወት
- በጨዋታው ሁሉም ህፃናት እንዲጫወቱ ማድረግ
- ከጨዋታው በኋላ ምንና እንዴት እንደተጫወቱ በመጠየቅ የአይንን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- ይህ ጨዋታ በአንድ ክፍለ ጊዜ ሁሉንም ህፃናት ማጫወት የማይቻል ስለሆነ በሌላ ክፍለ ጊዜ ያልተጫወቱ ልጆች እንዲጫወቱ ማድረግ የሚያስልግ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች እንደ <<አኩኩሉ>> የመሳሰሉ በአካባቢያቸው የተለመዱ ጨዋታዎችንም ማጫወት ይቻላል።

ምዘና ፡- አይናቸውን ሸፍነው በዳበሳ ብቻ እቃዎችን ፈልገው በማግኘት መጫወታቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- ዓይንን የሚጎዱ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- ዓይን የሚጎዱ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዓይን ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ዓይናቸውን ታመው ያውቁ እንደሆነ መጠየቅና ማወያየት
- ዓይንን ሊጎዱ /ሊያሳምሙ/ ስለሚችሉ ነገሮች መጠየቅና ማወያየት
- ከከፍተኛ ብርሃን ዓይንን እንዴት በእጅ መከለል እንደሚቻል ማሣየትና ማለማመድ

ምዘና ፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ዓይን የሚጎዱ ነገሮችን መለየታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- ለአይን ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄ

ዓላማ፡- ለአይን ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዓይን ስዕል፣ የመዝሙር ካሴት/መጽሐፍ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ዓይንን በንጽህና ለመጠበቅ መታጠብ፣ በቆሻሻ እጅ አለመንካት፣ ፀሐይ ላይ መስታወትንና ሌሎች አንፀባራቂ ነገሮችን አለመመልከት ወዘተ… እንዳለባቸው ማስረዳት
- ፊትን ከመታጠብ በፊት እጅን መታጠብ፤ ፊትን ሲታጠቡ ዓይንንም መታጠብ እንደሚያስፈልግ ማስረዳት
- "እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው " የተባለውን መዝሙር አብሮ መዘመር
- በመዝሙሩ ላይ ፊትን መታጠብ በሚለው ስንኝ ጊዜ ፊትን የመታጠብ እንቅስቃሴ ጋር ዓይንን ማጠብ እንዳለ እንዲገነዘቡ ዓይንን የመታጠብ እንቅስቃሴን በማሣየት እንዲዘምሩ ማድረግ አብሮም መዘመር

ምዘና ፡- ለአይን ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ መረዳታቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. ጆሮዎችን መንከባከብ | 4.1. 4.1. ጆሮዎቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የጆሮ ጥቅምን መናገር

ዓላማ ፦ የጆሮን ጥቅም ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የጆሮን ጥቅም የሚገልፅ ፅሁፍ፣ ጎላ ብሎ የተሳለ የጆሮ ስዕል፣ ባለቀለም እርሳሶች /ከለር/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ስለጆሮ ጥቅም የሚገልፅ ፅሁፍ ማዘጋጀት
- ለሕፃናቱ በማንበብ እንዲያዳምጡ ማድረግ
- አድምጠው የተረዱትን እንዲናገሩ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የጆሮን ስዕል እና ባለቀለም እርሳሶች በመስጠት ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ

ማስታወሻ ፦ መስማት የተሳናቸው ሰዎች እንዳሉ በማስረዳት ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚግባቡት የምልክት ቋንቋ በመጠቀም እንደሆነ እናየተፃፈ ነገርን ማንበብ እንደሚችሉ ሊገባቸው በሚችል ቀላል ቃላት ማስረዳት ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ የጆሮን ጥቅም መናገራቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ የድምፅን ምንጭ መለየት

ዓላማ ፡- የድምፅን ምንጭ መለየት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎላ ብሎ የተሳለ የጆሮ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- "የጠራህን ዕወቅ" ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት፡-
    - አንድ ሕፃን ፊቱን አዙሮ እንዲቆም/እንድትቆም ማድረግ
    - ከተቀመጡት ህጻናት መካከል አንዱ በስሙ እንዲጠራው እና የተጠቆመው ህጻን ሲጠራው እንዲያዳምጥ ማድረግ
    - ከዛም ፊቱን ወደ ጓደኞቹ አዙሮ ጓደኞቹን /ክፍሉን/ እያየ ማን እንደጠራው እንዲናገር ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ይህንን ተግባር ሁሉም ሕፃናት በየተራ እንዲያከናውኑት ማድረግ አስፈላጊ ነው። |

ምዘና ፡- በጨዋታው ወቅት የድምፅ ምንጭንመለየት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ሦስት ፡- ጆሮን በጥንቃቄ መያዝ

ዓላማ ፡- ጆሮ ሊደረግለት የሚገባ ጥንቃቄዎችን ይዘረዝራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎላ ብሎ የተሳለ የጆሮ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጆሮአቸውን ታመው ያውቁ እንደሆነ መጠየቅና ማወያየት
- በጆሮ ውስጥ ምንም ነገር መጨመር፣ በሰው ጆሮ ላይ መጮህ እና እየተጯጯሁ ማውራት ተገቢ እንዳልሆነ ማስረዳት
- ለማጠናከሪያነት የሚከተለውን ገጠመኝ መንገር

ገጠመኝ ፡-

አንድ ቀን ምን እንዳየሁ ታውቃላችሁ? አበበ በቀለ የተደበቀበትን ቦታ ሲፈልግ ከኋላው አየውና ቀስ ብሎ ተጠግቶ ጆሮው ላይ ተያዝክ! ብሎ ጮኸበት በቀለ ደንግጦ ወደ ቀና እግሩን ድንጋይ መታው አለቀሰ እግሩን መምህሯ አከመችለት ግን ማልቀሱን አላቆመም ምን ሆነህ ነው? ሲባል ጆሮዬን አመመኝ አለ። ለወላጆቹ ተነገረና ሃኪም ቤት ወሰደው አሳክመውት ተሻለው ልጆች አበበ ያደረገው ልክ ነው?

ምዘና ፡- ጆሮ ሊደረግለት የሚገባውን ጥንቃቄዎች መናገር መቻላቸዉንጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቁውጤቶች | ብቃት |
|---|---|
| 5. 5. የማሽተት የስሜት አካላትንመጠቀም እና መንከበካብ | 5.1. በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን ሽታ መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የአፍንጫን ጥቅም መናገር

ዓላማ፡- የአፍንጫን ጥቅም ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአፍንጫ ስዕል፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስለ አፍንጫ ጥቅም በሚከተለው መልኩ ማወያየት፡-
  - ለተወሰነ ሰከንድ ሕፃናት በአንድ እጃቸው አፍንጫቸውን በሌላ እጃቸው አፋቸውን እንዲይዙ ማድረግ
  - ቀጥሎም አፋቸውን እንዲይዙ አፍንጫቸውን እንዲለቁ ማድረግ
  - አፍንጫቸውን ሲለቁምን እንደተሰማቸው በመጠየቅ ስለ አፍንጫ ጥቅም ማስገንዘብ
- የአፍንጫ ስዕልን ለእያንዳንዳቸው መስጠትና በእርሳስ እንዲያደምቁ ማድረግ

ምዘና ፡- የአፍንጫ ጥቅምን መናገር መቻላቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ጥሩ እና መጥፎ ሽታን መለየት

ዓላማ ፡- ጥሩ እና መጥፎሽታን ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- አምስቱ የስሜት አካላት የተባለውን መዝሙር ማዘመር
- ሽታን ማሽተት የሚቻለው በምን እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- ጥሩና መጥፎ ሽታ ሽቶአቸው ያውቁ እንደሆነ መጠየቅ
- ጥሩ ሽታ ደስ የሚል መጥፎ ሽታ ደግሞ ደስ የማይል መሆኑን ማስረዳት
- ጥሩ ወይም መጥፎ የሚሸቱ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ካቃታቸው ፍንጭ መስጠት ያስፈልጋል

ለምሳሌ፡- የቆሸሸ ገንዳ፣ የቆሸሸ ውሃ ቦዮች፣ ወዘተ…መጥፎ ሽታ እንዳላቸውና ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ወዘተ…ጥሩ ሽታ እንዳላቸው መጠቆም።

ምዘና ፡- ጥሩ ወይም መጥፎ የሚሸቱ ነገሮችን መለየታቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- ሽታ መለየት

ዓላማ ፡- በማሽተት ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሽታን መለያ ጆግ/ ጠርሙስ/፣ ፍራፍሬዎችና አትክልቶች /ሎሚ፣ ሙዝ፣ ነጭ ሽንኩርት ወዘተ.../

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህፃናቱ የሚያውቋቸውን ፍራፍሬዎችና የጓሮ አትክልቶች በማሳየት ምን እንደሆኑ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማነቃቃት
- በመቀጠልም ብርሀን በማያሳይ ሽታን መለያ ጆግ ወይም ጠርሙስ ውስጥ አንድ ፍራፍሬ ወይም አትክልት ህፃናቱ ሳያዩት በመክተት
- ወደ ህፃናቱ አፍንጫ በማቅረብ አሽተው ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- ትክክል መሆንና አለመሆናቸውን ከእቃው ውስጥ አውጥቶ በማሳየት ራሳቸው እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- ሽታን የሚገልፁ ስንኞችን ደጋግመው እንዲናገሩማለማመድ

ለምሣሌ፡- ሽተተን ሽተተን ሎሚው
ሽተተን ሽተተ ንማንጐው
ብሉት ብሉት አለን ሽታው
የቆሸሻ ገንዳ ሽታ
ልጆች ያስይዛል በሽታ
እንራቅ እንራቅ ከቆሻሻ ሽታ
እንዳንያዝ በጉንፋን በሽታ

ምዘና ፡- በማሽተት ነገሮችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- የሽታዎችን ስያሜ መናገር

ዓላማ ፡- በእንቆቅልሽ ጨዋታ የሽታዎችን ስያሜ ለይተው ይናገራሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእንቆቅልሽ መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- እንቆቅልሾችን እንደሚከተለው በማዘጋጀት ማጫወት

ጠያቂ ፡- እንቆቅልህ/ሽ

ተጠያቂ ፡- ምን አውቅልህ/ሽ?

ጠያቂ ፡-ድቡልቡል ኳስ እመስላለሁ

ወደ አፍንጫ ሲያስጠጉኝ እሸታለሁ

ልጆች ልጠው ሲበሉኝ

አካባቢውን በጥሩ ሽታ እሞላለሁ

እኔ ማነኝ ?

ተጠያቂ፡- ብርቱካን

ምዘና ፡- እንቆቅልሽን በማጫወት የነገሮችን ሽታ ስያሜ በመለየት መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- አፍንጫን የሚጎዱ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- አፍንጫን ለአደጋ የሚያጋልጡ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሹል ነገሮች ስዕል፣ ጥራጥሬ፣ዶቃዎች፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- "አምስቱ የስሜት አካላት" መዝሙርን መዘመር
- አፍንጫን ለአደጋ ሊያጋልጡ ስለሚችሉ ነገሮች በመጠየቅ ማወያየት
- በአፍንጫ ውስጥ ምንም ነገርመክተትእንደማይገባ ማስረዳት

ለምሣሌ ፡- ሹል ነገሮችን፣ ጥራጥሬ፣ ዶቃዎች፣ እርሳስ ወዘተ...

ምዘና ፡- ጥያቄዎችን በመጠየቅ አፍንጫን ለአደጋ የሚያጋልጡ ነገሮችን መለየታቸውንማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- አፍንጫን ማጽዳት

ዓላማ ፦ አፍንጫን ማጽዳት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የመፀዳጃ ቤት ወረቀት/ ሶፍት/፣ መሀረብ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- አፍንጫቸውን በሚከተለው መልኩ ማፅዳት እንደሚችሉ ማስገንዘብ
- የመፀዳጃ ቤት ወረቀትን በመጠቀም አንዱን የአፍንጫ ቀዳዳ በአውራ ጣት በመያዝ እና' 'እንፍ" በማለት እንዴት በመፀዳጃ ቤት ወረቀት/ሶፍት/ አፍንጫቸውን ማጽዳት እንደሚችሉ ማሣየት
- ሕፃናት ከመምህራቸው እንደተመለከቱት የአፍን ጫቀዳዳዎችን በየተራ ማጽዳትን እንዲለማመዱ ማድረግ
- የተጠቀሙበትን ወረቀት በቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ መክተትን እንዲተገብሩና ልምድ እንዲያደርጉት እገዛ ማድረግ

ምዘና ፦ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸዉ አፍንጫቸውን ማጽዳት መቻላቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. የመቅመስ ስሜት አካልን መጠቀም እና አፍን መንከባከብ | 6.1. የምግቦችን ጣዕም መለየት |

ተግባር አንድ ፦ የአፍን ክፍሎች መለየት

ዓላማ፡- የአፍን ክፍሎች ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአፍ ስዕል፣ ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጐላ ብሎ የተሳለ የአፍ ስዕልን በማሣየት ምን እንደሆነ፣ በውስጡ ምን እንዳለ እና አገልግሎቱ ምን እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- የሰው ፊት ስዕል ያለበትን በወረቀት ላይ የተሳለ ስዕልን ለእንያንዳንዱ ልጅ መስጠት
- የከንፈርን ቅርጽ ብቻ እንዲያደምቁና ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- በመጨረሻም ‹‹የት አለ አፋችን**?** የት አለ ጥርሳችን**?** የት አለ ከንፈራችን**?** የት አለ ምላሳችን**?**›› በማለት በዜማ መጠየቅ እነሱም በዜማና በተግባር እንዲያሳዩ ማድረግ

ምዘና ፡- የአፍን ክፍሎች መለየታቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ ማረጋገጥ።



ተግባር ሁለት ፡- ጣዕምን በመቅመስ መለየት

ዓላማ ፡- የተለያዩ ጣዕሞችን በመቅመስ ለመለየት ይሞክራሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጣፋጭነት ያላቸው ምግቦች/ስኳር፣ ማር፣ ከረሜላ፣ ወዘተ…/ መራራነት ያላቸው ቅጠሎች / ጤናአዳም ፣ ዳማከሴ፣ ወዘተ…/፣የተለያዩ ጣፋጭ ምግቦች ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን በስም መጥራት ሕፃናት ምግቦቹን ከዚህ በፊት በልተው ያውቁ እንደሆነና እንዳልሆነ መጠየቅ
- ይጣፍጣል፣ ይመራል፣ ያቃጥላል በማለት የምግቦቹን ጣዕም እንዲናገሩ ማበረታታት
- ንጽህናቸው የተጠበቀ ጣፋጭነት እና መራራነት ያላቸውን ምግቦችንና ቅጠሎች ወደ ክፍል ማምጣት ለሕፃናቱ በማሣየት ምን እንደሆኑ መጠየቅ
- እነዚህ የምግብ ዓይነቶችና ቅጠሎች ሕፃናቱም ላስ በማድረግ እንዲያጣጥሙና ጣዕሙን ጣፋጭ መራራ በማለት እንዲናገሩ ማድረግ
- “ቀምሰህ ዕወቅ” የሚለውን ጨዋታ በማጫወት ማጠናከር

ለምሳሌ ፡- ሙዝ ይጣፍጣል፤ ቃሪያ ፣ በርበሬ፣ ሚጥሚጣ ያቃጥላል፣ ወዘተ

ምዘና ፡- የተለያዩ ጣእሞችን በመቅመስ መለየት መቻላቸውን መገምገም፡፡

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6.. የመቅመስ ስሜት አካልን መጠቀምና አፍን መንከባከብ | 6.2.አፋቸውን በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ፡፡ |

ተግባር አንድ ፡- አፍን መንከባከብ

ዓላማ ፦ አፋቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የውሃ ጆግ፣ ውሃ፣ ማስታጠቢያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሕፃናት ምን ዓይነት ምግቦችን በይበልጥ እንደሚወዱ መጠየቅ
- ጣፋጭ ምግቦችን አዘውትሮ መመገብ ለጥርስ ጠንቅ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግ
- እንደዚሁም ከምግብ በኋላ አፋቸውን በውሃ በተገቢው መንገድ መጉመጥመጥ እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- ይህ ካልሆነ ግን ጥርሳቸው ሊበላሽና አፋቸው ሊሸት እንደሚችል ማስረዳት
- ይህንንም ለማጠናከር በተግባር ማሣየት እና እነሱም በተግባር እንዲለማመዱ ዕድሉን መስጠት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፦ ሕፃናት ሁልጊዜ ከምግብ በኋላ አፋቸውን መጉመጥመጣቸውን በመከታተል ልምዱን እንዲያዳብሩ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፦ አፋቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው መገንዘባቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

## ተግባር ሁለት ፦ ጥርስን ሊያበላሹ የሚችሉ ምግቦችን መለየትና ማዛመድ

ዓላማ ፡- ጥርስን ሊያበላሹ የሚችሉ ምግቦችን በመለየት ያዛምዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስእል ማዛመጃ ሰሌዳዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን ጥርስን ሊያበላሹ የሚችሉ ምግብ ስእሎችን/ከረሜላ፣ ብስኩት፣ ቸኮሌት፣ ስኳር ወዘተ.../ ተራ በተራ በማሳየት ምን እንደሆኑ መጠየቅ
- በየጠረጴዛቸው ላይ ማዛመጃ ሰሌዳውንና የተቆራረጡ ስእሎችን በመስጠት እንዲያዛምዱ ማድረግ
- ሲጨርሱም ምንን ከምን ጋር እንዳዛመዱና ያዛመዷቸው ስእሎች ምን እንደሆኑ በመጠየቅ ጥርስን ሊያበላሹ የሚችሉ ምግቦችን እንዲለዩ ማድረግ

ምዘና ፡- ጥርስን ሊያበላሹ የሚችሉ ምግቦችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ሶስት ፡- ጥርስን መንከባከብ

ዓላማ ፡- ጥርሳቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጥርስብሩሽ ወይም የእንጨት መፋቂያ፣ ኩባያ ወይም ብርጭቆ፣ የጣፋጭ ምግቦች ስዕል፣ የጥርስ ብሩሽ እና የኩባያ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በጥንድ ያሉ የተለያዩ ለጥርስ መበላሸት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የምግብ ዓይነቶችን ስዕል በመስጠት እንዲያዛምዱ ማድረግ
- ጥርስን እንዴት ማፅዳት እንዳለባቸው በሚከተለው መልኩ ማስረዳት፡-
    - የጥርስ ብሩሽን ወይም የእንጨት መፋቂያን በመጠቀም ከላይ ወደ ታች ጥርስን እንዴት ማጽዳት እንደሚቻል መምህር በተግባር ማሣየት
    - በአንዱ የጥርስ ብሩሽ /መፋቂያ/ ሌላ ሰው መፋቅ እንደሌለበት እና የጥርስ ሣሙናም መዋጥ እንደሌለበት ማስረዳት
- ለሕፃናት ለእያንዳንዳቸው ኩባያ ወይም ብርጭቆና የጥርስ ብሩሽ ስዕልን መስጠት
- የፈለጉትን ከለር መር .ቀቡ ማ
- ሲጨርሱም ምን እን ን እንደ ፃድረግ

ምዘና ፡- ጥያቄ በመጠየቅ እና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸዉን በመከታተል ጥርሳቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው መረዳታቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 7.በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መግለጽ | 7.1. ስለነገሮች እና ቁሶች ባህርይ፣ የሙቀት መጠንና ቅርጽን መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- በመዳሰስ የነገሮችን ባህርይ መለየት

ዓላማ ፡- የነገሮችን ባህርይ በመዳሰስ ለይተው ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዳሰስ ሰሌዳዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሶስት ደረጃ ያላቸውን የመዳሰስ ሰሌዳዎች /ለስላሣ፣ ሸካራ፣ በጣም ሸካራ/ ለሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ መስጠት
- በእጃቸው እንዲዳስሱና የትኛው ለስላሳ የትኛው ሸካራ እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የነገሮችን ባህርይ በመዳሰስ መለየት እና መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሁለት ፡- ነገሮችን በመዳሰስ በባህሪያቸው መመደብ**

ዓላማ ፡- ነገሮችን በመዳሰስ በባህሪያቸው ይመድባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዳሰስ እና የቀለም ሰሌዳ የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶች /የሣሙና ፓኮ፣ የመዳሰስ ሰሌዳ፣ የቀለም ሰሌዳ፣

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለየዩ በአካባቢያቸው የሚገኙ ሸካራና ለስላሣ የሆኑ ቁሰቁሶችን መስጠት
- ሕፃናቱ በባህሪያቸው እንዲመድቡና በመጨረሻም እነዚህ ሸካራ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ለስላሣ ናቸው በማለት እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ነገሮችን በመዳሰስ በበህሪያቸው መመደብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሶስት፡- በመዳሰስ የነገሮችን ምንነት መለየት**

ዓላማ ፡- የነገሮችን ምንነት ሳያዩ በመዳሰስ ብቻ ለይተዉ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶች፣ የማያሳይ ከረጢት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናት የሚያውቋቸውን የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት
- አንዱን ቁስ በማያሳይ ከረጢት ውሰጥ መክተት
- አንድ ፈቃደኛ ሕፃን በማስነሳት እጁን /እጇን በከረጢት ውስጥ ከትቶ/ ከታሳያወጣ/ ሳታወጣ ዕቃውን በመዳበስ ምን እንደሆነ እንዲናገር /እንድትናገር ማድረግ
- ትክክል መሆን አለመሆኑን አውጥቶ/ታ በማየት ራሱ/ሷ እንዲገመግም/ እንድትገመግም ማድረግ
- በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሁሉንም ሕፃናት ማሳተፍ

ምዘና ፡- የነገሮችን ምንነት በመዳሰስ መለየት እና መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።


ተግባር አራት ፡- በመዳሰስ ቅርፆችን  መለየት

ዓላማ ፦ በመዳሰስ ብቻ ሳያዩ ቅርፆችን በመለየት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የጂኦሜትሪ ቅርፆች /ክብ፣ ጐነ ሶስት፣ ጐነ አራት፣ ካሬና ሞላላ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን /ክብ፣ ጐነ ሶስት፣ጐነ አራት፣ ካሬና ሞላላ/ በየጠረጴዛቸው መስጠት
- ጣቶቻቸውን በመጠቀም ቅርጾቹን እንዲለዩ ማድረግ
- "ዳሰህ ዕወቅ" የሚለውንጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት፡-
    - ከሕፃናቱ ፊት ለፊት ባለው ጠረጴዛ ላይ አምስቱን ቅርፆች /ክብ፣ ጐነ ሶስት፣ ጐነ አራት፣ ካሬና ሞላላ/ ማሰቀመጥ
    - ፈቃደኛ የሆኑ ሕፃናትን በማስወጣት ዓይናቸዉን ላላ አድርጎ በጨርቅ ማሠር
    - ከዛም አንዱን ቅርጽ በእጃቸዉ ላይ በማድረግ ዳሰዉ ቅርጹን እንዲናገሩ ማድረግ
    - ልክ ከሆነ ማስጨብጨብ ከተሳሳተ ፍንጭ በመስጠት እንደገና እንዲሞክሩ ዕድሉን በመስጠት ሁሉም ሕፃናት በየተራ እንዲጫወቱ ማበረታታት



ምዘና ፦ በመዳሰስ ቅርፆችን መለየታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፦ ከተበካ ጭቃ ወይም ወረቀት የተለያዩ ቅርፆችን መስራት

**ዓላማ ፡- በተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት የተለያዩ ቅርፆችን ይሰራሉ።**

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቦካ ወረቀት ወይም ጭቃ፣የጠረጴዛ ላስቲክ**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጠረጴዛዎቻቸውን በላስቲክ መሸፈን
- በጥንቃቄ የተቦካ ጭቃን ወይም እንዲሁም የተቦካ ወረቀት መስጠት
- ሕፃናት ጣቶቻቸውን ተጠቅመው የተለያዩ ቅርፆችን እንዲሠሩ ማድረግ
- ሲጨርሱም የሠሩት ምን እንደሆነ ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩና እንዲናገሩ ማድረግ
- በመጨረሻም ሊደርቅ የሚችልበት ቦታ ላይ ማስቀመጥ

ምዘና ፡- የተለያዩ ቅርፆችን መስራት መለማመዳቸውን በመመልከት ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- በመንካት የነገሮችን ሙቀት መለየት

ዓላማ ፡- በመንካት የነገሮችን ሙቀት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሃ መያዣ ንኬል እና ፕላስቲክ ጆግ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የነገሮችን ሙቀት በመንካት መግለፅ እንዲችሉ በሚከተለው መልኩ ማለማመድ፡-
  - ሁለት የንኬል ወይም የፕላስቲክ ጆጐችን ማዘጋጀት
  - በአንደኛው ጆግ ውስጥ ለብ ያለ ውሃ በሌላኛው ቀዝቃዛ ውሃ ማድረግ
  - ሕፃናቱ እጃቸውን ጆግ ውስጥ በመክተት የተሰማቸውን ስሜት ይቀዘቅዛል፣ያ ቃጥላል፣ ይሞቃል ወዘተ...በማለት እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- በመንካት የነገሮችን ሙቀትና ቅዝቃዜ መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 8. ጤናን የመጠበቅና የአጠባበቅ ስርዓቶችን መለማመድ | 8.1. የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ። |

## ተግባር አንድ ፡- የምግብ ጠቃሚነትን መረዳት

ዓላማ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የምግብ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሁሉንም ሕፃናት ጠዋት ከቤታቸው ቁርሳቸውን ምን በልተው እንደመጡ፣ ምን ዓይነት ምግቦችን መመገብ እንደሚወዱ በመጠየቅ ማወያየት
- ሕፃናትም ሆኑ አዋቂዎች የተለያዩ ምግቦችን እንደሚመገቡና እነዚህም ምግቦች ለሰውነታችን ጠቃሚ እንደሆኑ መግለጽ
- “ማን ነው የሚበልጠው?” ተረትን በመተረክ ማጠናከር

ምዘና ፡- የምግብ ጠቃሚነትን መረዳታቸዉን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

ዓላማ

**ተግባር ሁለት ፡- የምግብ ዓይነቶችን መለየት**

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ምግቦች የተሳሉበት የስእል ወረቀት፣ ነጭ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ስዕል ለእያንዳንዳቸዉ መስጠት
- በዓይነታቸው እንዲመድቡአቸው ማድረግ
- ከዛም ቀለም/ከለር/ እንዲቀቧቸው ማድረግ
- በስዕሉ ግርጌ የምግቡን ዓይነት ሕፃኑን በመጠየቅ ስሙን መፃፍ

ምዘና ፡- የምግብ ዓይነቶችን መለየታቸዉን ማረጋገጥ።



**ተግባር ሶስት ፡- የሚወዱትን ምግብ መሳልና መግለጽ**

ዓላማ ፦ የምግብ ዓይነቶችን ስያሜ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ነጭ ወረቀት፣ባለቀለም እርሳስ/ከለር/፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ልጅ ግማሽ ነጭ ወረቀት/ እርሳስና ባለቀለም እርሳስ /ከለር/ መስጠት
  - የሚወዱትን የምግብ ዓይነት እንዲስሉ እና ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
  - በስዕሉ ግርጌ የምግቡን ዓይነት ሕፃኑን በመጠየቅ ስሙን መፃፍ

ምዘና ፦ የሚወዱትን ምግብ መሳልና መናገር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አራት ፦ የአመጋገብ ሥርዓትን መረዳት እና መተግበር

ዓላማ ፦ የአመጋገብ ሥርዓትን ተረድተዉ ይተገብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የአመጋገብ ሥርዓትን የሚያሣዩ ስዕሎች/ፖስተሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- እነዚህን በመጠቀም ሕፃናት ምግብ ሲመገቡ ሊጠብቁ የሚገባቸውን የአመጋገብ ሥርዓት ማስረዳት
- በምግብ ሰዓት ማውራት፣ መጥኖ አለመጉረስ፣ የአፍን ሳይውጡ ሌላ መጉረስ፣ ወዘተ**...** የሚያስከትለውን ችግር በገጠመኝ መልክ መንገር
- በምግብ ሰዓት በአግባቡ /በሥርዓት/ እንዲመገቡ ማበረታታት

ምዘና ፦ የአመጋገብ ሥርዓትን ተረድተዉ መተግበራቸዉን በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ መከታተል።

ዓላማ ፦ በመስሎ ጨዋታ የአመጋገብ ስርዓትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ለመስሎ መጫወት የሚያገለግሉ መጫወቻ ቁሳቁሶች (ሰሃኖች፣ ማንኪያዎች፣ ሹካዎች ወዘተ**...**)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- <<ቤተሰብ ቤተሰብ>> የመሳሰሉትን የመስሎ መጫወት ጨዋታዎች ማዘገጀት
- ጨዋታዎቹን በመጠቀም ተገቢውን የአመጋገብ ስርዓት ተከትለው እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፦ በመስሎ ጨዋታዉ ወቅት በመከታተል የአመጋገብ ስርዓት መለማመዳቸዉን መከታተል።



ተግባር ስድስት ፦ በድራማ የአመጋገብ ሥርዓትን መለማመድ

ዓላማ ፡- በድራማ የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለተዘጋጀዉ ድራማ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የአመጋገብ ሥርዓትን የሚያሳይ አጭር ድራማ ማዘጋጀት
- በድራማዉ ዉስጥ ሕፃናቱን ተዋንያን በማድረግ የአመጋገብ ሥርዓትን ማለማመድ

ምዘና ፡- ድራማዉን በመከታተል የአመጋገብ ስርዓትን መለማመዳቸዉን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡- የአመጋገብ ሥርዓትን መተግበር

ዓላማ ፡- የአመጋገብ ሥርዓትን ተረድተዉ ይተገብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ኩባያዎች /የዉሃ ኮዳዎች/፣ ቁራጭ ፎጣ፣ ሹካ፣ ማንኪያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህጻናት በእጃቸዉ የሚመገቡትን ምግብ እንዴት ጣቶቻቸዉን ብቻ በመጠቀም መመገብ እንዳለባቸዉ ማስረዳት
- ህጻናት ምግብ ሲመገቡ በሹካና በማንኪያ የሚበሉ ምግቦችን እንዴት መመገብ እንዳለባቸዉ ማሳየት
- ኩባያዎችን /የዉሃ ኮዳዎችን/ ምግብ ባልነካ እጃቸዉ መያዝ እንዳለባቸዉ በመንገር ማሳየት
- በሚመገቡበት ወቅት ይሄንን በተግባር መፈጸማቸዉን መከታተልና አስፈላጊዉን እርዳታ ማድረግ
- ምግቦችን ሳያንጠባጥቡ ሙብላት እንደሚገባና በልተዉ ሲጨርሱ ያቀረቡላቸዉን ሰዎች ማመስገን እንዳለባቸዉ መግለጽ
- በተግባር መፈጸማቸዉን በመከታተል ልምድን እንዲመሰርቱ ማድረግ
- ቁራጭ ፎጣን በመጠቀም ጠረጴዛ እንዴት ማጽዳት እንደሚቻል ማሳየት
- ተረኛ ህጻናት በየዕለቱ ተራቸዉን ጠብቀዉ እንዲያጸዱ ማለማመድ

ምዘና ፡- የአመጋገብ ስርዓትን ተረድተዉ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸዉ መተግበራቸዉን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 9. አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ | 9.1. አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፡- የአካል ክፍሎችን መለየት**

ዓላማ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአካል ክፍሎች ስዕል፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር/፣ ወረቀት ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሁሉንም የአካል ክፍሎች የያዘ ስዕል ለእያንዳንዱ ልጅ መስጠት
- በጠረጴዛቸው የተለያዩ ባለቀለም እርሳስ/ከለሮችን/ ማቅረብ
- እንዲቀቡ እና እያንዳንዱን የሰውነት ክፍል ምን እንደቀቡ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ስዕሎችን ቀለም በመቀባት የአካል ክፍሎቻቸውን መለየታቸዉን መገምገም።

**ተግባር ሁለት ፡- የአካል ክፍሎችን ፐዝል መገጣጠም**

ዓላማ ፡- ፐዝልን በመገጣጠም የአካል ክፍሎችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአካል ክፍሎች ስዕል፣ የአካል ክፍሎች ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከ 4-5 ቦታ የተቆራረጡ የሰውነት ክፍሎች ፐዝልን በመጠቀም እንዴት መገጣጠም እንደሚቻል በሚከተለው መንገድ ማሣየት፡-
  - መጀመሪያ የተሟላ አካል ያለውን ማሣየት
  - ቀጥሎም እያንዳንዱን ቁርጥራጭ ማሣየት
  - የትኛው የሰውነት ክፍል ሊሆን እንደሚችል መጠየቅ
  - ከሕፃናቱ ጋር ፐዝሉን መግጠም
  - በመቀጠልም ፈቃደኛ የሆነ/የሆነች ሕፃን በማስነሳት ፐዝሉን እንዲገጥም/እንድትገጥም ማድረግ
- በዚህ ሁኔታ ሁሉንም ሕፃናት ማሳተፍ

ምዘና ፡- ፐዝል በመገጣጠም የአካል ክፍሎችን መለየታቸዉን ማረጋገጥ።

### ተግባር ሶስት ፡- የአካል ክፍሎችን ተግባራት መለየት

ዓላማ ፡- የአካል ክፍሎችን ተግባራት ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- እንጣጥ ብሎ በመዝለል፣ በማጨብጨብ፣ ወዘተ... ምን እንዳከናወኑ እና በየትኛው የሰውነት ክፍል እንዳከናወኑት መጠየቅ
- እንቆቅልሽን በመጠየቅ ሕፃናት በየትኛው የሰውነት ክፍል ምን ተግባር ሊያከናውኑ እንደሚችሉ እንዲረዱ ማድረግ

  ለምሣሌ፡-

  እኔ ከሰውነት ክፍል አንዱ ነኝ

  ምግብ ለማኘክ እጠቀማለሁ

  እኔ ማነኝ**?** በማለት መጠየቅ እና ማወያየት

ምዘና ፡- እንቆቅልሾችን በመጠየቅ የአካል ክፍሎቻቸውን ተግባራት መለየታቸዉን መገምገም።



### ተግባር አራት ፡- አካልን ንጽሕና መጠበቅ

ዓላማ ፡- አካላቸውን በንጽሕና መጠበቅ እንዳለባቸዉ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአካል ክፍሎች ስዕል፣ የአካል ክፍሎች ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ምን እንዳደረጉ መጠየቅ
- የሰውነት ክፍሎቻቸው የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን እንደሚረዱአቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ

  ለምሣሌ ፡- በእጆች በማጨብጨብ፣ በጆሮ መስማት፣ በአይን ማየት፣ በአፍንጫ ማሽተት ወዘተ...
- የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑባቸውን አካላቸውን በንጽሕና መጠበቅ እንዳለባቸው እና እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ማወያየት

ምዘና ፡- አካላቸውን በንጽሕና መጠበቅ እንዳለባቸዉ መረዳታቸዉን ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- ንጽሕና መጠበቂያ መንገዶችን መናገር

ዓላማ ፦ አካላቸውን በንጽሕና ለመጠበቅ እና ለመንከባከብ ምን ምን ማድረግ እንዳለባቸዉ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የአካል ክፍሎች ስዕል፣ የአካል ክፍሎች ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሕፃናት ሁልጊዜ ጠዋት ከእንቅልፋቸው ተነስተው ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑ በመጠየቅ ማወያየት
- ሕፃናት እጃቸውን ፊታቸውን እና እግራቸውን ማን እንደሚያጥባቸው፤ መቼ እና ለምን እንደሚታጠቡ በመጠየቅ ማወያየት
- ሕፃናት በየቀኑ ፊታቸውን እና እግራቸውን መታጠብ እንዳለባቸው ማስረዳት
- እጃቸው ግን ከምግብ በፊትና በኋላ እንዲሁም ከመፀዳጃ ቤት መልስ ሁልጊዜ በውሃ እና በሣሙና መታጠብ እንዳለባቸው ማስገንዘብ

ምዘና ፦ አካላቸውን በንጽሕና ለመጠበቅ እና ለመንከባከብ ምን ምን ማድረግ እንዳለባቸዉ መናገር መቻላቸዉን ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር ስድስት ፦ የግል ንጽሕናን መጠበቅ አስፈላጊነት

ዓላማ ፦ የግል ንጽሕናን የመጠበቅ አስፈላጊነትን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የላሊቱ ሉሊት ተረትን አጠር አድርጎ መንገር
- የግል ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ችግር እንዲገነዘቡ ማድረግ
- የላሊቱ ሉሊት መዝሙርን በማዘመር መልዕክቱን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ የግል ንጽሕናን የመጠበቅ አስፈላጊነትን መረዳታቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሰባት ፦ የግል ንጽህና ያለመጠበቅ ጉዳት

ዓላማ ፡- የግል ንጽህና አለመጠበቅ የሚያስከትለዉን ጉዳት ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት ፊታቸውን፣ እጃቸውን እና እግራቸውን ራሳቸውን ችለው መታጠብን መለማመድ እንዳለባቸው መንገር
- በመቀጠልም ፀጉራቸውንና ሰውነታቸውን ማን እንደሚያጥባቸውና ለምን እንደሚታጠቡ በመጠየቅ ማወያየት
- ፀጉራቸውን እና ሰውነታቸውን በየጊዜው ካልታጠቡ ፀጉራቸው ተባይ ሊያፈራ እንደሚችል ማስረዳት
- ሰውነታቸውም መጥፎ ጠረን/ደስ የማይል ሽታ/ ሊያመጣ እንደሚችል መግለጽ
- የግል ንጽህናን መጠበቅ አስፈላጊነቱን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- አካላቸውን በንጽሕና አለመጠበቅ የሚያስከትለዉን ጉዳት መናገር መቻላቸዉን ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር ስምንት ፡- እጅ እና ፊትን መታጠብ

ዓላማ ፡- እጃቸዉን እና ፊታቸዉን በመታጠብ አካላቸውን በንጽሕና መጠበቅ እና መንከባከብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሣሙና፣ ውሃ፣ ፎጣ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- እጅን ሳይታጠቡ ምግብ መመገብ የሚያስከትለውን ጉዳት /ችግር/ በተረት እና በገጠመኞች መንገር
- “እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው”” የሚለውን መዝሙር ማዘመር
- ለሕፃናት ዕይታ አመቺ ቦታ በመቆም በሳሙና እና በውሃ እጅን እንዴት አድርጎ መታጠብ እና እንዴት መጥረግ እንደሚቻል ማሣየት
- ያለሣሙና በውሃ ብቻ በሁለት እጅ ፊታቸዉን እንዴት አድርገው መታጠብ እንዳለባቸው ማሣየት
- በመቀጠልም ሕፃናት በየተራ ባዩት መሠረት እጃቸውን እና ፊታቸውን እንዲታጠቡ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ይህንን ተግባር ከክፍል ውጪ የሕፃናት የመታጠቢያ ቧንቧዎችን በመጠቀም ማከናወን ይቻላል። |

ምዘና ፡- እጅ እና ፊትን በመታጠብ አካላቸውን በንጽሕና መጠበቅ እና መንከባከብ መለማመዳቸዉን በማየት ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 10. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ ጡንቻዎችን መጠቀም | 10.1 በሰውነት ክፍሎቻቸው ተገቢውን እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ። |

ዓላማ ፡- ተግባር አንድ ፡- ሚዛንን ጠብቆ መራመድ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጠመኔ/ ቾክ ወይም ገመድ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሰፋ ባለ ቦታ ላይ /በክፍል ወይም በግቢ ውስጥ/እጅ የመዘርጋት ያህል ተራርቀው ወደ ጎን እንዲቆሙ ማድረግ
- ከሕፃናት ፊትለፊት በቾክ መስመር መስራት ወይም ምልክት ማድረግ
- የተሰመረውን መስመር ጠብቆ መራመድ እንደሚቻል በተግባር ማሳየት
- እያንዳንዳቸው በተሰመረው መስመር ላይ እንዲራመዱ ማለማመድ
- ወገባቸውን ይዘው ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ማድረግ
- መነሻና መድረሻን በቾክ ምልክት በማድረግ ማሳየት
- በእግር ጣቶቻቸው እስከ አንድ ሜትር ያህል/አራት ወይም አምስት እርምጃ/ ወደፊት መራመድን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ሚዛናቸውን ጠብቀው መራመዳቸዉን በማየት መገምገም።



ተግባር ሁለት፡- ሚዛንን ጠብቆ መራመድ፣ መሮጥና መዝለል

ዓላማ ፡- ሚዛናቸውን ጠብቀው ይራመዳሉ፣ ይሮጣሉ እንዲሁም በሁለት እግራቸው ይዘላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጠመኔ/ ቾክ ፣ 15-20 ሳ.ሜትር ከፍታ ያለው ሳጥን

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአንድ ረድፍ ማሰለፍ
- በሁለት የተሰመሩ መስመሮች መካከል የተወሰነ ርቀት መራመድን እንዲለማመዱ ማድረግ
- በረድፍ እጃቸውን ዘርግተው መሮጥን ማለማመድ
- ወገባቸውን ይዘው እንዲሮጡ በማድረግ ማለማመድ
- ሳጥን ላይ እንዲቆሙ ማድረግና በሁለት እግራቸው ወደታች መዝለልን ማለማመድ
- በመካከላቸው ከ10-15 ሴ.ሜትር አራርቀ ሁለት ገመዶችን በትይዩ በመሬት ላይ መዘርጋት
- በሁለት እግር ገመዱን ሳይረግጡ እንጣጥ ብሎ እንዴት እንደሚዘለል ማሳየትና እነሱም በየተራ እንዲዘሉ ማድረግ

> ማስታወሻ **፡-** ወገብን ይዞ መሮጥ እጅን ዘርግቶ ከመሮጥ ከበድ ስለሚል መምህር ህፃናቱን ሲያሰሩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል እንደዚሁም ህፃናቱ የሚሮጡበት እና የሚዘሉበት አካባቢ ምቹ መሆኑን አስቀድሞ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ሚዛናቸውን ጠብቀው መራመድ፣ መሮጥና በሁለት እግራቸው መዝለል መቻላቸውን በማየት መገምገም።



ተግባር ሦስት ፡- የሰውነት ቅልጥፍና የሚጠይቁ ጨዋታዎችን መጫወት

ዓላማ ፡- የሰውነት ቅልጥፍና የሚጠይቁ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትናንሽ ኳሶች፣ ጎማዎች፣ መሰላል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከቅርብ ርቀት ትንሽ ኳስን በመወርወር በተተከለ ጎማ ውስጥ ማሾለክን በማሳየት እንዲጫወቱ ማድረግ
- መሬት ላይ በግማሽ በተተከሉ ትላልቅ ጎማዎች /ቱቦዎች/ መሹለክለክን በማሳየት እንዲጫወቱ ማድረግ
- መሰላሎችን መውጣትና መውረድን እንዲለማዱ ማበረታታት
- ትናንሽ ጎማዎችን በማንከባለል እንዲጫወቱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ህፃናቱ መሰላል ሲወጡና ሲወርዱ አጠገባቸው መሆን የሚያስፈልግ ሲሆን መሰላል ላይ መውጣት ያልፈለጉትን ህፃናት ማስገደድ የለብንም። |

ምዘና ፡- ጨዋታዎችን በቅልጥፍና መጫወታቸዉን በማየት መገምገም።



## ተግባር አራት ፡- ሚዛንን ጠብቆ በንቃት መንቀሳቀስ

ዓላማ ፦ ሚዛናቸዉን ጠብቀዉ በንቃት በመንቀሳቀስ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ትንሽ ጨርቅ/መሀረብ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ህጻናቱን በሁለት ቡድን በመክፈል /በትልቅና በትንሽ ቡድን/ እጅ ለእጅ እንዲያያዙ ማድረግ
- ትልቁ ቡድን ህፃናት ሲሽከረከሩ የትንሹ ቡድን ህፃናት ትልቁ ጎማ ተሽከረከረ እያሉ እንዲያጨበጭቡ ማድረግ
- ትንሹ ቡድን ህፃናት ሲሽከረከሩ የትልቁ ቡድን ህፃናት ትንሹ ጎማ ተሽከረከረ እያሉ እንዲያጨበጭቡ ማድረግ
- ህፃናት እጅ ለእጅ በመያያዝ ክብ በመስራት ቁጭ ብለው "መሀረቤን ያያችሁ" ጨዋታን እንዲጫወቱ ማድረግ
- ፈጣኑ ባቡርና ሰለሜ ሰለሜ ጨዋታን መስመራቸውን እና ሚዛናቸውን ጠብቀው ከአንዱ ወደሌላው አቅጣጫ እየተዘዋወሩ እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፦ ሚዛናቸውን ጠብቀው በንቃት በመንቀሳቀስ መጫወታቸዉን በማየት መገምገም።

ተግባር አምስት ፦ ቀላል የአካል እንቅስቃሴዎችን መስራት

ዓላማ ፡- ቀላል የአካል እንቅስቃሴዎችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የወረቀት አበባ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በረድፍ እንዲሰለፉ ማድረግ
- በእጆቻቸዉ ላይ የወረቀት አበባ ማስያዝ
- አበባዉን ወደ ግራ ወደ ቀኝ፣ ወደ ላይ ወደ ታች እንዴት ማወዛወዝ እንደሚቻል ማሳየት
- እንደተመለከቱት እንዲያወዛዉዙ መምራትና ማለማመድ
- ህጻናት እግሮቻቸዉን ትንሽ ከፈት አድርገዉ እጃቸዉን በወገብ አድርገዉ እንዲቆሙ ማድረግ
- ወደፊት ጎንበስ በማለት ጉልበቶቻቸዉን በእጆቻቸዉ ነክተዉ እንዲመልሱ ማሳየትና የተወሰነ ጊዜ በመደጋገም እንዲሰሩ ማድረግ
- ህጻናት እግሮቻቸዉን በመግጠም እጆቻቸዉን ወደታች አድርገዉ እንዲቆሙ ማድረግ
- አንድ ሲባል እጃቸዉን ወደፊት እንዲዘረጉ ሁለት ሲባል እጃቸዉን እንደዘረጉ ቁጭ እንዲሉ በማድረግ እጅን ዘርግቶ ቁጭ ብድግን ማለማመድ
- አቋቋማቸዉ ከላይ እንደተጠቀሰዉ ሆኖ አንድ ሲባል እጃቸዉን ወደ ላይ እንዲያነሱ ሁለት ሲባል እንዲያጨበጭቡ ማድረግ
- ህጻናት እግራቸዉን ወደፊት ዘርግተዉ ወገባቸዉን ይዘዉ በወለል ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ
- አንድ ሲባል እጆቻቸዉን ወደፊት እንዲዘረጉ ሁለት ሲባል የእግር ጣቶቻቸዉን እንዲነኩና ሶስት ሲባል ወደነበሩበት አቀማመጥ እንዲመልሱ በማድረግ ማለማመድ
- እጅ ለእጅ ተያይዘን እንሽከረከራለን የሚለዉን ጨዋታ ማጫወት

| |
|---|
| እነዚህን የሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴዎች በእርጋታ እንዲሰሩ ማሳሰብ እና አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ የማይችሉ ሕፃናትን አለማስገደድ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- ቀላል የአካል እንቅስቃሴዎችን መስራት መቻላቸውን መከታተል።

ዓላማ ፡- ትዕዛዝ ተቀብለዉ በቅልጥፍና በመንቀሳቀስ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ብሎኮች፣ ኳስ፣ ኪዩቦች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በሜዳ ላይብሎኮች፣ ኳስ፣ ኪዩቦች፣ መጫወቻዎች በተለያየ ርቀት ማስቀመጥ
- ትእዛዝ ተከትሎ በተለያየ አቅጣጫ ምንም ነገር ሳይነኩ መዟዟርን በጨዋታ መልክ ማለማመድ

ምዘና ፡- ትዕዛዝ ተቀብለዉ በቅልጥፍና በመንቀሳቀስ መጫወት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፡- ትእዛዝ ተቀብሎ በቅልጥፍና መንቀሳቀስ

ተግባር ሰባት ፡- ትእዛዝ ተቀብሎ መጫወት

ዓላማ ፡- ትዕዛዝ ተቀብለዉ በቅልጥፍና ይጫወታሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- <<ጓደኛህን ፈልግ>> ጨዋታን በሚከተለዉ መልኩ ማጫወት፡-
  - በተለያየ ሁኔታ ተበታትነዉ እንዲቀሳቀሱ ማድረግ
  - ቁጥር ሲጠራ በጠራዉ ቁጥር መጠን ካገኟቸዉ ህጻናት ጋር እንዲተቃቀፉ መንገር

ምዘና ፡- ትዕዛዝን ተቀብለዉ በቅልጥፍና መጫወታቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- በሁለት እግራቸው እየዘለሉ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ኳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በህጻናት ፊት ኳስ በማንጠር መቁጠር
- አብረው እንዲቆጥሩ ማድረግ
- በመቀጠልም "እንደ ኳስ እንንጠር" በማለት የኳስን መንጠር ተከትለው እንዲዘሉ /እንዲያነጥሩ/ በማድረግ ማጫወት

…ከታተል።

ተግባር ስምንት ፡- "እንደ ኳስ እንንጠር" ጨዋታ መጫወት

ተግባር ዘጠኝ ፡- የኳስ ቅብብሎሽ ጨዋታ መጫወት

መጫወት

ዓላማ ፡-የኳስ ቅብብሎሽ ጨዋታ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ኳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሶስት ህጻናት በመራራቅ በወለል ላይ እግሮቻቸውን በመዘርጋት ተቀምጠው ሶስት መዓዘን እንዲፈጥሩ ማድረግ
- ኳስ መስጠትና በወለል ላይ በማንከባለል እየተቀባበሉ እንዲጫወቱ ማድረግ
- ኳሷን ሲያቀብል/ስታቀብል ከሶስት መዓዘኑ የወጣችበት/የወጣችባት ህጻን ከጨዋታ ይወጣና /ትወጣና ሌላ ህጻን በቦታው ይተካል።

ማስታወሻ ፡- ይህን ጨዋታ እንደ ክፍሉ ስፋት በአንድ ጊዜ የተወሰኑ ቡድኖችን ማጫወት ይቻላል።

ምዘና ፡- የኳስ ቅብብሎሽ ጨዋታ መጫወት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አስር ፡- ክር ዶቃ ውስጥ መክተት

መጫወት

ዓላማ ፡-ክር ዶቃ ውስጥ መክተት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክር፣ የተለያዩ ቀለምና ሰፋፊ ቀዳዳ ያላቸው ዶቃዎች ወይም የእስኪሪቢቶ ቀፎ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ክር በተለያዩ ቀለም ያላቸው ትላልቅ ዶቃዎች ውስጥ እንዴት መክተት እንደሚቻል ማሳየት
- ለእያንዳንዱ ህጻን አምስት አምስት የተለያየ ቀለም ያላቸው ዶቃዎችና መክተቻ ሲባጎ /ክር/ በመስጠት እንዲከቱ ማድረግ
- በየጠረጴዛቸው እየተዘዋወሩ በማየት ለከበዳቸው ፍንጭ መስጠት
- የሰሩትን በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እንዲያሳዩና ቀለማቱን እንዲናገሩ ማበረታታት

> ማስታወሻ፡- ለህጻናቱ አስቀድሞ የተሰጣቸውን ዶቃዎች ወደ አፋቸው፣ አፍንጫቸው እና ጆሮአቸው ውስጥ መክተት እንደሌለባቸው በማስጠንቀቅ መንገር እና መከታታተል ያስፈልጋል። ይህን ተግባር ለመተግበር በቀላሉ የእስኪሪቢቶ ቀፎዎችን በተለያየ መጠን በመቁረጥ መጠቀም ይቻላል።

ምዘና ፡- ረቂቅ /ትናንሽ ጡንቻዎቻቸውን በመጠቀም በዶቃ ውስጥ ክር ወይም ሲባጎ ማስገባት መለማመዳቸውን መገምገም።



ተግባር አስራ አንድ ፡- ወረቀት መቁረጥ

መጫወት



ዓላማ ፡- ወረቀትን በመቀስ መቁረጥ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፕላስቲክ /ለልጆች ታስቦ የተሰራ/ መቀስ፣ ባለቀለም ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መቀስን በመጠቀም ወፍራም ባለቀለም ወረቀቶችን በመቀስ እንዴት መቁረጥ እንደሚቻል ማሳየት
- ለሁሉም ህጻናት መቀስና ወረቀት መስጠት
- በትክክል መቀሱን እንዲይዙና በአንዱ እጃቸው ደግሞ የሚቆርጡትን ወረቀት በመያዝ እንዲቆርጡ ማድረግ
- ህጻናቱ በመቀስ መቁረጥን ከተለማመዱ በኋላ በወፍራም ወረቀት ላይ መስመር በማስመር መስጠትና መስመሩን ተከትለው እንዲቆርጡ ማለማመድ
- ህጻናቱ መስመርን ተከትለው ቀጫጭን መስመሮችን እንዲቆርጡ ማድረግ
- የተቆራረጡትን ወረቀቶች በመገጣጠም መንገድ፣ መሰላል፣ የመሳሰሉ ነገሮች በመስራት እንዲጫወቱ ማድረግ

ማስታወሻ፡- ህጻናቱ መቀስን በሚጠቀሙበት ጊዜ ራሳቸውን እንዳይቆርጡ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ህጻናት እገዛ ማድረግና ማበረታታት ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- መቀስን በመጠቀም ወረቀት መቆራረጥ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ ሁለት ፡- እርሳስ አያያዝ እና አጠቃቀም

መጫወት

ዓላማ ፦ እርሳስ አያያዝ እና አጠቃቀምን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ መጠን ያላቸው ወረቀቶች፣ ጎላ ብሎ የተሳለ ስዕል፣ ትናንሽ ስዕሎች እና ባለቀለም እርሳስ/ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ጎላ ብሎ የተሳለ ስዕልን ለህጻናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ መለጠፍ
- ከላይ ወደ ታች፣ ከግራ ወደ ቀኝ ወይም አግድም ከመስመር ሳይወጡ እንዴት መቀባት እንደሚቻል መሳየት
- ትናንሽ ስዕሎቹን ለእያንዳንዱ ህጻናቱ መስጠት
- ህጻናቱም ከላይ ወደታች /ከግራ ወደቀኝ/ ከመስመር ሳይወጡ መቀባትን እንዲለማመዱ ማድረግ
- የቀቡትን ስዕል መጠሪያ ስምና የቀቡትን የቀለም ዓይነት በመጠየቅ እንዲናገሩ ማረታታት

ምዘና ፦ እርሳስ አያያዝ እና አጠቃቀም መለማመዳቸውን በማየት መገምገም።

ተግባር አስራ ሶስት ፦ ስእል መሳል እና መቀባት

መጫወት

ዓላማ ፡- ስዕሎችን ስለው ይቀባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ መጠን ያላቸው ወረቀቶች፣ እርሳሶች፣ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ግማሽ ወረቀትን በማጣጠፍ ትናንሽ መጽሀፎችን በመስራት ማሳየት
- በተመለከቱት መሰረት እንዲሰሩ ማድረግ
- በየገጹ ላይ ቀለል ያሉ ስዕሎችን እንዲስሉና ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- ብርቱካን፣ ቤት፣ ጸሀይ፣ ወዘተ...
- ገፆችን እየገለጹ የቀቡትን ስዕል እንዲመለከቱ ማበረታታት

ማስታወሻ፡- እያንዳንዱ ህጻን መፅሀፍ ማዘጋጀት ይኖርበታል። ህጻናት ሲሰሩ እየተዘዋወሩ በማየት ድጋፍ ማድረግና ማበረታታት እንዲሁም ሲጨርሱ የሰሩትን ለእይታ አመቺ የሆነ ቦታ ላይ መለጠፍ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ስዕሎችን መሳል እና መቀባት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ አራት ፡- ፒዝል መገጣጠም

መጫወት

ዓላማ ፡- ፐዝሎችን ይገጣጥማሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾች እና የሰው ምስል የተሰሩ ፐዝሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለህጻናት እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም 4 እና 5 ቦታ ላይ የተቆራረጡ ፐዝሎችን ገጣጥሞ ምስሉ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- የተቆራረጡትን ፐዝሎች ለህጻናቱ ማደል
- ሁሉም ህጻናት ፐዝሎቹን እንዲገጥሙ ማድረግ
- ፐዝሎችን መግጠም ከከበዳቸው እንደየአስፈላጊነቱ ፍንጭ በመስጠት እንዲገጣጥሙ ማድረግ

ምዘና ፡- ፐዝሎችን መገጣጠም መቻላቸውን መመዘን።

ተግባር አስራ አምስት ፡-ትእዛዝን ተከትሎ በመዝለል

መጫወት

መጫወት

ዓላማ ፡- በሁለት እግራቸው እየዘለሉ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባለቀለም ኖክ ወይም ገመድ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከክፍል ውጪ መሬት ላይ በባለ ቀለም ኖክ ወይም በገመድ ህፃናቱ የሚያውቋቸውን የጂኦሜትሪ ቅርጾች አጠገብ ለአጠገብ መሬት ላይ መስራት
- ሶስት ህፃናት ከተሰሩት ቅርጾች አጠገብ እንዲቆሙ ማድረግ
- የቅርጹ ስም ሲጠራ በተጠራው ቅርጽ ውስጥ እንጣጥ ብሎ ገብቶ በመቆም እንዲጫወቱ ማድረግ
- ትክክል መሆንና አለመሆናቸውን የክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- ሁሉም ህጻናት በየተራ በጨዋታው እንዲሳተፉ ማድረግ

ምዘና ፡- በሁለት እግራቸው እንጣጥ በማለት በተጠራው ቅርፅ ውስጥ መዝለል መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ ስድስት ፡- ቅርጾችን መቆራረጥና መለጣጠፍ

መጫወት

መጫወት

ዓላማ ፡- መስመርን ጠብቀው ቅርጾችን በመቆራረጥ ይለጥፋሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ መቀስ፣ ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለህጻናት ካሬ፣ ጎነ ሶስት፣ ጎነ አራትና ክብ በወፍራም ወረቀት ላይ መሳል
- በመጀመሪያ መምህር ለእይታ አመቺ ቦታ በመቆም እንዴት ቅርጽን ቆርጦ ማውጣት እንደሚቻል ማሳየት
- ሁሉም ህጻናት መስመሩን ተከትለው እንዲቆርጡ ማድረግ
- የተቆራረጡትን ወረቀቶች በነጭ ወረቀት ላይ እንዲለጥፉ በማድረግ የተለያዩ ምስሎችን እንዲሰሩ ማለማመድ

ምዘና ፡- ቅርጾችን መቆራረጥ መቻላቸውን መከታተል።

## ተግባር አስራ ሰባት ፡- ቅርጾችን መገንባት

መጫወት

መጫወት

ዓላማ ፡- በግንባታ ብሎኮች የተለያዩ ቅርጾችን ይገነባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የግንባታ ብሎኮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህጻናቱን በቡድን በመከፋፈል የግንባታ መጫወቻዎችን መስጠት
- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን እንዲገነቡ ማድረግ
- ህፃናቱ ሲሰሩ እየተዘዋወሩ በመመልከት ማበረታታትና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ማድረግ
- ሲጨርሱም ምን እንደሰሩ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩና እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በግንባታ ብሎኮች የተለያዩ ቅርጾች መስራት መቻላቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 11. በነፃነትፈጠራን መግለጽ | 11.1. ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ማድነቅና በጥንቃቄ መያዝ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ስዕል ቀለም መቀባት

መጫወት

መጫወት

ዓላማ ፡- ከመስመር ሳይወጡ ስዕሎችን ቀለም ይቀባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ስዕል፣ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእያንዳንዱ ልጅ በወረቀት ላይ የተሳሉ የተለያዩ ስዕሎችን መስጠት
- ከመስመር ሳይወጡ የፈለጉትን በባለቀለም እርሳስ /ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- የቀቡትን ስዕል ለክፍል ጓደኞቻቸው በማሳየት ምን እንደሆነና ምን ዓይነት ቀለም እንደቀቡት እንዲናገሩ እና እንዲያደንቁ ማበረታታት

ምዘና ፡- ከመስመር ሳይወጡ ስዕሎችን ቀለም መቀባት መቻላቸውን በማየት መገምገም::

ተግባር ሁለት ፡- የሚወዱትን ገጸባህሪ መሳልና ማድነቅ

መጫወት



መጫወት

ዓላማ ፡- የሚወዱትን ገጸባህሪመሳል እና ማድነቅ ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ የተረት መፅሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናት ዕድሜያቸውን የሚመጥን ተረት መንገር
- ከተረቱ ውስጥ ማንን እንደወደዱ እና ለምን እንደወደዱ እንዲናገሩ ማድረግ
- ወረቀት እና እርሳስ በመስጠት የወደዱትን ገፀባህሪ እንዲስሉ ማድረግ
- ለክፍል ጓደኞቻቸው የሳሉትን በማሣየት ማን ምን እንደሳለ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የሚወዱትን ገጸባህሪ መሳልና ማድነቅ መለማመዳቸዉን መገምገም፡፡

ተግባር ሶስት ፡- ቅርጾችን መስራት እና ማድነቅ

ማድነቅ

መጫወት

መጫወት

ዓላማ ፡- የተለያዩ ቅርጾችን መስራት እና ማድነቅ ይሞክራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጠረጴዛ መሸፈኛ ላስቲክ፣ ጭቃ ወይም የተቦካ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የህጻናቱን ጠረጴዛዎች ላስቲክ መሸፈን
- በየጠረጴዛቸው በቂ የተቦካ ወረቀት ወይም ጭቃ መስጠት
- ለህጻናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን እንዴት ማድቦልቦልና ቅርጽ መስራት እንደሚቻል ማሳየት
- በጭቃ ድስት፣ ማንኪያ የመሳሰሉትን በመስራት ማሳየት
- ለህጻናቱም ጭቃ በመስጠት በእጃቸው እያድቦለቦሉ ኳስ፣ ጠፍጣፋ፣ ሞላላ፣ የመሳሰሉ ቅርጾችን በመስራት እንዲጫወቱ ማድረግ
- ህጻናቱ በራሳቸው ተነሳሽነት የፈለጉትን ነገር እንዲሰሩ እድሉን መስጠት
- የሰሩትን ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩና ምን እንደሰሩ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የተለያዩ ቅርጾችን መስራት እና ማድነቅ መሞከራቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- አስተውለው ያዩትን መናገር

ዓላማ ፦ ስላዩት ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮች ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ህፃናት ከክፍል ውጪ በመውጣት በግቢያቸው ውስጥ እንዲዘዋወሩ እና አስተውለው እንዲመለከቱ ማድረግ
- ከምልከታ በኋላ ግቢ ውስጥ ሲዘዋወሩ ምን ምን ነገሮችን እንደተመለከቱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- ጓደኞቻቸው ሲናገሩ ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡና እነሱም ጓደኞቻቸው ያዩትን ነገር የት እንደተመለከቱ እንዲናገሩ በማድረግ ሁሉንም ህፃናት ማሳተፍ

ምዘና ፦ ስላዩት ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮች መናገር መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፦ በማስመሰል መጫወት

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸው የሚያዩዋቸዉን ነገሮች አስመስለዉ በመጫወት ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ማድነቅ ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናቱን ከክፍል ውጪ በሚገኝ ቦታ ላይ በመውሰድ በክብ ቅርጽ እንዲቆሙ ማድረግ

ለምሳሌ ፡- መምህር ‹‹ እንደዛፍ ቅርንጫፎቻችንን እናወዛውዝ ”ሲሉ መምህርን ተከተለው እጃቸውን ወደ ጎን በማወዛወዝ ይጫወታሉ።

‹‹መኪናችንን እናሽከርክር›› ሲሉ እጃቸውን ወደፊት በማሽከርከር እና የመኪና ድምጽን በማውጣት እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ

- በዚህ ሁኔታ በአካባቢያቸው የሚያዩዋቸዉን ነገሮች በማስመሰል መጫወትን እንዲለማመዱ ማድረግ
- በአካባቢያቸው ስለሚያዩአቸው ነገሮችና ስለሚያከናውኑት ተግባራት የሚገልጹ መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ማለማመድ

ለምሣሌ ፡- እኔ ዛፍ ነኝ ፣ ቀስ በቀስ ሸረሪቷ ፣ ወፊቷን እሆናለሁ ፣ ፊትን መታጠብ እንደዚህ ነው፣ የላሊቱ ሉሊት ወዘተ…

ምዘና ፡- በአካባቢያቸው የሚያዩዋቸዉን ነገሮች አስመስለዉ በመጫወት ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ማድነቅ መለማመዳቸዉን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡- ምትን ተከትሎ በመንቀሳቀስ መጫወት

ዓላማ ፦ የተለያዩ ነገሮችን በመገንባት የፈጠራ ችሎታቸውን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የግንባታ መጫወቻ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የተለያዩ የግንባታ መጫወቻዎች በመስጠት ሕፃናት የተለያዩ ነገሮችን በመገንባት እንዲጫወቱ ማድረግ
- ገንብተው ሲጨርሱ መምህርን በመጥራት ምን እንደገነቡ እንዲናገሩና እንዲያሣዩ እድሉን መስጠት

ምዘና ፦ የተለያዩ ነገሮችን ሲገነቡ በመከታተል የፈጠራ ችሎታቸውን መገምገም::

ተግባር ስድስት ፦ የመገንባት ጨዋታ መጫወት

ዓላማ ፡- ምትን ተከትለዉ በመጫወትየማዳመጥ ክህሎታቸውን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ ቀለም ያላቸው ሪቫኖች፣ ጣሳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናት እጃቸው ላይ ቀይና ቢጫ ሪቫን በማሰር ከክፍል ውጪ ባለው ሜዳ ላይ ይዞ መውጣት
- መምህር ጣሳ በመምታት ድምጽ ሲያሰሙ እንዲሮጡ ወይም እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ
- ምቱ ሲቆም ቀይ ያሰሩት እንዲቆሙ ቢጫያሰሩት ደግሞ ቁጢጥ ብለው እንዲቀመጡ በመንገር አስተውሎ የማዳመጥ ክህሎታቸውን እና ምትን ተከትሎ የመንቀሳቀስ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምዘና ፡- አስተውለው በማዳመጥ ምትን ተከትለው መንቀሳቀስ መቻላቸውን በመከታተል መገምገም።

ተግባር ስምንት ፡- ግቢን ማጽዳት

ዓላማ ፡- ግቢን በማጽዳት ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን በጽዳት እና በጥንቃቄ መያዝን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት፣ ሳሙና፣ ውሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናት በግቢ ጽዳት ውስጥ እንዲሳተፉ ፕሮግራም ማዘጋጀት
- ሁልጊዜ በሳምንት አንድ ቀን ከክፍል ጓደኞቻቸው እና ከመምህራኖቻቸው ጋር በጽዳቱ እንዲሳተፉ ማድረግ
- ሲጨርሱም እጃቸውን በሳሙና እና በዉሃ እንዲታጠቡ በማድረግ ልምዱን እንዲያዳብሩ ማበረታታት
- ወደ ክፍል ሲመለሱ ምን ተግባራት እንዳከናወኑ በመጠየቅ አስታውሰዉ እንዲናገሩ ማድረግ

| |
|---|
| ማሳሰቢያ ፡- ለሕፃናት የተረኝነት ሰሌዳን በማዘጋጀት በግቢ ውስጥ እና በክፍል ውስጥ የሚገኙ ዕፅዋትን እንዲንከባከቡ በማድረግ ኃላፊነት የመወጣትን ብቃት ከለጋነት ዕድሜያቸው ጀምሮ እንዲለማመዱ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- በግቢ ጽዳቱ ወቅት ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን በጽዳት እና በጥንቃቄ መያዝ መለማመዳቸዉን መገምገም።

## 2.1.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም --------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም ----------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ --------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት --------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት --------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመት መጀመሪያ | በዓመት አጋማሽ | በዓመት መጨረሻ |
| **1.** ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | | | |
| 1.1.እራሳቸውን መግለጽ ይችላሉ | | | |
| 1.2. ከማንም ጋር በነፃነት ግንኙነት መፍጠር ይችላሉ | | | |
| **2.**የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ተግባራቸውን መናገር | | | |

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመት መጀመሪያ | በዓመት አጋማሽ | በዓመት መጨረሻ |
| 2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ | | | |
| 2.2. በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚከናወኑትን ተግባራት በትክክል መናገር ይችላሉ | | | |
| **3.** ዓይኖችን መንከባከብ | | | |
| 3.1. ዓይኖቻቸው በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ | | | |
| **4.** ጆሮዎችን መንከባከብ | | | |
| 4.1. ጆሮዎቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ | | | |
| **5.** የማሽተት ስሜት ሕዋስን መጠቀም አፍንጫን መንከበካብ | | | |
| 5.1. በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን ሽታ መለየት ይችላሉ | | | |
| **6.** የመቅመስ ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ | | | |
| 6.1 . የምግቦችን ጣዕም መለየት ይችላሉ | | | |
| 6.1. አፋቸውን በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ | | | |
| **7.** በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መግለጽ | | | |
| 7.1. ስለነገሮችና ቁሶች ባህርይ፣ የሙቀት መጠንና ቅርጽ መለየት ይችላሉ | | | |
| 8.ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ሥርዓቶችን መለማመድ | | | |
| 8.1. የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ | | | |
| 9.አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ | | | |
| 9.1. አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ | | | |
| 10.ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም | | | |
| 10.1. በሰውነት ክፍሎቻቸው ተገቢውን እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ | | | |
| 10. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ | | | |
| 11.1. ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ማድነቅና በጥንቃቄ መያዝ ይችላሉ | | | |

## 2.2 ተቀባይነት ባለው መልኩ ከሌሎች ጋር ግንኙነት መፍጠር

### 2.2.1 ማብራሪያ

ተቀባይነት ባለው መልኩ ከሌሎች ጋር ግንኙነት መፍጠር ሕፃናት ከሰዎች ጋር ሊኖራቸው በሚገባው ግንኙነትና ማህበራዊነትን የማዳበር አቅጣጫ ላይ ያተኮረ ነው።

አንድ ሕፃን ከወላጆቹ፣ ከመምህራን፣ ክትትል ከሚያደርጉለትና ከዕድሜ እኩዮቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በመልካም ሁኔታ እንዲዳብር ሁኔታዎች ከተመቻቹለት ሕፃኑ ለራሱ እና ለሌሎች ምቹ የሆነ ማህበራዊ ሕይወት እንዲኖረውና የስሜት መረጋጋት እንዲያገኝ ይረዳዋል።

ስለዚህ ተቀባይነት ያላቸውን ልማዶችና የኑሮ ስርዓቶች መልመድ፣ ስሜትን በተገቢው መንገድ መግለጽ ከሌሎች ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር በአጠቃላይ ተገቢ ማሕበራዊ ሕይወትን ማዳበር ገና ከጠዋቱ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

መምህራንም ሆኑ ወላጆች በተቻለ መጠን ለልጆች አስፈሪ ነገሮችን ባለማውራት፣ የተለያዩ ማስፈራሪያ ቃላቶችንና ንግግሮችን ባለመናገር የራስን ፍርሃት ለልጆች ባለማሣየት ወዘተ... የሕፃናትን ተፈጥሮአዊ የልጅነት ፍርሃት ይበልጥ እንዳይጨምር /እንዳይባባስ/ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

መምህራን ስለእያንዳንዱ ሕፃን ባህርይ ከወላጆች ጋር በመወያየት ስለግላዊና ሕይወታቸው ግንዛቤ መያዝ ይኖርባቸዋል። ጉልህ የባህርይና የማህበራዊ ችግር ያለባቸው ሕፃናትን ለመርዳት ከባለሙያ ጋር መወያየት ወይም ወላጆች ሁኔታውን ተረድተው ባለሙያ እንዲያነጋግሩ ማድረግ በግዜው ችግሮችን ለመቅረፍ ያግዛል።

በሕፃንነታቸው ጥሩ የሆነ ማህበራዊ ትስስርና የስሜት መረጋጋት ያላቸው ሕፃናት በወደፊት ሕይወታቸው ስኬትና በትምህርት ቤትም ጥሩ ተሳትፎ ይኖራቸዋል። የተረጋጋ ሕይወት የሚመሠረተው ከሕፃንነት ጀምሮ እርጋታ ባለው እንክብካቤና በጥሩ ማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ማደግ ሲቻል ነው።

ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ጥሩ ማህበራዊ ሕይወት መሠረት ያልተጣለላቸውና የተረጋጋ ስሜት ይዘው ያላደጉ ሕፃናት ለድብርት፣ ለብስጭት፣ ለጉልበተኛነት ወይም በፍርሃት ለመሸማቀቅና ለአሉታዊ አመለካከት የተጋለጡ ይሆናሉ።

### **2.2.2.** አጠቃላይ ዓላማዎች

1. በቤትና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ የሚያገኙአቸውን ሰዎች መለየትና ማስተዋል፣ ኃላፊታቸውን መረዳትና መናገር እንዲችሉ ለማድረግ
2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው መናገር እንዲችሉና ጥሩ የስሜት ግንኙነት እንዲኖራቸው ለማድረግ
3. የሌሎችን ስሜት መረዳት፣ ስሜታቸውን መጋራት ያላቸውን ነገር የማካፈል ጥሩ ዝንባሌ እንዲኖራቸው ለማድረግ

### **2.2.3** የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከትና ለማወቅ ፍላጎት ማሣደርና መለየት
   - 1.1. በቤትና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ያሉትን ሰዎች በማስተዋል መናገር ይችላሉ
   - 1.2. ሰዎች በቤታቸውና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ያላቸውን ኃላፊነት በማየት መናገር ይችላሉ
   - 1.3. አብረዋቸው ለሚጫወቱ ጓደኞቻቸው ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሣየት ይችላሉ
2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ
   - 2.1. ሰዎች በቤታቸውና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ስለሚያከናውኗአቸው ተግባራት መናገር ይችላሉ /ወላጅ፣ ሞግዚት፣ቤተዘመድ/
   - 2.2. ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቁላቸውንና እንደሚንከባከቧቸው መግለጽ ይችላሉ
3. ሌሎችን መንከባከብና ያለንን ነገር ማካፈል
   - 3.1. የሌሎችን ስሜት መጋራት ይችላሉ

2.2.4 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት፣ ለማወቅ ፍላጎት ማሣደርና መለየት | 1.1. በቤትና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ያሉትን ሰዎች በማስተዋል መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የቤተሰብ አባላቶችን መለየት

ዓላማ ፦ የቤተሰብ  አባላቶቻቸዉን ለይተዉ ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- በጠዋት ሪፖርት ክፍለ ጊዜ አብረዋቸው የተለያዩ ነገሮችን ስላደረጉ የቤተሰብ አባላቶቻቸው እንዲናገሩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማበረታታት

ለምሣሌ፦ ከማን ጋር ሽርሽር ሄድክ? ማነው ገላህን/ሽን ያጠበህ/ሽ? ወዘተ…

ምዘና ፦ የቤተሰብ አባላቶቻቸዉን ለይተዉ መናገራቸዉን ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር ሁለት ፦ የቤተሰብ አባላትን ግንኙነት መናገር

ዓላማ ፦ በቤታቸዉ ያሉ ሰዎችን ግንኙነት ለይተዉ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦  የቤተሰብ አባላትን የሚያሣይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የቤተሰብ አባላትን የሚያሣይ ባለቀለም ከፍ ያለ ስዕል ማቅረብ
- በእርጋታ እንዲመለከቱ ማድረግ
- በስዕሉ ላይ ስለሚመለከቷቸው ሰዎች መጠየቅ

  ለምሣሌ፦ ስለ አባት፣ ስለ ወንድም፣ ስለ እህት ወዘተ…

- እነዚህን ሰዎች የት እንደሚያገኙአቸው? ግንኙነታቸው ምን እንደሆነ? እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ በቤታቸዉ ያሉ ሰዎችን ግንኙነት ለይተዉ መናገር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር ሶስት ፦ የሰዎችን መገለጫ መናገር

ዓላማ ፡- ሰዎች ያላቸዉን መገለጫ ለይተዉ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ አካላዊ መጠን ያላቸው ሰዎች ስዕል ወይም ፎቶግራፍ የያዘ አልበም

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያየ ዕድሜና አካላዊ መጠን ያላቸውን ሰዎች ስዕሎች ወይም ፎቶግራፎች የያዘ አልበም ማዘጋጀት /ከተቻለ በቁጥር በርከት ማድረግ/
- ሕፃናት አልበሙን አገላብጠው በማየት ረጅም ነው /ናት አጭር ነው /ናት ወዘተ... በማለት እንዲናገሩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማሣተፍ
- መናገር ከከበዳቸው ፍንጭ መስጠት

  ለምሳሌ፡- ይህ ስዕል/ፎቶ/ የትልቅ ሰው ነው? ልጅ ናት? ወፍራም ናት? ቀጭን ናት? ወዘተ... በማለት በመጠየቅ

ምዘና ፡- ሰዎች ያላቸዉን መገለጫ ለይተዉ መናገር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አራት፡- ድርጊቶችን ማስመሰል

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸዉ ያሉ ሰዎችን ድርጊቶች አስመስለዉ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመስሎ መጫወት ማዕዘን መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በመስሎ መጫወት ጨዋታ ማዕዘናት የተለያዩ ሰዎች ድርጊትን በማሣየት እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት
- በሚጫወቱበት ሰዓት አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ
- ድጋፍ በሚያስፈልግበት ወቅት ጨዋታው በማይረበሽ መልኩ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ

ምዘና ፡- በአካባቢያቸዉ ያሉ ሰዎችን ድርጊቶች አስመስለዉ መጫወት መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- ድርጊትን በማየት መግለጽ

ዓላማ ፡- የተለያዩ ድርጊቶችን መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ድርጊቶችን በማከናወን ላይ ያሉ ሰዎች ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ ድርጊቶችን በማከናወን ላይ ያሉ ሰዎችን ስዕል ማሣየት
- ስዕሉን በመመልከት በስዕሉ ላይ ስላዩአቸው ሰዎች መናገር እንዲችሉ ማወያየት
- ከከበዳቸው የተለያዩ ፍንጭ ሊሰጡ የሚችሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማገዝ

ምዘና ፡- የተለያዩ ድርጊቶችን መግለጽ መለማመዳቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጐት ማሣደር እና መለየት | 1.2. በቤታቸውና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ የሚሰሩ ሰዎች ያላቸውን ኃላፊነት በማየት መናገር ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፡- ስለጓደኞች መናገር**

ዓላማ ፡- ስለጓደኞቻቸው ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከማን ጋር እንደሚጫወቱ፣ ምን ምን ዓይነት ጨዋታዎች እንደሚጫወቱ እና ጓደኞቻቸው እነማን እንደሆኑ መጠየቅ
- በጓደኞቻቸው ፊት ስለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ እንዲሁም ማበረታታት

ምዘና ፡- ስለጓደኞቻቻው መናገር መቻላቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- ሰዎች የሚያከናዉኗቸዉን ተግባራት ስእል ቀለም  በመቀባት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባለቀለም እርሳስ/ከለር፣ የሚቀቡ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሰዎች የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናዉኑ የሚያሣይ ስዕልን ማደል

  ለምሣሌ ፡- ልጅ ያዘለች እናት፣ ልጅ የሚያጫውት አባት ወዘተ… ማድረግ

- እንዴት እንደሚቀባ ቀብቶ ማሣየት

ተግባር ሁለት ፡- ሰዎች የሚያከናዉኗቸዉን ተግባራት ስእል ቀለም መቀባትና መናገር

እያከናወኑ እንደሆነ እንዲናገሩ ማበረታታት

ለምሣሌ ፡- ልጅ ያዘለች እናት፣ ልጅ የሚያጫውት አባት ወዘተ… ማድረግ

ምዘና ፡- ሰዎች የሚያከናዉኗቸዉን ተግባራት ስእል ቀለም መቀባታቸውንና የቀቡት ስእል ላይ ያዩትን ተግባራት መናገራቸውን በማየትና በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- በአፀደ ሕፃናት ቅጥር ግቢ ዉስጥ የሚሠሩ ሰዎችን የስራ ድርሻ ለይተዉ ይናገራሉ።

ተግባር ሶስት ፡- የሰዎችን ስራ ድርሻ መለየት

የአተ

- በአፀደ ሕፃናት ግቢ ውስጥ ከሚሠሩ ሰዎች የማንን ስም እንደሚያውቁ መጠየቅ
- የሚያውቁትን ሰው ስም ሲናገሩ ምንድነው ሥራዋ/ዉ በማለት መጠየቅ

  ለምሳሌ፡- መምህር ናት/ነው?ጥበቃነዉ/ናት?

- በየተራ እንዲናገሩ ዕድል መስጠት እና ማበረታታት
- መናገር ካቃታቸው <<እኔ እከሌን አውቃለሁ። መምህር ናት። አንተስ? አንቺስ? ማንን ታውቃላችሁ?>> በማለት መጠየቅእና እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- በአፀደ ሕፃናት ቅጥር ግቢ የሚሠሩ ሰዎችን የስራ ድርሻለይተዉ መናገር መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የስራ ድርሻዎችን አስመስለዉ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመስሎ መጫወት ጨዋታ ማዕዘናት መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በመስሎ መጫወት ጨዋታ /የሱቅ፣ የቤተሰብ፣ የክሊኒክ ወዘተ.../ ማዕዘናት የፈለጉትን ሰው ሚና /የሥራ ድርሻ/ ይዘው እንዲጫወቱ ማድረግ
- የጨዋታው ጊዜ ሲያበቃ ምን ዓይነት ጨዋታ እና የማንን የሥራ ድርሻ ወክለው እንደተጫወቱ ማወያየት

ምዘና ፡- የስራ ድርሻዎችን አስመስለዉ መጫወት መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- የስራ ድርሻን መስሎ መጫወት

| የሚጠበቀ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት፣ ለማወቅ ፍላጐት ማሣደር እና መለየት | 1.3. አብረዋቸው ለሚጫወቱት ጓደኞቻቸው ተቀባይነት ያለውን ባህርይ ማሳየት ይችላሉ። |

ዓላማ ፡- ተግባር አንድ ፡- በሕብረት መስራት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለጽዳት አስፈላጊ ዕቃዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሁሉም ሕፃናት የግቢያቸውን ንጽህና መጠበቅ እንዳለባቸው ማስረዳት
- በሕብረት የጽዳት ሥራ የሚሰሩበትን ፕሮግራም ማዘጋጀት
- በቡድን መከፋፈልና በሕብረት /በቡድን/ የሚሠሩትን ሥራ መጥኖ መስጠት
- ሲሰሩ ተባብረው መሥራታቸውን እና ለሥራ ያላቸውን ስሜት መከታተል
- ከሥራ በኋላ ምን? እንዴት? ከማን? ጋር እንደሠሩ መጠየቅ
- አብሮ የመሥራትና የመረዳዳት ስሜት አስፈላጊነት በደረጃቸው እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- በሕብረት የመስራት ችሎታቸዉን በማየት መገምገም።

ዓላማ ፡- በጋራ ሲጫወቱ ተቀባይነት ያለው ባህሪ ማሳየትን ያዳብራሉ።

የመርጃ

**ተግባር ሁለት ፡- ተቀባይነት ያለው ባህሪ ማሳየት**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሌሎች ሰዎችም ሆነ የጓደኞቻቸውን ዕቃ ለመውሰድ ወይም ለመዋስ ከፈለጉ በቅድሚያ መጠየቅ /ማስፈቀድ/ እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ
- የተለያዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ ሕፃናቱ እንዲለማመዱ ማድረግ እንዲሁም መምህር ምሳሌ ሆነዉ ማሳየት
- የተለያዩ የክፍል ውስጥ ጨዋታዎችን አብረው እንዲጫወቱ ማድረግ
- በሕብረት የተጫወቱባቸውን መጫወቻዎች ሁሉም ተረዳድተው ወደ ቦታው እንዲመልሱ እና ቦታውን የማጽዳት ልምድ እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በጋራ ሲጫወቱ ተቀባይነት ያለው ባህሪ ማሳየታቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ ሕግን አክብረዉ በጋራ መጫወትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በክፍል ውስጥና ውጭ የሚገኙ መጫወቻዎች፣ የተረት መጽሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የተለያዩ በሕግ የሚመሩ ጨዋታዎችን /አረንጓዴ አረንጓዴ፣ ጭራ ነቀላ፣ያዕቆብ/ ማቀድና ማጫወት
- የጨዋታውን ሕግና ሂደት እንዲረዱና ለጨዋታ ሕግ ተገዢ መሆንን እንዲለማመዱ ማድረግ
- ከክፍል ውጭ ባሉ መጫወቻዎች ላይ ሕፃናት በትዕግሥት ተራቸውን ጠብቀው ሳይገፋፉ እንዲጫወቱ ማለማመድ
- ተራን ጠብቆ መጫወትን፣ ሌሎችን ሲጫወቱ ባለማቋረጥና ባለመረበሽ የመጫወት ልምድን እንዲያዳብሩ ማድረግ
- ሕፃናትን በጋራ /በሕብረት/ በመጫወት ከክፍል ውጪ እንዲሁም በክፍል ውስጥ የሚገኙ መጫወቻዎች የአንድ ሕፃን ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሕፃናት መሆናቸውን ማስገንዘብ
- የ ... ረግ እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- የ ... ሊኖርባቸው ማስረዳት

ተግባር ሶስት ፦ ሕግን አክብሮ መጫወት

- “ማነው የሚበልጠው?” ተረትን መተረት
- በሕብረት ጨዋታ ላይ ሁልጊዜ አንድ ሕፃን ብቻ የጨዋታ ጀማሪ እንደማይሆን ማስረዳት
- በአንዳንድ የውድድር ጨዋታዎች ላይ መሪ ወይም አጫዋች ሊሆን የሚችለው ጨዋታውን ያሸነፈ እንደሚሆን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ ሕግን አክብረዉ በጋራ መጫወት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ ጥሩ ባህሪን ለይተዉ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሀፍ፣ የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- "የውርዬና ቦቢን" ተረት መተረክና ሥራ አክባሪነትን፣ ይቅርታ ጠያቂነትን፣ ተረዳድቶ መሥራትን፣ ለሥራ ያለመለገምን ወዘተ… እንዲረዱ ማድረግ
- "ጥንቸል ጉረኛው" መዝሙርን አብሮ መዘመርና ከመዝሙሩ የሚያገኙትን ጥሩና አላስፈላጊ ባህሪን በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፦ ጥሩ ባህሪን ለይተዉ መናገር መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፦ ሰዎችን በእድሜያቸው ማክበር

ተግባር አራት ፦ ጥሩ ባህሪን መለየት

ዓላማ ፡- ሰዎችን በእድሜያቸው የማክበር ባህልን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በዕድሜ የገፉ የወንድና የሴት ምስል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህጻናቱ በዕድሜ የገፋ የወንድና የሴት ምስልን ማሳየት
- እነሱ በሚኖሩበት ቤት አካባቢ እንደነዚህ ዓይነት ትላልቅ ሰዎች መኖራቸውንና አለመኖራቸውን መጠየቅ
- ማን ብለው እንደሚጠሯቸው፣ ከእነሱ በምን እንደሚለዩ ወዘተ... መጠየቅና ማወያየት
- በዕድሜያቸው የገፉ ሴቶችን እማማ፣ ወንዶቹን አባባ በማለት መጥራትን ማለማመድ
- አዋቂዎች ሰላምታ ሲሰጡአቸውም የአክብሮት ቃልን መጠቀም እንዳለባቸው ማስተማር
- ለአዋቂዎች ዕቃዎችን ሲሰጡም ሆነ ከእነሱ ሲቀበሉ በሁለት እጃቸው ጎንበስ በማለት አመስግነው መቀበል እንዳለባቸው መንገር

ምዘና ፡- ሰዎችን በእድሜያቸው መለየትና እንደት ማክበር እንዳለባቸው መረዳታቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- በእድሜ የገፉ ሰዎችን የማክበር ባህልን በተግባር መለማመድ

ዓላማ ፡- በእድሜ የገፉ ሰዎችን የማክበር ባህልን በተግባር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አዋቂዎች የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ አልባሳት እና ቁሳቁሶች

ለምሳሌ፡- ነጠላ፣ ከዘራ፣ ሻሽ፣ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- አዋቂዎች የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ አልባሳትንና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት

  ለምሳሌ፡- ነጠላ፣ ከዘራ፣ ወዘተ…
- በመጀመሪያ መምህር በዕድሜ እንደገፋ ሰው በመልበስና በመምሰል ለህጻናቱ ሰላምታ መስጠት
- ከዛም የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመስጠት ህጻናት በንግግርና በድርጊት ለአዋቂዎች ያላቸውን ክብር እንዴት እንደሚገልጹ በማሳየት እንዲለማመዱ ማበረታታት ከተሳሳቱም እርማት መስጠት

ምዘና ፡- በእድሜ የገፉ ሰዎችን በተግባር የማክበር ባህል ማዳበራቸውን መገምገም።



ተግባር ሰባት ፡- ስጦታ ማዘጋጀት

ዓላማ ፡- መልካም ነገር ለሚያደርጉላቸው ሰዎች ሰጦታ አዘጋጅተው ይሰጣሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር፣ ወረቀት፣ ኮላ ወዘተ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትናንሽ ወረቀት ላይ ሁሉም ህጻናት የሚፈልጉትን ነገር እንዲስሉና ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- የሁሉንም ህጻናት ስዕሎች በትልቅ ወረቀት ላይ መለጠፍ
- ጉብኝት በሚሄዱበት ጊዜ ለሚያስጎበኛቸው ሰው ከአንገታቸው ጎንበስ በማለት ሰላምታ መስጠት እንዳለባቸው ማስተማር እና ማለማመድ
- ከጉብኝት መጨረሻ ላይም ያስጎበኛቸውን ሰው ማመስገን እንዳለባቸው በመንገር ላስጎበኛቸው ሰው በመጀመሪያ የተዘጋጀውን ስዕል በስጦታ መልክ እንዲያበረክቱ ማድረግ

ምዘና ፡- ስጦታ በማዘጋጀት መልካም ነገር ለሚያደርጉላቸው ሰዎች መስጠት መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።



ተግባር ስምንት ፡- የውሸትን ጉዳት መረዳት

ዓላማ ፡- መዋሸት ጉዳት እንደሚያስከትል ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍ፣ የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/፣ ለድራማ የሚሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ውሸታሙ እረኛ ተረትን በመንገርና መዝሙሩን በማዘመር ውሸታም መሆን ጥሩ እንዳልሆነ ማስተማር
- ውሸታም ሰውን ሰዎች እንደማይወዱትና መዋሸት ራስን እንደሚጎዳ እንዲረዱ ማድረግ
- ይንንም በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ማነቃቃትና ማበረታታት

ምዘና ፡- መዋሸት ጥሩ ባህሪ እንዳልሆነና ጉዳት እንደሚያስከትል መረዳታቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር ዘጠኝ ፡- የጥሩ ስነምግባር መገለጫዎችን መለየት

ዓላማ ፦ የጥሩ ስነምግባር መገለጫዎችን ለይተው ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሀፍ ለድራማ የሚሆኑ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የውርዬና ቦቢን ተረት ለህጻናቱ በመተረክ ተባብሮ የመስራትን ጠቀሜታ መንገር
- ሲያጠፉ ይቅርታ መጠየቅና ይቅርታ ሲጠይቁም ይቅርታ ማድረግ ጥሩ እንደሆነ እንዲረዱ ማድረግ
- ይህንንም በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ማነቃቃትና ማበረታታት
- የራስ ያልሆነ ንብረትን ለባለቤቱ መመለስ ተገቢና የሚያስመሰግን ተግባር መሆኑን በገጠመኞች መንገር
- ህጻናት በክፍልና ከክፍል ውጪ ወድቆ ያገኙትን የእነሱ ያልሆነ ንብረትን አምጥተው ለመምህር ሲሰጡ በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት በጎ ተግባሩን አጉልቶ መናገርና ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ማድረግ

ምዘና ፦ የጥሩ ስነምግባር መገለጫዎችን ለይተው መናገር መቻላቸውን መገምገም።



ተግባር አስር ፦ ጥሩ ስነምግባር ማዳበር

ዓላማ ፦ ጥሩ ስነምግባርን ማዳበር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ትንሽ አራት ማዕዘን የወንበር ሳጥን

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ትንሽ አራት ማዕዘን የሆነ የወንበር ሳጥን ከእንጨት በማዘጋጀት ህጻናቱ በተለያዩ ስዕሎችና ወረቀቶች እንዲያሸበርቁት ማድረግ
- ወንበሯን ሁልጊዜ ህጻናቱ በማይደርሱበትና ለዕይታ አመቺ የሆነ ቦታ ላይ ማስቀመጥ
- ህጻናት በጎ ምግባርን ሲሰሩ ወንበሯን አውርዶ ከህጻናቱ ፊት በማስቀመጥ ጥሩ ስነ ምግባር ያሳየን/ያሳየችን ህጻን ጠርቶ ወንበሩ ላይ ማቆም
- ያደረጉትን በጎ ምግባር ለክፍል ጓደኞቻቸው በመንገር እንዲጨበጨብላቸው ማድረግ
- ሌሎቹም ህጻናት በጎ ተግባር /ምግባር/ ለመፈጸም እንዲነቃቁ ማድረግ
- የሳጥን ወንበሩን ወደ ነበረበት ቦታ መመለስ

ምዘና ፦ ጥሩ ስነምግባር ማዳበር መጀመራቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ አንድ ፦ ከወላጆች ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር

ዓላማ ፡- ከወላጆቻቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠር ማድረግ ያለባቸውን ተረድተው ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ መዝሙር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህጻናትን ወላጆቻቸው ምን ምን እንደሚገዙላቸው መጠየቅ
- ወላጆቻቸው የተለያዩ ነገሮች ሲገዙላቸውና መልካም ነገር ሲያደርጉላቸው ምን መልስ እንደሚሰጡ መጠየቅ
- ለሚደረግላቸው መልካም ነገር ሁሉ አመሰግናለሁ ማለት እንዳለባቸው ማስረዳት
- የተለያዩ ጥፋቶችን ሲያጠፉ ወላጆቻቸውንም ሆነ ሌሎችን ይቅርታ መጠየቅ እንዳለባቸው መንገር
- በመጨረሻም "ወላጆቼን መምህሬን እወዳለሁ" የሚለውን መዝሙር በማዘመር ትምህርቱን ማጠናከር

ምዘና ፡- ከወላጆቻቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠር ማድረግ ያለባቸውን ተረድተው እያደረጉ እንደሆነ ወላጆቻቸውን በመጠየቅ መከታተል።

## ተግባር አስራ ሁለት ፡- የለጋስነት ባህሪን ማዳበር

ዓላማ ፡- የለጋስነት ባህሪ ማዳበር ይለማመዳሉ።።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከህጻናቱ ወላጆች ጋር በመነጋገር ህጻናቱ የማይለብሱት ልብስና የማያደርጉት ጫማ ካለ እንዲያመጡ በማድረግ ለችግረኞች የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- በህጻናቱ ለጋ አእምሮ ውስጥ የተቸገረን ሰው አቅም በቻለ መጠን የመርዳት የበጎ ተግባር ጽንሰ ሀሳብ እንዲቀርጽ ማድረግ
- በወር ወይም በሁለት ወር አንድ ቀን መወሰንና ህጻናቱ 10 ሳንቲም እንዲያመጡ በማድረግ ለችግረኛ ህጻናት የመማሪያ ቁሳቁስ ተገዝቶ በክፍሉ ህጻናት ስም የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት

ምዘና ፡- የለጋስነት ባህሪ ማዳበር መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ ሶስት ፡- ሰዓት የማክበር ልምድን ማዳበር

ዓላማ ፦ ሰዓት የማክበር ልምድ ያዳብራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ህጻናት ከጨዋታ ወደ ክፍል ሲገቡ ለክፍል ጓደኞቻቸውና ለመምህራን እንዴት አደራችሁ እንዲሉ ማለማመድ
- ማለት የማይችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ራስን ዝቅ በማድረግ ሰላምታ ሰጥቶ መግባት እንዳለባቸው ማለማመድ
- ህጻናት ጠዋት አርፍደው ሲመጡ በጓደኞቻቸው ፊት በመቆም መምህርና የክፍል ጓደኞቼ ስላረፈድኩኝ ይቅርታ ብለው እንዲጠይቁ ማድረግና ህጻናቱም ይቅርታ አድርገንልሃል/ሻል ለሁለተኛው አታርፍድ/አታርፍጂ በማለት ይቅርታ መጠየቅንና ማድረግን እንዲማሩ ማለማመድና ማርፈድ ጥሩ እንዳልሆነ እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፦ ሰዓት የማክበር ልምድ ማዳበር መጀመራቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | 2.1. ሰዎች በቤታቸውና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ስለሚያከናውኑአቸው ተግባራት መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ተግባራትን አስመስሎ መጫወት

ዓላማ ፡- ሰዎች የሚያደርጓቸውን የተለያዩ ተግባራት አስመስለዉ መጫወት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለመስሎ መጫወት የሚያገለግሉ የተለያዩ አልባሳት እና ቁሳቁዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ወላጆችን፣ ሞግዚቶችን፣ መምህራኖችን ወዘተ በየተራ ስማቸውን መጥቀስ
- ምን እንደሚያደርጉላቸውና ለምን እንደሚያደርጉላቸው መጠየቅ
- ሕጻናቱ ከላይ ስለተጠቀሱት ሰዎች ሙያ መናገር እንዲችሉ ማበረታታት
- ሰዎች የሚያደርጓቸውን የተለያዩ ተግባራት ሊያንፀባርቁ የሚችሉባቸውን የተለያዩ የመስሎ መጫወት ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ማጫወት

ማስታወሻ ፡- ሚና ሲመርጡ ግን የራሳቸውን ፍላጐትና ዝንባሌ ተከትለው እንዲሆን ነፃነት መስጠት ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ሰዎች የሚያደርጓቸውን የተለያዩ ተግባራት አስመስለዉ መጫወት መለማመዳቸዉን መገምገም።

**ዓላማ ፦ ለሌሎች መደረግ ያለበትን እንክብካቤ ይረዳሉ።**

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሐፍት፣ የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/**

**የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦**

- “ትንሹ ዮናስ” እና ሌሎች የሰዎችን እንክብካቤ የሚገልፁ መሰል ተረቶችን መርጦ መተረክ
- ከታሪኩ የትኛው ገፀባህሪ /ባለ ታሪክ/ እንዳስደሰታቸው ወይም እንደወደዱት ለምን እንደወደዱት፣ የትኛው ገፀባህሪ /ባለ ታሪክ/ እንዳሳዘናቸውና ለምን እንዳዘኑ እንዲናገሩ በማድረግ ማወያየት
- የተረቱን ይዘት በጥያቄና መልስ እንዲረዱ ማድረግ፣
- ማገዝ
- ትኩረት በማድረግ ማጠቃለል
- “ሃሎ ሃሎ” መዝሙርን ከሕፃናት ጋር አብሮ በመዘመር የጓደኝነትን ጥሩ ባህሪ እንዲረዱ ማድረግ

**ተግባር ሁለት ፦ ለሌሎች መደረግ ያለበትን እንክብካቤ መረዳት**

**ምዘና ፦ ለሌሎች መደረግ ያለበትን እንክብካቤ መረዳታቸዉን መገምገም።**

ዓላማ ፡- እንክብካቤ ስለሚያደርጉላቸው ሰዎች ያላቸዉን ስሜት መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘ[illegible]

**ተግባር ሦስት ፡- ስሜትን በስእል መግለጽ**
መረዳት

- ለሕፃ[illegible] ከወላጅ፣ ከመምህር ወይም ከሞግዚት የፈለጉትን እንዲስሉና ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- ማንን እና ለምን እንደሳሉ በመጠየቅ ስሜታቸውን እንዲያንፀባርቁ ማበረታታት

> ማስታወሻ፡- ሕፃናት በአካባቢያቸው ማለትም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የሚገኙ ሙያተኞች ስለሚያደርጉላቸው እንክብካቤ እንዲናገሩ እና እንዴት እነዚህን ሙያተኞች ማክበር እንደሚገባቸው ማወያየት።

ምዘና ፡- እንክብካቤ ስለሚያደርጉላቸው ሰዎች ያላቸዉን ስሜት ለመግለጽ መሞከራቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | 2.2. ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቁላቸውና እንደሚንከባከቧቸው መግለጽ ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፡- እንክብከቤ ስለሚያደርጉላቸው ሰዎች መናገር**

ዓላማ ፡- እንክብከቤ ስለሚያደርጉላቸው ሰዎች ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለመስሎ መጫወት የሚያገለግሉ አልባሳት እና ቁሳቁስ፣ የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- "እናት አባቴን እወዳለሁ" የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ
- እናት እና አባታቸው ስለሚያደርጉላቸው ጥንቃቄና እንክብካቤ እንዲናገሩ የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- በመስሎ መጫወት በተለይ በቤተሰብ ጨዋታ እንዲሳተፉ ማበረታታት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- የጨዋታ ማዕዘናት ለሁሉም ሕፃናት ላይበቁ ስለሚችሉ ያልተጫወቱ ሕፃናት የሚጫወቱበትን ሁኔታ በየጊዜው በማመቻቸት የትምህርታዊ፣ የግንባታ ወዘተ... ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- እንክብከቤ ስለሚያደርጉላቸው ሰዎች መናገር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- ለሌሎች ጥንቃቄ የማድረግ አስፈላጊነትን መረዳት

ዓላማ ፡- ለሌሎች ጥንቃቄ የማድረግን አስፈላጊነት ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በተረት ወይም በገጠመኝ መልክ ለሌሎች ያስቡና ይጠነቀቁ ስለነበሩ ሰዎች ማቅረብ
- ሰዎች እርስ በርስ እንዳይቀያየሙ /እንዳይጐዳዱ/ እንዴት ይጠነቀቁ እንደነበር በተረዱት ላይ ማወያየት
- የሌሎች ሰዎችን ስሜት መረዳትና ሌሎችን አለማስከፋት ጥሩ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግ።

ምዘና ፡- ለሌሎች ጥንቃቄ የማድረግን አስፈላጊነት መረዳታቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- ሰዎች የሚያደርጉላቸዉንጥንቃቄ ተረድተዉ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሥዕሎች፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ሂደ ቅደም ፡-

**ተግባር ሦስት ፡- ሰዎች ስለሚያደርጉላቸው ጥንቃቄ መናገር**

- 
- ለእያንዳንዳቸው የተለያየ ስእል በመስጠት ቀም እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም የምን ስእልን ቀለም እንደቀቡና ቀለም የቀቧቸው ሰዎች እነሱን እንዴት እንደሚንከባከቡቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- መልሳቸውን መሠረት በማድረግ እያንዳንዳቸው በቤት ውስጥ እና ውጪ እንዲሁም በትምህርት ቤታቸው እንዴት እንደሚንከቧከቧቸው ማስገንዘብ

ምዘና ፡- ስለሚደረግላቸዉ ጥንቃቄ ተረድተዉ መናገራቸዉን መገምገም።

## ተግባር አራት ፦ ለሌሎች ጥንቃቄ ማድረግን መለማመድ

ዓላማ ፦ ለሌሎች ጥንቃቄ ማድረግን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ለመስሎ መጫወት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- መስሎ መጫወት ጨዋታዎች ማዘጋጀት
- በመስሎ መጫወት ጨዋታዎች አብረዋቸው ለሚጫወቱ ጓደኞቻቸው መጠንቀቅ ማለትም የሚያስቆጣ ነገር ቢያጋጥም እንኳን አለመሳደብ፣ አለመገፋተር፣ አለመማታት፣ መጫወቻዎችን አለመቀማት ከጨዋታ ውጣ /ጪ/ ብሎ አለማባረር ወዘተ… ተገቢ ባህሪ እንደሆነ ማስገንዘብ
- በጨዋታ ሂደት ላይ ሚና ይዞ በመግባት /አብሮ በመጫወት /እንዲገነዘቡ ማድረግ
- መምህር ከላይ የተጠቀሱትን አላስፈላጊ ንግግሮችንና ባህርያትን ባለመናገርና ባለማሣየት አርአያ ሆኖ መገኘት

ምዘና ፦ ለሌሎች ጥንቃቄ ማድረግ መለማመዳቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ሌሎችን መንከባከብና ያለን ነገር ማካፈል | 3.1. የሌሎችን ስሜት መጋራት ይችላሉ። |

## ተግባር አንድ ፦ የስሜት መገለጫዎችን መለየት

ዓላማ ፡- የስሜት መገለጫዎችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የሰዎችን ስሜት የሚያሳዩ ስዕሎች ወይም ፎቶግራፎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የሰዎች የስሜት መገለጫዎች /የተከፉ፣ የተቆጡ፣ የተደሰቱ ወዘተ.../ የሚታዩባቸውን ስዕሎች ከተቻለም ፎቶግራፎች ማሣየት
- ስላዩት ስሜት ተገቢውን የስሜት መግለጫ ቃል በመጠቀም ተከፍቷል፣ አዝኖአል፣ ተደስቷል ወዘተ... ብለው እንዲናገሩ ማበረታታት
- ሲደሰቱ፣ ሲያዝኑ፣ ሲቆጡ ወዘተ...በፊት ገጽታቸው ላይ እንዴት ዓይነት መገለጫዎች እንደሚታዩባቸው በየተራ እየተነሱ እንዲያሳዩ ማድረግና ማበረታታት

ምዘና ፡- የስሜት መገለጫዎችን ምንነት በመጠየቅ እና እንዲያሳዩ በማድረግ የስሜት መገለጫዎችን መለየታቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ሁለት ፡- ከመዝሙር እና ከተረቶች የስሜት መገለጫዎችን መለየት

ዓላማ ፡- ከመዝሙር እና ከተረቶች የስሜት መገለጫዎችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረትመጽሐፍት፣ የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- "የላሊቱ ሉሊት" ተረትን መተረክና አዳምጠው ማንን እንደወደዱ፣ ለምን እንደወደዱ፣ ማን ደስ እንዳላቸው ወዘተ... ከስሜት መገለጫ ጋር እንዲናገሩ ማድረግ
- ተረቱን ከነመዝሙሩ ደግመው እንዲናገሩና እንዲዘምሩ ማድረግ
- የባለታሪኮቹን ስሜት በተለያየ መንገድ መግለፅን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ከመዝሙር እና ከተረቶች የስሜት መገለጫዎችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- የሰዎችን ስሜት ከፊት ገፅታ እና እንቅስቃሴ መረዳት

ዓላማ ፡- የሰዎችን ስሜት ከፊት ገፅታ እና እንቅስቃሴ መረዳትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የሰዎችን ስሜት የሚገልፁ ስዕሎች ወይም ፎቶግራፎች፣ የተረት መጽሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለመዱና ተቀባይነት ያላቸውን የማህበራዊ ኑሮ ስርዓቶችን እንደ ጓደኝነት፣ መረዳዳት፣ መተዛዘን የመሳሰሉትን ሊያስተምሩ የሚችሉ ተረቶችን መተረክ
- በትረካው ሂደት ላይም በተቻለ መጠን የባለታሪኮቹን ስሜት በፊት ገጽታ፣ በአካላዊ እንቅስቃሴና በድምፅ ቃና ማሣየት
- ከተረቱም በኋላ ሌሎች የሚገኙበትን ሁኔታና ስሜት እንዴት እንደተረዱ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት
- የሌሎች ሰዎች ስሜትን ከፊት ገጽታና በአካላዊ እንቅስቃሴ መረዳትን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የሰዎችን ስሜት ከፊት ገጽታ እና ከአካላዊ እንቅስቃሴ መረዳት መለማዳቸውን መገምገም።

**ተግባር አራት ፡- ለሌሎች ስሜት ተገቢዉን ምላሽ መስጠት**

ዓላማ ፦ ለሌሎች ስሜት ተገቢዉን ምላሽ ስለመስጠት ይረዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በግቢ ውስጥ ሲሮጥ የወደቀ ጓደኛቸው ሲያለቅስ እንደነበረ ገጠመኝ መንገር
- እነርሱ ከልጁ ጋር ቢሆሩ ኖሮ ወይም አይተውት ቢሆን ምንና እንዴት ያደርጉ እንደነበር እንዲናገሩ ማበረታታት
-

ምዘና ፦ ለሌሎች ስሜት ተገቢዉን ምላሽ ስለመስጠት መረዳታቸዉን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፦ የታማኝነትን ጥቅም ተረድተዉ በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ ይተገብራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የራስ ያልሆነ ንብረትን ለባለቤቱ መመለስ ተገቢና የሚያስመሰግን ተግባር መሆኑን ገጠመኞችን፣ ታሪኮችን በማውራት ታማኝ መሆን እንደሚገባ ማስረዳት

ምዘና ፦ የታማኝነትን ጥቅም መረዳታቸዉን እና በእለት ተእለት ህይወታቸዉ መተግበራቸዉን መከታተል።

ተግባር አምስት ፦ ስለታማኝነት ጥቅም መረዳት



ተግባር ስድስት ፦ ለሁኔታዎች ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት ማሳየት

ዓላማ ፡- ለሁኔታዎች ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት ማሳየትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የሰዎችን ስሜት የሚገልፁ ስዕሎች ወይም ፎቶግራፎች፣ የተረት መጽሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የልደት ቀን በዓላቸው ለሆኑ ሕፃናት /ጓደኞቻቸው/ እንዴት እንደሚዘምሩላቸው ማለማመድና የተለማመዱትን በልደት በዓሉ ላይ እንዲንፀባርቁ ማድረግ።

ምዘና ፡- በእለት ተእለት ህይወታቸዉለተለያዩ ሁኔታዎችተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት ማሳየት መለማመደቸዉንመገምገም።

**2.2.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

**2.1.5** የምልከታ መከታተያ ቅፅ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም --------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም ----------------------------------------------- ዓመተ ምህረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ------------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ------------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት ------------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፦ የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመት መጀመሪያ | በዓመት አጋማሽ | በዓመት መጨረሻ |
| **1.** በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጐት ማሣደርና መለየት | | | |
| 1.1 በቤትና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ያሉትን ሰዎች በማስተዋል መናገር ይችላሉ | | | |
| 1.2 ሰዎች በቤታቸውና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ያላቸውን ኃላፊነት በማየት መናገር ይችላሉ | | | |
| 1.3 አብረዋቸው ለሚጫወቱ ጓደኞቻቸው ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሣየት ይችላሉ | | | |
| **2.** ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | | | |
| 2.1 ሰዎች በቤታቸውና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ስለሚያከናውኗአቸው ተግባራት መናገር ይችላሉ /ወላጅ፣ ሞግዚት ፣ቤተዘመድ/ | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2.2 ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቁላቸውንና እንደሚንከባከቧቸው መግለጽ ይችላሉ | | | |
| **3.** ሌሎችን መንከባከብና ያለንን ነገር ማካፈል | | | |
| 3.1 የሌሎችን ስሜት መጋራት ይችላሉ | | | |

# ቋንቋን በአግባቡ መጠቀም

## 3.3.1. ማብራሪያ

ቋንቋ መግባቢያና ሃሳብን፣ ፍላጐትንና ስሜትን ወዘተ…ለሌላው ለመግለጽ የሚያስችል መሣሪያ ነው። በመሆኑም በዚህ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች በአካባቢያቸው የሚነገረውን ቋንቋ እንዲረዱ፣ሃሳባቸውን በንግግር የመግለጽ ልምድን እንዲያዳብሩ፣የቃላት ክምችታቸው እንዲዳብር፣ ነገሮችን ማገናዘብና አዳዲስ ሃሳቦችን ማመንጨት እንዲችሉና እንዲሁም ለማንበብና ለመፃፍ ዝግጁ እንደሆኑ መምህራን ለሕፃናቱ ምቹ አካባቢን መፍጠርና እገዛ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ቋንቋ ለአእምሮ /ግንዛቤ/ መዳበር ከፍተኛ እገዛ ስለሚያደርግ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

በአፀደ ሕፃናት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች በቋንቋ /ንግግር/ አማካኝነት ፍላጐታቸውን መግለጽና ማሟላት፣ ከሌሎች ጋር ግንኙነት መፍጠርና ማዳበር፣ አካባቢያቸውን በይበልጥ ማወቅና መረዳት፣ መረጃን መለዋወጥና የሌሎችን ድርጊት መቆጣጠር ስለሚያስችላቸው ቋንቋን /ንግግርን/ ለመማር ከፍተኛ ፍላጐትና ተነሳሽነት ይታይባቸዋል።

በተለይ በዚህ ዕድሜ ማለትም ከ4-5 ዓመት ያሉ ሕፃናት በአጠገባቸው ያሉ ሰዎችን በተደጋጋሚ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አካባቢያቸውን ይበልጥ ለማወቅ ፍላጐትና ጉጉት የሚያድርባቸው ዕድሜ መሆኑን መምህራንን ተገንዝበው ለሕፃናቱ ጥያቄ ሳይሰለቹና በወቅቱ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል። ይህም ሕፃናቱ አካባቢያቸውን የማወቅና የመረዳት ጉጉታቸው ከመጨመሩም በላይ ከመምህራኖቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት በፍቅር፣ በደስታና በአመኔታ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይረዳቸዋል።

## 3.3.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን አድምጠው ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡና የድምፆችን አቅጣጫና ምንጭ እንዲለዩ ማድረግ
2. በደረጃቸው ተረቶቹንና መዝሙሮችን አድምጠው መልዕክቱን እንዲረዱ መልሰው እንዲዘምሩና እንዲተርኩ ማድረግ
3. ራሳቸውንና አካባቢያቸውን ሰዋሰዋዊ የአነጋገር ስርዓትን በመከተል በተገቢው መንገድ ለመግለፅ ጥረት እንዲያደርጉ ማድረግ
4. ስዕሎችን በማየት ማንበብንና መሪ ፊደላትን በድምፅና በቅርፅ በመለየት የተዋወቋቸውን ፊደላት ገጣጥመው ለማንበብና አስመስለው ለመፃፍ ሙከራ እንዲያደርጉ ማለማመድ

5 የተለያዩ ድርጊቶችን በማከናወን የእጅ ጡንቻዎቻቸው፣ የዓይንና የእጃቸው ቅንጅት እንዲዳብር ለማድረግና ለጽሁፍ ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ

### **3.3.3** የሚጠበቅ ውጤትና ብቃቶች

1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት
2. ለትዕዛዞችና ለመመሪያዎች ምላሽ መስጠት ይችላሉ
3. የድምፆችን አቅጣጫ ማመልከትና የድምፆችን ምንጭ መለየት ይችላሉ
4. የሰሙትን መናገር ይችላሉ
5. ተረቶችን አዳምጠው የተረዱትን መግለጽና መልሰው መናገር ይችላሉ
6. በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት
    - ራስንና አካባቢን በተገቢው መንገድ መግለጽ ይችላሉ
7. በማንበብ መደሰት ዕውቀት ማግኘትና መረዳት
    - ስዕሎችንና የፊደላት ቅርፆችን መለየትና መረዳት ይችላሉ
8. የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት
    - የተለያዩ ድርጊቶችን ለማከናወን እጃቸውንና ዓይናቸውን መጠቀም ይችላሉ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.1. ለትዕዛዞችና ለመመሪያዎች ምላሽ መስጠት ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፦ ለትእዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ መስጠት**

*የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦* በክፍል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች (አሻንጉሊት)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሁሉንም ሕፃናት በየተራ በስም በመጥራት ቀላል የሆኑ ሁለት መመሪያ ያላቸውን አቅጣጫ እና ቦታ ጠቋሚ ትዕዛዞችን መስጠት
- ሕፃናቱ በታዘዙት መሠረት መመሪያውን ተከትለው ማከናወን እና አለማከናወናቸውን መከታተል እና ማበረታታት
- ሁሉንም ሕፃናት በማሳተፍ በጥሞና የማድመጥ ክህሎትን ማዳበር

ለምሣሌ፦

ከክፍል ውጪና በሩን ቀስ ብለሽ አንኳኪ

አሻንጉሊቷን ውሰድና አልጋዋ ላይ አስተኛት

ምዘና ፦ ለትእዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ መስጠታቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም።

**ተግባር ሁለት ፦ ተረት ማዳመጥ**

ዓላማ ፡- ተረትን በጥሞና የማዳመጥ ክህሎትን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሕፃናቱን አቀማመጥ በ ‹ሀ› ቅርጽ ማስተካከል
- ተረት የመስማት ፍላጐታቸውን መቀስቀስ
- ለዕድሜያቸው ይመጥናል ተብሎ የታሰበውን /የተመረጠውን/ ተረት በሚስብ መልኩ /የፊት ገጽታን፣ አካላዊ እንቅስቃሴንና ተገቢውን የድምጽ አወጣጥ በመጠቀም/ ማቅረብ
- ተረቱ ተተርኮ ሲያልቅ ሕፃናቱን ተረቱ ደስ ይላል ወይ**?** ማንን ወደድክ/ሽ**?** ለምን**?** በማለት በመጠየቅ ማወያየት
- ሕፃናቱ የተሰማቸውን ስሜት በንግግር እንዲገልፁ ማበረታታት
- የተረቱን ይዘት በቅደም ተከተል ጥያቄዎችን በመጠየቅ አስተውለዉ ማዳመጣቸውን መገምገም
- ፈቃደኛ የሆነ/ች ሕፃን ተረቱን በመምህር እርዳታ መልሶ/ሳ እንዲተርክ/እንድትተርክ ዕድሉን መስጠትና ማበረታታት

ምዘና ፡- ተረትን በጥሞና የማዳመጥ ክህሎት ማዳበራቸውን በማየትና ለጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ በማዳመጥ መገምገም።

ዓላማ ፦ መልእክት ማስተላለፍ ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- አንድ ፈቃደኛ የሆነ/ች ሕፃን በመምረጥ በጆሮው/ዋ ቀስ ብሎ በሹክሹክታ አጭር መልዕክት ለሌላ ሕፃን እንዲነግር/እንድትነግር ማድረግ
- ሕፃናቱ ያዳመጡትን መልዕክት ለተነገርዋቸው ሕፃናት በትክክል ማስተላለፋቸውን እና አለማስተላለፋቸውን ሲናገሩ በማድመጥ መገምገም
- በዚህ ልፉ ማድረግ

ለምሣሌ፦

ተግባር ሶስት ፦ መልዕክት ማስተላለፍ

ምዘና ፦ መልእክት የማስተላለፍ ችሎታቸዉን በማየት መገምገም።

ተግባር አራት ፦ ያዳመጡትን ደግሞ መናገር

ዓላማ ፦ በተረት ውስጥ ያደመጡትን መልዕክት ደግመው መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሐፍ፣ ጭምብል/ማስክ/፣ አልባሳት፣ ወፍራም ክላሰር፣ እርሳስ፣ ከለሮች፣ ማጣበቂያ ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሕፃናት በተደጋጋሚ የሰሙትን ተረት በድራማ መልክ እንዲያቀርቡት ማድረግ
- በገፀባህርያቱ ቁጥር ልክ ሕፃናትን መምረጥ
- ከሕፃናቱ ጋር አብሮ ማስክና አልባሳት ማዘጋጀት
- በተደጋጋሚ ገፀባህርያቱን ተላብሰው እንዲጫወቱ ማለማመድ
- ለክፍል ጓደኞቻቸው፣ ለሌሎች ሕፃናት፣ መምህራን እና ለወላጆቻቸው በተለያዩ በዓላት ላይ እንዲያቀርቡት ማድረግ

ምዘና ፦ በተረት ውስጥ የሰሙትን መልእክት ደግመውመናገር መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፦ አስታዉሶ መናገር

ዓላማ ፡- ስለእረፍት ቀናቸው አስታዉሰዉ ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መምህር በተለይ ሰኞ ቀን ላይ የእረፍት ቀናትን /ቅዳሜና ዕሁድ/ እንዴት እንዳሳለፉ አጠር አድርጎ መናገር
- ቀጥሎም ለሕፃናቱ ዕድል በመስጠት እያንዳንዳቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- በሚናገሩበት ጊዜ ማበረታታትና ጓደኞቻቸው ሲናገሩ በጥሞና እንዲያዳምጡ ማድረግ

ምዘና ፡- ስለእረፍት ቀናቸው አስታዉሰዉ መናገር መቻላቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1.መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.2. የድምፆችን አቅጣጫ መመልከትና የድምፆችን ምንጭ መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- አካባቢን ትኩረት ሰጥቶ ማድመጥ

ዓላማ ፡- አካባቢያቸውን ትኩረት ሰጥተው በማዳመጥ ስላዳመጡት ነገር ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በግቢ /በክፍል/ ውስጥ ለተወሰኑ ሰከንዶች ፀጥ ብለው እንዲያዳምጡ ማድረግ
- ምን እንዳዳመጡ በመጠየቅ እንዲናገሩ በማበረታታት
- ከህፃናቱ እይታ በመሰወር የተለያዩ ድምፆችን በማሰማት ህፃናቱ የሰሙትን ድምፅ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- አካባቢያቸውን ትኩረት ሰጥተው ማዳመጣቸውንና ስላዳመጡት ነገር መናገር መቻላቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።



ተግባር ሁለት ፡- የድምጽን አቅጣጫ መለየት

ዓላማ ፡- የድምጽን አቅጣጫ መለየትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፊሽካ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከክፍል ውጪ ባለ ሜዳ ላይ ሕፃናት በሶስት ወይም በአራት ረድፍ እንዲሰለፉ ማድረግ
- ቀጥሎም ከሕፃናቱ ጀርባ ሁለት ልጆች ፊሽካ ይዘው እንዲቆሙ ማድረግ
- መምህር ቀስ ብለው ወደ አንዱ/ዷ ሕፃን ሲጠቁሙ ፊሽካውን እንዲነፉ/እንድትነፋ ማድረግ
- በረድፍየቆሙት ሕፃናት ድምጽ ወደሰሙበት አቅጣጫ እንዲያመለክቱ፣ እንዲሮጡ እና እንዲራመዱ በማዘዝ የድምጽን አቅጣጫ እንዲለዩ ማለማመድ

ምዘና ፡- የድምጽን አቅጣጫ ለይተው የማወቅ ችሎታቸዉን መገምገም።

ተግባር ሦስት ፡ የሰሙትን ድመፅ መለየትና ማስመሰል

**ዓላማ ፡- የሰሙትን ድምጽ ይለያሉ እንዲሁም አስመስለው ያወጣሉ።**

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-  የተለያዩ የእንስሳት ስዕል**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ እንስሳት ስእሎች ማሳየት

  ለምሳሌ፡- የውሻ፣ የድመት፣ የዶሮ፣ የጅብ፣ የበግ ወዘተ…

- ከስዕሎቹ ውስጥ የአንዱን እንስሳ ድምጽ አስመስሎ መጮኽ
- ህፃናቱ የሰሙት የምን ድምጽ እንደሆነ ስዕሉን በማሳየት እንዲናገሩ ማድረግ
- የሰሙትን ድምጽ አስመስለው እንዲያወጡ ማድረግ
- ደጋግመው እንዲሞክሩ በማበረታታት ማለማመድ

ምዘና ፡- የሰሙትን ድምጽ መለየትና አስመስለው ማውጣት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ድምጽን መለየትና አስመስሎ ማውጣት

ዓላማ ፡- ድምጾችን መለየትና አስመስለው ማዉጣትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የእንስሳት እና የቁሳቁሶች ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለእያንዳንዱ ሕፃን የተለያዩ እንሰሳቶችን እና ቁሳቁሶችን ስዕል መስጠት

  ለምሳሌ፡- ፊሽካ፣ መኪና፣ ዶሮ፣ በግ ወዘተ…
- መምህር የአንዱን ድምጽ ሲያሰሙ የሰሙትን ዓይነት ድምጽ የሚያወጡ እንሰሳትን ወይም ቁሳቁሶችን የያዙ ልጆች ወደ መምህር ጋር እንዲመጡ ማድረግ
- የምን ድምጽ እንደሆነ በመጠየቅ በህብረት ድምጹን እንዲያወጡት ማድረግ

ምዘና ፡- ድምጾችን መለየታቸዉንና አስመስሎ የማውጣት ችሎታቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ አስተውለው በማዳመጥ ሰዎችን በድምጽ መለየትን ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- “የጠራህን ዕወቅ›› የሚለውን ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት፦
  - ○ አምስት ፈቃደኛ የሆኑ ሕፃናትን ማስነሳት
  - ... ማድረግ

**ተግባር አምስት ፦ ሰዎችን በድምጽ መለየት**

  - ○ ... ስም መጠየቅ እና ከአራቱ ሕፃናት ራቅ ብሎ/ብላ ፊቱን/ፊቷን ወደ ግርግዳ አዙሮ/አዙራ እንዲቆም/እንድትቆም ማድረግ
  - ○ ከአራቱ ሕፃናት አንዱን/አንዷን በጣት በመንካት ፊቱን/ፊቷን ያዞረውን/ያዞረችውን ልጅ ስሙን/ስሟን እንዲጠራ ማድረግ።
  - ○ ፊቱን/ፊቷን ያዞረው/ያዞረችው ልጅ ፊቱን ወደሕፃናቱ በማዞር ማን እንደጠራው በድምጽ እንዲለይና የጠራውን ሕፃን ስም እንዲናገር ማድረግ
  - ○ በዚህ ዓይነት ሁሉንም ሕፃናት ማሣተፍ

ምዘና ፦ ሰዎችን በድምጽ የመለየት ችሎታቸዉን መገምገም።

**ተግባር ስድስት ፦ ድምጽን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት አስመስሎ ማውጣት**

ዓላማ ፡- ድምጽን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት አስመስለው ማዉጣትን ይለማመዳሉ፡፡

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከክፍል ውጪ ባለው ሜዳ ላይ ሕፃናቱን ይዞ መውጣት
- የተለያዩ እንስሳቶችን፣ አዕዋፎችን እና ዕቃዎችን ድምጽ በማውጣት እና እንቅስቃሴያቸዉን በማስመሰል ማሣየት
- ሕፃናቱም ያዩትን መሠረት በማድረግ ድምጽን በማውጣት ከእንቅስቃሴው ጋር በማቀናጀት እያስመሠሉ እንዲጫወቱ ማድረግ

  ለምሣሌ ፡- መምህር እኔ የእናንተ እናት/አባት/ነኝ፤ እናንተ የኔ ልጆች ናችሁ፤ እኔ የማደርገውን በማድረግ ትከተሉኛላችሁ፡፡ በማለት ጉንበስ ብሎ በአራት እግር ‹‹አው አው›› እያሉ መራመድ፡፡ ከዛም ቀና እንዲሉ በማድረግ አሁን ምን ነበርን በማለት መጠየቅ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ‹‹ፂው ፂው›› እያሉ እጃቸውን በመዘርጋት መብረር ከዛም ባሉበት በመቆም ምን መሰለው እንደነበር እንዲናገሩ በማድረግ ድምጽን ከእንቅስቃሴ ጋር አቀናጅቶና አስመስሎ መጫወትን ማለማመድ፡፡

ምዘና ፡- ድምጽን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት አስመስለው የማዉጣት ችሎታቸውን መገምገም፡፡



ተግባር ሰባት ፡- በጨዋታ ከአደገኛ ድምፅ መራቅን መለማመድ

ዓላማ ፡- በጨዋታ የመኪና ድምጽን በማዳመጥ ከትራፊክ አደጋ እራስን መጠበቅን ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናትን ከክፍል በማስወጣት ወደሜዳ በመውሰድ የመኪና መንገድን በቾክ መሥራት
- ግማሾቹ ሕፃናት አሽከርካሪ ግማሾቹ እግረኛ እንደሆኑና እግረኞቹ በመኪና መንገድ ጠርዝ ላይ እንዲጓዙ ማድረግ
- አሽከርካሪዎቹ የመኪና ጡሩንባ /ክላክስ/ ሲያሰሙ እግረኞቹ ፈጥነው ከመኪና ጠርዝ ላይ እንዲወጡ በማድረግ ማጫወት

ምዘና ፡- የመኪና ድምፅን በማዳመጥ ከትራፊክ አደጋ እራስን ለመጠበቅ መሞከራቸውን በማየት መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥ እና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.3. የሰሙትን መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የእረፍት ቀን ሪፖርት ማቅረብ

ዓላማ ፦ የእረፍት ቀን ሪፖርትን በተገቢው ሁኔታ ማቅረብን ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በየሣምንቱ የጠዋት ሪፖርት /ዜና/ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ማመቻቸት።
- ሕፃናት የእረፍት ጊዜያቸውን እንዴት እና ከማን ጋር እንዳሳለፉ አስታውሰው እንዲናገሩ በማድረግ የማስተዋል እና የማስታወስ ችሎታቸውን ማዳበር
- በሌሎች ፊት ቆሞ የመናገር ልምድን እና ሌሎች ሲናገሩ በጥሞና የማዳመጥ ልምድን እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምዘና ፦ የእረፍት ቀን ሪፖርትን በተገቢው ሁኔታ ማቅረብ መለማመዳቸውን በማዳመጥና በማየት መገምገም።

ተግባር ሁለት ፦ ተረትን አዳምጦ በስዕል መግለጽ

ዓላማ ፡- ካደመጡት ተረት የወደዱትን ገጸ-ባህሪ በስዕል መግለጽን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ የተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናት አጠር ያለ አስደሳች ገጠመኝ፣ ታሪክ ወይም ተረት መንገር
- ለእያንዳንዱ ልጅ ወረቀትና እርሳስ መስጠት
- ከሰሙት ያስደስታቸውን ወይም ያሳዘናቸውን ነገር በስዕል እንዲያንፀባርቁ ዕድሉን መስጠት
- የሳሉትን ስዕል ለክፍል ጓደኞቻቸው በማሣየት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማነቃቃት

ምዘና ፡- ካደመጡት ተረት የወደዱትን ገጸ-ባህሪ በስዕል የመግለጽ ችሎታቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- አጫጭር መልዕክቶችን አዳምጠዉ የማስተላለፍ ልምድን ያዳብራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መምህር አጫጭር መልእክቶችን ለህፃናቱ በየተራበመንገር መልእክትን ለጓደኞቻቸው፣ ለመምህራቸውና ለሞግዚታቸው እንዲያደርሱ ማድረግ
- ህፃናቱ የተነገራቸውን መልእክት በትክክል አዳምጠው ማስተላለፋቸውን የክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- ሁሉም ህጻናት መልእክትን በማስተላለፍ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ

ምዘና ፡- አጫጭር መልዕክቶችን አዳምጠዉ መልዕክት የማስተላለፍ ችሎታቸዉን በማየት መገምገም።



ተግባር ሶስት ፡- አጫጭር መልዕክቶችን ማስተላለፍ

ተግባር አምስት ፡- የመዝሙርን መልዕክት መናገር

ዓላማ ፡- መዝሙርን አዳምጠዉ የመዘመር ልምድን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሕፃናት መዝሙሮችን እንዲያዳምጡ ማድረግ
- ያዳመጡትን መዝሙር መልሰው እንዲዘምሩ ማድረግ
- የመዝሙሩን ይዘት/መልዕክት/ በመጠየቅ ማወያየት
- በትክክል ካለዳመጡ በድጋሚ ማስደመጥና ባዳመጡት መሠረት እንዲዘምሩ ማለማመድ

ምዘና ፡- መዝሙርን አዳምጠዉ የመዘመር ልምድን ማዳበራቸውን መገምገም።



ተግባር አራት ፡- መዝሙርን ማዳመጥ እና መዘመር

**ዓላማ ፡-** የመዝሙርን መልዕክት መናገር ይለማመዳሉ።

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-** የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/

**የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-**

- የተለያዩ የሕፃናት መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ማድረግ
- መዝሙሩ ስለማንና ስለምን እንደሆነ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መዝሙሩ ሕፃናትን ምን ሊያስተምር እንደሚችል /ምን መልዕክት እንዳለው/ እንዲረዱ ማድረግ
- መዝሙሩን ከዘመሩ በኋላ ራሳቸው የመዝሙሩን መልዕክት እንዲናገሩ ማበረታታት

**ምዘና ፡-** የመዝሙርን መልዕክት የመናገር ችሎታቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- በጥሞና ማዳመጥና የሰሙትን መልሰዉ መናገርን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍ፣ የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አጫጭር ከሕፃናት ሕይወት ጋር የተያያዙ ገጠመኞችን፣ ታሪኮችንና ተረቶችን በማውራት በጥሞና እንዲያዳምጡ ማድረግ
- የየራሳቸውን የተለያዩ ገጠመኞቻቸውን እንዲናገሩ በማበረታታት እርስ በእርስ

ተግባር ስድስት ፡- በጥሞና ማዳመጥና የሰሙትን መልሰዉ መናገር

- በተረቱ፣በመዝሙሮቹና በግጥሞቹ ውስጥ ያሉትን ከፍተኛ፣ ዝቅተኛና ለስላሳ ድምፆችን በማውጣት መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በጥሞና ማዳመጥና የሰሙትን መልሰዉ የማለት ችሎታቸዉን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡- የድራማ ጨዋታን መጫወት

ዓላማ ፡- በድራማ ጨዋታ የማዳመጥ እና የመናገር ክህሎታቸዉን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለድራማ የሚያገለግሉ አልባሳት እና ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናትም ሆነ መምህር ካቀረቧቸው ሪፖርቶች ውስጥ ለድራማ የሚስማማውን ርእስ መምረጥ
- ታሪኩን በጥያቄና መልስ መጠየቅና በአጭሩ ደግሞ በመተረክ እንዲያስታውሱ ማድረግ
- ገጸ ባህሪያቱን ተላብሰው የሚጫወቱ ህፃናትን መምረጥ
- ሕፃናቱ ገፀባህሪያቱን ተላብሰው በድራማ መልክ እንዲያቀርቡት ማለማመድ
- ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡት ማድረግ
- ከድራማው በኋላ ስለድራማው አቀራረብ አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማጠቃለል

ምዘና ፡- ድራማዉን ሲቀርቡ የማዳመጥ እና የመናገር ችሎታቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥ እና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.4 አጫጭር ተረቶችን እና መዝሙሮችን በማዳመጥ መልሰው መናገር እና መዘመር ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፡- ተረት ማዳመጥ እና መልሶ መተረት**

ዓ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጸሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናት የሚመጥኑ ተረቶችን በተገቢው መንገድ መተረክ
- ስለተረቱ የተሰማቸውን ስሜት መጠየቅ
- የተረቱን ይዘት እንዲረዱ በቅደም ተከተል ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ፈቃደኛ የሆነ/ች ልጅ ወጥቶ/ታ እንዲተርክ/እንድትተርክ ዕድሉን መስጠት
- ለሌሎች ሕፃናትም ዕድል በመስጠት የሰሚቸውንና የሚያውቋቸውን ተረቶች ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማበረታታት
- ሕፃናት የራሳቸውን ተረት በመፍጠር እንዲተርኩ ዕድሉን በመስጠት ማበረታታት

ምዘና ፡- ተረቶችን አዳምጠዉ መልሰዉ የመተረት ልምድ ማዳበር መጀመራቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- ተረቶችን በድራማ መልክ ማቅረብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍ፣ ጭምብል/ማስክ/ እና አልባሳት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በተከታታይ የሰሚቸውን ተረቶች ገፀባህርያት ለሕፃናቱ መስጠት
- ጭምብል/ማስክ/ እና አልባሳት ከመምህር ጋር አብሮ በማዘጋጀት ተረቱን በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ማለማመድ
- በመጨረሻም በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ እንዲያቀርቡት ማድረግ



**ተግባር ሁለት ፡- ተረትን በድራማ መልክ ማቅረብ**

ምዘና ፡- ተረቶችን በድራማ መልክ የማቅረብ ችሎታቸዉን መገምገም።

**ተግባር ሦስት ፡- ስዕልን በቅደም ተከተል ማደራጀት**

ዓላማ ፡- በተረት ውስጥ ያሉ ስዕሎችን በቅደም ተከተል ያደራጃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍት፣ በተረት ውስጥ ያሉ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በሰሙት ተረት ውስጥ ያሉ ስዕሎችን ቅደም ተከተላቸውን ባልጠበቀ ሁኔታ በጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
- ፈቃደኛ የሆነ/ች ሕፃን ስዕሎችን በቅደም ተከተል እንዲያደራጅ/እንድታደራጅ ማድረግ
- በመቀጠልም ሌሎችን ማሣተፍ

ምዘና ፡- በተረት ውስጥ ያሉ ስዕሎችን በቅደም ተከተል ማደራጀት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር አራት ፡- ተረቶችን በስዕል መግለጽ**

ዓላማ ፡- ያደመጧቸውን ተረቶች በስዕል ለመግለጽ ይሞክራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት በተደጋጋሚ የሰሙትን ተረት ይዘት ስዕል በመሣል እና ቀለም በመቀባት እንዲሠሩ ማድረግ
- ሕፃናቱ የሳሉትን እና ከለር የቀቡትን ስዕል ምን እንደሆነ እንዲያሣዩ እና እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ያደመጧቸውን ተረቶች በስዕል ለመግለጽ መሞከራቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፦ ተረቶችን በሞዴል መልክ ለመስራት ይሞክራሉ።

ተግባር አምስት ፦ ተረቶችን በሞዴል መስራት

የመርጃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናት በተደጋጋሚ የሰሙትን ተረት ይዘት በተቦካ ወረቀት ወይንም በጭቃ ሞዴል እንዲሠሩ ማድረግ
- ሕፃናቱ የሰሩትን ሞዴል በማሣየት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ ተረቶችን በሞዴል መልክ ለመስራት መሞከራቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት | 2. 1. ራሳቸዉን እና አካባቢያቸዉን በተገቢው መንገድ መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ፦ ስለራስ መናገር

ዓላማ ፦ ስለራሳቸው ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ከካርቶን የተዘጋጀ የድምጽ ማጉያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከሶፍት ካርቶን የድምጽ ማጉያ ማዘጋጀት
- መጀመሪያ መምህር የራስን ስም፣የመኖሪያ አድራሻን ወዘተ... መናገር
- እያንዳንዳቸው በተሟላ ዓረፍተ ነገርና አድማጭ ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ ስማቸውን፣ የመኖሪያ አድራሻቸውን፣ የሚወዱትን እና የሚችሉትን ነገር እንዲናገሩ ማበረታታት
- ህጻናቱ ስለራሳቸዉ የተለያዩ ቀላ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተሟላና ትርጉም ሊሰጥ የሚችል ዐረፍተ ነገር በመጠቀም ምላሽ እንዲሰጡ ማበረታታት

- የተፈለገውን አቅጣጫ ይዘው ካልተናገሩ በጥያቄዎች መምራት

ማስታወሻ ፡- ሲናገሩ ጣትን አፍ ውስጥ መክተት፣ እጆችን ማፋተግ፣ ማቀርቀር፣ ልብስን ወደ አፍ መክተት ወዘተ... ተፈላጊ ያልሆነ ባህሪ መሆኑን ሕፃኑ እንዲረዳና እንዲተው በተለያየ መንገድ መርዳት እና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የንግግርን ስርአት ተከትለው ስለራሳቸው መናገር መቻላቸውን የሚናገሩትን በማድመጥ

ተግባር ሁለት ፡- ለጥያቄዎች በንግግር ምላሽ መስጠት

ዓላማ ፡- ለሚጠየቁት ጥያቄ በተገቢው መልኩ በንግግር ምላሽ ይሰጣሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሻንጉሊት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አሻንጉሊትን እንግዳ አስመስሎ ማምጣት
- አሻንጉሊቷ የመጣችው/ ስሟን ጠርቶ/ ዛሬ ጠዋት ሕፃናቱ ከቤታቸው ሲመጡ ምን እንዳዩ ምን እንደተሰማቸው ወዘተ... እንዲነግሩኝ ነው ብላ የምትናገር በማስመሰል መናገር
- በየተራ ወደ ሕፃናቱ አሻንጉሊቷን ይዞ በመቅረብ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ለጥያቄው በንግግር መልስ እንዲሰጡና ስሜታቸውን በንግግር እንዲገልፁ ማበረታታት እና ማገዝ
- በተገቢውና ሥነ-ስርዓት ባለው መልኩ እንዲናገሩም መርዳት

ምዘና ፡- ለሚጠየቁት ጥያቄዎች በንግግር ምላሽ መስጠት መቻላቸውን ሲናገሩ በማዳመጥ መገምገም።

ዓላማ ፡- ያዩትን የሰውነት ክፍል መጠሪያ በትክክል ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-



ተግባር ሶስት ፡- ያዩትን የሰውነት ክፍል መጠሪያን መናገር

- ለሕፃናቱ ዕይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም መምህር የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ሲነኩ ሕፃናቱ እጅ በማውጣት የተነካውን የሰውነት ክፍል መጠሪያ እንዲናገሩ ማድረግ
- አንድ ሕፃን አጫዋች በማድረግ ሕፃኑ/ኗ የሚነካውን/ የምትነካዉን የሰውነት ክፍል መምህርት ትክክል ያልሆነ መጠሪያ ስም በመናገር የሕፃናቱን መልስ መከታተል

  ለምሣሌ፦ አፍንጫ ሲነካ ጆሮ በማለት መናገር ከዛም ሕፃናቱ ትክክለኛዉን ስያሜ ሲናገሩ በማመስገን ስህተትን በማረም ማጫወት

ምዘና ፡- ያዩትን በትክክል መናገር መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ተከታታይ ስእል ላይ ያዩትን መናገር

መናገር

ዓላማ ፡- ተከታታይ ስእልን በማየት ቅደም ተከተሉን ጠብቀው ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍት፣ ተከታታይነት ያላቸው ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ተረትን በመጠቀም የወደፊት ፍላጐቱ ምን እንደሆነ ስለተናገረ ሕፃን በአጭሩ መተረክና እያንዳንዳቸው ሲያድጉ ምን መሆን እንደሚፈልጉ በጓደኞቻቸው ፊት እንዲናገሩ ማበረታታት
- ተከታታይ ይዘት ያላቸዉን ስዕሎች በመጠቀም በስዕሉ ላይ ስለሚያዩት ነገር እንዲናገሩ መጠየቅ
- በተቻለ መጠን ተከታታይነቱን ጠብቀዉ ታሪኩን እንዲናገሩ ማለማመድ

ምዘና ፡- ተከታታይ ስእልን በማየት ቅደም ተከተሉን ጠብቀው መናገር መቻላቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።



ተግባር አምስት ፡- ሪፖርት ማቅረብ

መናገር



ዓላማ ፡- ያዩትን እና የሰሙትን ቅደም ተከተሉን ጠብቀው ሪፖርት ያቀርባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከካርቶን የተዘጋጀ የድምጽ ማጉያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በመጀመሪያ መምህር በዕረፍት ቀናቸዉ ስላዩትና ስለሰሙት መናገር
- ህጻናቱም እያንዳንዳቸዉ እየወጡ እንዲናገሩ ዕድል መስጠት
- በአካባቢያቸዉ የጉብኝት ፕሮግራም ማዘጋጀትና ከጉብኝቱ በኋላ ስላዩትና ስለሰሙት ነገር እንዲናገሩ ማበረታታት
- ጥያቄዎች በመጠየቅ እንዲያስታዉሱ ማገዝ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- በዝርዝር መናገር እንዲችሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ማበረታታት እንዲሁም ማስታወስ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- ያዩትን እና የሰሙትን ቅደም ተከተሉን ጠብቀው ሪፖረት የማቅረብ ችሎታቸዉን መገምገም።

ተግባር ስድስት ፡- በመፅሀፍ ላይ ስለሚያዩት ስእል ምንነት መናገር

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መጽሀፍቶች /መጽሄቶች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አገላብጠዉ ሊያዩት የሚችሉት ጎላ ያሉ ስዕሎች /በአካባቢ ያሉ ነገሮችን የሚያሳዩ/ ያለባቸዉን መጽሄቶች /መጽሃፍት/ መስጠት
- በጥሞና አገላብጠዉ እንዲያዩ ጊዜ መስጠት እና እያንዳንዳቸዉ አገላብጠዉ ስላዩት ስዕል እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በመፅሀፍ ላይ ስላዩት ስእል ምንነት መናገር መቻላቸውን ሲናገሩ ትኩረት ሰጥቶ በማየትና በማዳመጥ መገምገም።

ዓላማ ፡- በመዳሰስ ስለነገሮች ምንነት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቅማ ፡- ላፒስ፣ መቅረጫ፣ ስኒ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- <<በእጅህ ላይ ምን አለ?>> ጨዋታን በሚከተለዉ መልኩ ማጫወት፡-
  - ህጻናት በክብ እንዲቀመጡ ማድረግ
  - በተቀመጡበት ቦታ ሆነዉ እጃቸዉን ወደኋላ እንዲዘረጉ ማድረግ
  - በእጆቻቸዉ ላይ የተለያዩ ነገሮችን ማስቀመጥ

    ለምሳሌ፡- ላፒስ፣ መቅረጫ፣ ስኒ ወዘተ…
  - በመጀመሪያ ሳያዩ እየዳሰሱ በእጃቸዉ ላይ ስለተቀመጠዉ ነገር እንዲናገሩ ማድረግ
  - በመቀጠልም በአይናቸዉ እያዩ እንዲናገሩ ማድረግ

ተግባር ሰባት ፡- በመዳሰስ ስለነገሮች ምንነት መናገር

መናገር

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸዉ ስላሉ የተለያዩ ነገሮች ይናገራሉ።

ተግባር ስምንት ፡- በአካባቢ ስላሉ ነገሮች መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቅማ ፡- የቁሳቁሶች፣ የእንስሳት፣ የቤት ቁሳቁሶች፣ እና የእጽዋት ሎቶ

መናገር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የእንስሳት፣ የቤት ቁሳቁስ፣ የእጽዋት ሎቶን እንዲገጣጥሙ በማድረግ ስለገጣጠሙት እንዲናገሩ ማድረግ
- ህጻናት በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ እነሱም ሆኑ አዋቂዎች የሚጠቀሙባቸዉን ቁሳቁሶች በአካልም ሆነ በስዕል ማሳየት
- መጠሪያ ስሙንና አገልግሎቱን በመጠየቅ ህጻናቱም በተሟላ ዐረፍተ ነገር መልስ እንዲሰጡ ማበረታታት
- ተመሳሳይ ዕቃዎች ሆነዉ የተሰሩባቸዉ ማቴሪያሎች የተለያዩ የሆኑትን አስተዉለዉ

በማየት ልዩነታቸዉን እንዲያወጡ ማነቃቃት

ለምሳሌ ፡- የብረትና የፕላስቲክ ማንኪያ፣ ብርሃን የሚያስተላልፍና የማያስተላልፍ ብርጭቆና ኩባያ ወዘተ...

ምዘና ፡- በአካባቢያቸዉ ስላሉ የተለያዩ ነገሮች መናገር መቻላቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- በመስሎ መጫወት ጨዋታ በአካባቢያቸው ስላሉ ነገሮች ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሻንጉሊት፣ የመስሎ ጨዋታ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለመስሎ ጨዋታበሚያመችመልኩክፍሉንማደራጀት
- አስፈላጊውን ቁሳቁሶች በማሟላት ሕፃናት በአካባቢያቸው የሚያዩትንና ያዩትን ነገር በመስሎ መጫወት እንዲያንፀበርቁ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ጨዋታውን ለመጫወት ሕፃናቱ ያለማንም አስገዳጅነት ራሳቸው በመረጡት ቦታና ሚና መጫወት የሚችሉ ሲሆን መምህር ሕፃናቱ ሲጫወቱ በመዘዋወር ማየትና አንዳንዴም ማስተካከያ የሚያስፈልገው ቦታ ላይ እንደእንግዳ ታካሚ፣ ገዢ፣ ወላጅ ወዘተ... በመሆን በመግባት ማስተካከል ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- በመስሎ መጫወት ጨዋታ በአካባቢያቸው ስላሉ ነገሮች መናገር መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የሰሙትን ተረት ደግመው ለመናገር ይሞክራሉ።

ተግባር ዘጠኝ ፡- በመስሎ መጫወት ጨዋታ በአካባቢያቸው ስላሉ ነገሮች መናገር

መናገር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-



ተግባር አስር ፡- የሰሙትን ተረት ደግሞ መናገር

መናገር



- ለዕድሜያቸዉ የሚመጥን ተረትን ረጋ ብሎ መተረት
- በመቀጠልም ስለተረቱ የተሰማቸዉን ስሜት እንዲናገሩ ማድረግ
- የተረቱን ይዘት እንዲረዱ በቅደም ተከተል መጠየቅ
- በመጨረሻም ተረቱን መልሰዉ እንዲተርኩ ዕድሉን መስጠት ከከበዳቸዉ በጥያቄና መልስ መልክ ዕገዛ ማድረግ

ምዘና ፦ የሰሙትን ተረት ደግመው መናገር መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ አንድ ፦ መዝሙርን በቃል መያዝ

ዓላማ ፦ የሰሙትን መዝሙር በቃል ለመያዝ ይተባበራሉ።

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- አጫጭር የህጻናት መዝሙሮችን በቃላቸዉ እንዲይዙ ስንኝ በስንኝ ከፋፍሎ በማስጠናት እንዲዘምሩ ማድረግ
- የመዝሙሩን ይዘት በጥያቄና መልስ እንዲረዱ ማድረግ
- በቡድን በመከፋፈል እንዲዘምሩ ማድረግ እና በቃላቸዉ እንዲይዙት ደጋግሞ ማዘመር

ምዘና ፦ የአጫጭር የህጻናት መዝሙሮችን በቃላቸዉ ይዘዉ መዘመር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አስራ ሁለት ፦ የሰሙትን ተረት በድራማ መግለጽ

ዓላማ ፦ መናገር በተደጋጋሚ የሰሟቸውን ተረቶች በድራማ መልክ መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ለድራማ የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ እና አልባሳት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ገጸባህሪያቱን ተላብሰው የሚጫወቱ ህፃናት ለድራማው የሚያስፈልጋቸውን አልባሳትና ጭንብል በማድረግ እንዲዘጋጁ ማድረግ
- ህፃናቱ በተደጋጋሚ የሰሙትን ተረት/የሚቀርበውን ድራማ ታሪክ/ አጠር አድርጎ በክፍል

ውስጥ መተረክ

- ገጸባህሪያቱን ተላብሰው የሚጫወቱት ልጆች ድራማውን ሲያቀርቡ ሌሎች በጥሞና እንዲያዳምጡ ማድረግ
- በመጨረሻም ድራማውን ያቀረቡትን ህፃናት እንዲያመሰግኑ ማድረግ

ማስታወሻ ፦ ድራማን ለመተወን ህፃናት የረዥም ጊዜ ዝግጅት የሚያስፈልጋቸው ሲሆን ህፃናቱ ለተለያዩ በዓላት ላይ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል።

ምዘና ፦ በተደጋጋሚ የሰሚቻውን ተረቶች በድራማ መልክ መተወን መሞከራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች በቅደም ተከተል አስቀምጠዉ ምክንያታቸዉንም ያስረዳሉ፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በስዕል የተደገፉ የተረት መጽሃፍቶች፣ ተከታታይነት ያላቸዉ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች አዘበራርቆ በመስጠት ህጻናት በቅደም ተከተል

ተግባር አስራ ሶስት ፦ ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

- [illegible]

መናገር እንዲናገሩ ማበረታታት

ማስታወሻ ፦ ተረቱ ከዚህ በፊት የተዋወቁት ሊሆን ይገባል።

ምዘና ፦ ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች በቅደም ተከተል አስቀምጠዉ ምክንያታቸዉንም መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።



ተግባር አስራ አራት ፦ ሃሳብን በተገቢው መንገድ መግለፅ

መናገር



ዓላማ ፦ ሃሳብን በተገቢው መንገድ የመግለፅ ክህሎትን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሃሳብን በተገቢው መንገድ የመግለፅ ክህሎት እንዲያዳብሩ፡-
  - ሕፃናት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ነገሮች መጥተው ለመምህር ሲናገሩ መምህር ትኩረት በመስጠት አስተውሎ ማዳመጥ
  - ሲጨርሱም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅና እንዲመልሱ በማድረግ ሕፃናት አስተውሎ የማዳመጥ ክህሎትንና ሃሳብን በተገቢው መንገድ አድማጭ ሊረዳው በሚችል መልኩ የመግለጽ ልምድን እንዲያዳብሩ ማገዝ

ምዘና ፦ ሃሳባቸውን በተገቢው መንገድ መግለፅ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ አምስት ፦ “ማን ብዙ ቃላት ያውቃል?” ጨዋታን መጫወት

ዓላማ ፦ “ማን ብዙ ቃላት ያውቃል**?**” ጨዋታ በመጫወት የቃላት ክምችታቸውን ያዳብራሉ።
መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በስዕል የተደገፉ የተረት መጽሃፍቶች፣ ተከታታይነት ያላቸዉ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- “ማን ብዙ ቃላት ያውቃል?” የሚለውን የቃላት ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት፡-
  - በመጀመሪያ ምሳሌ በመስጠት ጨዋታውን እንዲረዱ ማድረግ

    ለምሳሌ ፦ በ- በግ፣ በ- በሬ፣ በ- በርወዘተ…
  - በመቀጠልም ሁለት ፈቃደኛ የሆኑ ሕፃናትን በማስወጣት አንድ መሪ ፊደልን በመንገር ጨዋታውን እንዲጫወቱ ማድረግ
  - አንዱ እንዲጀምር በማድረግ ማስጀመር
  - ቃላት ማውጣት ያልቻለ ልጅ እንደተሸነፈ በመቁጠር ማጫወት

- በጨዋታው ሁሉም ሕፃናት እንዲሳተፉ ማድረግና መሸነፍን በፀጋ መቀበልን ማለማመድ

ማስታወሻ፡- ከጨዋታው በፊት የጨዋታውን ሕግ ማሣወቅ ያስፈልጋል። እነዚህም፡-አንዱ ያለውን ደግሞ ማለት፣ መልስ ሳይመልሱ ብዙ መቆየትና ከጨዋታ ውጪ ያሉ ልጆች ለተጨዋቾቹ መልስ መናገር እንደማይቻል መግለጽ ናቸዉ።

ምዘና ፡- "ማን ብዙ ያውቃል?" የሚለውን የቃላት ጨዋታ በማጫወት እና ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቃላት ስብስባቸዉን መገምገም።

ተግባር አስራ ስድስት ፡- እንቆቅልሽ ጨዋታን መጫወት

ራሉ።

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእንቆቅልሽ መጽሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የእንቆቅልሽ አጠያየቅ ሂደትን በመከተል ሕፃናቱን እንቆቅልሽ መጠየቅ
- ሕፃናቱ መልሱን በትክክል ከተናገሩ ማሞገስና መልሱ ለምን እንደዛ ሊሆን እንደቻለ በመጠየቅ ማወያየት

ለምሣሌ፡- እንቆቅልሽ/ህ፡-

ምን አዉቅልሽ/ህ?

"ፀጉሯን አበጥራ ገበያ የምትወጣ?"

መልስ፡- ሱፍ

- ከተቻለ ሱፍን በማሳየት ፀጉሯ የተበጠረ እንደሚመስል መንገርና ገበያ የምትወጣ የተባለችው ሰዎች ለመሸጥ ገበያ ይዘዋት ስለሚሄዱ መሆኑን መንገር
- ከተሳሳቱ መልሱን ባህላዊውን ስርዓት በመከተል አገ ርስጠኝ /ስጪኝ/ በማለት በመጠየቅ ሕፃኑ /ኗ/ በተናገረው /ችው/ አገርመሠረት

-------- ሂጅ ምን አጥቼ ሁሉ በእጀ ሁሉ በደጀ

መልሱ እንዲህ ነው ብሎ በመንገር ማጫወት

እነሱም የሚያውቁትን እንዲጠይቁ ዕድሉን መስጠት

ምዘና ፡- እንቆቅልሽ በማጫወት ባህላዊ የአነጋገር ስርዓትን ተከትለው መጫወታቸውን ሃሳብን በቃላት የመግለጽ ችሎታቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- በነገሮች እና በድርጊቶች መካከል ያለውን ግንኙነት መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰዎችን ድርጊት የሚያሣዩ ስዕሎች፣ የተለያዩ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ተመሣሣይ ዕቃዎችን፣ ስዕሎችንና የሰዎችን ድርጊት የሚያሣዩ ስዕሎችን መስጠት
- እንዲያዛምዱና ለምን እንደዛአ ንዳዛመዱ መጠየቅ

ለምሣሌ፡- ኩባያና ብርጭቆ፣ ወንበርና በርጩማ፣ ሴት ልጅና ወንድ ልጅ፣ ድመትና

ተግባር አስራ ሰባት ፡- በነገሮች እና በድርጊቶች መካከል ያለ ግንኙነትን መግለጽ

መናገር

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3.በማንቡብ መደሰት፣ ዕውቀት ማግኘትና መረዳት | 3.1.ስዕሎችንና የፊደላት ቅርፆችን መለየትና መረዳት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ስዕልን ማንቡብ

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእያንዳንዱ ልጅ የተለያዩ ስዕሎችን መስጠት
- በስዕሉ ላይ ያዩትን ተራ በተራ እየወጡ ለጓደኞቻቸዉ በማሳየት እንዲናገሩ ማድረግ

- ሰዎች እና እንሰሳቶች የተለያየ ድርጊትን ሲያከናውኑ የሚያሣዩ ስዕሎች ጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
- ሕፃናት በየተራ እየመጡ አንዱን ስዕል በማንሳት በስዕሉ ላይ ምን እንዳዩ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ ስዕሎችን በማንበብ ያዩትንና የተረዱትን መናገር መቻላቸዉን መገምገም።

**ተግባር ሁለት ፦ ስዕልን ማዛመድ**

ዓላማ ፦ ተመሳሳይ ስዕሎችን ያዛምዳሉ።
መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ልጅ የተለያዩ ስዕሎች በመስጠት ስዕሉን እንዲመለከቱ ማድረግ
- ከዛም መምህር ጐላ ብሎ የተሳለ ስዕልን ለሕፃናቱ ማሳየት
- ተመሣሣዩን ስዕል የያዘ ህፃን ወደ መምህር አጠገብ ወጥቶ/ታ እንዲቆም/እንድትቆም ማድረግ
- በአንድነት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ ተመሳሳይ ስዕሎችን ማዛመድ መቻላቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፦ በስዕሎች መካከል ያሉ ልዩነቶችን ተረድተዉ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ተመሳሳይ የሆኑ ነገር ግን ትንሽ ልዩነት ያላቸዉ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ተመሳሳይ የሆኑ ነገር ግን ትንሽ ልዩነት ያላቸዉ ስዕሎችን ለህጻናቱ ዕይታ አመቺ ቦታ

**ተግባር ሶስት ፦ በስዕሎች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት**

መናገር

- ስዕሎቹን እንዲመለከቱና ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ማድረግ
- በስዕሎቹ መካከል ያለዉን ልዩነት እንዲናገሩ ማበረታታት
- ለእያንዳንዳቸው ተመሳሳይ ሆነዉ ትንሽ ልዩነት ካላቸዉ ስዕሎች ሁለት ሁለት በመስጠት በደንብ እንዲመለከቱ ማድረግ
- እያንዳንዱ/ዷ ህጻን እየተነሳ/ች የደረሰዉ/ሳትን ስዕል ምን እንደሆነና ልዩነቱ ምን እንደሆነ እንዲናገር/እንድትናገር ማበረታታት

ለምሳሌ ፡- ሁለት እኩል ቁመትና ጾታ ያላቸዉን ህጻናት ስዕል በማየት አንዱ ኮፍያ አድርጓል ሌላዉ አላደረገም ወዘተ...

ምዘና ፡- በስዕሎች መካከል ያሉ ልዩነቶችን መረዳት እና መናገር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- የፊደላትን ቅርጽ እና ስም መለየት

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደላት ካርዶች/ሰሌዳዎች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሶስት በቅርጻቸዉ ተመሳሳይ የሆኑ የፊደል ካርዶችን መምረጥ
- ፊደላቱ ህጻናትን መተዋወቅ እንደሚፈልጉ በማስመሰል መጠሪያ ስማቸዉን እና ቅርጻቸዉን ለህጻናቱ በመንገር ማስተዋወቅ
- ‹‹ማነኝ ማነኝ;›› የሚለዉን መዝሙር በማዘመር እያንዳንዱ ፊደል የራሱ የሆነ መጠሪያ ስም እንዳለዉ እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የፊደላትን ቅርጽ እና ስም መለየት መለማመዳቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- በመዳሰስ የፊደላትን ስምና ቅርጽ ይለያሉ።



ተግባር አምስት ፡- በመዳሰስ የፊደላትን ስምና ቅርጽ መለየት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአሸዋ ግርፍ ፊደል ሰሌዳ /በብርጭቆ ወረቀት የተሰራ ፊደል/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የአሸዋ ግርፍ ፊደል ሰሌዳ /በብርጭቆ ወረቀት የተሰራ ፊደል/ በመጠቀም ህጻናቱ እንዲዳስሷቸዉ እና ስማቸዉን እንዲናገሩ ማድረግ
- ዳሰው ያወቋቸውን ፊደላት በአየር ላይ እንዲፅፏቸው ማድረግ
- በመጨረሻም በጓደኞቻቸው ጀርባ ላይ በጠቋሚ ጣታቸው በመፃፍ ፊደሉን ማን እንደሆነ እንዲናገሩ በማድረግ የፊደሉን ድምፅና ቅርፅ እንዲለዩ ማበረታታት

ምዘና ፡- በመዳሰስ የፊደላትን ድምፅና ቅርጽ መለየት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፡- በተረት የፊደላትን ስምና ቅርጽ መለየት

ዓላማ ፡- በተረት የፊደላትን ስምና ቅርጽ ይለያሉ።
መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደል ካርዶች፣ የፊደላት ስምና ቅርጽ ላይ የተመረኮዘ አጭር ተረት ተረት /የተረት ተረት መጽሀፍ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የፊደል ካርዶችን በመጠቀም ተረቱን በመንገር ፊደላትን በደንብ እንዲለዩ መርዳት

  ለምሳሌ፡- ከዕለታት አንደ ቀን በአንድ ትንሽ መንደር ውስጥ የምትኖር "በ" የምትባል ባለ ሁለት እግር ፊደል ነበረች።ይቺ ፊደል እንደ እሷ ሁለት እግር ያለውና አብሯት የሚጫወት ፊደል ባለመኖሩ ብቸኛ ነበረች። አንድ ቀን ለምን እኔን የሚመስልና አብሮኝ የሚጫወት ጓደኛ አልፈልግም ብላ ከቤቷ ወጥታ ወደ ሌላ መንደር ጉዞ ጀመረች። በመንገድ ላይ ስትሄድ ከርቀት አንድ ትልቅ ዛፍ ስር እሷን የሚመስል ፊደል አየችና እየሮጠች ወደ ዛፉ ሄደች። ከዛም እሷን ለሚመስለው ፊደል ማን እንደሆነች፣ ከየትና ለምን እንደመጣች በዝርዝር ነገረችው። እሱም "ሰ" እንደሚባል ከነገራት በኋላ "በ" ን አትኩሮ በጣም የሚገርም ነው አንቺና እኔ በጣም እንመሳሰላለን፤ እኔ ከአንቺ የምለየው ጭንቅላቴ ላይ ቁንጮ ስላለኝ ብቻ ነው አላት። ከዛም በመቀጠል እህት እንዳለችው ነገራትና ድምጹን ከፍ አድርጎ "ሸ" "ሸ" እያለ እህቱን

ተጣራ። "ሽ" ም ከምትጫወትበት ቦታ በመምጣት ከ "በ" ጋር ተዋወቀች። "በ" ም "ሽ" ን አንቺና ወንድምሽ በጣም ትመሳሰላላችሁ፤ ከወንድምሽ የምትለይው አንቺ ጸጉርሽ ላይ ሪቫን ስላለሽ ነው አለቻትና "በ" የ"ሸ"ን ሪቫን ስለወደደችው እባክሽ ሪቫንሽን በጣም ስለወደድኩት እስቲ እኔም ጭንቅላቴ ላይ ላድርገው ብላ "ሽ" ን ጠየቀቻት። "ሽ"ም በጣም አዝናለሁ የእኔ ሪቫን ከጸጉሬ ላይ መውለቅ አይችልም በማለት እንደማይወልቅ ነገረቻት። ከዛም "በ" "ሰ" ና "ሽ" አንድ ላይ አባሮሽ፣ ድብብቆሽና ሌባና ፖሊስ ከተጫወቱ በኋላ ሲመሽ "በ" በሌላ ቀን መጥታ አብራቸው እንደምትጫወት ነግራቸው ደስ እያላት ወደ ቤቷ ተመለሰች።

ማስታወሻ፡- የተረቱ ይዘት የገጸባህሪያቱ /የፊደላቱ/ ድምጽና ቅርጽ ላይ በማተኮር በስዕል ተደግፎ መቅረብ ይኖርበታል። እንዲሁም ለህጻናት በፊደላት ስምና ቅርጽ ላይ የተመረኮዘ አጭር ተረት በሚዘጋጅበት ጊዜ ገፀ ባህሪያቱ ራሳቸዉ ፊደላቱ መሆን አለባቸዉ።

ምዘና ፡- በተረት የፊደላትን ቅርጽ እና ስም መለየት መቻላቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- በእንቆቅልሽ የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ ይለያሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደላት ካርዶች፣ የእንቆቅልሽ መጽሃፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- እንቆቅልሽ በመጠየቅ የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ እንዲለዩ ማድረግ

ለምሳሌ ፡- እንቆቅልሽ/ህ?

ምን አዉቅልሽ/ህ?

እኔ ከፊደላት ዘሮች አንዱ ነኝ፣ ሁለት እግር አለኝ፣ የተደፋ ብርጭቆ እመስላለሁ፣ እኔ ማነኝ? ወዘተ…



ተግባር ሰባት ፡- በእንቆቅልሽ የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ መለየት

ምዘና ፡- በእንቅቅልሽ የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ መለየት መቻላቸዉን መገምገም::

ዓላማ ፡- በጨዋታ የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ ይለያሉ።

ተግባር ስምንት ፡- በጨዋታ የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ መለየት

ሴ. ሜትር የፊደል

መናገር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን የተዋወቋቸውን ፊደላት በማሳየት የፊደላቱን መጠሪያ ስም እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠል ሶስት የተዋወቋቸውን የፊደል ካርዶች ካሳዩ በኋላ ህፃናቱ አይናቸውን እንዲጨፍኑ ማድረግ
- ህፃናቱ አይናቸውን ሲጨፍኑ አንዱን በመደበቅ ህፃናቱ አይናቸውን ገልፀው በማየት የተደበቀው ፊደል ምን እንደሆነ እንዲናገሩ በማድረግ ‹‹የጎደለዉን እወቅ›› ጨዋታን ማጫወት
- ‹‹ልትወጣ ነዉ፣ ልትወጣ ነዉ›› የሚለዉን ጨዋታም በዚህ መልኩ ማጫወት፡-
    - መምህር ለሁሉም ህፃናት የተጻፉትን ትንንሽ ፊደላት መስጠት
    - ከዛም መምህር ከህጻናቱ ፊት በመቆም ትልልቅ የፊደል ሰሌዳዎቹን ከኋላ ደብቆ መያዝ
    - ከዛም ‹‹ልትወጣ ነዉ፣ ልትወጣ ነዉ›› በማለት አንዱን ለህጻናቱ ማሳየት
    - መምህር የያዙትን አይነት ፊደል የያዙ ህጻናት እንዲያወጡ ማድረግ
    - የፊደሏን መጠሪያ ስም እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በጨዋታ የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ መለየት መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር ዘጠኝ ፡- በፊደል ፐዝል የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ መለየት



መናገር

ዓላማ ፡- የፊደል ፐዝል በመገጣጠም የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደል ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አራት ቦታ የተቆራረጠ የፊደል ፐዝል በማሳየት እንዴት እንደሚገጣጠም ማሳየት
- ሁለት ወይም ሶስት ህፃናት ከህፃናቱ ፊት ወጥተው የፊደል ፐዝልን እንዲገጣጥሙና የገጣጠሙት ፊደል ማን እንደሆነ እንዲናገሩ ማነቃቃት
- ትክክል መሆንና አለመሆናቸውን የክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያረጋግጡ ማድረግ

ምዘና ፡- የፊደል ፐዝል በመገጣጠም የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ መለየት መቻላቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- ፊደላትን ከላይ ወደታችና ከግራ ወደቀኝ ያነባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደል ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተዋወቋቸዉን ፊደላት ከላዩ ወደ ታች እና ከግራ ወደ ቀኝ መጻፍ
- ህፃናቱ በህብረት በተርታ እንዲያነቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ፊደላትን ከላይ ወደታችና ከግራ ወደቀኝ ማንበብ ችሎታቸዉን መገምገም።

ተግባር አስራ አንድ ፡- የፊደላት ዶሚኖ መጫወት

ዓ... ይለማመዳሉ።

ተግባር አስር ፡- ፊደላትን ማንበብ

መናገር

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደላት ዶሚኖ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህፃናቱ ሊገባቸው በሚችል መልኩ የዶሚኖ አጨዋወት ሂደትና ህጎችን መግለፅ
- በተዋወቋቸው ፊደላት የተዘጋጁ የፊደላት ዶሚኖዎችን በመስጠት ሁለት ሁለት በመሆን በጠረጴዛቸው ላይ እንዲጫወቱ ማድረግ

ለምሳሌ፡-

በከ    ሰለ    | ከ | ሽ |    ለኸ    ሸበ    ኸሰ

- ሲጫወቱ እየዟዟሩ በማየት አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት

ምዘና ፡- ህጉን ተከትለው በመጫወት የፊደላትን ድምጽ እና ቅርጽ መለየት መቻላቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ፊደላትን በማዛመድ የፊደላትን ድምጽ እና ቅርጽን መለየት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደላት ሎቶ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

ለምሳሌ ፡-

ኸለሸበሰከ    ለ    ሸ    ከ

በ    ኸ    ሰ



ተግባር አስራ ሁለት ፡- ተመሳሳይ ፊደላትን ማዛመድ

መናገር



- በጥንድ ያሉ የተዋወቋቸውን ፊደላት ለሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ መስጠት
- በቅርፃቸው ተመሣሣይ የሆኑ ፊደላትን እንዲያዛምዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይ ፊደላትን በማዛመድ የፊደላትን ድምጽ እና ቅርጽን መለየት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- የስዕሎችን እና የፊደላትን ስያሜ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ስዕሎች፣ ከላይ ወደ ታችና ከግራ ወደቀኝ የተዋወቋቸዉ ፊደላት የተጻፈባቸዉ ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህጻናት ስዕሎቹንና ከላይ ወደ ታችና ከግራ ወደቀኝ የተዋወቋቸዉ ፊደላት የተጻፈባቸዉን ወረቀቶች ለእያንዳንዳቸዉ መስጠት
- ህጻናት ወጥተዉ ስዕሎቹን /ፊደሎቹን/ ከላይ ወደታች እና ከግራ ወደቀኝ በማንበብ መጠሪያ ስማቸዉን እንዲናገሩ ማበረታታት

ተግባር አስራ ሶስት ፡- የስዕሎችን እና የፊደላትን ስያሜ መናገር

መናገር

ተግባር አስራ አራት ፡- ፊደላትን ገጣጥሞ ማንበብ

ዓላማ ፡- ፊደላትን ገጣጥሞ ማንበብ ይለማመዳሉ።

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደላት ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተተዋወቋቸውን ፊደላት የያዙ ፍላሽ ካርዶችን በመጠቀም አጠገብ ለአጠገብ በማስቀመጥ ፊደላቱን በመቁጠር ማንበብን እንዲለማመዱ ማበረታታት

- ያነበቡትን ቃል ትርጓሜ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ
- የህጻናቱን መልስ ካዳመጡ በኋላ ያነበቡት ቃል ትርጓሜን መንገር

ምዘና ፦ ፊደላትን ገጣጥመዉ ማንበብ መቻላቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፦ ቃላትን ማንበብ እና ትርጉማቸዉን መረዳት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ የቃላት ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ካርዶቹን በመጠቀም እያንዳንዱን ፊደል ከመምህር ጋር አብረው እየቆጠሩ ማንበብን እንዲለማመዱ ማድረግ
- የቃላቱን ትርጉም ማሣወቅ

ምዘና ፦ ቃላትን ማንበብ እና ትርጉማቸዉን መረዳት መለማመዳቸዉን ጥያቄዎች በመጠየቅ ማረጋገጥ።

## ተግባር አስራ ስድስት ፦ ተመሳሳይ ቃላት ማዛመድ

መናገር

ዓላማ ፦ ተመሳሳይ ቃላትን በማዛመድ ቃላትን ማንበብ እና ትርጉማቸዉን መረዳት ይለማመዳሉ።

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ የቃላት ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- እነዚህን ካርዶች ለእያንዳንዱ ህጻን በመስጠት ለማንም ሳያሳዩ እንዲያነቡ ማድረግ
- ቀጥሎም በትልቅ ወረቀት ላይ ቃላቱን ጽፎ ተራ በተራ ማሣየት
- ያንን ቃል የያዘ/ች ህጻን ከመምህር አጠገብ እንዲቆም/እንድትቆም ማድረግ

- ቃሉን በሕብረት እንዲያነቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይ ቃላትን በማዛመድ ቃላትን ማንበብ እና ትርጉማቸዉን መረዳት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- የቃላት ጨዋታዎችን በመጫወት ቃላትን ማንበብ እና ትርጉማቸዉን መረዳት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ የቃላት ዶሚኖ እና የቃላት ሎቶ

የአተገባበር ዘዴ ጥ

ከሰለ

- በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ የቃላት ዶሚኖ እና የቃላት ሎቶ ለሕፃናት መስጠት
- እየተጫወቱ ንባብን እንዲለማመዱ እድሉን መስጠት

ለምሳሌ፡-

ለበሰሸበሸበ ሸሸለበሰ ሰበሰበሸሸ ሸበሸበሰበሰበ

ሰበሰበ ሸሸ

ከለለ ሸበሸበ ለበሰ ዎች መጫወ

| | | |
|---|---|---|
| ከለለ | ሸሸ | ሸበሸበ |
| ለበሰ | ሰበሰበ | ከሰለ |

ምዘና ፡- የቃላት ጨዋታዎችን ሲጫወቱ ቃላት የማንበብ ክህሎታቸዉን መገምገም።
መናገር

ዓላማ ፡- የመጠሪያ ስማቸውን ፊደላት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቆራረጡ ወረቀቶች፣ ደብተር፣ ፋይል፣ ምሣ ዕቃ ወዘተ…



ተግባር አስራ ስምንት ፡- የመጠሪያ ስማቸውን ፊደላት መለየት

መናገር



የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በግል ንብረቶቻቸው ላይ በወረቀት ስማቸውን ጎላ አድርጎ መፃፍ

  ለምሳሌ፡- በስዕል ደብተራቸው፣ በፋይላቸው፣ በምሣ ዕቃቸው ወዘተ…
- የስማቸውን ፊደላት አስተውለው እንዲመለከቱ ማድረግ
- እያንዳንዱ ፊደል የስማቸውን ድምጽ እንደያዘ በመንገርስማቸው የተፃፈባቸውን ፊደላት እንዲለዩ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ይህ ተግባርበአንድ ክ/ጊዜ ተከናውኖ የሚያበቃ ሳይሆን በተደጋጋሚ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሁሉ የስማቸውን ፊደላት እንዲለዩ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- የመጠሪያ ስማቸውን ፊደላት መለየት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ ዘጠኝ ፡- የራስን ስም መለየት

ዓላማ ፡- የራሳቸዉን ስም ከሌሎች ስሞች ይለያሉ።
መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የክፍሉ ተማሪዎች ስሞች የተፃፈባቸዉ ካርዶች/ወረቀቶች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ስማቸውን በደንብ ከለዩ በኋላ እነዚህን ካረዶች/ወረቀቶች/ ለሕፃናቱ መስጠት
- የራሳቸውን ስም እንዲፈልጉ እና ሲያገኙት በከለር እንዲያከቡት ማድረግ

ምዘና ፡- የራሳቸዉን ስም ከሌሎች ስሞች መለየት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የራሳቸዉን ስም ፊደላት ከሌሎች ስሞች ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የህጻናቱን ስም አንዱን ፊደል አጉድሎ እና ሌሎች ፊደላት ከታች አራርቆ የተጻፈባቸዉ ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-



ተግባር ሀያ ፡- የራስን ስም ፊደላት ከሌሎች መለየት

መናገር



- የህጻናቱን ስም አንዱን ፊደል አጉድሎ እና ሌሎች ፊደላት ከታች አራርቆ የተጻፈባቸዉን ወረቀቶች ለእያንዳንዳቸዉ መስጠት
- የጎደላቸውን ፊደል ፈልገዉ እንዲያከቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የራሳቸዉን ስም ፊደላት ከሌሎች ስሞች መለየት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሀያ አንድ ፡- የተጀመሩ ስዕሎችን መጨረስ

ዓላማ


መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተጀምረው ያልተጨረሱ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- እነዚህን በመስጠት እነሱ እንዲጨርሷቸው ማድረግ
- ሲጨርሱም ለጓደኞቻቸው በማሣየት ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ማድረግና ማበረታታት

ለምሳሌ፡-



ምዘና ፡- በጅምር የቀሩ ስዕሎችን ተረድተው መጨረስ መቻላቸዉን መገምገም።



ተግባር ሀያ ሁለት ፡- መጽሃፍ አያያዝ እና አገላለጽ

ዓላማ ፡- የመጽሃፍ አያያዝ እና አገላለጽን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስዕል / የተረት/ መጽሃፍት፣ መጽሄቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መጽሃፍን በግራ እጅ በመያዝ በቀኝ እጅ ከታች ጠርዙን በመያዝ ከቀኝ ወደ ግራ እንዴት መግለጽ እንደሚቻል በማሳየት መንገር
- ህጻናቱም እየወጡ የመጽሃፍ አያያዝን እና አገላለጽን እንዲለማመዱ ማድረግ
- ለህጻናት የተለያዩ ስዕሎች ያላቸዉ መጽሄቶች እና መጽሃፎች በመስጠት የመጽሃፍ አያያዝን እና አገላለጽን እንዲለማመዱ ማድረግ
- መጽሃፍት በእርጥብ እጅ ከተያዙና ምግብና ዉሃ ከተንጠባጠበባቸዉ ሊበላሹ እንደሚችሉ በተግባር በማሳየት እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የመጽሃፍ አያያዝ እና አገላለጽ መለማመዳቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ህያ ሶስት ፡- የተጎዱ መፅሀፍትን ማከም

ዓላማ ፡- የተገነጠሉና የተቀደዱ መፅሀፍትን መጠገንን ይለማመዳሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከመጻሕፍት የተጻፈ ደብዳቤ፣ ፖስታ፣ የተገነጣጠሉ እና የተጎዱ የህጻናት ስዕል፣ የተረት መጽሀፍት፣ ለመጠገን የሚረዱ መሳሪያዎች (ፕላስተር፣ ክላሰሮች፣ መቀስ ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በህጻናት ተወዳጅ ከሆኑት የስዕልና የተረት መጽሃፍት አንዱ ዉስጥ ለህጻናት ደብዳቤ [illegible] ቶ ማንበብ
- መጽሃፍቱ በመገንጠላቸዉና በመቀዳደዳቸዉ ምክንያት እንደተጎዱና መጽሃፍቱን መናገር/መጠገን የሚረዱ መሳሪያዎች አብረዉ እንደተላኩ በመንገር አዉጥቶ ማሳየት
- ህጻናቱ መጽሃፍቱን ለመጠገን ፈቃደኛ መሆናቸዉን መጠየቅ
- ከዛም የተቀዳደዱትንና የተገነጠሉትን መጻህፍት ከህጻናቱ ጋር አብሮ መጠገን እና መሸፈን
- በመጨረሻም መጽሀፎቹ ጥገና ከተደረገላቸዉ በኋላ እንደተስተካከሉና ህጻናቱን

እንዳመሰገኗቸዉ መንገር

- እነሱም ሆኑ ሌሎች ህጻናት እና አዋቂዎች በደንብ እንዲይዟቸዉና እንዳይገነጥሏቸዉ አደራ እንዲሉ በመንገር ማጠቃለል

ምዘና ፡- የተጎዱ መጽሃፍትን መጠገንን መለማመዳቸዉን በማየት ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት ብ | ብቃት |
|---|---|
| 4. የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት | 4.1. የተለያዩ ድርጊቶችን ለማከናወን እጃቸዉን እና ዓይናቸዉን መጠቀም ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የልብስና የጫማ ፍሬሞችም መክፈት፣ መዝጋት፣ ማሰርና መፍታትን መለማመድ

መና ዓላማ ፡- ራሳቸውን ችለውየልብስና የጫማ ፍሬሞችን መክፈት፣መዝጋት፣ ማሰርና መፍታትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለየዩ መጠን ያላቸው የፕላስቲክ ዕቃዎች፣ ውሃ፣ አሸዋ የመሳሰሉት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የልብስ እና የጫማ ፍሬሞችን በመጠቀም እንዴት መክፈት፣ መዝጋት፣ ማስርና መፍታት እንደሚቻል ማሳየት
- ህፃናቱም ራሳቸውን ችለው መክፈትናመቆለፍ፣ ዚፕመዝጋትና መክፈት፣ የጫማ ማሰሪያ ማሰርና መፍታት እንዲለማመዱ ማድረግ
- በእለት ተእለት ህይወታቸውም የራሳቸውን ልብስ ቁልፍ መክፈትና መቆለፍ፣ የጫማ ማሰሪያቸውን መፍታትና ማሰር እንዲለማመዱ እድሉን መስጠት

ማስታወሻ ፡- ለወላጆቻቸውና ለአሳዳጊዎቻቸው በመንገር በቤት ውስጥም ዕድሉ እንዲሰጣቸውና እንዲለማመዱ ማድረግ።

ምዘና ፡- የልብስና የጫማ ፍሬሞችን መክፈት፣ መዝጋት፣ ማሰርና መፍታት መለማመድ መቻላቸውን ተግባሮቹን ሲተገብሩ በመመልከት መገምገም።

**ተግባርሁለት ፡- ወረቀቶችን መጨምደድ፣ መጠምዘዝ፣ መተልተልና መቆራረጥ**

ዓላማ ፡- ወረቀቶተን መጨምደድ፡ መጠምዘዝ፡ መተልተልና መቆራረጥ ይችላሉ
ዐናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ አገልግሎት የማይሰጡ ባለቀለም ወረቀቶች፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- እነዚህን ለሕፃናት በየጠረጴዛቸው ላይ መስጠት
- መምህር/ት የሚያደርጉትን በማየት እነሱም የተሰጣቸውን ወረቀት እንዲቀዱ፣ እንዲጠመዝዙ፣ እንዲጨመድዱ፣እንዲተለትሉ እና እንዲቆርጡት ማድረግ
- እያንዳንዱን ተግባር ሲያከናውኑ መምህር አሁን ሁላችሁም እንደ እኔ ወረቀቱን ቅደዱት በማለትና ምን እያደረጋችሁ ነዉ ብሎ በመጠየቅ ቃሉን ከተግባር ጋር ማዛመድ
- በመጨረሻም ሁሉም ሕፃናት የተቆራረጡትን ወረቀቶች ስብሰበው ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ እንዲጥሉማድረግ
- ከዛም እጃቸውን በውሃ እንዲታጠቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ወረቀቶችን መጨምደድ፣ መጠምዘዝ፣ መተልተልና መቆራረጥ መቻላቸውን በማየት መገምገም፡፡

ዓላማ ፡- ቁሳቁሶችን በቀለማቸው ይለያሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ቀለም ያላቸው ቁሳቁሶች /መጫወቻዎች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- እነዚህን ለህጻናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ መስጠት
- በቀለማቸው እንዲመድቡ ማድረግ
- ቁሳቁሶቹን /መጫወቻዎቹን / ለምን በአንድ ላይ ሊመድቡዋቸው እንዲችሉ በንግግር እንዲገልጹ ማድረግ



**ተግባር ሶስት ፡- ቀለማትን መለየት**

መናገር



ምዘና ፡- ቁሳቁሶችን በቀለማቸው መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የእጃቸዉን መዳፍ ያትማሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ የውሃ ቀለም፣ ድንች፣ ካሮት፣ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

**ተግባር አራት ፡- የእጅ መዳፍን ማተም**

- የውሃ ቀለምን በመጠቀም የእጃቸውን መዳፍ እንዴት ማተም እንደሚችሉ ማሳየት በመረጡት የውሃ ቀለም በወረቀት ላይ እንዲያትሙ ማድረግ

መናገር

- ባተሙበት ወረቀት ግርጌም ስማቸውንና ቀኑን መፃፍና ሲደርቅ በክፍል ግድግዳ ላይ መለጠፍ
- ሕፃናቱ በክፍል ውስጥ በመዘዋወር ስማቸው የተፃፈበትን ወረቀት በማንበብ የራሳቸውን ስራ እንዲለዩ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- በሌላ ክፍለ ጊዜ ይህንን የህትመት ሥራ ድንችን ካሮትንና የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን በመጠቀም ማለማመድ ይቻላል።

ምዘና ፡- እጃቸዉን ሲያትሙ በመከታተል የአይን እና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅታቸዉ መዳበሩን መገምገም።

**ተግባር አምስት ፡- ቅርጾችን መለየት**

ዓላማ ፡- ቁሳቁሶችን በቅርጽ ይለያሉ።

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጾች (ጎነ ሶስት፣ ጎነ አራት፣ ኩብ) እና የተለያዩ ቁሳቁሶች (ኩባያ/ጣሳ፣ ደብተር፣ ምሳ እቃ፣ ቦርሳ ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የጂኦሜትሪ ቅርጾችን እና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በየጠረጴዛቸው በመስጠት በየቅርጻቸው እንዲመድቡ ማድረግ
- ሲመድቡ እየተዟዟሩ በማየት ማበረታታትና አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት
- መድበው ሲጨርሱ ለመምህር እንዲያሳዩና ለምን እንደዛ ሊመድቡ እንዲቻሉ እንዲናገሩ ማድረግ
- የተለያዩ ቁሳቁሶችን በቅርጻቸዉ መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ምዘና ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶችን በቅርጻቸዉ መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ስድስት ፡- ቀለማትን፣ ቅርጾችን እና መጠንን መለየት

መናገር

ዓላማ ፡- የተለያዩ ነገሮችን በቀለማት፤ በቅርጽ እና በመጠናቸው ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በቀለማቸው በቅርጻቸው ወይም በቁመታቸው የተለያዩ ቁሳቁሶች የተለያዩ መጠን ያለቸው ሽመሎች (የእንጨት ቁርጥራጮች)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ቁሳቁሶቹን ለህጻናት መስጠት
- በቀለማቸው በቅርጻቸው ወይም በቁመታቸው እንዲመደቡ ማደረግ
- ሽመሎቹን በመስጠት በቁመታቸው መሰረት እንዲመድቡ ማድረግ
- እንዴት ሊመደቡ እንደቻሉ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የተለያዩ ነገሮችን በቀለማቸው በቅርጽ እና በመጠናቸው መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም ስእሎችን በመሙላት ይሰራሉ

ተግባር ሰባት ፡- በተለያዩ ነገሮች ስእሎችን መሙላት /ሲዶ ኮላጅ መስራት/



መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእህል ዘሮች፣ ላባዎች፣ ጥጥ፣ ወዘተ.. በወፍራም ክላሰር ላይ የተሳሉ ህጻናቱ የሚያውቁዋቸው ነገሮች፡- ኳስ፤ ቤት፤ ዶሮ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ በታ ላይ በመቆም ጎላ ብሎ የተሳለን ስእል የውስጥ ክፍሉን ኮላ በመለቅለቅና የተለያዩ የእህል ዘሮች፣ ላባዎች፣ ጥጥ፣ የመሳሰሉትን በመጠቀም በመሙላት ማሳየት
- ለህጻናቱም ቀለል ያሉ ስዕሎችን በመስጠት ባዩት መሰረት እንዲሰሩ ማድረግ
- ሲሰሩ ተዘዋውሮ በማየት ማበረታታትና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ

ምዘና ፡- ስእሎችን የተለያዩ ነገሮችን በመሙላት መስረታቸውን በማየት መገምገም።

ዓላማ ፡- የፊደላትን የውስጥ ክፍል ከመስመር ሳይወጡ በተለያዩ ነገሮች መሙላትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ማጣበቂያ /ኮላ/፤ ባለቀለም ቁርጥራጭ ወረቀቶች፤ በወረቀት ላይ ጎላ ጎላ ብለው የተጻፉ የተዋወቋቸው ፊደላት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጎላ ብሎ በድርብ የተፃፈ ህፃናቱ የሚያውቁትን ፊደል የውስጠኛውን ክፍል ማጣበቂያ /ኮላ/ በመለቅለቅ በተለያዩ ቁርጥራጭ ወረቀቶች በመሙላት ማሳየትና ምን ፊደል እንደሆነ መጠየቅ
- ለእያንዳንዱም ህፃን ከዚህ በፊት የተዋወቋቸውን በድርብ የተፃፈ አንድ ፊደል በመስጠት ባዩት መሠረት ከመስመር ሳይወጡ እንዲሰራ ማድረግ
- ሲጨርሱም በየተራ የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩና ምን ፊደል እንደሆነ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት
- በመጨረሻም በክፍል ውስጥ ለእይታ አመቺ በታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፡- የፊደላቱን የውስጥ ክፍል በተለያዩ ቁርጥራጭ ወረቀቶች ከመስመር ሳይወጡ

ተግባር ስምንት ፡- የፊደላትን የውስጥ ክፍል መሙላት

መናገር



ተግባር ዘጠኝ ፡- መሰረታዊ ቅርጾችን መስራት

ዓላማ ፡- መሰረታዊ ቅርጾችን መስራትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዛፍ ፍሬዎች፣ የክብሪት እንጨቶች፣ ቆርኪዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የክብሪት እንጨቶችን በመጠቀም ህጻናት የተዋወቋቸውን ቅርጾች /ፊደላት/ በየጠረጴዛቸው ላይ በመሄድ እንዴት እንደሚሰሩ ማሳየት
- ለህጻናቱም እድሉን በመስጠት እንዲለማመዱ ማድረግ
- የሠሩት ምን እንደሆነ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- መሠረታዊ ቅርጾችን መስራት መለማመዳቸውን መከታተል።

**ተግባር አስር ፡- ስዕሎችን ቀለም መቀባት**

ዓላማ ፡- የተለያዩ ስዕሎችን ከመስመር ሳይወጡ ቀለም በመቀባት ለጽሁፍ ይዘጋጃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ስዕሎች፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህጻናት ጎላ ብሎ የተሳለ ስዕልን ከመስመር ሳይወጣ እንዴት በባለቀለም እርሳስ/ ከለር/ መቀባት እንደሚቻል ማሳየት
- ለእያንዳንዳቸው ስዕሎች በመስጠት እንዲቀቡ ማድረግ
- የምን ስዕል እንደሆነና ምን ዓይነት ቀለም እንደቀቡት እንዲናገሩ ማበረታታት
- የራሳቸውን ስራ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲያስተያዩ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ ስዕሎችን ከመስመር ሳይወጡ ቀለም በመቀባት ለጽሁፍ መዘጋጀታቸውን መገምገም።



**ተግባር አስራ አንድ ፡- ስዕል መሳል እና ቀለም መቀባት**

መናገር



ዓላማ ፡- የተለያዩ ስዕሎችን በመሳል ቀለም ይቀባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት በማጣጠፍ የተዘጋጀ ትንሽ መጽሐፍ፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ወረቀትን በማጣጠፍ የተዘጋጀ መፅሐፍ ለእያንዳንዳቸው በመስጠት የፈለጉትን ነገር እንዲሰሩ ማድረግ
- በመቀጠልም የሳሉትን ስዕል የፈለጉትን ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- በመጨረሻም ምን እንደሳሉና ምን አይነት ቀለም እንደቀቡ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ።

ምዘና ፡- የተለያዩ ስዕሎችን መሳል እና ቀለም መቀባታቸውን በማየት መገምገም።

## ተግባር አስራ ሁለት ፡- ተረትን ተረድቶ በስዕል መግለጽ

ዓላ[illegible] ፡- ተረትን ተረድተው በስዕል [illegible]

መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳሶች /ከለሮች/፣ የተረት መጽሀፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህጻናቱ የሚመጥን አጭር ገጠመኝ፣ታሪክ ወይም ተረት መንገር
- በመቀጠልም ህጻናቱ ምን እንዳስደሰታቸውና እንዳላስደሰታቸው በመጠየቅ ማወያየት
- ቀጥሎም ለእያንዳንዱ ልጅ እርሳስ፣ ወረቀትና ባለቀለም እርሳሶች /ከለሮች/ በመስጠት ከሰሙት ታሪክ ውስጥ ያስደሰታቸውን፣ ያሳዘናቸውን ወዘተ... እንዲስሉና ቀለም እንዲቀቡት ማድረግ

ምዘና ፡- ተረትን ተረድተው በስዕል መግለጽ መለማመዳቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- በድርብ የተጻፉ ፊደላትን ቀለም ይቀባሉ እንዲሁም ስያሜያቸዉን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎላ ጎላ ብለው በድርብ የተጻፉ ፊደላት፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጎላ ጎላ ብለው በድርብ የተጻፉ ፊደላትን ለህጻናትን በመስጠት ከመስመር ሳይወጡ እንዲቀቡ ማድረግ
- የቀቡትን ፊደል መጠሪያ ስምና የቀቡትን የቀለም ዓይነት ምን እንደሆነ ወጥተው በጓደኞቻቸው ፊት እንዲናገሩ ማድረግ
- ስራቸውን በክፍል ውስጥ ለእይታ አመቺ በሆነ ቦታ ስማቸውን በመጻፍ መለጠፍ

ምዘና ፡- በድርብ የተጻፉ ፊዳላትን ቀለም መቀባታቸውንና ስያሜያቸውን መናገር መቻላቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም።

ዓላ ... ዳሉ።

**ተግባር አስራ ሶስት ፡- ፊደላትን ቀለም መቀባትና ስያሜያቸዉን መናገር**

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክር፣ ዱልዱም መርፌ፣ ወፍራም ክላሰሮች ላይ ተስለው አልፎ

**ተግባር አስራ አራት ፡- የተለያዩ ቅርጾችን መጥለፍ**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

ስያሜያቸዉን መናገር

- ወፍራም ክላሰሮች ላይ ተስለው አልፎ አልፎ በዱልዱም መርፌ የተበሱ የተለያዩ ቅርጾችን መናገር የሱፍ ክር በመጠቀም እንዴት እንደሚጠለፍ ማሳየት
- ለእያንዳንዳቸው በክላሰር ላይ የተሰራ ስእል፣ዱልዱም መርፌና የሱፍ ክርን በመስጠት ባዩት መሰረት እንዲለማመዱ ማድረግ
- ሲጨርሱም የሰሩት ምን እንደሆነ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ዱልዱም መርፌን በመጠቀም በቀዳዳ ውስጥ መርፌና ክርን በማስገባትና በማስወጣት መጥለፍ መለማመዳቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን መስመር ጠብቀው ያደምቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ በነጠብጣብ የተሰሩ የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አንድ ሳይደምቅ የተሰራን የጂኦሜትሪ ቅርፅ መስመር ጠብቆ እንዴት ማድመቅ እንደሚቻል ለህፃናቱ ማሳየት
- ለእያንዳንዳቸው ሁለት ወይም ሶስት የጂኦሜትሪ ቅርፆች ሳይደምቁ የተሰሩበትን ወረቀትና እርሳስ በመስጠት ባዩት መሠረት ቅርጾችን መስመር ጠብቀው እንዲያደምቁ ማድረግ
- ሲጨርሱም ያደመቁትን ቅርፅ እንዲናገሩ ማበረታታት
- የሰሩትን ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፡- የቅርጾችን መስመር ጠብቀው ማድመቃቸውን በማየት ማረጋገጥ።

## ተግባር አስራ አምስት ፡- ቅርጾችን ማድመቅ

ዓላማ ፡- ስዕሎችን መስመር ጠብቀው ያደምቃሉ።

ስያሜያቸዉን መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ በነጠብጣብ የተሰሩ ጎላ ያሉ ስዕሎች (ቤት፣ መኪና፣ አበባ፣ የመሳሰሉት)

መናገር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ ደምቀው ያልተሰሩ ስዕሎቹን ለህጻናት በመስጠት መስመሩን ጠብቀው ማድመቅን እንዲለማመዱ እድሉን መስጠት
- የሰሩትንም በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እንዲያሳዩና ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ



## ተግባር አስራ ስድስት ፡- ስዕሎችን ማድመቅ

ስያሜያቸዉን መናገር

መናገር



- ከወረቀቱ ግርጌ ስማቸውንና ቀኑን በመፃፍ ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፦ ስዕሎችን መስመር ጠብቀው ማድመቃቸውን በማየት መገምገም

ዓላማ ፦ መሰረታዊ መስመሮችን መስራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀቶች፣ እርሳስ፣ ትልቅ ወረቀት ላይ የተሰሩ መሰረታዊ መስመሮች (ቋሚ፣ አግዳሚ፣ስያፍ፣ቅንፍ፣ዚግዛግ፣ነጠብጣብ፣ ወዘተ...)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መሰረታዊ መስመሮችን በአየር ላይ እየሰሩ ለህጻናቱ ማሳየት
- ያዩትን በአየር ላይ በመስራት እንዲለማመዱ ማድረግ
- በተሰጣቸው ወረቀት ላይ መሰረታዊ መስመሮቹን እንዲሰሩ ማድረግ
- መሰረታዊ መስመሮችን በማገጣጠም የተለያዩ ምስሎችን እንዴት እንደሚሰሩ ማሳየትና ማለማመድ

ለምሳሌ፦ መንገድ፣ መሰላል፣ መስቀል፣ ጸሀይ፣ ዝናብ፣ ወዘተ...

ምዘና ፦ መሰረታዊ መስመሮችን መስራት መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ ሰባት ፦ መሰረታዊ መስመሮች መስራት

ስያሜያቸዉን መናገር

ዓላማ ፦ የፊደላት ነጠብጣብን በማድመቅ ፊደላትን መጻፍ እና ስያሜያቸውን መናገር መለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ እርሳስ፣ ጎላ ጎላ ተደርገው በነጠብጣብ የተጻፉ የተዋወቋቸው ፊደላት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከዚህ በፊት የተዋወቋቸውን በነጠብጣብ የተሰሩ ፊደላትን ለእያንዳንዱ ህጻናት በመስጠት ነጠብጣቡን ተከትለው እንዲያደምቁ ማድረግ



ተግባር አስራ ስምንት ፦ የፊደላት ነጠብጣብን ማድመቅ

ስያሜያቸዉን መናገር

መናገር



- ከዚያም በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው ፊደሉን እያሳዩ "ማነኝ ማነኝ? ፤ ልጆች እውቁኝ" ብለው በመዘመር የክፍል ጓደኞቻቸውን እንዲጠይቁ ማድረግ

ምዘና ፦ የፊደላት ነጠብጠብን በማድመቅ ፊደላትን መጻፍ እና ስያሜያቸውን መናገር መለማመዳቸውን መከታተል።

ዓላማ ፦ ፊደላትን በቀለም መጻፍ ይለማመዳሉ።

ተግባር አስራ ዘጠኝ ፦ ፊደላትን በቀለም መጻፍ

ስያሜያቸዉን መናገር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

መናገር

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን የውሃ ቀለምን በመጠቀም ጠቋሚ ጣትን ቀለም ውስጥ እየነከሩ የተዋወቋቸውን ፊደላት ቅርጾች በመጻፍ ማሳየት
- ለህፃናቱም በየጠረጴዛቸው ላይ የውሃ ቀለምና ወረቀትን በመሰጠት ባዩት መሠረት ከሚያውቋቸው ፊደላት ደስ ያላቸውን በመስራት እንዲለማመዱ እድሉን መስጠት
- በመቀጠልም መምህር የነገሯቸውን ፊደላት እንዲፅፉና ፅፈው ሲጨርሱም ቀለም ባልነካው እጃቸው ከፍ አድርገው እንዲያሳዩ ማድረግ

ምዘና ፦ ፊደላትን በቀለም መጻፍ መለማመዳቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ ፊደላትን መጻፍ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ እርሳስ፣ በወረቀት ላይ የተሰሩ የተዋወቋቸው ቅርጾች እና ፊደላት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦



ተግባር ሀያ ፦ ፊደላትን መጻፍ

ስያሜያቸዉን መናገር



- በወረቀት ላይ የተሰሩ የተዋወቋቸው ፊደላትን ለእያንዳንዱ ህጻን መስጠት
- ከስሩ አስመስለው እንዲሰሩ እና እንዲጽፉ እድሉን መስጠት
- ሲሰሩ እየተዟዟሩ በማየት ማበረታታትና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ
- በመጨረሻም ምን ፊደልን እንደጻፉ በመጠየቅ ማበረታታት

ምዘና ፡- ፊደላትን መጻፍ መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

**2.3.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -----------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም -------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም --------------------------------------------- ዓመተ ምህረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ---------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ---------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት---------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመቱ መጀመሪያ | በዓመቱ አጋማሽ | በዓመቱ መጨረሻ |
| **1.** መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽመስጠት | | | |
| 1.1. ለትዕዛዞችና ለመመሪያዎች ምላሽ መስጠት ይችላሉ | | | |
| 1.2. የድምፆችን አቅጣጫ ማመልከትና የድምፆችን ምንጭ መለየት ይችላሉ | | | |
| 1.3. የሰሙትን መናገር ይችላሉ | | | |
| 1.4. ተረቶችን አዳምጠው የተረዱትን መግለጽና መልሰው መናገር ይችላሉ | | | |
| **2.** በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት | | | |
| 2.1. ራስንና አካባቢን በተገቢው መንገድ መግለጽ ይችላሉ | | | |
| **3.** በማንበብ መደሰት ዕውቀት ማግኘትና መረዳት | | | |
| 3.1 3.1. ስዕሎችንና የፊደላት ቅርፆችን መለየትና መረዳት ይችላሉ | | | |
| **4.** የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት | | | |
| 4.1. የተለያዩ ድርጊቶችን ለማከናወን እጃቸውንና ዓይናቸውን መጠቀም ይችላሉ | | | |

## 2.4 በዕለት ተዕለት እቅስቃሴ የሂሣብ ስሌትና ጽንሰ ሐሳብን መጠቀም

### 2.4.1 ማብራሪያ

ሂሣብ በቀጥታ በዕለት ተዕለት ተሞክሮ ላይ ተመስርቶ በነገሮች መካከል ያለ ግንኙነትን ለመረዳት የሚጠቅም ሲሆን በሁሉም የሕይወት መስክ ይገኛል። የሕፃናት የዕለት ተዕለት ገጠመኝም ከሂሣብ ጋር የተገናኘ ነው። ሕፃናት ሂሣባዊ ጽንሰ ሐሳቦችን እንዲረዱ ወይም ሂሳባዊ አስተሳሰብ (Mathemetical Thinking) እንዲያዳብሩ በቁሳቁሶች የዳበረ አካባቢ ያስፈልጋቸዋል በተጨማሪም ቁሳቁሶችን እየተጠቀሙ በራሳቸው አቅም እንዲንቀሳቀሱና አካባቢያቸውን እየፈተሹ እንዲማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ ሕፃናት ራሳቸውን ችለው በደረጃቸው ማሰብ የሚችሉ ችግር የመፍታት ዝንባሌ ያላቸውና የሂሣብ ትምህርትን በመዝናናትና በደስታ የሚማሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

> የሂሣብ ጽንሰ ሐሳቦች ቀስ በቀስ እያደጉ የሚኖሩና ከሌሎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ጋር የተለያዩ ሲሆኑ ብዙ እና ጥቂትን ትልቅና ትንሽ ቁሶችን ከመለየት የጀመሩት የሂሣብ ጽንሰ ሐሳብ ቀስ በቀስ ቁጥሮችን ወደመለየትና ስሌት እያደገ /እየዳበረ/ ይሄዳል። ስለሆነም የሂሣብ ትምህርት የሕፃናትን አእምሮ የሚያዳብርና በደስታ የሚሳተፉበት እንዲሆን እንቅስቃሴው ተግባራዊና ከዕለት ተዕለት ክንውኖች ጋር የተያያዘ ሆኖ ታቅዶ፣ ከዕድሜና ችሎታቸው ጋር በተመጣጠነ መልኩ መከናወን ይኖርበታል።

### 2.4.2 አጠቃላይ ዓላማ

1. የቁሳቁሶችንና ቅርፆችን ተመሣሣይነትና ልዩነት ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት እንዲችሉ ለማድረግ
2. ቁሳቁሶችንና ቁጥሮችን ከ 1-20 መቁጠርና የገንዘብ አይነቶችንና ምስላቸውን መለየት እንዲችሉ ለማድረግ
3. በቦታና በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት፣ የሳምንቱን ቀናት ወራትን ልዩ ቀናትን መናገር እንዲችሉ ለማድረግ
4. ሰዎችን፣ ዕቃዎችን፣ አካባቢን መሠረት በማድረግ ቦታንና ርቀትን መግለጽ እንዲችሉ ለማድረግ

### **2.4.3** የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. የቁሶችን ባህርይ መፈተሽ መረዳትና መለየት

 1.1 በተለያዩ ቁሳቁሶችና ቅርፆች መካከል ያለውን ተመሣሣይነትና ልዩነት ማውጣት ይችላሉ

2. ነገሮችን በባህርያቸው መሠረት ማወዳደር

 2.1.በነገሮች መካከል ያለ ዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት ይችላሉ

3. ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት

 3.1. ቁሳቁሶችንና ቁጥሮችን ከ 1-20 መቁጠር ይችላሉ

4. በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መሰፈርቶችንና መሳሪያዎችን መጠቀም

 4.1.በቦታና በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት መጠቆም ይችላሉ

5. የጊዜ ጽንሰ ሐሳብን መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም

 5.1.የሳምንቱን ቀናት ወራትን የበዓል /ልዩ/ ቀናትን መናገር ይችላሉ

6. የቦታን ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም

 6.1 ሰዎችን፣ ዕቃዎችን አካባቢን መሠረት በማድረግ ቦታንና ርቀትን መግለጽ ይችላሉ

7. ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት፣ መግለጽና መጠቀም

 7.1 የገንዘብ ዓይነቶችንና ምስላቸውን መለየት ይችላሉ

2.4.4 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ፣ መረዳት እና መለየት | 1.1. በተለያዩ ቁሳቁሶችና ቅርፆች መካከል ያለውን ተመሣሣይነት እና ልዩነት ማውጣት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ ቁሳቁሶችን ማዛመድ

መናገር

ዓላማ ፦ ጥንድ የሆኑ ቁሳቁሶችን ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ኳሶች፣ ጠጠሮች፣ ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ዶቃዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-



- ኑ ቁ ረብ ኳሶች፣ ጠጠ ዎች፣ ፣ ዶ
- ጥንድ የሆኑትን አንዱን አውጥቶ ማሣየት
- በፊታቸው ከቀረቡት ውስጥ ጥንድ የሆኑትን ለይተው በማውጣት አንድ ላይ እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- አንድ ላይ ያስቀመጧቸውን በምን እንደሚመሳሰሉ መጠየቅ እና እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- <u>ጥንድ የሆኑ ቁሳቁሶችን በባህረ መለየት መቻላቸውን መገምገም፡፡</u>

ተግባር ሁለት ፡- ቁሳቁሶችን በመጠን ማዛመድ

መናገር

ዓላማ ፡- በመጠን የሚመሳሰሉ ቁሳቁሶችን ያዛምዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ኳሶች፣ ጠጠሮች፣ ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ዶቃዎች ወዘተ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያየ ቀለም የተቀቡ በመጠን የሚመሳሰሉ እና የሚለያዩ ቁሳቁሶች በመምህር ጠረጴዛ ላይ ማቅረብ
- ከየዓይነቱ አንዳንድ በሕፃናት ጠረጴዛ መደርደር
- በፊታቸው ያለዉን አንዱን ቁስ በመያዝ ወደ መምህር ጠረጴዛ በየተራ ወጥተው ተመሣሣዩ ላይ በመደረብ እንዲያመሳስሉ ማድረግ
- አዛምደው ሲጨርሱ በጠረጴዛቸው ላይ የቀሩት በምን እንደተለዩ በመጠየቅ ተመሣሣይነት እና ልዩነትን ማውጣት እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የሚመሳሰሉ እና የሚለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠን ማዛመድ መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- ቁሶችን በቅርጽ በመደረብ ልዩነታቸውን ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከችፕውድ የተዘጋጁ ጐነ ሶስት፣ ካሬ፣ ጐነ አራት፣ ክብ፣ ሞላላ ቅርጾች፣ በትልቅ ነጭ ወረቀት ላይ የተሳሉ ቅርፆች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከችፕውድ የተዘጋጁ ክብ፣ ጐነ ሶስት እና ጐነ አራት ቅርፆችበጥንድ ማደል
- እያንዳንዱን እያነሱ ምን እንደሚባል መናገር
- በተመሣሣዩ ላይ ደርበው እንዲያስቀምጡ እና እንዲያወዳድሩ ማድረግ
- በትልቅ ነጭ ወረቀት ላይ የተሳሉትን ቅርፆች ከፊት በመዘርጋት ከችፕውድ ከተዘጋጁት ቅርጾች ጋር ተመሣሣዮቹን ቅርጾች እንዲደርቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ቁሶችን በቅርጽ በመደረብ ልዩነታቸውን መገንዘባቸውን መከታተል።


## ተግባር አራት ፡- ተመሣሣይ ቅርፆችን ማዛመድ

ዓላማ ፡- ተመሣሣይ ቅርፆችን ያዛምዳሉ፡፡ መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቅርፆች ሎቶ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተመሣሣይ ቅርፆች ሎቶን ማቅረብ
- የማዛመድ ጨዋታን እንዲጫወቱ ማድረግ



ምዘና ፦ ተመሣሣይ ቅርፆችን ማዛመድ መቻላቸውን መገምገም፡፡

ተግባር አምስት ፦ ቅርጾችን በስም መለየት

ዓላማ ፦ የተለያየ ጎን ያላቸውን ቅርጾች በስም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጐነ ሶስት፣ ካሬ፣ ጐነ አራት፣ክብ፣ ሞላላ ምስሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከተለያየ ባለቀለም ወረቀት የተቆረጡ ክብ፣ ጐነ ሶስት፣ ጐነ አራት፣ ካሬ፣ ሞላላ ምስሎች በየጠረጴዛቸው ላይ ማስቀመጥ
- መምህር ክብን አንስተዉ ሲያሳዩ ህጻናት የሚመሳሰለውን በእጃቸው ወደላይ እንዲያነሱ እና እንዲያሳዩ ማድረግ
- ምን እንደሚባል በመጠየቅ ክብ መሆኑን ማስረዳት
- በእጃቸው የክቡን ዙሪያ እንዲዳስሱ ዳሶ ማሣየት
- ክብ የሚመስሉ ምን ነገሮች እንደሚያውቁ መጠየቅ እና ማወያየት
- ጐነ ሶስትንም አንስቶ ማሣየት
- ከፊታቸው ካሉት መርጠው በማውጣት እንዲያሳዩ ማድረግ
- ምን እንደሚባል መጠየቅ እና ስሙን በመናገር ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ
- ጐኖቹን አብሮ በእጅ ማሰቆጠር
- ጐነ አራትንም በዚሁ መልክ ማስለየት

ምዘና ፦ የተለያየ ቅርጾችን እየዳሰሱ ጐኖቹን በመቁጠር በስም መለየታቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ በካሬና በጐነ አራት ቅርፅ መካከል ያለውን ልዩነት ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ካሬና ሌሎች ጐነ አራት ሎጂካል ብሎኮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦



ተግባር ስድስት ፦ የካሬንና የጐነ አራት ቅርጽን ልዩነት መለየት

- ካሬና ሌሎች ጐነ አራት ሎጂካል ብሎኮች መስጠት
- ሊያዩ በሚችሉት መንገድ በፊታቸው በጥብጣብ /ማስመሪያ/ በየተራ ጐኖቻቸውን መለካት
- ካሬ ሲለካ አራቱም ጐን እኩል መሆናቸውን እንዲያስተውሉ ማድረግ
- ሌሎች ጐነ አራቶችን መለካት እና ልዩነታቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በካሬና በጐነ አራት ቅርፅ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሰባት ፡- ክብ እና ሞላላ ቅርፅን መለየት

ዓላማ ፡- የክብ እና የሞላላ ቅርፅ ባህሪን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክብ እና ሞላላ ቅርጽ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የክብና ሞላላን ልዩነት እንዲገነዘቡ ለማድረግ በትክክል የተዘጋጀ ክብና ሞላላን ማንከባለል
- ክብ በማንኛውም አቅጣጫ እንደሚንከባለል ሞላላ ግን የሚንከባለለው በአንድ አቅጣጫ እንደሆነ እንዲያስተውሉ ማድረግ
- በተግባር አንከባለው ልዩነቱን እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የክብ እና የሞላላ ቅርፅን ልዩነትን መረዳታቸውን መገምገም።

ተግባር ስምንት ፡- ነጠብጣብ በማድመቅ ቅርፆችን መለየት

ዓላማ ፡- ነጠብጣብ በማድመቅ የቅርጹን ስያሜ እና የቀለሙን ዓይነት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጉ'ነ ሶስት፣ ጉ'ነ አራት፣ ክብና ሞላላ ቅርፆችን በነጠብጣብ በአንድ ወረቀት ላይ ሰርቶ መስጠት
- እንዲያደምቁ እና ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- የቅርጹን ስያሜ እና የቀለሙን ዓይነት እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ ጥያቄዎች በመጠየቅ በነጠብጣብ ያደመቁትን ቅርፅ ስያሜ እና የቀለም ዓይነት መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ዘጠኝ ፦ ቅርፆችን መሳል

ዓላማ ፦ ቅር[illegible]ይነት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዳቸው እርሳስ እና ወረቀት መስጠት
- ከተዋወቋቸው ቅርፆች ውስጥ አንድ ቅርጽ እንዲሠሩ መንገር
- የተጠየቁትን ቅርጽ ሰርተው ሲጨርሱ ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- የሳሉት ቅርፅ ምን እንደሆነና ምን አይነት ቀለም እንደቀቡት እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ ቅርፆችን በስዕል በመስራት የቅርጹን ስያሜ እናየቀለም ዓይነት መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ የስእሎችን የውስጠኛ ክፍል በተለያዩ ነገሮች ይሞላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጉ'ነ ሶስት፣ ካሬ፣ ጉ'ነ አራት፣ ክብ፣ የተቆራረጡ ትናንሽ የወረቀት ቁርጥራጮች፣ ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለየዩ ቅርፆች/ሣህን፣ አግዳሚ ወንበር፣ ሳጥን፣ ኳስ ወዘተ.../ የተሳሉበትን ወረቀትበክብ፣ በጉ'ነ ሶስትና በጉ'ነ አራት በማዘጋጀት ማደል



ተግባር አስር ፦ የስእሎችን ውስጠኛ ክፍል በተለያዩ ነገሮች መሙላት

- ትናንሽ የወረቀት ቁርጥራጮቹን መስጠት
- የስዕሉን ውሰጥ ኮላ መቀባት እና በተቆራረጡ ትትናንሽ የወረቀት ቁርጥራጮች ቅርፆቹ እንዴት እንደሚሞሉ ማሣየት እና እንዲሞሉ ማድረግ
- የሠሩትን በማድነቅ ምን ቅርጽ እንደሠሩ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የቁሳቁሶችን የውስጠኛ ክፍል በተለያዩ ነገሮች መሙላትና ቅርፁን መናገራቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

**ተግባር አስራ አንድ ፡- የጐደለውን ክፍል መለየት**

ዓላማ ፡- የ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ምስሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የጐደለ ክፍል ያላቸው ምስሎችን ማሣየት
- የጐደለውን ክፍል መናገር
- የምስሉን ስያሜ የመናገር ጨዋታን በውድድር መልክ ማጫወት

ምዘና ፡- የምስሉን የጐደለ ክፍል በማየት መናገር መቻላቸውን መገምገም።

**ተግባር አስራ ሁለት ፡- የቅርፆችን ሞዴል መስራት**

ዓላማ ፡- ሞዴል በመስራት የተለያዩ ቅርፆችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጭቃ/የተበካ ወረቀት/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ምን ምን ዓይነት ቅርፆች እንዳሉ እንዲናገሩ ማድረግ
- የቅርፆችን ሞዴል ከጭቃ ወይም ከተቦካ ወረቀት በመሥራት ማሣየት እና ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- እነሱም ደስ ያላቸውን ነገር እንዲሰሩ እድሉን መስጠት

- የሰሩት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ሲጨርሱም በወረቀት ላይ ስማቸውን በመፃፍ የሰሩትን ወረቀቱ ላይ በማስቀመጥ እንዲደርቅ ማድረግ

ማስታወሻ ፦ የተለያዩ ሞዴሎችን በተለያየ ክፍለ ጊዜ እንዲሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ የቅርፆችን ሞዴል በመስራት ቅርጾቹን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ ቀለም በመቀባት ቅርፆችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ቀደም ሲል የተዋወቋቸውን በወረቀት ላይ የተሳሉ ቅርፆችን መስጠት
- ቅርፆቹን ከመስመር ሳይወጡ እንዲቀቡ ማድረግ
- የቀቡአቸውን ቅርፆች በስም እንዲለዩና እንዲናገሩ ማበረታታት

ም … ን ጥያቄ በመጠየቅ

ተግባር አስራ አራት ፦ ቅርፆችን ወረቀት አስደግፎ መሳል

ዓላማ ፦ ቅርፆችን ወረቀት አስደግፎ መሳል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ እርሳስ፣ ወረቀት፣ የጂኦሜትሪ ቅርፆች፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦



ተግባር አስራ ሦስት ፦ ቅርፆችን ቀለም መቀባት

- የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በወረቀት ላይ በማስደገፍ ቅርፁን ማንሳት
- ህፃናቱ ባዩት መሠረት ቅርፆችን እንዲሰሩ እና ሲጨርሱም ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- በመጨረሻም የስራ ውጤቶቻቸው ግርጌ ስማቸውን በመጻፍ ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፦ ቅርፆችን ወረቀት አስደግፎ መሳል መለማመዳቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ አምስት ፦ ቁሳቁሶች እና ቅርፆችን መለየት

ዓላማ ፦ በተለያዩ ቁሳቁሶችና ቅርፆች መካከል ያለውን ተመሣሣይነት እና ልዩነት ማውጣት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያየ መጠን ያላቸው ቁሳቁሶች (ኳሶች፣ ጠጠሮች፣ ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ዶቃዎች)፣ ጐነ ሶስት፣ ካሬ፣ ጐነ አራት፣ ክብ፣ ሞላላ፣ ከረጢት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ቁሳቁሶቹን ከረጢት ዉስጥ መክተት
- ጐነ ሶስት፣ ካሬ፣ ጐነ አራት፣ ክብ፣ ሞላላ ቅርጾቹን ለህጻናቱ ማደል
- “ቅርፁን ጠቁም” ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት
    - ሕፃናት በሙሉ ወደ መምህር እንዲመለከቱ ማድረግ
    - ከረጢት ማሣየት እና ከረጢቱ ውስጥ ምን ያለ ይመስላችኋል ብሎ መጠየቅ
    - [illegible] ርፁን ከፍ በማድረግ ቀድሞ የጠራ እንዲጨበጨብለት በማድረግ ማበረታታት

ምዘና ፦ በቁሶች እና በቅርፆች መካከል ያለውን ተመሣሣይነት እና ልዩነት በማመሳሰል መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ ስድስት ፦ ቅርፆችን በቅርጽ ቦርዶች ውስጥ መክተት

ዓላማ ፦ [illegible]

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጐነ ሶስት፣ ካሬ፣ ጐነ አራት፣ ክብ፣ ሞላላ ቅርጾች፣ የቅርፅ ቦርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያየ መጠን ያላቸውን የጂኦሜትሪ ቅርፆችን የያዘ ቦርድ በመጠቀም በትክክለኛ ቦታ ቅርፆችን እንዴት መከተት እንደሚቻል ማሳየት
- ለህፃናቱም የተለያየ ቅርፅና መጠን ያላቸውን የጂኦሜትሪ ቅርፆች በመስጠት በየተራ እየተነሱ በትክክለኛ ቦታ ላይ እንዲከቱ በማድረግ ማጫወት
- ቅርፆቹን በትክክለኛ ቦታ ላይ መክተትና አለመክተታቸውን ጓደኞቻቸው እንዲያረጋግጡ ማድረግ

ምዘና ፦ ቅርፆችን በትክክለኛ ቦታቸው ላይ መክተት መቻላቸውን በማየት መገምገም።

ዓላማ ፦ ቁሳቁሶችን በቅርጽ፣ በመጠን እና በቀለም በመለየት ይመድባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያየ ቀለም፣ መጠን እና ቅርጽ ያላቸው ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያየ ቀለም፣ መጠንና ቅርጽ ያላቸው ቁሶችን በማቅረብ በቅርጽ፣ በቀለም በመጠን በመመደብ ሰርቶ ማሣየት
- ለህፃናቱም በየጠረጴዛቸው በመስጠት በመጠናቸው በቅርፃቸውና በቀለማቸው እንዲመድቡ ማበረታታት
- ሲጨርሱም እንዴት አንድ ላይ ሊመድቧቸው እንደቻሉ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት

ምዘና ፦ ቁሳቁሶችን በቅርጽ፣ በመጠን እና በቀለም መለየትና መመደብ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ ሰባት ፦ ቁሳቁሶችን መመደብ

ዓላማ ... ለም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የቅርፅ ፓዝሎች



ተግባር አስራ ስምንት ፦ ፓዝሎችን መገጣጠም

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ በታ ላይ በመሆን አራት በታ የተቆራረጡ እንጨቶችን በመገጣጠም በመስራት ምስሉን ማሳየትና ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- ለህፃናቱ ሶስትና አራት በታ የተቆራረጡ እንጨቶችን በመስጠት ገጣጥመው ያገኙትን ቅርፅ ለጓደኞቻቸው በማሳየት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር አስራ ዘጠኝ ፡- ቅርፆችን በዓይነት መመደብ

ዓላማ ፡- ቅርፆችን በቀለም፣ በቅርጽ፣ በመጠን ይመድባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- 64 ቱ ሎጂካል ብሎኮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- 64 ቱን ሎጂካል ብሎኮች በታትኖ ለህፃናቱ መስጠት
- በቀለም፣ በቅርጽ፣ በመጠን እንዲመደቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዴት እንደዛ ሊመድቡ እንደቻሉ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ቅርጾችን በቀለም፣ በቅርጽ፣ በመጠን መመደብ መቻላቸውን በማየት መገምገም።

ዓላማ ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን በአይነት በመለየት ስብስብ መፍጠርን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተቆጣሪ ነገሮች (ኳሶች፣ ጠጠሮች፣ ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ዶቃዎች ወዘተ...)፣ ክር ወይም ሲባጎ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮችን እና የስብስብ መሥሪያ ክር ወይም ሲባጎ ማደል



ተግባር ሀያ ፡- ስብስብ መፍጠር

- በክር አጥር እንዴት እንደሚሠራ ማሣየት
- በአጥራቸው ውስጥ ተቆጣሪ ነገሮችን ቀስ በቀስ በመከተት በቅርጽ፣ በመጠን እና በቀለም ስብስብ እንዲመሠርቱ ማለማመድ

ምዘና ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን በአይነት በመለየት ስብስብ መመስረት መለማመድ መቻላቸውን መከታተል፡፡

ዓላማ ፡- በመለካት የነገሮችን መጠን ይገልፃሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፡- የአሸዋ ሳጥን፣ የውሃ መያዣ ኮዳዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቀማ ፡-

- የአሸዋ መስፈርን እና የውሃ ከአንድ እቃ ወደ ሌላ እቃ ማገላበጥ ጨዋታን የተለያዩ መጠን ባላቸው ነገሮች እንዲጫወቱ መምራት
- ሲጫወቱ እየተዟዟሩ በመመልከት በመለካት መጠንን በንግግር እንዲገልፁ ማነቃቃት

ምዘና ፡- በጨዋታው በመለካት የነገሮችን መጠን መግለጻቸውን በመከታተል መገምገም፡፡

ተግባር ሀያ ሁለት ፡- ቀላል እና ከባድ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡-

ተግባር ሀያ አንድ ፡- መጠንን መለካት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፡- የተለያየ መጠን ያላቸው ቁሳቁሶች (ጠጠሮች፣ ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች ወዘተ...)፣ የፍሊት ቆርቆሮ ክዳን ፣ የጫማ ቀለም ቆርቆሮ

የአተገባበር ዘዴ ጥቀማ ፡-

- በፍሊት ቆርቆሮ ክዳን ወይም በሌላ ተመሣሣይ ነገር /የጫማ ቀለም ቆርቆሮ ሊሆን ይችላል/ ሚዛን ማዘጋጀት
- ቀላል እና ከባድ ነገሮችን እየመዘኑ ከባድ የሆነው እንዴት ሚዛኑን ዝቅ እንደሚያደረግ እንዲገነዘቡ ማድረግ
- እነሱም ለአይን ሲታዩ ትልቅ ወይም ትንሽ የሚመስሉ ነገሮችን በመመዘን ቀላልና ከባድ ነገሮችን እንዲለዩ ማበረታታት

- ሲጨርሱም ምን እንደተጫወቱና እንዴት እንደተጫወቱ በመጠየቅ በመመዘን የእቃዎችን ክብደትና ቅለት ማወቅ እንደሚቻል እንዲገነዘቡ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ሚዛንን በጨዋታ ሠዓት እንዲጠቀሙበት ማበረታታት ተገቢ ነዉ። |

ምዘና ፡- ቀላል እና ከባድ ነገሮችን በመመዘን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

### ተግባር ሀያ ሦስት ፡- ርቀትን በእርምጃ መለካት

ዓላማ ፡- ርቀትን በእርምጃ መለካት ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በመምህር መቀመጫ እና በሕፃናት መቀመጫ መካከል ያለውን ርቀት በምን መለካት የምንችል ይመስላችኋል ብሎ መጠየቅ
- በእርምጃ እንዴት እንደሚለካ ማሣየት
- ሕፃናት በየተራ በእርምጃ እንዲለኩ ማድረግ
- ሁለት ሕፃናት በተወሰነ ርቀት እንዲቆሙ ማድረግ
- በመካከላቸው ያለውን ርቀት በእርምጃ እንዲለኩ ማድረግ

ምዘና ፡- በእርምጃ ርቀትን መለካት መለማመዳቸውን መገምገም።

### ተግባር ሀያ አራት ፡- ቁመት መለካት

ዓላማ ፡- ቁመት መለካት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ወፍራም ወረቀት፣ስእሎች /ፀሐይ፣ ኮከብ፣ ቅጠል፣ ጨረቃ ወዘተ.../

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በክፍል ውስጥ በግድግዳ ላይ 1.20 ሳንቲ ሜትር ያህል ቀጠን ያለ ወፍራም ወረቀት ማዘጋጀት
- በወረቀቱ ላይ ብሩህ ቀለም ያላቸውና ሕፃናት የሚያውቋቸውን ነገሮች በየ 5 ሳ.ሜ ልዩነት መለጠፍ

ለምሣሌ፡- ፀሐይ፣ ኮከብ፣ ቅጠል፣ ጨረቃ ወዘተ…

- ሕፃናት ወረቀቱን በመጠቀም ቁመታቸውን እንዲለኩ ማድረግ
- በየጊዜው በመለካት የትኛው ምልክት ላይ እንደደረሱ ማየት
- ለውጣቸውን እንዲያስተውሉ እና የመለካት ዝንባሌአቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ቁመታቸውን እንዲለኩ በማድረግ የመለካት ዝንባሌአቸውን ማዳበር መጀመራቸውን መከታተል።

ዓላማ ፡- ነገሮችን በቁመት ማወዳደር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክላስር፣ ማስመሪያ፣ እርሳስ፣ወረቀት፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ቁሳቁሶች

የአተገ

**ተግባር ሀያ አምስት ፡- በቁመት ማወዳደር**

- ክላሰር ከ 2-3 ሴንቲ ሜትር ስፋት 30 ሴንቲ ሜትር ቁመት በመቁረጥ የመለኪያ ጥብጣብ ማዘጋጀት
- በጥብጣብ በተሠራ ማስመሪያ የተለያዩ ነገሮችን መለካት እንዲለማመዱ ማድረግ
- ከቁሳቁሶች መካከል በጣም ትልቁን፣ ትንሹን በማውጣት መጠየቅ እና በአበላላጭ ቃላት መግለጽ እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ነገሮችን በቁመት ማወዳደር መለማመዳቸውን መከታተል።

**ተግባር ሀያ ስድስት ፡- አንድ ለአንድ ማዛመድ**

ዓላማ ፡- አንድ ለአንድ በማዛመድ የማካፈልን ጽንሰ ሃሳብ ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ ጠጠር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- 1 0 በወረቀት የተጠቀለሉ የጨዋታ ከረሜላዎች ማቅረብ
- አሥር ሕፃናት በጓደኞቻቸው ፊት እንዲቆሙ ማድረግ

- ለእያንዳንዱ አንዳንድ እንዲያድሉ በማድረግ አንድ ለአንድ ማገናኘትን ማለማመድ

ምዘና ፡- አንድ ለአንድ በማዛመድ የማካፈል ጽንሰ ሃሳብን መተዋወቅ መጀመራቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. ነገሮችን በባህርያቸው መሠረት ማወዳደር | 2.1. በነገሮች መካከል ያለ ዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት ይችላሉ። |

ዓላማ

ተግባር አንድ ፡- ሸካራና ለስላሳን ማወዳደር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዳሰስ ሰሌዳዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የመዳሰስ ሰሌዳን በመጠቀም እንዴት መዳሰስ እንደሚቻል ማሣየት
- እንዲዳስሱ ዕድሉን በመስጠት የቱነው ሸካራ**?** የቱ ነው ለስላሣ**?** ይህ ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ
- የ **3** ደረጃ ትምህርት ዘዴን በመጠቀም ሸካራ እናለስላሳን በማወዳደር እንዲለዩ ማለማመድ

ምዘና ፡- በመዳሰስ ሸካራ እናለስላሳን በማወዳደር መለየት መለማመዳቸውን መከታተል።

ዓላማ ፡- ትንሽ እና ትልቅ ነገሮችን በማወዳደር ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ኳስ፣ ሽመሎች /የተቆራረጡ እንጨቶች/፣ ጠጠሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ትልቅና ትንሽ የሆኑ የተለያዩ ነገሮችን ከሕፃናት ፊት በጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ



ተግባር ሁለት ፡- ትንሽ እና ትልቅ ነገሮችን ማወዳደር

- ትልቅ እና ትንሽ በማወዳደር ማሣየት
- ተመሣሣይ መጠን ያላቸውን እያወጡ እንዲያሳዩ ማድረግ
- ትንሽና ትልቅ የሆኑትን አንድ ዓይነት ነገሮች አውጥተው ጐንለጐን በማስቀመጥ ይህ ትንሽ ነው፣ ይህ ደግሞ ትልቅ ነው። በማለት በማወዳደር እንዲናገሩ መርዳት

ለምሳሌ፡-



ማስታወሻ ፡- በዚሁ ዓይነት በጣም ረጅም፣ በጣም አጭር፣ በጣም ቀላል፣ በጣም ከባድ በማለት እንዲያወዳድሩ ማድረግ ይቻላል።


ምዘና ፡- ትንሽ እና ትልቅ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የተለያዩ ነገሮችን ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ይደረድራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርፆች፣ ሽምበቆ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሶስት የተለያየ መጠን ያላቸውን አንድ ዓይነት የጂኦሜትሪ ቅርፆች በወረቀት ቆርጦ ማዘጋጀት(ውፍረቱ ተመሳሳይ የሆነ ሽምበቆን የተለያየ ቀለም በመቀባት ትንሽ፣ ትልቅ በጣም ትልቅ በማድረግ መቆራረጥ) እና ለሕፃናት ማደል
- ከትንሽ ወደ ትልቅ ከትልቅ ወደ በጣም ትልቅ እንዴት እንደሚቀመጥ ማሣየት
- ሕፃናት በፊታቸው ያሉትን ቅርፆች ባዩት መሠረት በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- ትንሹን፣ ትልቁን በጣም ትልቁን ለይተው እንዲያመለክቱ በየተራ መጠየቅ
- ከትንሽ ወደትልቅ እየደረደሩ እንዲጫወቱ ማድረግ





ተግባር ሦስት ፡- ከትንሽ ወደ ትልቅ መደርደር

ምዘና ፡- የተለያዩ ነገሮችን ከትንሽ ወደ ትልቅ መደርደር መቻላቸውን መከታተል።

ዓላማ ፡- ከባድ እና ቀላል ነገሮችን ያወዳድራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከረጢት፣ ጥጥ፣ አሸዋ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አሸዋ የተሞሉ ትናንሽ ከረጢቶችን እና በጥጥ የተሞሉ ተመሣሣይ መጠን ያላቸው ከረጢቶችን ማዘጋጀት
- ከረጢቶቹን በእጃቸው በማንሳት እና መጠናቸውን በመለካት ቀላል እና ከባድን እንዲያወዳድሩ ማድረግ
- ውጤቱን እንዲናገሩ ማበረታታት
- እንዴት አሸዋው ከባድ ነው ጥጡ ቀላል ነው ሊሉ እንደቻሉ ጥያቄ በመጠየቅ ማወያየት

ምዘ[illegible]

ተግባር አራት ፡- ከባድ እና ቀላል ነገሮችን ማወዳደር

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽና ነገሮችን በባህርያቸው መሠረት ማወዳደር | 3.1. ቁሳቁሶችን እና ቁጥሮችን 1-20 መቁጠር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- በዓይነት መለየት እና መቁጠር

ዓላማ ፡- [illegible]

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የባህር ዛፍ እና የጥድ ፍሬዎች፣ ዶቃዎች፣ ጠጠሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የባህር ዛፍ እና የጥድ ፍሬዎች፣ ዶቃዎች፣ ጠጠሮች ወዘተ… ማደል
- ከተሰጣቸው ውስጥ የጥድ እና የባህር ዛፍ ፍሬዎችን ለይተው እንዲያወጡ ማድረግ
- በዓይነት የተለዩትን ተቆጣሪዎች ወደ ጐን በመደርደር በእርጋታ አብሮ መቁጠር

ምዘና ፡- የተለያዩ ነገሮችን በዓይነታቸዉ ለይተው መቁጠር መቻላቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን ይቆጥራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተቆጣሪ ነገሮች (የባህር ዛፍ እና የጥድ ፍሬዎች፣ ዶቃዎች፣ ጠጠሮች ፣ ቆርኪዎች ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ተቆጣሪ ነገሮችን በመስጠት ወደ ጐን፣ ወደላይ፣ ወደታች ወዘተ… በተለያየ አቅጣጫ በማስደርደር መቁጠርን ማለማመድ
- የቆጠሩትን መጠን እንዲናገሩ ማድረግ
- ትክክል መሆንና አለመሆናቸውን ጓደኞቻቸው እንዲያረጋግጡ ማድረግ

ምዘና ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን በዓይነታቸዉ በመደርደር መቁጠር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

## ተግባር ሁለት ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን መቁጠር

ዓላማ ፡- የተለያዩ ምስሎችን ይቆጥራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወረቀት የተዘጋጁ የተለያዩ ምስሎች (የአእዋፍ፣ የብርቱካኖች ወዘተ…)



## ተግባር ሶስት ፡- ምስሎችን መቁጠር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ሕፃን ከ 1 ዐ ያልበለጠ የተለያዩ ምስሎች መስጠት
- ምስሎቹን በዓይነታቸዉ እንዲለዩ ማድረግ
- ጉን ለጉን በመደርደር እንዲቆጥሩ ማድረግ

ምዘና ፦ የተለያዩ ምስሎችን በዓይነታቸዉ መለየት እና መቁጠር መቻላቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፦ ጣታቸዉን ተጠቅመዉ ይቆጥራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ጣቶቻቸውን በመጠቀም ከ 1-10 እንዲቆጥሩ ‹‹ትንሽ ትንሽ ወፎችን›› አብሮ መዘመር
- “አውራ ጣት” የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ጣቶቻቸውን በማጠፍ በቅደም ተከተል እንዲቆጥሩ ማድረግ
- ጣቶቻቸውን ሲቆጥሩ በአንዱ እጃቸው የቆጠሩአቸውን ጣቶች ወደ አንድ አቅጣጫ በማጠጋጋት እንዲቆጥሩ ማድረግ

ምዘና ፦ ጣታቸዉን ተጠቅመዉ መቁጠር መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አራት ፦ በጣት መቁጠር

ዓላማ ፦ ብዙ እና ጥቂትን በመቁጠር ያወዳድራሉ።



ተግባር አምስት ፦ ብዙ እና ጥቂት ማወዳደር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሲባጐ ወይም ክር፣ ለስብስብ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሲባጐ ወይም ክር ለሕፃናት በማደል አጥር እንዴት እንደሚሠራ ማሣየት
- ሁለት አጥሮች እንዲሠሩ ማድረግ
- ተቆጣሪዎችን እየቆጠሩ ቀስ በቀስ ወደ አጥሩ ውስጥ እንዲከቱ ማድረግ
- በአንዱ አጥር ጥቂት ተቀጣሪዎች በሌላው አጥር ብዙ ተቀጣሪዎች እንዲከቱ በማድረግ “ብዙ” እና “ጥቂት” በማለት እንዲያወዳድሩ ማድረግ
- በሠሩአቸው ሁለት አጥሮች ውስጥ ያሉትን ተቆጣሪዎች በመጀመሪያ ጥቂቱን ከስብስቡ አጥር ውስጥ እየቆጠሩ በማውጣት ወደጐን እንዲደረድሩ ማድረግ
- ቀጥሎም ብዙውን ከስብስቡ አጥር እያወጡ ከመጀመሪያዎቹ ስር ወደጐን መደርደር
- ተቀጣሪዎቹን አንድ ለአንድ እንዲያዛምዱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- የተቆጣሪዎቹ ብዛት ከ10 መብለጥ የለበትም። |

ምዘና ፡- ብዙ እና ጥቂት ነገሮችን በመቁጠር ማወዳደር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የቁጥር አሃዞችን በስምና በቅርፅ ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቁጥር ሰሌዳዎች፣ ከክላሰር የተሰሩ ትናንሽ የፊደል ካርዶች

## ተግባር ስድስት ፡- የቁጥር አሃዞችን መተዋወቅ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የጎላ ብሎ የተሰራ የቁጥር ሰሌዳን በማሳየት ምን እንደሆነ በመጠየቅ ማነቃቃት
- የህፃናቱን መልስ ካዳመጡ በኋላ ስንት ቁጥር እንደሆነ መናገር
- ደግመው ቁጥሩን ከመምህር በኋላ እንዲጠሩ ማድረግ

- ማነኝ ማነኝ መዝሙርንና ልትወጣ ነው ልትወጣ ነው ጨዋታን በማጫወት የቁጥር አሃዙን በድምፅና በቅርፅ እንዲለዩ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፦ ከ 1-10 ያሉ የቁጥር አሃዞችን በአንድ ጊዜ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ ከፋፍሎ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፦ የቁጥር አሃዞችን በድምፅና በቅርፅ መለየትና ስያሜውን መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

| |
|---|
| ተግባር ሰባት ፦ የቁጥር አሃዞችን ቅርጽ መለየት |

ዓላማ ፦ የቁጥር አሃዞችን ቅርጽ ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በብርጭቆ ወረቀት ወይም በአሸዋ ግርፍ የተሰሩ ቁጥር አሃዞች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- በብርጭቆ ወረቀት ወይም በአሸዋ ግርፍ የተሰሩ ቁጥር አሃዞች በየጠረጴዛቸው ላይ ማደል
- ዓይናቸውን ጨፍነው በመዳሰስ የቁጥሩን ቅርጽ ለመረዳት እንዲችሉ መርዳት
- የዳሰሱትን ቁጥር በአየር ላይ በመፃፍ እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፦ የቁጥር አሃዞችን ቅርጽ መለየት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፦ የቁጥር አሃዞችን ቀለም ይቀባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ባለቀለም እርሳስ/ከለር/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦



| |
|---|
| ተግባር ስምንት ፦ የቁጥር አሃዞችን ቀለም መቀባት |

- በድርብ የተፃፉ የቁጥር አሃዞችን መስጠት
- ከመስመር ሳይወጡ ከለር መቀባትን እንዲለማመዱ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- በአንድ ጊዜ የሚቀቧቸው ቁጥሮች መብዛት የለባቸውም፡፡

ምዘና ፡- የቁጥር አሃዞችን ቅርጽ መለየት መለማመዳቸዉን መገምገም፡፡

ዓላማ ፡- በነጡብጣብ የተሰሩ የቁጥር አሃዞችን ነጡብጣቡን በመገጣጠም ያደምቃሉ፡፡

የመርጃ

ተግባር ዘጠኝ ፡- የቁጥር አሃዞችን ማድመቅ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በነጡብጣብ የተፃፉ የቁጥር አሃዞችን በየግላቸው መስጠት
- እንዴት ማድመቅ እንደሚቻል በማሣየት በእርሳስ እንዲያደምቁ ማድረግ
- ሲጨርሱም የትኛውን የቁጥር አሃዝ እንዳደመቁ ለጓደኞቻቸው በማሳየት እንዲናገሩ ማድረግ
- ካደመቁት የቁጥር አሃዝ ግርጌ ስማቸውን በመፃፍ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፡- የቁጥር አሃዞችን ማድመቅና ያደመቁትን ቁጥር በድምፅና በቅርፅ መለየታቸውን በመጠየቅ መገምገም፡፡

ዓላማ ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን መቁጠር እና ከቁጥር አህዝ ጋር ማዛመድ ይጀምራሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቁጥር ካርዶች፣ ተቆጣሪ ነገሮች (ጠጠሮች፣ ወረቀት፣ የሕፃናት ስዕሎች ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- 1 ዐ ስዕሎች በትንንሹ ስሎ መቁረጥ
- ስዕሎቹን በተለያየ ቁጥር መስጠት



ተግባር አስር ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን መቁጠር እና ከቁጥር አህዝ ጋር ማዛመድ

- ቆጥረዉ ስንት እንደሆኑ እንዲናገሩ መጠየቅ
- ጠጠሮችን ከረሜላ አስመስሎ መጠቅለል
- የተጠቀለሉትን ከረሜላዎች ለሕፃናት በተለያየ መጠንማደል
- የቁጥር አሃዝን ከማሣየት በፊት ማስቆጠር
- ሲቆጥሩ የደረሱበትን የመጨረሻ ቁጥር እንዲጠሩ ማድረግ
- የቁጥሩን አሃዝ ካርድ በማሣየት ማጠናከር

ምዘና ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን መቁጠር እና ከቁጥር አሀዝ ጋር ማዛመድ መጀመራቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ አንድ ፡- የቁጥር አሃዞችን ቅርጽ መለየትና ማንቡብ

ዓላማ ፡- የቁጥር አሃዞችን ቅርጽ መለየት እና ማንቡብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተቆጣሪዎች ከላይ ቁጥር ከታች የተፃፈበት ሰሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሰሌዳዉን በመጠቀም ተቆጣሪዎችን ቆጥረው በመጨረሻ ለደረሱበት ቁጥር አሃዝ መስጠት እንዲለማመዱ ማድረግ

ለምሣሌ፡- አንድን ጠቋሚ ጣትን በማሣየት ወዘተ...

ምዘና ፡- የቁጥር አሃዞችን ቅርጽ መለየት እና ማንቡብ መለማመዳቸዉን ጥያቄ በመጠየቅ መከታተል።

ዓላማ ፡- የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪዎች ጋር ያዛምዳሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቀረጹ የቁጥር አሃዞች፣ የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች (ጠጠሮች፣ ቆርኪዎች ወዘተ...)



ተግባር አስራ ሁለት ፡- የቁጥር አሃዞቹን ከመጠን ጋር ማዛመድ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ በየጠረጴዛቸው ተቆጣሪ ነገሮችን መስጠት
- የቁጥር አሃዝ በማሣየት ባዩት የቁጥር አሃዝ ልክ ተቆጣሪዎችን ቆጥረው እንዲያወጡ ማድረግ
- ልክ መሆንና አለመሆናቸውን ትኩረት ሰጥቶ መከታተል

ምዘና ፡- የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪዎች ጋር ማዛመድ መቻላቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪው መጠን ልክ ያደራጃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቀረጹ የቁጥር አሃዞች፣የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች (ጠጠሮች፣ ቆርኪዎች ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ በየጠረጴዛቸው ተቆጣሪ ነገሮች በክላሰር ላይ የተጻፉ የቁጥር ካርዶችን መስጠት
- የቁጥር ካርዱን ከፊት ለፊታቸው በማስቀመጥ ከስሩ ተቆጣሪዎቹን በቁጥር መጠናቸው እንዲያደራጁ ማድረግ
- … ት

ተግባር አስራ ሶስት ፡- የቁጥር አሃዞቹን በተቆጣሪ መጠን ማደራጀት

… ቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አስራ አራት ፡- ቁጥርን ከመጠን ጋር የማዛመድ ጨዋታን መጫወት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቀረጹ የቁጥር አሃዞች፣የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች (ጠጠሮች፣ ቆርኪዎች ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከክፍል ውጪ ባለው ባዶ ሜዳ ላይ በክብ እንዲቆሙ ማድረግና የጨዋታውን ሂደትና ህግ መግለጽ
- መምህር ሲያጨበጭቡ ቀስ ብለው ሳይገፋፉ እንዲሮጡ ማድረግ
- መምህር ጭብጨባውን አቁመው ቁጥር ሲጠሩ በተጠራው ልክ መጠን እንዲያያዙ በማድረግ ማጫወት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ይህንን ጨዋታ እየለመዱት ሲሄዱ የቁጥር አሃዝን በማሳየት ማጫወት ይቻላል። |

ምዘና ፡- ቁጥሮችን ከመጠን ጋር በማዛመድ መጫወት መቻላቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- ጭብጨባ በመቁጠር ከቁጥር አሃዞች ጋር ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቁጥር ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- <<ጭብጨባውን ቁጠር>> ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት፡-
- ፀጥ ብለው ጭብጨባውን እንዲያዳምጡ ማድረግ
- ጭብጨባውን ቆጥረው በፊታቸው ካለው የቁጥር ካርዶች አንስተው እንዲያሣዩ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ይህንን በሙዚቃ መሳሪያዎች ድምጽ ማድረግ ይቻላል። |

ምዘና ፡- ጭብጨባ በመቁጠር ከቁጥር አሃዞች ጋር ማዛመድ መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ አምስት ፡- ጭብጨባን ከቁጠር አሃዞች ጋር ማዛመድ



ተግባር አስራ ስድስት ፡- የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪዎች ጋር ማዛመድ

ዓላማ ፡- የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪዎች ጋር ማዛመድ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ስዕሎቹን ከቁጥር አሃዝ መጠን ጋር በማዛመድማሣየት
- የተለያዩ ስዕሎችንና የቁጥር አሃዝ ካርዶችን መስጠት
- እነሱም ባዩት መሰረት እንዲያዛምዱ ማድረግ

ለምሳሌ፡- አንድ አበባ ከአንድ ቁጥር አሃዝ ጋር ሁለት ኳስ ከሁለት ወዘተ…

ምዘና ፡- የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪዎች ጋር ማዛመድ መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ ስምንት ፡- የአሃዝ ዶሚኖ መጫወት

ዓላማ ፡- የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች በመጠቀም በአሃዝ ልክ ይደረድራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በትልቅ የተቀረፁ የቁጥር አሃዞች፣ ጠጠሮች፣ ፍሬዎች፣ ባቄላ፣ ቦለቄ፣ ወዘተ**…**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የቁጥር አሃዞቹን በየተራ በቦርድ ላይ ማስቀመጥ
- በአሃዙ ልክ የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች በመጠቀም እንዲገነቡ ማሣየት እና ማሠራት

ምዘና ፡- የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች በመጠቀም በአሃዝ ልክ መደርደር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።



ተግባር አስራ ሰባት ፡- በአሃዝ ልክ የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች መደርደር

ዓላማ ፡- የአሃዝ ዶሚኖ በመጫወት መቁጠር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ዶሚኖ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የቁጥር ዶሚኖ ማዘጋጀት
- የአጨዋወት ሂደትና ህጉን መግለፅ
- ሁለት ሁለት ሆነው እንዲጫወቱ ማድረግ
- ሲጫወቱ በመዟዟር ማየትና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ

ምዘና ፡- የአሃዝ ዶሚኖ በመጫወት መቁጠር መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4.በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሣሪያዎች መጠቀም | 4.1. በቦታና በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት መጠቆም ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የመጠንን ልዩነትን መረዳት

ዓላማ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሸዋ፣ ጎድጓዳ ሰሃን፣ የተለያየ መጠን ያላቸው መስፈሪያዎች ወዘተ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በክፍል ውስጥ በጎድጓዳ ሰሃን አሸዋ ማቅረብ
- ካልሆነም በግቢ ውስጥ የሚገኝ የአሸዋ ገንዳን መጠቀም
- ከትንሽ ዕቃ ወደ ትልቅ ዕቃ ከትልቅ እቃ ወደ ትንሽ ዕቃ በማገላበጥ እንዲጫወቱ በማድረግ ነገሮችን በሚመጥናቸው ዕቃ መክተትን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- አሸዋ በመስፈር ጨዋታ ሲጫወቱ በመከታተል በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት መረዳታቸዉን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- በመጠንን መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት

ዓላማ ፡- በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሃ መያዣ እቃ፣የተለያየ መጠን ያላቸው ኩባያዎች ወይም ጠርሙሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በግማሽ ሊትር የውሃ ዕቃ የተሞላ ውሃን ወደ አንድ ሊትር መያዣ ውስጥ መገልበጥ
- የዕቃውን ልዩነት እንዲያስተዉሉ ማድረግ
- ውሃ ከትልቅ ኩባያ ወደ ትንሽ ኩባያ ከትንሽ ኩባያ ወደ ትልቅ ኩባያ በማገላበጥ እንዲጫወቱ ማድረግ
- የውሃውን መትረፍ እና የተገለበጠበትን ኩባያ አለመሙላት እንዲያስተውሉ በማድረግ ማጫወት

ማስታወሻ ፡- በውሃ ምትክ ጥራጥሬ መጠቀም ይቻላል።

ምዘና ፡- በመጠንን መካከል ያለውን ልዩነት መረዳታቸዉን ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ መጠን ያላቸው ቁሳቁሶች (ኩባያዎች፣ጠርሙሶች፣ ሰሃኖች፣ ማንኪያዎች ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያየ መጠን ያላቸው ቁሳቁሶችን ጎን ለጎን ማስቀመጥ
- ትንሽ እና ትልቅ መሆናቸውን በማወዳደር እንዲናገሩ ማበረታታት



ተግባር ሶስት ፡- በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት መናገር

ምዘና ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠቀም በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

**ተግባር አራት ፡- የቦታን እና የመጠን ልዩነትን መረዳት**

ግብ ፡- የቦታ እና የመጠን ልዩነቶችን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ፐዝል የመገጣጠም ጨዋታን እንዲጫወቱ አራትና አምስት ቦታ የተቆራረጡ ቁርጥራጭ እንጨቶችንና ሰሌዳውን ማዘጋጀት
- መጀመሪያ ላይ የሚገጠመውን ቁራጭ እንጨት ቅርፁን አስተውለው ማየትና የት ቦታ ላይ መገጠም እንደሚችል አስቀድመው እንዲያስቡ ማነቃቃት
- በቡድን የተለያዩ ፐዝሎችን በመስጠትበየተራ እየገጣጠሙ እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- ፐዝል  በመጠቀም የቦታ እና የመጠን ልዩነቶችን መረዳታቸዉን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 5. የጊዜ ጽንሰ ሐሳብን መረዳት እና መገለጫዎቹን መጠቀም | 5.1. የሳምንቱን ቀናት፣ ወራትንና የበዓል /ልዩ/ ቀናትን መናገር ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ  ፡- ቀን እና ማታ የሚታዩ ለውጦችን መናገር**

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፀሀይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብትን የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ  ፡-

- "መሸ ነጋ" ጨዋታን በማጫወት የመምሸት እና የመንጋት ልዩነት ግንዛቤያቸውን ማጠናከር
- በቀን ፀሐይ፣ በምሽት ጨረቃ እና ከዋክብት እንደሚገኙ በእንቆቅልሽ መልክ ማጫወት ለምሣሌ ፡- "በሰማይ ላይ እንኖራለን ጨለማን ለማጥፋት እኔና ልጆቼ ብርሃንን እንሰጣለን እኛ ማነን**?**"ወዘተ
- በምሽት /በጨለማ/ አንድ ሕፃን ተኝቶ የሚያሣይ ስዕል ማቅረብ
- ስዕሉን እንዲመለከቱ ማድረግና በስዕሉ ላይ ስለሚያዩት እንዲናገሩ ማድረግ
- "ሕፃኑ የተኛው ምን ጊዜ ይመስላችኋል**?**" በማለት መጠየቅ እና እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ቀን እና ማታ የሚታዩ ለውጦችን መናገር መቻላቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- በቀን እና በማታ የሚደረጉ ተግባራትን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፀሀይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብትን የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- "መቼ ምን አደረግሁ**?**" ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት፡-
  - በሕፃናት ፊት መቆም እና ፊት የመታጠብን እንቅስቃሴ በማሣየት <<መቼ ምን አደረግሁ?>> ብሎ መጠየቅ
  - ሕፃናት ድርጊቱን በማየት <<ጠዋት ፊትሽን/ፊትህን ታጠብሽ/ታጠብክ።>> እንዲሉ መምራት

ተግባር ሁለት ፡- ቀን እና ማታ የሚደረጉ ተግባራትን መለየት

- በዚህ ዓይነት ገልጾ የሆኑ ቀላል ድርጊቶችን በእንቅስቃሴ በማሳየት መቼ፣ ምን? ለሚለው ጥያቄ መልስ እንዲመልሱ በማበረታታት ማጫወት
- "ጠዋት ተነስቼ" የሚለውን መዝሙር በማዘመር ስለምን እንደዘመሩ በመጠየቅ ማወያየት

ጠዋት ተነስቼ

ጠዋት ተነስቼ

ቁርሴንም በልቼ

ልሂድ ት/ቤት ቦርሳዬን አንግቼ

ምዘና ፡- በቀን እና በማታ የሚያከናወኑ ተግባራትን መለየታቸዉን ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- የሳምንቱን ቀናት በስም ይለያሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/፣የቀን መቁጠሪያ/ካላንደር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- "የሳምንቱ ቀናት" መዝሙርን ማዘመር

ተግባር ሦስት ፡- የሳምንቱን ቀናት መተዋወቅ

- የዕረፍትእና የትምህርት ቀናት የትኞቹ እንደሆኑ መጠየቅና ማስረዳት
- በዕረፍት ቀናት የት እንደሚሆኑና ምን እንደሚሠሩ በመጠየቅ ማስረዳት እና ማወያየት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- በየዕለቱ ጠዋት ክፍል ሲገቡ የቀኑን ካላንደር የማስተካከል ልምድ እንዲኖራቸው በማድረግ ማለማመድ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- የሳምንት ቀናት በስም መለየታቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ክረምትና በጋ ወቅቶችን መተዋወቅ

ዓላማ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ የአየር ንብረትን የሚያሳይ ስዕል፣ የቀን መቁጠሪያ/ካላንደር፣ በአፀደ ሕፃናት ዉስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ስዕል /ፎቶግራፍ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአፀደ ሕፃናት ዉስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በስዕል /ከተቻለ በፎቶግራፍ/ በማቅረብ ማሣየት
- ተግባራቱ መቼ መቼ እንደሚከናወኑ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ክረምትንና በጋን በተረት መልክ እንዲሁም በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ያለውን ለውጥ በስዕል ማሣየት

ለምሣሌ ፡- በክረምት በጣም ይዘንባል፣ ይበርዳል፣ ሰዎች አለባበሳቸው ይቀየራል ወዘተ…

በበጋ ፀሐይ ኃይለኛ ነው፣ ይሞቃል፣ ሰዎች ቀላል ልብስ ይለብሳሉ፣ ወዘተ…

ምዘና ፡- በክረምትና በበጋ ወቅት የሚከሰቱ ለውጦችን መለየታቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- ጊዜን ገላጭ ቃላቶችን በመጠቀም ለጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባለ ቀለም እርሳስ፣ የተረት መጽሀፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጊዜን ገላጭ ቃላትን የያዘ ተረት ማውራት
- ስለ ተረቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ከጊዜ መገለጫዎች ጋር የተገናኙ ቃላትን በአግባቡ ተጠቅመው እንዲመልሱ ማበረታታት
- የሰዓት ስዕልን በማደል ቀለም ማስቀባት እና ስለ ሰዓት ማወያየት

ምዘና ፡- ጊዜን ገላጭ ቃላቶችን በመጠቀም ለጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- የፍጥነት እና የዝግታን ልዩነት ከጊዜ አንጻር ይለያሉ።

ተግባር አምስት ፡- ጊዜን ገላጭ ቃላቶችን በመጠቀም ለጥያቄዎች ምላሽ መስጠት



ተግባር ስድስት ፡- ፍጥነት እና ዝግታን መለየት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የግንባታ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የግንባታ ቁሳቁሶችን መስጠት
- ባቡር እንስራ በማለት ባቡር እንዴት እንደሚሠራ ማሣየት
- ከዚያም ሕፃናቱ እንዲሠሩ ማድረግ
- “ባቡራችን እናስኪደው፣ ባቡር ሲነሳ ቀስ ብሎ ነው” በማለት እንደባቡር የተሠራውን እንጨት ቀስ እያሉ ማስኬድ
- ቀስ በቀስ ፍጥነት በመጨመር ባቡሩን ማስኬድና ቀስ ማለትን መፍጠንን የመለየት ግንዛቤአቸውን ለማዳበር በጨዋታ መልክ ማለማመድ
- እጃቸዉን እንደመኪና መሪ በመጠቀም በዝግታና በፍጥነት እንዲያሽከረከሩ በማድረግ ዝግታንና ፍጥነትን በተግባር እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፦ ፍጥነትን እና ዝግታን መለየትና በእንቅስቃሴ መግለጽ መቻላቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. የቦታን ጽንሰ ሐሳብ መረዳት እና መገለጫዎቹን መጠቀም | 6. 1. ሰዎችን፣ ዕቃዎችን እናአካባቢን መሠረት በማድረግ ቦታን እና ርቀትን መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ የእቃዎችን መገኛ ከራስ መገኛ አንፃር መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች (አሻንጉሊቶች፣ ባንዲራዎች፣ አበባዎች /የወረቀት ሊሆኑ ይችላሉ/፣ ኳሶች፣ስእሎች ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- አሻንጉሊቶችን ወይም በአካባቢ ሊገኙ የሚችሉ ቁሳቁሶችን ሕፃናቱ ከሚገኙበት ቦታ ብዙ

ሳይርቅ ማስቀመጥ

- ቁሳቁሶቹ/አሻንጉሊቶቹ/ የተቀመጡበትን ቦታ ከራሱ/ከራሷ/ መገኛ አንፃር እንዲናገር/እንድትናገር በመጠየቅ ማበረታታት/

 ለምሣሌ፡- አሻንጉሊቷ ከእኔ ፊት ተቀምጣለች፣ ከእኔ ኋላ ተቀምጣለች ወዘተ… በማለትእንዲናገር/እንድትናገር መምራት

- ሕፃናትን ወደፊት በመጥራት ከሌላ ሕፃን ፊት፣ ኋላ፣ ከሌሎች ሕፃናት መካከል እንዲቆም በማድረግየት እንደሚገኝ/እንደምትገኝ እንዲናገር/ እንድትናገር ማበረታታት እና ማለማመድ

ምዘና ፦ የእቃዎችን መገኛ ከራስ መገኛ አንፃር ተረድተው መናገር መቻላቸዉን ጥያቄዎች በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ ቦታን ገላጭ ትእዛዝን ሰምተው ይፈፅማሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ አሻንጉሊቶች፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- አሻንጉሊትን /ስም ሰይሞ/ ተናጋሪ ማድረግ
- አሻንጉሊቱ/ቷ የጠየቀውን/ችውን ጥያቄ የተለያዩ ሕፃናት እንዲፈጽሙ በማድረግ ስለቦታ ያላቸውን ግንዛቤ ማጠናከር

 ለምሳሌ ፦ አሻንጉሊቱ/ቷ ከወንበሩ ላይ አስቀምጡኝአለ/አለች፤መቀመጫው አልተመቸኝም ከአበባው በግራ በኩል ባለው ወንበር አስቀምጡኝአለ/አለች፤ ሹራቡን ከፊት ለፊቴ ባለው ጠረጴዛ ላይ አስቀምጡልኝአለ/አለች፤ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ከተቀመጥኩበት ወንበር ፊት፣ ኋላ፣ ግራ፣ ቀኙ ወዘተ… አስቀምጡ አለ/አለች። ወዘተ… በማለት በጨዋታ መልክ የቦታ ግንዛቤአቸውን ማዳበር

ምዘና ፦ ቦታን ገላጭ ትእዛዝን ሰምተው መፈፀም መቻላቸውን በማየት መገምገም።



ተግባር ሁለት ፦ ቦታን ገላጭ ትእዛዝን ሰምቶ መፈፀም

ተግባር ሶስት ፦ ቦታን በተገቢዉ ቃላት መግለጽ

ዓላማ ፡- እቃዎች የተቀመጡበትን ቦታን በተገቢዉ ቃላት ይገልጻሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በስዕል ላይ ከላይ፣ ከታች፣ አጠገብ፣ በተለያየ ነገር ላይ የተቀመጡ ነገሮች ወዘተ... በማሣየት ምን የት እንደተቀመጠ ማስረዳት
- የተለያዩ ነገሮችን በስዕሉ ላይ እንዳዩት እንዲያስቀምጡ መጠየቅ እና የት እንዳስቀመጡ እንዲናገሩ በማድረግ ማለማመድ

ምዘና ፡- ቦታን በተገቢዉ ቃላት መግለጽ መቻላቸውን መከታተል።

## ተግባር አራት ፡- ግራ እና ቀኝ መለየት

ዓላማ ፡-

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባንዲራዎች፣ አበባ፣ ኳስ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ባንዲራ፣ አበባ፣ ኳስ ወዘተ...በየጠረጴዛቸው ላይ ማስቀመጥ
- ምግብ በሚመገቡበት እጃቸው ባንዳራውን አንስተው እንዲያሳዩ መጠየቅ
- ምግብ የሚመገቡበት እጃቸው ቀኝ እጃቸው እንደሆነ መንገር
- ምግብ የማይመገቡበት እጃቸው ግራ እጃቸው እንደሆነ መንገር
- በቀኝ እጃቸው ባንዲራውን ወደ ላይ አንሱ ከዘም በግራ እጃችሁ አበባውን አንሱ በማለት ሲሳሳቱ በርጋታ በማረም ማለማመድ
- ኳሷን በግራ በኩል ላለው ጓደኛህ አቀብል፣ በቀኝ በኩል ላለው አቀብል በማለት ግራና ቀኝን መለየት ማለማመድ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ከሕፃናቱ መካካል በግራ እጅ የሚመመገብ/የምትመገብ ህፃን እንደሚኖር/እንደምትኖር ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፦ ግራ እና ቀኝ እጃቸውን መለየት መጀመራቸውን መከታተል።

ዓላማ ፦ ውስጥና ውጭን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች(አበባዎች /የወረቀት ሊሆኑ ይችላሉ/ ኳሶች ወዘተ...)፣ ቅርጫት/ጫማ ካርቶን

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ቁሳቁሶችን በጠረጴዛ ላይ ፊት ለፊታቸው ማስቀመጥ
- በጠረጴዛ ላይ ምን ይታያችኋል በማለት መጠየቅ
- የሚያዩትን እንዲናገሩ ማድረግ
- የጫማ ካርቶን በጠረጴዛ ላይ ከቁሳቁሶቹ አጠገብ ማስቀመጥ
- ቁሳቁሶቹን በካርቶኑ ውስጥ እንዲከቱ በየተራ በመጥራት መጠየቅ
- ከካርቶኑ ውስጥ ቁሳቁሱን እንዲያወጡ እና ከካርቶኑ ውጭ እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- በዚህ አይነት ውስጥና ውጭን እንዲለዩ ማለማመድ
- ቢሳሳቱ መልሶ ማሣየት እና ደጋግመዉ እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፦ ውስጥ እና ውጭን መለየታቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 7.ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት መግለጽና መጠቀም | 7.1. የገንዘብ ዓይነቶችን እና ምስላቸውን መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አምስት ፦ ውስጥና ውጭ መለየት

ተግባር አንድ ፦ የብር ኖቶችን መለየት

ዓላማ ፦ [illegible] ላቸውን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የብር ኖቶች፣ ፎቶኮፒ የተደረጉ የብር ኖቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የአንድ፣ የአምስት፣ የአሥር ብር ኖቶችን ማሣየት
- ያውቋቸው እንደሆነ መጠየቅ
- ፎቶ ኮፒ የተደረገውን ማሣየት እና መስጠት
- እንዲመለከቱ መምራት እና የብር ኖቶቹ በቀለማቸው፣ በምስላቸውና በመጠናቸው ልዩነታቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የብር ኖቶች በቀለማቸው፣ በመጠናቸውና በምስላቸውን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የሳንቲም ዓይነቶችን እና ምስላቸውን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሳንቲሞች

ተግባር ሁለት ፡- ሳንቲሞችን መለየት

የአተገባ

- የተለያዩ ሳንቲሞችን በመስጠት ስንት ስንት እንደሆኑ መጠየቅ
- እንዳቸው ከአንዳቸው በምን እንደሚለያዩ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲረዱ ማድረግ
- ምን ሊገዛባቸው እንደሚቻል መጠየቅ እና ማወያየት

ማስታወሻ ፡- ይህን ተግባር በአንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ጨዋታዎች በመተግበር ግንዛቤያቸውን ማዳበር ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የሳንቲም ዓይነቶችን እና ምስላቸውን መለየት መጀመራቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።



ተግባር ሶስት ፡- የሳንቲሞችን ምስል በወረቀት መስራት

ዓላማ ፡- የሳንቲሞችን ምስል በወረቀት ላይ ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀቶች፣ እርሳሶች፣ ሳንቲሞች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ወረቀትን በሳንቲሞች ላይ በማድረግ በእርሳስ ወደ አንድ አቅጣጫ ቀስ ብሎ በመቸክቸክ ምስላቸው እንዴት እንደሚወጣ ማሣየት
- ለእያንዳንዳቸውም ሳንቲምና ወረቀትን በመስጠት ባዩት መሠረት እንዲሠሩ ማድረግ
- ሲጨርሱም ስንት ሳንቲምን እንደሰሩ ለጓደኞቻቸው በማሳየት እንዲናገሩ ማድረግ
- በመጨረሻም ተመሳሳይ ሳንቲሞችን አንድ ላይ በማድረግ በትልቅ ወረቀት ላይ መለጠፍና ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ መስቀል

ምዘና ፡- የሳንቲሞችን ምስል በመስራት ልዩነታቸውን መገንዘባቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የገንዘብ ዓይነቶችን እና ምስላቸውን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፎቶ ኮፒ የተደረጉ ብር ኖቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ፎቶ ኮፒ የተደረጉ የብር ኖቶችን በየጠረጴዛቸው የብር ኖቶችን በመስጠት አተኩረው እንዲያዩ ማድረግ
- አንዳቸው ከአንዳቸው በምን እንደሚለያዩ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት
- መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ በምስላቸው እንዴት እንደሚለዩ በማሳየት መግለፅ
- ‹‹ሱቅ ሱቅ›› ጨዋታን እንዲጫወቱ በማድረግ ማጠናከር

ምዘና ፡- የገንዘብ ዓይነቶችን እና ምስላቸውን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ለየት

**2.4.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -----------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም ------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም --------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ----------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ----------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት----------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ ፦ የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመቱ መጀመሪያ | በዓመቱ አጋማሽ | በዓመቱ መጨረሻ |
| 1. የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ መረዳትና መለየት | | | |
| 1.1 በተለያዩ ቁሳቁሶችና ቅርፆች መካከል ያለውን ተመሣሣይነትና ልዩነት ማውጣት ይችላሉ | | | |
| 2. ነገሮችን በባህሪያቸው መሠረት ማወዳደር | | | |
| 2.1. በነገሮች መካከል ያለዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት ይችላሉ | | | |
| 3. ቁጥሮችን ማስተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት | | | |
| 3.1. ቁሳቁሶችንና ቁጥሮችን ከ 1-20 መቁጠር ይችላሉ | | | |
| 4. በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሣሪያዎችን መጠቀም | | | |
| 4.1 በቦታና በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት መጠቀም ይችላሉ | | | |
| 5. የጊዜ ፅንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም፣ | | | |
| 5.1. የሳምንቱን ቀናት ወራትን የበዓል /ልዩም ቀናትን መናገር ይችላሉ | | | |
| 6. የቦታ ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | | | |
| 6.1. ሰዎችን፣ ዕቃዎችን አካባቢን መሠረት በማድረግ ቦታንና ርቀትን መገለጽ ይችላሉ | | | |
| 7. ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት፣መግለጽና መጠቀም | | | |
| 7.1 የገንዘብ ዓይነቶችንና ምስላቸውን መለየት ይችላሉ | | | |

## 2.5 ከአካባቢ ጋር በሚፈጠር መስተጋብር አካባቢን ማጥናት በመግባቡ ማጣጣም

### 2.5.1. ማብራሪያ

በአፀደ ሕፃናት ዕድሜ ክልል ያሉ ልጆች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አዲስ ነገርን ለማወቅና ለመማር ከፍተኛ ፍላጐትና ጉጉት ያላቸው ሲሆን የስሜት አካላቶቻቸውንና ቋንቋን በመጠቀም አካባቢያቸውን መፈተሸ፣ ማወቅና መረዳት የሚጀምሩበት፤ አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦችን የሚማሩበትና የነገሮችን መንስኤና ውጤት መፈለግ የሚጀምሩበት ዕድሜ ነው።

ስለዚህም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ፡-

- ሕፃናት የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ወላጆችን በማንቃት በማስተማር
- የስሜት አካላቶቶቻቸውን በአግባቡ በመጠቀም የነገሮችን ባህሪይ እንዲረዱ እገዛ በማድረግ
- አካባቢያቸውን አስተውለው እንዲመለከቱና እንዲፈትሹ ዕድሉን በመስጠት
- በደረጃቸው የተለያዩ ሙከራዎችን እንዲያደርጉና የሚከሰተውን ለውጥ እንዲረዱ በማድረግ
- ለሚጠይቁት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ በመስጠት ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

የሕፃናት አእምሮ 90 በመቶ የሚዳብረው እስከ 6 ዓመት ባለው ዕድሜ እንደሆነ ጥናቶች ይገልፃሉ። የተመጣጠነ ምግብና ማነቃቂያ የሕፃናት አእምሮ ለመዳበርም ወሳኝ ናቸው።

### 2.5.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. በአካባቢያቸው የሚገኙ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን በባህሪያቸው እንዲለዩ ማድረግ
2. በአካባቢያቸው የሚገኙትን አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችና ለሰዎች የሚሰጡትን ግልጋሎት እንዲያውቁና ሀገር የመውደድ ዝንባሌ እንዲያድርባቸው ማድረግ
3. አካባቢያቸውን በንጽህና መጠበቅን እንዲለማመዱና ራስንና ሌሎችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ አደገኛ ነገሮች ለመከላከል ሙከራ ማድረግን እንዲለማመዱ ማድረግ
4. ስዕሎችንና ቅርፆችን በመሥራት የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና በደረጃቸው የተለያዩ ሙከራዎችን በማከናወን የነገሮችን ባህሪ እንዲረዱ ማድረግ

## **2.5.3** የሚጠበቅ ውጤትና ብቃት

1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ
    1.1. በቤታቸውና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን ሰዎች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት ይችላሉ
2. በአካባቢያቸው የሚገኙ አስፈላጊ ቦታዎችን ማወቅና ማድነቅ
    2.1. በአካባቢያቸው ሰለሚገኙት ቦታዎች መናገር ይችላሉ
    2.2. ሀገርን የመውደድ ዝንባሌ ያሳድራሉ
3. አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ
    3.1. አካባቢን በንጽህና መጠበቅ ይችላሉ
4. በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ
    4.1. ራስንና ሌሎችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ አደገኛ ነገሮች መከላከል ይችላሉ
5. የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ
    5.1. የመኪና ጐማዎችን መጠን ብዛትና ጥቅም መናገር ይችላሉ
6. በስነስዕልና ቅርፃ ቅርፅ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠርና ማድነቅን ራስን መግለጽ
    6.1. ስዕሎችንና ቅርፃ ቅርፆችን መሥራት ይችላሉ

## **2 5.4** የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1.የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | 1.1.በቤታቸው እና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን ሰዎች፣ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- በቅርብ አካባቢ የሚገኙ ሰዎችን መለየት

ዓላማ ፡- በቅርብ አካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎችን ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በአጸደህጻናት የሚገኙ መምህራንን፣ ሞግዚቶችን፣ የጽዳትና የጥበቃ ሠራተኞችን በስም፣ በመልክ፣ በፆታና በሙያቸው እንዲለዩ ማድረግ

  ለምሣሌ፡- በእንቆቅልሽ <<እኔ ሁልግዜ ሕፃናት ብቻቸውን ከግቢ እንዳይወጡ በር ላይ ቆሜ እጠብቃለሁ እኔ ማነኝ**?**>>

  መልዕክትን በመላክ << ለመምህር……… ይህንን ስጫት /ነይ ብለሽ ንገሪያት/>>

  በጥያቄ <<እኔ እናንተን ሳስተምር ለእናንተ እርሳስ የምትቀርጽላችሁ እርሳስ የምትሰጣችሁ ማናት**?**>>

ምዘና ፡- በቅርብ አካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎችን በስም፣ በመልክ፣ በፆታና በሙያቸው መለየት መቻላቸውን እንቆቅልሽና ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- በክፍላቸው ያሉትን ህጻናት በስምና በመልክ ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በክፍል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ዕቃዎች ወይም መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእያንዳንዱ ህጻን በየተራ ሁለት ዕቃ መስጠት
- የሁለት ህጻናትን ስም በመንገር ዕቃውን እንዲሰጥ/እንድትሰጥ ማድረግ
- ትክክል መሆን እና አለመሆናቸውን የክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያረጋግጡ ዕድሉን መስጠት

ምዘና ፡- በክፍላቸው ያሉትን ህጻናት በስም እና በመልክ መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሦስት ፡- የወላጆችን ስም እና ሙያ መለየት

ተግባር ሁለት ፡- የክፍል ጓደኞችን መለየት

ዓላማ ፡- የወላጆቻቸውን ስም እና ሙያ ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት በየተራ እየወጡ የወላጆቻቸውን ስምና ሙያቸውን እንዲናገሩ ማድረግ
- ከከበዳቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ድጋፍ ማድረግ
- የወላጆቻቸውን ሙያ የማያውቁ ህጻናት ካሉ ወላጆቻቸውን ጠይቀዉ በሚቀጥለው ጊዜ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የወላጆቻቸውን ስም እና ሙያ መለየት መቻላቸውን በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- የመጫወቻ እቃዎችን እና የጨዋታውን መጠሪያ ስም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ የሚገኙ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በየጊዜው በክፍል እና በግቢ ውስጥ ባሉ መጫወቻዎች እንዲጫወቱ ዕድሉን መስጠት
- ከጨዋታ በኋላ ምን እንደተጫወቱና በምን እንደተጫወቱ በመጠየቅ ማስታወስ
- ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና የጨዋታውንና የመጫወቻዎቹን መጠሪያ ስም እንዲያውቁ

ተግባር አራት ፡- የመጫወቻ እቃዎችን እና የጨዋታዎችን መጠሪያ ስም መለየት



ተግባር አምስት ፡- የአትክልቶችን መጠሪያ ስም እና ጥቅም መገንዘብ

ዓላማ ፡- የአትክልቶቹን መጠሪያ ስም እና ጥቅም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በግቢ ውስጥ ያሉ አትክልቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በግቢ ውስጥ ያሉትን አትክልቶችን አስተውለው እንዲመለከቱ ማድረግ
- የአትክልቶቹን መጠሪያ ስም እና ምን ጥቅም እንደሚሰጡ በመጠየቅ እና ማወያየት
- በሚኖሩበት አካባቢ መኖራቸውን በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- ይህንን በተለያየ ጊዜ ማከናወን ይገባል።

ምዘና ፡- የአትክልቶቹን መጠሪያ ስምና ጥቅም መለየታቸውን መገምገም።

ተግባር ስድስት ፡- አትክልቶችን መንከባከብ

ዓላማ ፡- አትክልቶችን በመንከባከብ የሚታየውን ለውጥ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአትክልት ችግኞች፣ የአትክልት ውሃ ማጠጫ፣ የተለያዩ የአፈር አይነቶች፣ ጣሳ፣ባልዲ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተረኝነት ሰሌዳ ማዘጋጀት
- ሕፃናት በተራቸው መሠረት በግቢ ውስጥና በክፍል ውስጥ ያሉትን አትክልቶች እንዲንከባከቡ ማድረግ
- በአትክልቶች ላይ የሚታየውን ለውጥ እንዲከታተሉና እንዲረዱ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- በክፍል ውስጥ እና በክፍል በር አካባቢ በፕላስቲክ እቃ ወይም በቆርቆሮ መትከል ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- አትክልቶችን በመንከባከብ የሚታየውን ለውጥ መገንዘባቸውን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡- የጓሮ አትክልቶች መለየት

ዓላማ ፡- የጓሮ አትክልቶችን ስም፣ ቀለም፣ ቅርጽ፣ ጥቅም ወዘተ… ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጓሮ አትክልቶች፣ ፍራፍሬዎች፣ ጥራጥሬዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከሶስት ያልበለጡ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን በክፍል ውስጥ ማምጣት
- ሕፃናቱ አስተውለው እንዲመለከቱ፣እንዲያሸቱ እና እንዲዳስሱ ማድረግ
- ምን እንድሆነ፣ ምን አይነት ቀለምና ቅርጽ እንዳለው መጠየቅ
- በምን አይነት መንገድ ለምግብነት እንደሚቀርብ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

  ለምሳሌ ፡- ጥሬውን፣ ተቀቅሎ፣ተጠብሶ ወዘተ…
- ሁሉም ለምግብነት የሚያገለግሉ እና የጓሮ አትክልት ተብለው እንደሚጠሩ ግንዛቤ ማስጨበጥ

ማስታወሻ ፡- በዚህ ዓይነት መንገድ ፍራፍሬዎችን እና ጥራጥሬዎችን በቀጣይ ክፍለ ጊዜያት ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የጓሮ አትክልቶችን ስም፣ ቀለም፣ ቅርጽ፣ ጥቅም ወዘተ… ለይተው ማወቃቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የቤትና የዱር እንስሳትን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቤትና የዱር እንስሳት ስእሎች፣ የአዕዋፍ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-



ተግባር ስምንት ፡- የቤትና የዱር እንስሳትን መለየት

- የተለመዱ እና ሕጻናት በተለያዩ አጋጣሚዎች በአካልም በስዕልም ሆነ በፊልም አይተዋቸው የሚያውቋቸውን የቤት እንስሳትን እና የዱር እንስሳትን ስዕል በወፍራም ክላሰር /ካርቶን/ ላይ በመለጠፍ ማዘጋጀት
- ስእሎቹን ለእያንዳንዳቸው አንድ አንድ መስጠት
- ለጓደኞቻቸው በማሳየትም እንደሆኑ እና የት እንደሚኖሩ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

ማስታወሻ፡- ሁሉንም በአንድ ክፍለጊዜ ማስተዋወቅ ስለማይቻል በተለያየ ክፍለጊዜ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የቤትና የዱር እንስሳትን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የቤት እንስሳት አኗኗር፣ አመጋገብ እና ጥቅም ይረዳሉ።

ተግባር ዘጠኝ ፡- የቤት እንስሳት አኗኗር፣ አመጋገብ እና ጥቅም መረዳት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከ 3 ያልበለጡ የቤት እንስሳትን ስዕል ማሣየት
- የቤት እንስሳት አኗኗር፣ አመጋገብ እና ጥቅም በማወያየት የሚያውቁትን ሁሉ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት
- መልሳቸውን መሠረት በማድረግ እንሰሳት በአኗኗቸው፣ በአመጋገባቸውና በጥቅማቸው እንደሚለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- "የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ።" የሚለውን መዝሙር በመዘመር ማጠናከር

ማስታወሻ ፡- በዚህ አይነት የዱር እንሰሳትንና አእዋፍንም ማስተዋወቅ ያስፈልጋል እንደዚሁም ሁሉንም የቤት እንሰሳት፣ የዱር እንሰሳትና አእዋፍን በአንድ ክፍለ ጊዜ ማስተዋወቅ ስለማይቻል በተለያየ ክፍለጊዜ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የቤት እንስሳትን አኗኗር፣አመጋገብና ጥቅም መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የዱር እንስሳትን አኗኗርና አመጋገብ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዱር እንስሳት ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከ 3 ያልበለጡ የዱር እንስሳትን ስዕል ማሣየት
- የዱር እንስሳት አኗኗርና አመጋገብ በማወያየት የሚያውቁትን ሁሉ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት
- መልሳቸውን መሠረት በማድረግ እንሰሳቱ በአኗኗርና በአመጋገባቸው እንደሚለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- እንስሳቱን መሠረት ያደረገ እንቆቅልሽ በመጠየቅ ማጠናከር

ማስታወሻ ፡- ሁሉንም የዱር እንሰሳትና አእዋፍን በአንድ ክፍለጊዜ ማስተዋወቅ ስለማይቻል በተለያየ ክፍለ ጊዜ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የዱር እንስሳትን አኗኗርና አመጋገብ መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የአዕዋፍ አኗኗርና አመጋገብ ይረዳሉ።

ተግባር አስር ፡- የዱር እንስሳት አኗኗርና አመጋገብ መረዳት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአእዋፍ ስእሎች፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-



ተግባር አስራ አንድ ፡- የአዕዋፍ አኗኗርና አመጋገብን መረዳት

- በተለያየ አጋጣሚ ያዩዋቸውን የተለያዩ የአእዋፍ ስዕል ለህጻናቱ በመስጠት ባለቀለም እርሳስ/ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- የቀቡት ስእል ምን እንደሆኑ፣ የት እንደሚኖሩ እና አመጋገባቸውን በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት
- የቀቡት ስእል ምን እንደሆኑ፣ የት እንደሚኖሩ እና አመጋገባቸውን በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት
- "ወፊቷን እሆናለሁ" የሚለውን መዝሙር በማዘመር ማጠናከር

ምዘና ፦ ስለአዕዋፍ አኗኗርና አመጋገብ መገንዘብ መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ የእንስሳቶችን ልጆች ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የቤትና የዱር እንስሳት ስዕሎች፣ የአዕዋፍ ስዕሎች

ተግባር አስራ ሁለት ፦ የእንስሳት ልጆችን መለየት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ህጻናት እንስሳትን እና ልጆቻቸውን እንዲለዩ ልጆቼ የት ነው ያላችሁት? የሚለውን ጨዋታ እንደሚከተለው ማጫወት
- የተለያዩ እንስሳቶችን እና ልጆቻቸውን የሚያሳይ ስእል በወፍራም ካርቶን ላይ በመለጠፍ ማዘጋጀት
- የእንስሳትን ልጆች ስዕል ለእያንዳንዱ ህጻን መስጠት
- መምህር የአንዱን እንስሳ ልጆች ምስል የያዙ ህጻናት እዚህ ነን እዚህ ነን እያሉ በመውጣት ስእሎቻቸውን ከፍ አድርገው በመያዝ ከመምህር አጠገብ እንዲቆሙ ማድረግ
- የተሳሳቱ ካሉ የራሳቸውን ስዕል ከመምህር ጋር እንዲያስተያዩና ስህተታቸውን እንዲያርሙ በማድረግ ማጫወት

ምዘና ፦ የእንስሳቶችን ልጆች መለየት መቻላቸውን ተግባሩን በመከታተል ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ ሶስት ፡- ስለ እንስሳት አኗኗር እና አመጋገብ መረዳት

ዓላማ ፡- ስለ እንስሳት አኗኗር እና አመጋገብ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቤትና የዱር እንስሳት ስዕሎች፣ የአዕዋፍ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናትን እንስሳት የሚገኙበት ቦታ ሽርሽር /ጉብኝት/መውሰድ

  ለምሳሌ፡- አንበሳ ግቢ
- የእንስሳቱን አኗኗር እና አመጋገብ እንዲጎበኙ ማድረግ
- ከጉብኝት በኋላ በክፍል ውስጥ ስላዩት ነገር ማወያየት

ማስታወሻ ፡- ጉብኝት ከመሄዳቸው በፊት የት፣መቼ፣ ለምን፣ እንዴት እንደሚሄዱና በአቅማቸው ሊያደርጉ የሚገባቸውን ጥንቃቄ አስቀድሞ መግለፅ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ስለእንስሳት አኗኗር እና አመጋገብ መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ አራት ፡- የእንስሳቶች እንቅስቃሴ እና ባህሪ መለየት

ዓላማ ፡- የተለያዩ እንስሳቶችን እንቅስቃሴ እና ባህሪ ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቤትና የዱር እንስሳት ሎቶ /ዶሚኖ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የእንሰሳት ሎቶ/ዶሚኖ አዘጋጅቶ በመስጠት እንዲጫወቱ ማድረግ
- የጐደለውን ዕወቅ እንቆቅልሽ በማጫወት ማጠናከር

- የተለያዩ እንሰሳቶችን እንቅስቃሴ እና ባህሪ የሚገልፁ መዝሙሮችን በማዘመር የመዝሙሩን መልዕክት እንዲረዱት ማድረግ

  ለምሳሌ፦ ወፊቱን እሆናለሁ፣ ቀስ በቀስ ሽረሪቷ፣ እንሰሳቶች ሁሉ፣ ጥንቸል ጉረኛው ወዘተ...

ምዘና ፦ የተለያዩ እንሰሳቶችን እንቅስቃሴ እና ባህሪ መለየታቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ እንሰሳትን እና አዕዋፍን ስእል ቀለም ይቀባሉ እንዲሁም ቅርፁን ቀደው ያወጣሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ የእንሰሳት እና የአዕዋፍ ስዕል ባለቀለም እርሳስ፣ መቀስ

ገባር አስራ አምስት ፦ እንሰሳትን እና አዕዋፍን ስእል ቀለም መቀባትና ቀዶ ማውጣት

እንዲያወጡ ማድረግ

- ሲጨርሱም ቀለም የቀቡትንና ቅርፃቸውን ቀደው ያወጡትን እንስሳ እና አእዋፍ ለጓደኞቻቸው በማሳየት የምን ስእል እንደሆነ እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት
- ትክክል መሆንና አለመሆናቸው ጓደኞቻቸው እንዲገመግሙ ማድረግ

ምዘና ፦ የእንስሳት እና የአእዋፍ ስዕል ቀለም መቀባታቸውንና ቅርፁን ቀደው ማውጣታቸውን ሲተገብሩ በማየት ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ የተለያዩ የአፈር አይነቶችን እና አሸዋን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ቀይ እና ጥቁር አፈር፣ አሸዋ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦



ተግባር አስራ ስድስት ፦ የተለያዩ የአፈር አይነቶችን እና አሸዋን መለየት

- በግቢ ውስጥ የተለያዩ የአፈርና የአሸዋ አይነቶችን ማዘጋጀት
- ህጻናቱ በእጃቸው በመንካት ምን እንደሆነ እና ልዩነታቸውን እንዲናገሩ ማድረግ
- በአካባቢያቸው እንዳለ እና እንደሌለ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውል በመጠየቅ ማወያየትና ግንዛቤ ማስጨበጥ

ምዘና ፡- የተለያዩ የአፈር አይነቶችን እና የአሸዋን ልዩነት መገንዘብ መጀመራቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- ስለፀሃይ የሚያውቁትን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፀሃይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህጻናቱ ፀሃማ በሆነ ቀን ከክፍሉ ውጪ ይዞ በመውጣት ሰማን እንዲመለከቱ እና ያዩትን እንዲናገሩ ማድረግ
- ፀሃይ ሁልጊዜ ሰማይ ላይ እንደምትኖር እና እንደማትኖር መጠየቅ
- ፀሃይ መቼ እንደምትኖርና እሷ ሳትኖር በፀሃይ ቦታ ምን እንደሚተካ በጥያቄ ማወያየት
- ...ይን ጥቅም በመጠየቅ ማወያየትና ...

ተግባር አስራ ሰባት ፡- ስለፀሃይ መናገር

ምዘና ፡- ስለ ፀሃይ መናገር መቻላቸውን በጥያቄ መገምገም።

ተግባር አስራ ስምንት ፡- የአየር ጸባይ መገለጫዎች

ዓላማ ፡- የአየር ፀባይ መገለጫዎችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ የአየር ንብረትን የሚገልጹ ስእሎች፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትልቅ ወፍራም ወረቀት ላይ የአየር ጸባይ መገለጫዎችን የሚያሳይ ስእል በሚከተለው መንገድ መስራት
- ወረቀቱን በትልቅ ክብ ቆርጦ በማውጣት እኩል አራት ቦታ ከፍሎ ማስመር
- በእያንዳንዱ ክፋይ ፀሃያማ፣ዳመናማ፣ንፋሳማ እና ዝናባማ ቀን የሚያሳይ ስእል መሳል

  ለምሳሌ፡-
    - ፀሃያማ ፡- ጥርት ያለ ሰማይ ላይ ፀሃይን በቢጫ ከለር መሳል።
    - ደመናማ ፡- ሰማዩን አልፎ አልፎ ጠቆር ያለ ግራጫ ቀለም በመቀባት ፀሃይን በደመና ተሸፍኖ የሚያሳይ ስእል መሳል
    - ነፋሻማ ፡- ዛፎችን፣ ቅጠሎችን ወደ አንድ አቅጣጫ ዘመው የሚያሳይ ስእል መሳል
    - ዝናባማ ፡- የጠቆረ ሰማይን የዝናብ ጠብታንና ጃንጥላ የያዙ ሰዎችን በመሳል ማዘጋጀት
- ካርቶን በክብ በመቁረጥ የክቡ መሃል ላይ ትንሽ የምትንቀሳቀስ አቅጣጫ ጠቋሚ ማያያዝና ለህጻናቱ እይታ አመቺ የሆነ ቦታ ላይ መለጠፍ
- እያንዳንዱን የአየር ፀባይ በመጠቆሚያዋ በማመልከት ስዕሉ ላይ ምን እንዳስተዋሉ በመጠየቅ የአየር ጸባዮችን እንዲረዱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- በየቀኑ ይህንን ስዕል በማሳየት የእለቱን የአየር ጸባይ እንዲናገሩ ማድረግ። |

ምዘና ፡- የአየር ፀባይ መገለጫዎችን መረዳት መቻላቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- በቤት ውስጥና በቤት አካባቢ ሊገኙ የሚችሉ ነፍሳቶችን ስያሜ፣ አኗኗር እና አመጋገብ ያሳያል።

ተግባር አስራ ዘጠኝ ፡- ስለትናንሽ ነፍሳት መረዳት

የመር … ሉት ነፍሳት ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ በቤት ውስጥና በቤት አካባቢ ሊገኙ የሚችሉ ነፍሳቶች ስዕል ማሳየት

  ለምሳሌ፡- ዝንብ፣ ጉንዳን፣ ሸረሪት፣ በረሮ፣ ትንኝ ወዘተ…
- ስለአኗኗራቸውና አመጋገባቸው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ትናንሽ ነፍሳቶችን ከህጻናቱ ጋር አብሮ መፈለግ

  ለምሳሌ፡- በድንጋይ ስር፣ በግርግዳ ላይ፣ በዛፍ ላይ ወዘተ…
- ነፍሳቶቹን ቀረብ ብለው እንዲመለከቷቸው ማድረግና ሕጻናቱ ያዩትን እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- በቤት ውስጥና በቤት አካባቢ ሊገኙ የሚችሉ ነፍሳቶችን ስያሜ፣ አኗኗር እና አመጋገብ መረዳት መጀመራቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የመስመጥ እና የመንሳፈፍ ልዩነት ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎድጓዳ ብርሃን የሚያሳይ የፕላስቲክ ሳህን ወይም ባልዲ፣ ቀለል ያሉ ሊንሳፈፉ ወይም ሊሰጥሙ ሚችሉ ቁሳቁሶች፣ ውሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህጻናቱን ከክፍል ውጪ በግቢ ውስጥ በማዘዋወር የሚያገኙዋቸውን የወዳደቁ ቅጠሎች፣ የዛፍ ፍሬዎች፣ ጠጠሮች፣ ቆርኪዎች ወዘተ…እንዲሰበስቡ ማድረግ
- በትልቅ ጉድገዋድ ሳህን ውስጥ ውሃ ማድረግ
- ሁሉም ህጻናት ያገኙትን ነገር ውሃ ውስጥ በመጨመር የሚከተለውን ለውጥ እንዲያስተውሉ እና እንዲናገሩ ማድረግ
- የትኞቹ እንደሰመጡ የትኞቹ እንደተንሳፈፉ ማወያየት

ምዘና ፡- የመስመጥ እና የመንሳፈፍን ልዩነት መረዳት መቻላቸውን ሙከራ ሲያደርጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ዓ

ተግባር ሀያ ፡- መስመጥ እና መንሳፈፍን መረዳት



ተግባር ሀያ አንድ ፡- የሚሰጥሙ እና የሚንሳፈፉ እቃዎችን መለየት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎድጓዳ ብርሀን የሚያሳይ የፕላስቲክ ሳህን ወይም ባልዲ፣ ቀለል ያሉ ሊንሳፈፉ ወይም ሊሰጥሙ የሚችሉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- <<የማን ምን ሆነ?>> የሚለዉን ጨዋታ በክፍል ውስጥ በሚከተለው መንገድ በማካሄድ የዕቃዎችን ባህሪ እንዲረዱ ማድረግ
- ለሁሉም ሕፃናት አንድ አንድ ዕቃ መስጠት

  ለምሳሌ፡- ላጺስ፣ ቆርኪ፣ የበር ቁልፍ፣ የልብስ ቁልፍ፣ ከወረቀት የተሰራ መርከብ፣ ትንሽ የፕላስቲክ ኳስ፣ የሃይላንድ ክዳን ወዘተ…
- ለህጻናት እይታ አመቺ ቦታ ላይ ብርሃን በሚያስተላልፍ ጎርጓዳ ሳህን ውሃ በማድረግ ጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
- ሁሉም ሕጻን እየወጡ በእጃቸው ላይ የያዙትን እቃ ምን እንደሆነ በማሳየት እና በመንገር ውሃው ውስጥ መጨመር እና ውጤቱን ለጓደኞቻቸው እንዲህ በማለት እንዲናገሩ ማበረታታት

ለምሳሌ፡- የኔ ወረቀት መርከብ ተንሳፈፈች፣ የኔ የቤት ቁልፍ ሰመጠች

ምዘና ፡- የሚሰምጡ እና የሚንሳፈፉ እቃዎችን በሙከራ መለየት መቻላቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
| --- | --- |
| 2. በአካባቢ የሚገኙ አስፈላጊ ቦታዎችን ማወቅና ማድነቅ | 2.1. በአካባቢያቸው ስለሚገኙ ቦታዎች መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- አገልግሎት መስጫ ተቋማትን መለየት

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ስዕሎች፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳሶች/ከለሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች መኖራቸውን መጠየቅ
  ለምሳሌ፡- ሱቅ፣ ት/ቤት፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ ሐኪምቤት፣ መድኃኒት ቤት፣ ወፍጮ ቤት ወዘተ
- የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ስዕሎችን እና ምልክቶቻቸውን በማሣየት ማወያየት
- ለሁሉም ህጻናት ስዕል እና ባለቀለም አርሳስ መስጠት
- በአካባቢያቸው ከሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አንዱን ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም ለመምህር እንዲያሳዩ እና ምን እንደቀቡ እንዲናገሩ ማበረታታት

> ማስታወሻ ፡- በአንድ ክፍለ ጊዜ ሁሉንም የአገልግሎት መስጫ ተቋማት መተዋወቅ ስለማይችሉ በተለያየ ክፍለጊዜ እንዲተዋወቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- አገልግሎት መስጫ ተቋማትን መጎብኘት

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ይጎበኛሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ስዕሎች፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ከለሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች መኖራቸውን መጠየቅ
  ወፍጮ ቤት ወዘተ
- የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ስዕሎችን እና ምልክቶቻቸውን በማሣየት ማወያየት
- ለሁሉም ህጻናት ስዕል እና ባለቀለም አርሳስ መስጠት
- በአካባቢያቸው ከሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አንዱን ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም ለመምህር እንዲያሳዩ እና ምን እንደቀቡ እንዲናገሩ ማበረታታት

ማስታወሻ ፡- በአንድ ክፍለጊዜ ሁሉንም የአገልግሎት መስጫ ተቋማት መተዋወቅ ስለማይችሉ በተለያየ ክፍለጊዜ እንዲተዋወቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ከጉብኝት በኋላ በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን መለየታቸዉን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ተግባራት ይረዳሉ።

ተግባር ሶስት ፡- የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን ተግባራት መረዳት

የአ

- የተለያዩ ትርጉም የሚሰጡ ታሪኮችን በመንገር የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን ተግባራት እንዲረዱ ማድረግ

ለምሳሌ፡-

ከእለታት አንድ ቀን ጩቡዴ ሆዱን አመመውና ለመታከም ወደ ጋራዥ ሄደ ከዛ በኋላ ሲርበው ደግሞ ምግብ ለመብላት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደ ከዚያም ቦርሳውን ይዞ ትምህርት ለመማር ወደገበያ ሄደ። ወዘተ... እያሉ በመንገር ትክክል መሆኑን እና አለመሆኑን እና አለመሆኑን በመጠየቅ በየትኛው ቦታ ምን አይነት አገልግሎት ማግኘት እንደሚቻል በማወያየት ግንዛቤ ማስጨበጥ

ምዘና ፡- የሚሰምጡ እና የሚንሳፈፉ እቃዎችን በሙከራ መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸው የሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ባለሞያዎችን ተግባር ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ባለሞያዎችን እና አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች



ተግባር አራት ፡- የባለሞያዎችን ተግባር መለየት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያዩ ባለሞያዎችን እና አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን የሚያሳዩ ስዕሎችን በየጠረጴዛቸው ላይ በመስጠት ባለሙያንና ተቋማትን በማዛመድ እንዲጫወቱ እድሉን መስጠት
- አዛምደው ሲጨርሱ ለምን እንደዛ ሊያዛምዱ እንደቻሉ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት
- መልሳቸውን መሠረት በማድረግ በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች ተግባርን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ በአካባቢያቸው የሚያገኙ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ባለሞያዎችን ተግባራት መገንዘባቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ በአካባቢያቸው የሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ባለሞያዎችን ተግባር ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ለመስሎ መጫወት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለመስሎ መጫወት ጨዋታ በሚመች መልኩ ክፍሉን ማደራጀት
- ሕጻናት በአካባቢያቸው ያዩትን እና የሰሙትን አገልግሎት መስጫ ተቋም ተግባር በጨዋታቸው እንዲያንጸባርቁ እድሉን መስጠት
- በጨዋታ ሂደት ላይ ክትትል በማድረግ አስፈላጊ በሆነ ቦታ ላይ ድጋፍ ማድረግ

ተግባር አምስት ፦ በመስሎ ጨዋታ የባለሞያዎችን ተግባር መለየት

[illegible] መስሎ ጨዋታውን በመመልከት መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. በአካባቢ የሚገኙ አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | 2.1. ሀገርን የመውደድ ዝንባሌ ያሳድራሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የኢትዮጵያ ባንዲራ ቀለማት መለየት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የሀገራችን ባንዲራ ምን ምን ዓይነት ቀለም እንዳለው መጠየቅ
- የተለያዩ ሃገር ባንዲራዎችን በማሣየት የኢትዮጵያ የትኛው እንደሆነ እንዲናገሩ በማድረግ የሀገራችንን ባንዲራ ማሣየት
- ለሁሉም ሕጻናት ወረቀት እርሳስ እና ባለቀለም እርሳሶች መስጠት
- የሃገራችንን ባንዲራ እንዲስሉ እና ተገቢውን ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- በመጨረሻም ስማቸውን ከስር በመፃፍ በክፍል ውስጥ እንዲለጥፉት ማድረግ
- ባንዲራችን የሚለውን መዝሙር በማዘመር የሀገራችንን መጠሪያ ስምና የባንዲራ ቀለሟን እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የኢትዮጵያን ባንዴራ ቀለማትን መለየታቸውን የሳሉትን በመመልከት መገምገም፡፡

ዓላማ ፡- የኢትዮጵያን "`ካርታ ቅርፅ ይለያሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ የኢትዮጵያ ካርታ፣ የኢትዮጵያ ካርታ ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሁሉም ህጻናት የተለያዩ ባለቀለም እርሳሶችን በመስጠት የሚወዱትን ቀለም እንዲመርጡ ማድረግ
- የኢትዮጵያን ካርታ በመስጠት በመረቱት ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ እና የቀቡትን በክፍል ውስጥ መለጠፍ
- የኢትዮጵያን ካርታ ፐዝል እንዲገጣጥሙ በማድረግ ማጠናከር



ተግባር ሁለት ፡- የኢትዮጵያን ካርታ ቅርጽ መለየት

ምዘና ፦ የኢትዮጵያን ካርታ ቅርጽ መለየታቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ የኢትዮጵያን ህዝብ መዝሙር ይዘምራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የኢትዮጵያ ባንዲራ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር በማዘመር በቃላቸው እንዲይዙት ማለማመድ

ምዘና ፦ የኢትዮጵያን የህዝብ መዝሙር መዘመር መልመዳቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሶስት ፦ የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር መዘመር**

ዓላማ ፦ ለሀገራቸው መልካም ስራ ያበረከቱ ሰዎችን ያውቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የታዋቂ ሰዎች ፎቶ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የታዋቂ ሰዎችን ፎቶ በማሳየት እነማን እንደሆኑና አይተዋቸው ያውቁ እንደሆነ መጠየቅ
  ለምሳሌ፦ ሐይሌ ገብረስላሴ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ አበበች ጎበና ወዘተ…
- መልሳቸውን ከሰሙ በኋላ እነዚህ ታዋቂ ሰዎች ለሀገራችን ምን እንዳደረጉ በደረጃቸው መግለፅ

> ማስታወሻ፦ በአንድ ክፍለጊዜ ሁሉንም ታዋቂ ሰዎች መተዋወቅ ስለማይችሉ በተለያየ ክፍለ ጊዜ ማስተዋወቅ ይገባል።

ምዘና ፦ ለህገራቸው መልካም ስራ ስላበረከቱ ሰዎችን በመልክና በተግባራቸው መተዋወቃቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
| --- | --- |
| 3. አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ | 3.1. አካባቢን በንጽህና መጠበቅ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ ንጽህናን የመጠበቅ ጥቅምን መረዳት

ዓላ... መቁዋወቅ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የኢትዮጵያ ባንዲራ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የግልና የአካባቢ ጽዳት ጋር የተያያዙ ዜናዎች፣ ገጠመኞች፣ ታሪኮች በመንገር የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቅ ያለውን ጥቅም ማወያየት
- በአቅማቸው የግልና የአካባቢ ፅዳትን በአቅማቸው እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግ
- የግልና የአካባቢ ፅዳት ጠቀሜታን በደረጃቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቅን ጥቅም መረዳታቸዉን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ የግልና የአካባቢ ንጽህናን ለመጠበቅ የምንጠቀምባቸዉን መሳሪያዎችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ አካባቢን ለማጽዳት የምንጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች /ስዕል/፣ ወረቀት፣ እርሳስ እና ባለቀለም እርሳስ

...ር ሁለት ፦ የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቂያ መሳሪያዎችን መለየት፣ መተዋወቅ

አገልግሎት እንደሚውሉ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት

- መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ እያንዳንዱን ቁሳቁስ በማሳየት መጠሪያ ስሙንና አገልግሎቱን መግለፅ
- የግልና የአካባቢ ንፅህና መጠበቂያ ስእሎችንና ባለቀለም እርሳስን በመስጠት ስእሎቹን ቀለም እንዲቀቧቸው ማድረግ
- ሲጨርሱም የቀቡትን ቁስ ስእል ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩና ምን እንደሆነና ለምን አገልግሎት እንደሚውል እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የግል እና የአካባቢ ንጽህናን ለመጠበቅ የምንጠቀምባቸዉን መሳሪያዎች መለየታቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- ጠረጴዛ እና የክፍል ንጽህና መጠበቅ

ዓላማ ፡- ጠረጴዛቸዉን እና ክፍላቸዉን በአቅማቸዉ ያፀዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረኝነት ሰሌዳ፣ ውሃ የተነከረ ትንሽ ፎጣ /ጨርቅ/፣ ትንሽ መጥረጊያ፣ የቆሻሻ ማፈሻ ትሪ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በቤታቸው ምግብ ከበሉ በኋላ የተመገቡበትን ጠረጴዛ ማን እንደሚያፀዳ በመጠየቅ ማነቃቃት
- የህጻናቱን መልስ ካዳመጡ በኋላ ህጻናት በአቅማቸው ስራ በመስራት ወላጅን ማገዝ እንዳለባቸውና ከዚህም አንዱ የተመገቡበትን ጠረጴዛ ማፅዳት መሆኑን መግለፅ
- የተመገቡበትን ጠረጴዛ ውሃ በተነከረ ፎጣ በማፅዳትና መሬት ላይ የወዳደቁትን የምግብ ትርፍራፊዎች በመጥረጊያ ጠርጎ በቆሻሻ ማፈሻ ላይ በማድረግ እንዴት ማፅዳት እንደሚቻል ማሳየት
- ህጻናቱ ባዩት መሠረት በተግባር እንዲለማመዱ አስፈላገውን ቁስ በማቅረብ እንዲለማመዱ ማድረግ
- ምግብ ከበሉ በኋላ የዕለቱ ተረኞች የተመገቡበትን ጠረጴዛ እና ክፍሉን እንዲያፀዱ ማለማመድ

ምዘና ፡- ጠረጴዛቸዉን እና ክፍላቸዉን በአቅማቸዉ ማፀዳት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር አራት ፡- የአካባቢ ንጽህና መጠበቅ

ዓላማ ፡- የአካባቢ ንጽህና መጠበቅ አስፈላጊነትን ይረዳሉ እንዲሁም በአቅማቸዉ ያጸዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት፣ ውሃና ሳሙና

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከክፍል ውጪ ህፃናቱን ይዞ በመውጣት ግቢያቸውን እንዲመለከቱና ግቢያቸው ንፁህ መሆንና አለመሆኑን በመጠየቅ ማወያየት
- መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ ቆሻሻዎቸን መሬት ላይ መጣል እንደሌላባቸውና ቆሻሻን ማስቀመጥ ያለባቸው በግቢ ውስጥ ባሉ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ ብቻ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ማድረግ
- በሕብረት ‹‹ትናንሽ ወረቀቶች›› መዝሙር እየዘመሩ ግቢያቸው ውስጥ የወዳደቁ ቅጠሎችን የብስኩት ልጣጮችን ወዘተ… እንዲሰበስቡ ማድረግ
- የሰበሰቡትን ቆሻሻዎች በቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ እንዲጥሉ ማድረግ
- ሲጨርሱ እጃቸውን በውሃና በሳሙና እንዲታጠቡ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- መምህር የተጠቀሙበትን ሶፍት እንደዚሁም እርሳስና ከለር ቀርፀው ቆሻሻውን ወደ ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ በመጣል ለሕፃናቱ አርአያ በመሆን ሕፃናቱም እርስዎን በማየት ልምዱን እንዲያዳብሩ መርዳትናበዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ እንዲተገብሩት መከታተል እና ማበረታታት።

ምዘና ፡- የአካባቢ ንጽህና መጠበቅን አስፈላጊነት መረዳታቸዉን እንዲሁም በአቅማቸዉ ማጽዳት መቻላቸዉን መከታተል።

**ተግባር አምስት ፡- ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት መረዳት**

ዓላማ ፡- የግልና የአካባቢ ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጻህፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ተረት፣ ገጠመኝ ወይም ታሪክ በመጠቀም የግል እና የአካባቢን ንጽህና አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ማስረዳት
- ሕፃናት በቤታቸውም ሆነ በአካባቢያቸው ቆሻሻ በተከማቸበት ቦታ መጫወት እንደሌለባቸው ማስገንዘብ

> ማስታወሻ ፡- ይሄን ተግባር በአንድ ቀን ብቻ እንዲማሩት ሳይሆን በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ እንዲተገብሩት ስለሆነ ማስታወስ እና መከታተል ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የግልና የአካባቢ ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት መጠየቅ

**ተግባር ስድስት ፡- በሕብረት የማጽዳት ጠቃሚነትን መረዳት**

[illegible]

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሕብረት ጽዳትን የሚያሳዩ ግጥሞች/መዝሙሮች/ ተረቶች መፀሐፍ፣ የተለያዩ አካባቢን ለማጽዳት የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶች፣ ሳሙና፣ ዉሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሰዎች በሕብረት ቤታቸውን እና አከባቢያቸውን ሲያፀዱ የሚያሣዩ ስዕሎች ማሣየት
- ስለ ስዕሎቹ በማወያየት በህብረት የማጽዳት ጠቃሚነትን እንዲረዱ ማድረግ

- ግጥሞች፣ መዝሙሮች፣ ተረቶች፣ ገጠመኞች ወዘተ... መንገር

  ለምሳሌ፡- ‹‹ትናንሽ ልጆች በህብረት ››

- ሕፃናት እየዘመሩ በሕብረት ግቢያቸውን እንዲያፀዱ ማድረግ
- ሲጨርሱም በውሃና በሳሙና እጃቸውን እንዲታጠቡ ማድረግ

ምዘና ፡- በሕብረት ማጽዳት መለማመዳቸዉን ሲያጸዱ በመመልከት መገምገም።

ዓላማ ፡- ቁሳቁሶችን በሥርዓት መያዝ እና ማስቀመጥ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጽዳት ዕቃዎች ስዕል ወይም ሎቶ፤ የተለያዩ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ስዕሎቹን ወይም ሎቶዎቹን ማዛመድ ጨዋታን እንዲጫወቱ ማድረግ

ተጠቀሙበትን

ተግባር ሰባት ፡- ቁሳቁሶችን በሥርዓት መያዝ እና ማስቀመጥ

ማስታወሻ፡- ሁሌም በሚጫወቱበት ወቅት የመጫወቻ ቁሳቁሶችን በሥርዓት መያዝን እና በሥርዓት ማስቀመጥን እንዲለማመዱ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ቁሳቁሶችን በሥርዓት መያዝ እና ማስቀመጥ መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር ስምንት ፡- አትክልት መትከል እና መንከባከብ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአትክልት መትከያ ባልዲ፣ የአትክልት ችግኝ /ዘር፣ የአትክልት የውሃ ማጠጫ፣ አፈር፣ ውሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ ከሕፃናቱ ጋር የተለያዩ አትክልቶችን መትከል
- ሕፃናት በወጣላቸው የተረኝነት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲንከባከቡ ማለማመድ

ምዘና ፡- አትክልቶችን መትከል እና መንከባከብ መለማመዳቸዉን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | 4.1. ራሳቸዉን እና ሌሎችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ አደገኛ ነገሮች መከላከል ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- አደገኛ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- አደገኛ ነገሮትን ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ በአካባቢ የተከሰቱ አደጋዎች ዜናን ለሕፃናቱ በደረጃቸው ሊገባቸው በሚችል መልኩ መንገር
- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የአደጋውን አስከፊነት እንዲገነዘቡ ማድረግ
- እነሱም በቤታቸው በአካባቢያቸው የተከሰቱ የተለያዩ አደጋዎችን እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት
- የህፃናቱን መልስ መሠረት በማድረግ የመኪና አደጋ፣ እሳት፣ ኤሌትሪክ፣ ስለታማና ሹል ነገሮች ወዘተ አደገኛ ነገሮች እንደሆኑና መጠንቀቅ እንዳለባቸው ማስገንዘብ

ምዘና ፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አደገኛ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- ራስን ከአደገኛ ነገሮች መከላከል

ዓላማ ፦ ራሳቸዉን ከአደገኛ ነገሮች እንዴት መከላከል እንዳለባቸዉ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መፅሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- በአካባቢያቸው ሊከሰቱ የሚችሉ አደገኛ ነገሮች የትኞቹ እንደሆኑ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት
- እሳት፣ ኤሌክትሪክ፣ የመኪና አደጋ፣ስለታማና ሹል የሆኑ ነገሮች ወዘተ አደገኛ ነገሮች መሆናቸውን መግለፅ
- ሕፃናትም ሆኑ አዋቂዎች በመንገድ ላይ ሲጓዙ አስተውለው እና የመንገዱን ግራ ብቻ ይዘው መጓዝና መሻገር ያለባቸውም ቐንጉርጉር በተሰመረው መስመር ላይ ብቻ /በዜብራ/ እንዳለባቸው ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ሕፃናት በቤት ውስጥም ሆነ በውጪ እነሱም ሆኑ ሌሎች ህፃናት በክብሪት፣ስለታማ በሆኑ ነገሮች መጫወት እንደሌለባቸው ማስገንዘብ
- አደጋዎች ከመድረሳቸው በፊት በአቅማቸው ሊወሰዱ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎችን ማሣወቅ
- የ‹‹ትንሹ ዮናስ›› ተረትበመተረት ማጠናከር

ምዘና ፦ ራሳቸዉን ከአደገኛ ነገሮች እንዴት መከላከል እንዳለባቸዉ መረዳታቸውን መገምገም።

**ተግባር ሶስት ፦ የትራፊክ ህግን መረዳት**

ዓላማ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለየዩ የትራፊክ አደጋዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያዩ የትራፊክ አደጋዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ ፊልሞች በማሳየት ማወያየት
- እነሱም ሆነ ወላጆቻቸው መንገድ ሲያቋርጡ በቐንጉርጉር መስመር ላይ ብቻ መሆን

እንዳለበት ማስገንዘብ

- መጓዝ ያለባቸው በእግረኛ መንገድ ላይ ብቻ እንደሆነ፣ በመኪና መንገድ ላይ መጫወት እንደሌለባቸውና የእግረኛ መብራት አረንጓዴ ሲበራ ብቻ መሻገር እንዳለባቸው ማስገንዘብ

ምዘና ፡- የትራፊክ ህግን መረዳታቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ዓላማ ፡- በጨዋታ ከትራፊክ አደጋ እራሳቸውን መከላከል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ካርቶኖች፣ ቀለሞች /ከለሮች፣ ቀጭን እንጨት፣ ማጣበቂያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የመንገድ ትራፊክ መብራት ጨዋታን በዚህ መልኩ በማጫወት ግንዛቤ ያስጨብጡ
- ሶስት ትላልቅ ካርቶኖችን ኩብ አድርጎ መቁረጥ
- እያንዳንዱን በፊትና በጀርባው ቀይ ቢጫና አረንጓዴ ቀለም መቀባት
- በቀጭን እንጨት ላይ ማጣበቅ /መለጠፍ/
- በግድዳው ላይ በቾክ ወይም በገመድ የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ መስራት

ተግባር አራት ፡- በጨዋታ የትራፊክ ህግን ማክበርን መለማመድ

- አሽከርካሪ ህጻናት ጎማ ካለ እያንከባለሉ ከሌለ እጃቸውን እንደመኪና መሪ እያሽከረከሩ በሁለት አቅጣጫ እንዲጓዙ ማድረግ
- እግረኞች በእግረኛ መንገድ ላይ እንዲጓዙ ማድረግ
- የትራፊክ ህግን የተላለፉ አሽከርካሪዎችም ሆኑ እግረኞች ከጨዋታ ውጭ እንዲሆኑ

ማድረግ

ማስታወሻ ፦ የትራፊክ ደህንነት ትምህርት በአጸደ ህጻናት የሚለውን ጽሁፍ መጠቀም ይቻላል።

ምዘና ፦ በጨዋታ ከትራፊክ አደጋ እራሳቸውን መከላከል መለማመዳቸውን በመመልከት መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 5. የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳት እና ሙከራ ማካሄድ | 5.1. የመኪና ጐማዎችን መጠን ብዛትና ጥቅም መናገር ይችላሉ |

ተግባር አንድ ፦ የእንቅስቃሴ አይነቶች መለየት

ዓላማ ፦ ሶስቱን መሰረታዊ የእንቅስቃሴ አይነቶች ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የሚራመዱ፣ የሚበርሩ እና የሚንሳፈፉ እንስሳት እና መጓጓዣዎች ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሶስቱን መሰረታዊ እንቅስቃሴዎች ማለትም መራመድ፣ መብረር እና መንሳፈፍ/ መዋኘትን ማስተዋወቅ
- እንቅስቃሴዎቹን በአካላዊ እንቅስቃሴ በማሳየት ከመምህር ጋር አብረው እንዲሉ ማድረግ
- የሚራመዱ፣ የሚበርሩ እና የሚንሳፈፉ እንስሳትን እና መጓጓዣዎችን ስእሎች በመስጠት እንዲያዛምዱ ማድረግ

  ለምሳሌ፦ ወፍ እና አውሮፕላን፣ ተራማጅ እንስሳን እና አውቶሞቢል/ መኪናን እንዲሁም አሳን እና መርከብ /ጀልባን
- አዛምደው ሲጨርሱ ለምን እንደዛ ሊያዛምዱ እንደቻሉ በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፦ ሶስቱን መሰረታዊ የእንቅስቃሴ አይነቶች መለየት መቻላቸውን ሲያዛምዱ በማየት መገምገም።

ዓላማ ፦ የዓሳን እና የመርከብ /ጀልባ/ የመንሳፈፍ እንቅስቃሴን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ መዘፍዘፊያ እና ውሃ፣ የአሳ እና የመርከብ /ጀልባ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ህጻን ግማሽ ወረቀት በማደል የወረቀት ጀልባ አሰራርን ማሳየት
- ከዚያም ጀልባ በምን ላይ እንደሚንቀሳቀስ በመጠየቅ ማወያየት
- በክፍል ውስጥ ሰፋ ያለ ውሃ የሚይዝ ባልዲ ወይንም መዘፍዘፊያ ውስጥ ግማሽ ድረስ ውሃ መሙላት
- ህጻናቱ በወረቀት የሰሩትን ጀልባ በዚያ ውሃ ውስጥ እያንሳፈፉ እንዲጫወቱ ዕድል መስጠት
- ከዚያም በውሃ ውስጥ የሚኖር እና እንዲዘህ የሚንሳሰፍ/የሚዋኝ እንስሳ ምንድን ነው**?**
- ማድረግ

**ተግባር ሁለት ፦ የመንሳፈፍ እንቅስቃሴ**

ምዘና ፦ የመንሳፈፍ እንቅስቃሴን መረዳት መቻላቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ የመብረር እንቅስቃሴን ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ መዘፍዘፊያ እና ውሃ፣ የአሳ እና የመርከብ /ጀልባ ስዕል

**ተግባር ሦስት ፦ የመብረር እንቅስቃሴን መገንዘብ**

የአተገ

- **“**ወፊቷን እሆናለሁ**”** መዝሙርን በእንቅስቃሴ በማዘመር እጆቻቸውን እንደ ወፍ እንደ

አውሮፕላን በፍጥነትና በዝግታ በማንቀሳቀስ እንዲጫወቱ ማድረግ

- ትልቁ ጉማ ትንሹ ጉማ ተሽከርከረ ጨዋታን በተግባራዊ እንቅስቃሴ ጋር በማዛመድ ማጫወት
- በደረጃቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሕፃናት አካባቢአቸውን አስተውለው እንዲመለከቱ፣ እንዲቃኙና እንዲገነዘቡ ማድረግ
- ለምሣሌ ወፎች የት እንደሚኖሩ መጠየቅ በአካባቢያቸው አኗኗራቸውን እንዲመለከቱ ማድረግ።
- ‹‹ወፊቷ›› የሚለውን መዝሙር ማዘመር

ምዘና ፦ የሚበርሩ እንስሳትን ከሚበርሩ መጓጓዣዎች ጋር ማዛመድ መቻላቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ የመኪና ጎማዎች ጥቅምን ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ህፃናቱን ለትንሽ ደቂቃ ከግቢ ውጪ ይዞ በመውጣት መኪናዎች በሚተላለፉበት መንገድ ዳር ላይ ቆመው በመንገድ ላይ የሚሄዱትን ተሽከርካሪዎች እንዲመለከቱ ማድረግ
- መኪናዎቹ እንዲጓዙ የሚያደርጓቸውን ጉማዎች አስተውለው እንዲመለከቱ ማነቃቃት
- በመቀጠልም ሕፃናቱን ወደ ክፍል ይዞ በመግባት ምን እንደተመለከቱና መኪናዎቹ በምናቸው ሊንቀሳቀሱ እንደቻሉ ምን ያህል ጉማዎች እንዳላቸው በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፦ የመኪና ጎማዎች ጥቅምን መረዳት መቻላቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ

> ማስታወሻ ፦ ሕፃናቱን ከግቢ ውጪ ይዘን ስንወጣ ረዳት ያስፈልጋል ከፍተኛ ጥንቃቄም ማድረግ ይገባል።

ዓላማ ፦ ከወረቀት የጎማ ቅርፆችን ይሰራሉ



ተግባር አራት ፦ የመኪና ጎማዎችን ጥቅም መረዳት

ተግባር አምስት ፦ ከወረቀት የጎማ ቅርፅን መስራት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባለ ቀለም ወረቀት፣የተለያየ መጠን ያላቸው ክብ ቅርፆ ማውጫዎች፣ ትልቅ ነጭ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን መሀሉ ክፍት የሆነ ክብ ቅርጽ ማውጫን በመጠቀም ባለቀለም ወረቀት ላይ በማድረግ የክቡን የውስጥና የውጪ ጠርዝ ተከትሎ በማስመር የጎማ ቅርፅ መስራት
- በመቀጠልም የተሰመረውን መስመር ተከትሎ ቀዶ በማውጣት የጎማ ቅርፅ ሰርቶ በማሳየት ምን እንደሆነ መጠየቅ
- ለህፃናቱም በየጠረጴዛቸው ወረቀትና ክብ ቅርጽ መስሪያውን በመስጠት ባዩት መሠረት እንዲሰሩ ማድረግ
- ሲጨርሱ የሁሉንም ጎማዎች በነጭ ወረቀት ላይ በመለጠፍ በክፍል ውስጥ መስቀል

ምዘና ፡- ከወረቀት የጎማ ቅርፅ መስራት መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ፡

ተግባር ስድስት ፡- ከባህር ዛፍ ቅጠል እሽክርክሪት በመስራት መጫወት

ዓላማ ፡- ከባህር ዛፍ ቅጠል እሽክርክሪት በመስራት ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የባህር ዛፍ ቅጠል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናቱም የባህር ዛፍ ቅጠሎትን በመስጠት ባዩት መሠረት እሽክርክሪት እንዲሠሩ ማድረግ
- ሰርተው ሲጨርሱ ከክፍል ውጪ ይዘውት በመውጣት በአውራ ጣትንና ጠቋሚ ጣቶቻቸውን በመያዝ እንዲሮጡ ማድረግ
- በሚሮጡበት ጊዜ ያዩትን ለውጥ መጠየቅ ሲቆሙ ለምን እንደማይሽከረከር ሲሮጡ ለምን እንደሚሽከረከር በመጠየቅ የሚሽከረከረው በንፋስ ኃይል መሆኑን እንዲረዱ

ማድረግ፡፡

ምዘና ፡- ከባህር ዛፍ ቅጠል እሽክርክሪት በመስራት መጫወታቸውን በማየት መገምገም፡፡

**ተግባር ሰባት ፡- ከሞባይል ካርድ መጫወቻ በመስራት መጫወት**

ዓላማ ፡- ከሞባይል ካርድ መጨወቻ በመስራት ይጫወታሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የባለ 50 እና 100 ብር የሞባይል ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አገልግሎት የሰጡና የማያገለግሉ የሞባይል ካርዶችን እኩል ሁለት ቦታ ማጠፍ
- በመቀጠልም ትንሽ የእጅ መያዣ ከእጥፋቱ ላይ በመተው መዘርጋት ከዛም እጥፋቱን ይዞ በማሽከርከር ለሕፃናቱ ማሣየት
- ለእያንዳንዱ ልጅም የሞባይል ካርዱን በመስጠት መምህርን በመከተል እንዲያጥፉና ሲጨርሱም በጠረጴዛቸው ላይ እያሽከረከሩ እንዲጫወቱበት ማድረግ

ምዘና ፡- ካገለገሉ የሞባይል ካርድ መጫወቻ እሽክርክሪት በመስራት መጫወታቸውን በማየት መገምገም፡፡

ዓላማ ፡- በማግኔት የሚሳቡና የማይሳቡ ነገሮችን ይለያሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ማግኔት፣ ትናንሽ ሚስማሮችና ብሎኖች፣ የልብስ ቁልፎች፣ ትናንሽ የሻንጣ ቁልፎች ወዘተ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ብረት ነክ የሆኑ እና ያልሆኑ ትናንሽ ቁሳቁሶችንና ማግኔትን ማዘጋጀት
- ከዛም ለሕፃናቱ ማግኔትንና ቁሳቁሶችን በጠረጴዛቸው ላይ በማድረግ ማግኔቱን ወደ ቁሳቁሶቹ በማስጠጋት የትኛውን ዕቃ ማግኔቱ እንደሚስበውና የትኛውን እንደማይስበው



**ተግባር ስምንት ፡- በማግኔት የሚሳቡና የማይሳቡ ነገሮችን መለየት**

ሙከራ በማድረግ እንዲናገሩ ማድረግ

- ማግኔት ብረት ነክ የሆኑ ነገሮችን የመሳብ ሀይል እንዳለው በደረጃቸው እንዲረዱ ማድረግ

> ማስታወሻ ፡-ማግኔትንም ሆኑ ሌሎች ትናንሽ ነገሮችን ወደአፋቸው ማስጠጋት እንደሌለባቸው አስቀድሞ ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

ምዘና ፡- በማግኔት የሚሳቡና የማይሳቡ ነገሮችን ሙከራ በማድረግ መለየታቸውን በማየት ማረጋገጥ፡፡

ዓላማ ፡- የአረፋ እንክብሎችን በመስራት ይጫወታሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ንፁህ የእስክሪብቶ ቀፎዎች፣ ትናንሽ ንፁህ የፕላስቲክ ብልቃጦች፣ ውሃና ፈሳሽ የእጅ ሳሙና

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ንፁህ የእስክሪብቶ ቀፎዎችን በሕፃናቱ ቁጥር በማዘጋጀት በዕቃ ላይ ውሃና ሣሙና መበጥበጥ
- መምህር አስቀድሞ የእስክሪብቶ ቀፎውን በተበጠበጠው ውሃና ሳሙና ላይ ነክሮ በማውጣት ቀስ ብሎ ወደ ውጪ በመንፋት በርካታ እንክብሎችን ሰርቶ ማሳየት
- [illegible]ል በጠረጴዛቸው ላይ በተቀመጠው አረፋ ለቃ ውስጥ ነክረው በማውጣት የአረፋ እንክብሎች በመሥራት

> ተግባር ዘጠኝ ፡- የአረፋ እንክብሎችን በመስራት መጫወት

> ማስታወሻ ፡- እያንዳንዱ ሕፃን በራሱ ቀፎ ብቻ መጫወት / መጠቀም እንዳለበትና ወደ አፉ ውስጥ እንደማይገባ መንገር ያስፈልጋል፡፡

ምዘና ፡- የአረፋ እንክብል በመስራት መጫወት መቻላቸውን በማየት መገምገም፡፡

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. በስነስዕል እና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅ እና ራስን መግለጽ | 6.1 . ስእሎችን እና ቅርፃ ቅርፆችን መሥራት ይችላሉ፡፡ |

**ተግባር አንድ ፦ የታዘዙትን ስዕል መሳል**

ዓላማ ፦

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ህጻን ወረቀት እና እርሳስ መስጠት
- ሁሉም አንድ ዓይነት ስዕል እንዲስሉ ርዕስ መስጠት
- ሲጨርሱም በስዕሉ ግርጌ ስማቸውን መፃፍ
- የሕፃናቱን ሥራ ግርግዳ ላይ መለጠፍ

| |
|---|
| ማስታወሻ፦ ስማቸውን መፃፍ የሚችሉ ህጻናት ካሉ እና ራሳቸው ለመፃፍ ፍላጐት ካላቸው እንዲጽፉ እድሉን መስጠት። |

ምዘና ፦ የታዘዙትን ስእል መሳል መቻላቸውን በማየት መገምገም።

**ተግባር ሁለት ፦ ሃሳባቸውን በስዕል መግለጽ**

ዓላማ ፦

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳሶች /ከለሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለሕፃናት ወረቀት፣ እርሳስ እና ባለቀለም እርሳሶች /ከለሮች መስጠት
- የፈለጉትን እንዲስሉ እና ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱ እያንዳንዱ ህጻን ምን እንደሰሩ መጠየቅ
- የሰሩትን ስዕል መጠሪያ ስም ከስዕሉ ግርጌ መፃፍ
- የሳሉትን ስዕል ወጥተው ለጓደኞቻቸው እንዲያሣዩ እና እንዲናገሩ ማድረግ
- ስሜትን፣ ሃሳብን፣ ፍላጐትን በስዕል የማንፀባረቅ ክህሎትን እና ልምድን እንዲያዳብሩ

መርዳት

ምዘና ፡- በስዕል ሃሳባቸውን መግለጽ መቻላቸውን የሳሉትን ስዕል በማየት እና የሚሰጡትን ማብራሪያ በመስማት መገምገም።

ዓላማ ፡- የሰሩትን ስእሎች ቀለም በመቀባት መሠረታዊ ቀለማትንና ሁለተኛ ቀለሞችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የዱቄት ቀለሞች/ቀይ፣ ቢጫ፣ ሰማያዊ/፣ ብርሃን የሚያስተላልፉ ሶስት ብርጭቆዎችን እና የውሃ ኮዳዎች ማቅረብ ፣ ሶፍት፣ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት፣ ውሃና ሳሙና

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት በ "ሀ" ቅርጽ እንዲቀመጡ ማድረግ
- ፊት ለፊታቸው በጠረጴዛ ላይ መሠረታዊ የዱቄት ቀለሞች /ቀይ፣ ቢጫ፣ ሰማያዊ/ ብርሃን የሚያስተላልፉ ሶስት ብርጭቆዎችን እና የውሃ ኮዳዎች ማቅረብ
- ከሁለቱ የዱቄት ቀለም በማንኪያ በመቆንጠር ብርጭቆ ውስጥትንሽ ውሃ ጨምሮ በማንኪያ ማማሰል
- ምን ዓይነት ቀለሞች ተደባልቀው ምን ዓይነት ቀለሞችን እንደፈጠሩ ሕፃናቱ በማየት

**ተግባር ሦስት ፡- ስእሎችን በመቀባት ቀለማትን መተዋወቅ**

ለምሳሌ፡- ቀይ እና ቢጫ ሲደባለቁ ብርቱካንማ

ሰማያዊ እና ቢጫ ሲደባለቁ አረንጓዴ

ሰማያዊ እና ቀይ ሲደባለቁ ወይንጠጅ ቀለም እንደሚሰጡ እንዲረዱ ማድረግ

- በጣት ቀለምን እየነከሩ በወረቀት ላይ ስዕል በመሣል ማሳየት
- ለእያንዳንዱ ሕፃን ወረቀት እና በጠረጴዛቸው ላይ የተለያዩ ቀለም መስጠት
- ባዩት መሠረት ጠቋሚ ጣታቸውን ቀለሙ ውስጥ እየነከሩ የፈለጉትን ነገር እንዲስሉ ዕድሉን መስጠት
- ሲጨርሱ በተሰጣቸው ቁራጭ ሶፍት ጣታቸውን አጽድተው ሶፍቱን ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ እንዲጥሉ ማድረግ
- ከስዕሉ ግርጌ ስማቸውን በመፃፍ ምን እንደሳሉና ምን ዓይነት ቀለምን እንደተጠቀሙ

እንዲናገሩ ማድረግ/

- በመጨረሻም እጃቸውን በውሃና በሳሙና እንዲታጠቡ ማድረግ

ምዘና ፦ መሰረታዊና ሁለተኛ ቀለማትን መለየታቸውን የቀቡትን ስእል ቀለም በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ ከተቦካ ወረቀት ወይም ጭቃ የተለያዩ ቅርፆችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተቦካ ወረቀት ወይም ጭቃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተቦካ ወረቀት ወይም ጭቃ ወዘተ ለሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ መስጠት
- የተለያዩ ቅርፆችን እንዲሰሩ ማበረታታት
- ሰርተው ሲጨርሱ ምን እንደሰሩ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት
- የሰሩትን በወረቀት ላይ በማድረግና ከግርጌ ስማቸውን በመጻፍ የሚደርቅበት ቦታ ላይ ማስቀመጥ

ምዘና ፦ የተለያዩ ቅርፆችን መስራት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አምስት ፦ ምስሎችን በተለያዩ ነገሮች ማጣበቅ

ዓላማ ፦ ምስሎችን በተለያዩ ነገሮች በመለጠፍ ይሞላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የእንስሳ /የአዕዋፍ/ ምስል፣ ኮላ፣ የተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎች እና

ተግባር አራት ፦ ቅርፃ ቅርፆችን መሥራት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- በትልቅ ወረቀት ላይ የተሳለ የእንስሳ /የአዕዋፍ/ ምስልበየጠረጴዛቸው መስጠት
- ውስጡን ማጣበቂያ እና ኮላ መለቅለቅ
- የተለያዩ ቅጠላቅጠሎች እና አዝርዕቶች እንዲሞሉት ማድረግ

- ሲጨርሱ ከስሩ የሕፃናቱን ስም በመፃፍ ግርግዳ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፦ ምስሎች ላይ የተለያዩ ነገሮችን መለጠፍ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፦ በወረቀት ቅርጽን መስራት

ዓላማ ፦ ወረቀቶችን በማጣጠፍ ቅርጾችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለሕፃናት የተለያየ ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች መጽሔቶች ወዘተ....ማዘጋጀት
- ወረቀት በማጣጠፍ የተለያዩ ቅርጾችን እንዴት እንደሚሠሩ ማሣየት

  ለምሳሌ ፦ ጀት፣ ሽክርክሪት ወዘተ...
- ለእያንዳንዱ ሕፃን በመስጠት መምህርን በመከተል እነሱም እንዲሠሩ ማበረታታት

ማስታወሻ ፦ የሰሩአቸውን ቅርጾች በውጭ ጨዋታ ክፍለ ጊዜ እንዲጫወቱባቸው ማበረታታት ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ ወረቀት በመጠቀም ሁሉም ህፃናት ቅርጾችን መስራት መሞከራቸውን መከታተል።

ዓላማ ፦ ወረቀቶችን በመጠቅለል የተለያዩ ጌጣጌጦችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወፍራም ክለሳር፣ ክር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ወፍራም ክለሳርን በተለያየ ቅርጽ መቁረጥ
- መካከሉን በመብሳት ከክር ጋር በየጠረጴዛቸው መስጠት
- ሕፃናቱ በቀዳዳ ውስጥ ክርን በማስገባት የእጅ አምባር እና የአንገት ጌጥ ለራሳቸው

ተግባር ሰባት ፦ በወረቀት ጌጣጌጥ መስራት

እንዲሠሩ ማድረግ

ማስታወሻ ፦ ከከበዳቸው አሠራሩን በእርጋታ ማሣየት እና ሁለም ህፃናት እንዲተገብሩት ማበረታታት ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ ወረቀት በመጠቀም ሁሉም ህፃናት የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን መስራት መለማመዳቸውን መገምገም።


ተግባር ስምንት ፦ የልደት ካርድ መስራት

ዓላማ ፦ የልደት ካርድ ያበራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወፍራም ክለሰር፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ኮላ፣ ትናንሽ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- በየወሩ መጨረሻ ላይ በወሩ ውስጥ ለተወለዱ ልጆች ልደታቸውን ለማክበር ፕሮግራም መያዝ
- ለዝግጅቱ የመልካም ልደት መግለጫ ካርዶችን እንደሚከተለዉ በመስራት ማዘጋጀት፡-
    - ክላሰር ለሁለት ማጠፍ
    - ክላሰሩ ላይ መሳል ወይም የተለያዩ ነገሮችን መለጠፍ
- ራሳቸው እንዲሠሩ ማለማመድ
- የሚያዘጋጁአቸውን ካርዶች ስጦታ እንዲሰጡ ማድረግ



ማስታወሻ ፦ ለወላጆች ቀን፣ ለእናቶች ቀን፣ ለአባቶች ቀን ወዘተ… የስጦታ ካርዶችን እንዲሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የልደት ካርዶችን መስራት መለማመዳቸዉን መከታተል።

## **2.5.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም --------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም ----------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ -----------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት -----------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት -----------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመቱ መጀመሪያ | በዓመቱ አጋማሽ | በዓመቱ መጨረሻ |
| 1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | | | |
| 1.1 በቤታቸውና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን ሰዎች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት ይችላሉ። | | | |
| **2.** በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | | | |
| 2.1 በአካባቢያቸው ሰለሚገኙት ቦታዎች መናገር ይችላሉ። | | | |
| 2.2 ሀገርን የመውደድ ዝንባሌ ያሳድራሉ። | | | |
| **3.** አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ | | | |
| 3.1 አካባቢን በንጽህና መጠበቅ ይችላሉ። | | | |
| **4.** በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | | | |
| 4.1 ራስንና ሌሎችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ አደገኛ ነገሮች መከላከል ይችላሉ። | | | |
| **5.** የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ | | | |
| **5.1** የመኪና ጐማዎችን መጠን ብዛትና ጥቅም መናገር ይችላሉ። | | | |
| **6.** በስነ ሥዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለጽ | | | |
| 6.1 ቅርፃ ቅርፆችን መሥራት ይችላሉ። | | | |

# አባሪ

| መዝሙር | ጨዋታ | ተረት |
|---|---|---|
| 1. 1. እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ | 1. 1.ትልቁ ጎማ ተሽከረከር | 1. |
| 2. 2. የቱ ነው እጃችን | 2. 2.እጅ ለእጅ ተያይዘን | 2. 1.ትንሿ አይጥ |
| 3. 3. በምን ምን እናደርጋለን | 3. 3.እንሽከረከረላለን | |
| 4. 4. አምስቱ የስሜት አካላት | 4. 4.አረንጓዴ አረንጓዴ | |
| 5. 5. ፊትን መታጠብ እነደዚህ ነው | 5. 5.የተነካውን የሰውነት ክፍል ተናገር | |
| 6. 6. እጅን መታጠብ እነደዚህ ነው | 6. 6.ማን እንዴት ይጨኻል | |
| 7. 7. ቀስበቀስ ሸረሪቷ | 7. 7.የጠራህን ዕወቅ | |
| 8. 8. ወፊቷን እሆናለሁ | 8. 8.ቀምሰህ ዕወቅ | |
| 9. 9. አሻንጉሊቴ | 9. 9.ማ ቀድሞ ያውቃል | |
| 10. እናት አባቴን እወዳለሁ | 10.ቀለም መለየት ጨዋታ | |
| 11. ጥንቸል ጉረኛው | 11.አሻንጉሊቷን ፈልገህ አግኝ | |
| 12.የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ | 12.ምን እያደረኩ እንደሆነ ተናገር | |
| 13.ደስተኛ የሆነ | 13.አያ ጅቦ አለህ | |
| 14.ቁጥር መቁጠር ደስ ይላል | 14.እኔ ዛፍ ነኝ | |
| 15.ትንሽ ትንሽ ወፎች | 15.ተመሳሳዩን አግኝ | |
| 16.አምስት ሙዞች አሉኝ | 16.ቀድሞ የሚያስር ማ ነው | |
| 17.አምስት አረንጓዴ ጠርሙሶች | 17.ማን ቀድሞ ይቆልፋል ወይም ይፈታል | |
| 18.ሁልጊዜ ይህን እናደርጋለን | 18.ማ ነው ጎበዝ ሰዓሊ | |
| 19.ወደ ሱቅ እሄዳለሁ | 19.በቅርጹ ውስጥ ኳሱን ክተት | |
| 20.ትናንሽ ወረቀቶች | 20.የወንበር ሽሚያ ጨዋታ | |
| 21.ጥርስን መፋቅ እንደዚህ ነው | 21.ፈልገህ አግኝ ጨዋታ | |
| 22.ጎበዙ ተማሪ | 22.አሽትተህ እወቅ | |
| 23.ወፊቷ | 23.ማን ተቀየረ | |
| | 24.የመንገድ ትራፊክ ምልክት | |

# ጨዋታ

1. <u>እጅ ለእጅ ተያይዘን</u>

እጅ ለእጅ ተያይዘን እንሽከረከራለን መደነስ እንችላለን

መዘመር እንችላለን

2. እኔ ዛፍ ነኝ

እኔ ዛፍ ነኝ

እነዚህ ቅርንጫፎች ናቸው /እጆችን መዘርጋት/

ንፋሱ ሲነፍስ

እንደዚህ እንደዚያ /እጆቻቸውን ያንቀሳቅሱአቸዋል/

**መዝሙር**

1. <u>በምን ምን እናደርጋለን?</u>

| | |
|---|---|
| መምህር | እናያለን ሲሉ /በዜማ/ |
| ሕፃናት | በዓይናችን ይላሉ /በዜማ/ |
| መምህር | እንሮጣለን /በሩጫ መልክ በዜማ/ |
| ሕፃናት | በእግራችን |
| መምህር | እንሰማለን |
| ሕፃናት | በጆሮአችን |
| መምህር | እንቀምሳለን |
| ሕፃናት | በምላሳችን |
| | እናሸታለን |
| | በአፍንጫችን ወዘተ..... |

2. <u>ቀስ በቀስ ሸረሪቷ</u>

ቀስ በቀስ ሸረሪቷ ወደ ላይ ወደ ላይ ወጣች

ንፋሱ ነፍሶ ሲያወዛውዛት

ዝናቡ ዘንቦ ወደታች ወደታች ጣላት

3. <u>እንደ ዛፍ እወዛወዛለሁ</u>

እንደ ዛፍ እወዛወዛለሁ

እንደ ወፍ እበራለሁ

እንደ ፌንጣ እዘላለሁ ወዘተ.....

**4.** ወፊቷን እሆናለሁ

ወፊቷን እሆናለሁ

በአየር ላይ እበራለሁ

ከዛፎቹም በላይ

ወደ ላይ ወደ ላይ

ቢራቢሮን እሆናለሁ

በአየር ላይ እበራለሁ

ከአበቦቹም በላይ

ወደ ላይ ወደ ላይ

**5.** ጥንቸል ጉረኛው

ጥንቸል ጉረኛው አፈረ

ኤሊ ትጉህ ተከበረ

ጥንቸል ጉረኛው ሲነዛ ጉራ

ኤሊ አሸነፈ ሮጠ በተስፋ

አጨበጨቡ ዱኞች እንሰሳት

በኤሊ ኮሩ ቀሰሙ ትምህርት

**6.** የቤት እንሰሳት መዘመር ይችላሉ

የቤት እንሰሳት መዘመር ይችላሉ /2/

ድመት ትዘምራለች ትደንሳለች

የቤት እንሰሳት መዘመር ይችላሉ /2/

ውሻስ ምን አለ ምን ምን አለ?

የቤት እንሰሳት መዘመር ይችላሉ /2/

ዶሮስ ምን አለ ምን ምን አለ?

ሆሆ ምን ምን እያሉ?

ሚያው ሚያው ሚያው ትላለች

ሆሆ ምን ምን እያሉ?

ው ው አለ አጥንት ቆረጠመ

ሆሆ ምን ምን እያሉ?

ኩኩሉ አለ ከአጥር ላይ ዘለለ

**7.** ደስተኛ የሆነ

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ

ደስተኛ የሆነ ይዘላል

ደስተኛ የሆነ ደስታውን

ዱብ ዱብ በማለት ይግለፅ

8. <u>እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው</u>

እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው

ፊትን መታጠብ እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው

ፀጉርን ማበጠር እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው ወዘተ.....

9. <u>አምስት ሙዞች አሉኝ</u>

አምስት ሙዞች አሉኝ

ለማን ልስጣቸው?

ለሃና ሰጠሁ 4 ቀረኝ

ለሄኖክ ሰጠሁ 3 ቀረኝ

ለአስቴር ሰጠሁ 2 ቀረኝ

ለአሹ ሰጠሁ 1 ቀረኝ

ለራሴ አንድ ወሰድኩ ስንት ቀረኝ?

10. <u>ትንሽ ትንሽ ወፎች</u>

አንድ ሁለት ሶስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

አራት አምስት ስድስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

ሰባት ስምንት ዘጠኝ ትንሽ ትንሽ ወፎች

አሥር ትናንሽ ወፎች

11. <u>አምስቱ የስሜት ሕዋሳት</u>

አምስቱ አምስቱ

የስሜት ህዋሳት

የስሜት የስሜት

አዝማች ህዋሳት ህዋሳት

**×2** ዓይን አፍንጫ (**×2**)

ምላስ ጆሮና (**×2**)

እጃችን ናቸው (**×2**)

ዓይን አለኝ አያለሁ

ጆሮ አለኝ እሰማለሁ

በአፍንጫዬም አሸታለሁ (**×2**)

በምላሴም እቀምሳለሁ (×2)

መዳሰሻ እጅም አለኝ (×2)

የስሜት ህዋሴን እወቁልኝ

**12.** . <u>ሁልጊዜ ይህን እናደርጋለን</u>

ሁልጊዜ ጠዋት ስንነሳ

ፊታችንን እንታጠባለን

ቁርሳችን እንበላለን

ሁልጊዜ ይህን እናደርጋለን

**13.** <u>ወደ</u> ሱቅ እሄዳለሁ(የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን ማስተዋወቅ)

| | |
|---|---|
| እኔ ወደ ሱቅ ከእናቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| እኔ ወደ ሱቅ ከአባቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| ሄጄም ብስኩት እገዛለሁ | እገዛለሁ |
| ሄጄም ደብተር እገዛለሁ | እገዛለሁ |
| ተመልሼም ወደ ቤቴ እመጣለሁ | እመጣለሁ |
| እኔ ወደ ሃኪም ቤት ከእናቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| ሄጄም ያመመኝን እታከማለሁ | እታከማለሁ |
| ተመልሼ ድኜም ወደ ቤቴ እመጣለሁ | እመጣለሁ |

**14.** <u>ትናንሽ ወረቀቶች</u>

ትናንሽ ወረቀቶች

ትናንሽ ወረቀቶች

መሬት ላይ ወድቀዋል

ወለሉ /ግቢውን /አቆሸሹት

አንሷቸው አንሷቸው

**15.** <u>ጉብዙ ተማሪ</u>

ጉብዙ ተማሪ በጣም ጠንቃቃ ነው

በመንገድ ላይ ሲሄድ እያስተዋለ ነው

መኪና ሲመጣ ከሩቅ እንዲታየው

የመንገዱን ግራ ይዞ ነው የሚጓዘው

**16.** <u>ወፊቷ</u>

ወፊቷ ከየት ይሆን ቤትሽ?

የምትገቢውን ዞረሽ

በሰማይ ስትበሪ

አጥሩን ስትሰብሪ

ቤትሽን ስትሰሪ

መሆኑን አወቅሁኝ

ወፊቱ ልታርፊ ልተኚ

## ተረት

### ትንሿ አይጥ

ውሮ ጠዋት ተነስቶ ውጪውን ሲመለከት ፀሐይ ወጥታ ደስ የሚል ሙቀት እየሰጠች ነው። ውሮ ከቤቱ በራፍ ላይ ጋደም ብሎ ፀሐይ መሞቅ ጀመረ ሙቀቱም ደስ አለው ከተኛበት ቤት ግድግዳ ስር ኮሽ-ኮሽ የሚል ድምፅ ሰማና

ቀና ብሎ ሲያይ ትንሽ ቀዳዳ ከግድግዳው ስር ተመለከተ ግን ቀዳዳው አካባቢ ምንም አላየም ተመልሶ ጋደም አለ አሁንም ኮሽ-ኮሽ የሚል ድምጽ ሰማና ቀ-ና ብሎ ሲመለከት አንዲት ትንሽ አይጥ ከቤቱ ግድግዳ ሥር ባለው ትንሽ ቀዳዳ አንገቷን አውጥታ ውጪውን ታያለች ውሮ ሊይዛት ብድግ ሲል ጉድጓዱ ውስጥ ግብት አለች። ውሮ ተናደደ "ቆይ እንደገና ትመጪለሽ" በማለት ዛተና ጋደም ብሎ መጠበቁን ቀጠለ። ትንሿ አይጥ ከጉድጓድ ውጪ ያለውን ማየት ስለፈለገች እንደገና ብቅ አለች ውሮም በፍጥነት ሊይዛት ተነሳ ትንሿ አይጥ ፈጥና ወደጉድጓዱ ዘላ ስትገባ በጉድጓዱ ጫፍ ላይ የነበረ ድንጋይ እግሯን መታት፣ እያነከሰች ወደ ጉድጓድ ውስጥ ገባች፣ ስታነክስ ጉድጓዱ ውስጥ ያለችው እናቷ አየቻትና "ልጄ ምን ሆነሽ ነው የምታነክሺው? ወደ ውጪ ወጣሽ እንዴ? ውሮ ይበላሻል ወደ ውጪ አትውጪ አላልኩሽም? የእናት ትዕዛዝ አለመስማት ጥሩ አይደለም" ስትላት ትንሿ አይጥ በማዘን "እናቴ ይቅርታ አድርጊልኝ ሁለተኛ አልወጣም ምክርሽን እፈጽማለሁ" ብላ ጐንበስ ብላ ይቅርታ ስትጠይቅ እናቷ እቅፍ አድርጋ የተመታውን እግሯን አሻሸችና አስተኛቻት እግሯም ቀስ እያለ ዳነላት ከዛ ቀን ጀምሮ ትንሿ አይጥ የእናቷን ምክር በደንብ ማዳመጥና መፈፀም ጀመረች ይባላል።

ተረቱን መልሱ።

## **2.1.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ------------------------------------------ ቡድን--------------

የህጻኑ ስም----------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር-------------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም ------------------------------------------
2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም ------------------------------------------

3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም ------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| 1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | | | |
| 1.1.እራሳቸውን መግለጽ ይችላሉ<br>• ስምን፣ አድራሻን፣ የልደት ቀንን፣ እና የግል ፍላጎትን በመናገር ራስን ማስተዋወቅ መቻል | | | |
| 1.2. ከማንም ጋር በነፃነት ግንኙነት መፍጠር ይችላሉ<br>• የእረፍት ቀንን እንዴት እንዳሳለፉ ለጓደኞቻቸው ሲናገሩ ተገቢውን የንግግር ሥርዓት ተከትሎ መናገር መቻል | | | |
| 2.የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ተግባራቸውን መናገር | | | |
| 2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ<br>• የሰውነት ክፍሎችን መለየት መቻል | | | |
| 2.2. በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚከናወኑትን ተግባራት በትክክል መናገር ይችላሉ<br>• የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መናገር መቻል | | | |
| 3. ዓይኖችን መንከባከብ | | | |
| 3.1. ዓይኖቻቸው በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ<br>• የዓይንን ጥቅም መናገር መቻል | | | |
| 4. ጆሮዎችን መንከባከብ | | | |
| 4.1. ጆሮዎቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ<br>• የጆሮን ጥቅም መናገር መቻል | | | |
| 5. የማሽተት ስሜት ሕዋስን መጠቀም አፍንጫን መንከበካብ | | | |
| 5.1. በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን ሽታ መለየት ይችላሉ<br>• የአፍንጫን ጥቅም መናገር መቻል | | | |
| 6. የመቅመስ ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ | | | |
| 6.1 የምግቦችን ጣዕም መለየት ይችላሉ<br>• የአፍን ክፍሎች መለየት መቻል | | | |
| 6.2 አፋቸውን በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • አፍን እንዴት መንከባከብ እንደሚገባመናገር መቻል | | | |
| 7. በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መግለጽ | | | |
| 7.1. ስለነገሮችና ቁሶች ባህርይ፣ የሙቀት መጠንና ቅርጽ መለየት ይችላሉ<br>• የነገሮችን ባህርይ በመዳሰስ መለየትና መናገር መቻል | | | |
| 8.ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ሥርዓቶችን መለማመድ | | | |
| 8.1. የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ<br>• የምግብ ጠቃሚነትን መረዳት መቻል | | | |
| 9.አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ | | | |
| 9.1. አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ<br>• ስዕልን ቀለም በመቀባት የአካል ክፍሎችን መለየት መቻል | | | |
| 10.ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም | | | |
| 10.1. በሰውነት ክፍሎቻቸው ተገቢውን እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ<br>• ሚዛንን ጠብቆ መራመድ መቻል | | | |
| 11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ | | | |
| 11.1. ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ማድነቅና በጥንቃቄ መያዝ ይችላሉ።<br>• ስዕሎችን ከመስመር | | | |

### **2.2.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ---------------------------------------- ቡድን-------------

የህጻኑ ስም-------------------------------------------እድሜ-------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም---------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር-------------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም ----------------------------------------
2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም ----------------------------------------
3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም ----------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል።

| | መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 |
| በ | **1.** በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጎት ማሣደርና መለየት | | | |

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| 1.1 በቤትና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ያሉትን ሰዎች በማስተዋል መናገር ይችላሉ<br>• የቤተሰብ አባላትን ለይቶ መናገር መቻል | | | |
| 1.2 ሰዎች በቤታቸውና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ያላቸውን ኃላፊነት በማየት መናገር ይችላሉ<br>• ስለጓደኞቻቻው መናገር መቻል | | | |
| 1.3 አብረዋቸው ለሚጫወቱ ጓደኞቻቸው ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሣየት ይችላሉ<br>• በሕብረት መስራት መቻል | | | |
| 2. **2.** ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | | | |
| **2.1** .ሰዎች በቤታቸውና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ስለሚያከናውኗአቸው ተግባራት መናገር ይችላሉ /ወላጅ፣ ሞግዚት ፣ቤተዘመድ/<br>• ሰዎች የሚያደርጓቸውን የተለያዩ ተግባራት አስመስሎ መጫወት መቻል | | | |
| **2.2** . ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቁላቸውንና እንደሚንከባከቧቸው መግለጽ ይችላሉ<br>• እንክብከቤ ስለሚያደርጉላቸው ሰዎች መናገር መቻል | | | |
| 3. **3.** ሌሎችን መንከባከብና ያለንን ነገር ማካፈል | | | |
| 3.1 የሌሎችን ስሜት መጋራት ይችላሉ<br>• የስሜት መገለጫዎችን መለየት መቻል | | | |

**2.3.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና**

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ------------------------------------------ ቡድን--------------

የህጻኑ ስም----------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር--------------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም
2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም
3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| **1. 1.** መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽመስጠት | | | |
| 1.1. ለትዕዛዞችና ለመመሪያዎች ምላሽ መስጠት ይችላሉ<br>• ለትእዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ መስጠት መቻል | | | |
| 1.2. የድምፆችን አቅጣጫ ማመልከትና የድምፆችን ምንጭ መለየት ይችላሉ<br>• አካባቢን ትኩረት ሰጥቶማዳመጥና ስላዳመጡት ነገር መናገር | | | |

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| መቻል | | | |
| 1.3. የሰሙትን መናገር ይችላሉ<br>• የእረፍት ቀንሪፖርትን በተገቢው ሁኔታ ማቅረብ መቻል | | | |
| 1.4. ተረቶችን አዳምጠው የተረዱትን መግለጽና መልሰው መናገር ይችላሉ<br>• ተረትን አዳምጦ መልሶ መተረክ መቻል | | | |
| 2. **2.** በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት | | | |
| 2.1. ራስንና አካባቢን በተገቢው መንገድ መግለጽ ይችላሉ<br>• የንግግርን ስርአት ተከትሎስለራስ መናገር መቻል | | | |
| 3. **3.** በማንበብ መደሰት ዕውቀት ማግኘትና መረዳት | | | |
| 3.2 3.1. ስዕሎችንና የፊደላት ቅርፆችን መለየትና መረዳት ይችላሉ<br>• ስዕሎችን በማንበብ ስላዩትና ስለተረዱት ነገር መናገር መቻል | | | |
| 4. **4.** የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት | | | |
| 4.1. የተለያዩ ድርጊቶችን ለማከናወን እጃቸውንና ዓይናቸውን መጠቀም ይችላሉ<br>• የልብስና የጫማ ፍሬሞችን መክፈት፣ መዝጋት፣ ማሰርና መፍታት መቻል | | | |

**2.4.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና**

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ------------------------------------------ ቡድን--------------

የህጻኑ ስም----------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር--------------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም------------------------------------------
2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም ------------------------------------------
3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| **1. 1. የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ መረዳትና መለየት** | | | |
| 1.1. በተለያዩ ቁሳቁሶችና ቅርፆች መካከል ያለውን ተመሣሣይነትና ልዩነት ማውጣት ይችላሉ<br>• ጥንድ የሆኑ ቁሳቁሶችን በባህሪያቸው መለየት መቻል | | | |
| **2. 2. ነገሮችን በባህሪያቸው መሠረት ማወዳደር** | | | |
| 2.1. በነገሮች መካከል ያለዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት ይችላሉ<br>• በመዳሰስ ሸካራ እናለስላሳን ነገሮችንበማወዳደር መለየት መቻል | | | |
| **3. 3. ቁጥሮችን ማስተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት** | | | |

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| 3.1. ቁሳቁሶችንና ቁጥሮችን ከ 1-20 መቁጠር ይችላሉ<br>• የተለያዩ ነገሮችን በዓይነታቸዉ ለይቶ መቁጠር መቻል | | | |
| 4. **4.** በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሣሪያዎችን መጠቀም | | | |
| 4.1 በቦታና በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት መጠቆም ይችላሉ<br>• በመጠን መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት መቻል | | | |
| 5. **5.** የጊዜ ፅንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም፣ | | | |
| 5.1. የሳምንቱን ቀናት ወራትን የበዓል /ልዩም ቀናትን መናገር ይችላሉ<br>• ቀን እና ማታን የሚታዩ ለውጦችን መናገር መቻል | | | |
| 6. **6.** የቦታ ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | | | |
| 6.1. ሰዎችን፣ ዕቃዎችን አካባቢን መሠረት በማድረግ ቦታንና ርቀትን መገለጽ ይችላሉ<br>• የእቃዎችን መገኛ ከራስ መገኛ አንፃር መናገር መቻል | | | |
| **7.** ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት፣መግለጽና መጠቀም | | | |
| 7.1. የገንዘብ ዓይነቶችንና ምስላቸውን መለየት ይችላሉ<br>• የብር ኖቶች በቀለማቸው፣ በመጠናቸውና በምስላቸው መለየት መቻል | | | |

### **2.4.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመመደበኛትምህርትቤትስም ------------------------------------------ ቡድን--------------

የህጻኑ ስም----------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር-------------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም ------------------------------------------
2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም------------------------------------------
3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም ------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| **1.**የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | | | |
| 1.1 . በቤታቸውና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን ሰዎች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት ይችላሉ<br>• በቅርብ አካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎችን በስም፣ በመልክ፣ በፆታና በሙያቸው መለየት መቻል | | | |
| **2. 2.** በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | | | |
| 2.1. በአካባቢያቸው ሰለሚገኙት ቦታዎች መናገር ይችላሉ<br>• በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን መለየት መቻል | | | |
| 2.2.ሀገርን የመውደድ ዝንባሌ ያሳድራሉ<br>• የኢትዮጵያን የሀገራቸውን ባንዴራ ቀለማትን መለየት መቻል | | | |
| **3. 3.** አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ | | | |
| 3.1. አካባቢን በንጽህና መጠበቅ ይችላሉ<br>• የግልና የአካባቢ ንጽህና የመጠበቅ ጥቅም መረዳት መቻል | | | |
| **4. 4.** የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | | | |
| 4.1. ራስንና ሌሎችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ አደገኛ ነገሮች መከላከል ይችላሉ | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • ራሳቸዉን ከአደገኛ ነገሮች እንዴት መከላከል እንዳለባቸዉ መረዳት መቻል | | | |
| 5. **5.** የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ | | | |
| 7. 5.1. የመኪና ጐማዎችን መጠን ብዛትና ጥቅም መናገር ይችላሉ<br>• ሶስቱን መሰረታዊ የእንቅስቃሴ አይነቶች መለየት መቻል | | | |
| 6. **6.** በስነ ሥዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለጽ | | | |
| 6.1. ቅርፃ ቅርፆችን መሥራት ይችላሉ<br>• የታዘዙትን ስእል መሳል መቻል | | | |